



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ሀ

*የገፀባህሪያትን "የመናገር" መብት አይከለክልም!!*

# FM 66.6

## (አቢሲኒያ 24)

" ...አፍ

ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል..."

ማስታወሻ፡- ይህ መፅሐፍ 70% ምናባዊ ፈጠራ ሲሆን 30% በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

አዘርግ 2005



Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

ይህን አዝናኝ አስተማሪ መፅሐፍ መልሶ ለማሳተም ሆነ ወደ አስቂኝ አስተማሪ ፊልም ለመለወጥ የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

## ቀደምት ስራዎች

1. የሆነ የሆነ ነገር ይሠማኛል .2003
2. ኢያሪኮ 777-2004
3. ኢያሪኮ 888-2004
4. ኢያሪኮ 999-2005
5. አዳምና ሄዋን ....2005

ቀጣይ ምርጥ መፅሐፍ
አ... ዘንደኪ
በሚያዚያ 2006 ዓ.ም
ገበያ ላይ ይውላል

t.me/OLDBOOKSPDF

# ሐ

## ምዕራፍ ዜሮ

ለውድ አንባቢያን

ከአዘርግ

የኢያሪኮ ጉዞ መጠናቀቂያው ላይ ደረሰ!!... የኢያሪኮ 777... 888...999 ባቡር ጉዞ ማሳረጊያው ይህ FM66.6 የተሰኘው መፅሐፍ ነው... የምትማሩበት እና ዘና የምትሉበት ንባብ እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ ... መፅሐፉን በማንበቦ ከልብ አመሠግናለሁ!!

እሁንም ለወጣት ፀሐፍት የምለው በርቱ! ተስፋ እንዳትቆርጡ! ምክኒያቱም ሥነ-ፅሁፍ ጥረት እና ትዕግስትን ይፈልጋል... ሳትሰላቹ ቀጥሉ!!

አዘርግ ነኝ



t.me/OLDBOOKSPDF

## መታሰቢያነት፡-

ጠማማ አስተሳሰብ
ለሌላቸውና በወሬ
ሳይሆን "በሥራ" ለሚያምኑ
የሀበሻ ልጆች ትሁንልኝ!!


t.me/OLDBOOKSPDF

# 1

# አቢሲኒያ በከፍታ ት/ቤት

ከጠዋቱ 4:05

ሰኔ 28/10/2005

"በውስጤ የሚሰማኝን ታላቅ ደስታ በቃላት እንዴት መግለፅ እንዳለብኝ አላውቅም:: በሕይወት ዘመኔ በጣም ብዙ ደስታዎችን አይቻለሁ! እንደ ዛሬ ግን ተደስቼ አላውቅም:: እንደምታውቁት በኢትዮጵያ ውስጥ አዲስ አበባ ፣ ደብረዘይት፣ ጅማ እና ባህር ዳር ደረጃቸውን የጠበቁ አራት ኢንተርናሽናል ሆቴሎች አሉኝ... ጎንደር እና ቦረና ሁለት ግዙፍ የሰሊጥ እርሻዎች አሉኝ... በመላው ኢትዮጵያ ከሞያሌ በስተቀር 12 ግዙፍ ፋብሪካዎች አሉኝ... ባጠቃላይ ከ28 አክሲዮኖች ጋር ግዙፍ ድርሻዎች አሉኝ... ይህን ሁሉ ሀብት የወረስኩት ከእናት አባቴ አይደለም! እንደ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በድህነት ነው ያደኩት፣ የምበላው አያጣሁ ቁርሴን ሳልበላ ነበር ት/ቤት የምሄደው ፣ የምቀይረው ልብስ ስለሌለኝ ዓመቱን ሙሉ አንድ ሱሪ ነበር የማደርገው ፣ ምሽት በመንገድ ሙብራት ነበር የማነበው... የድህነት ሕይወትን ከማንም በላይ አውቀዋለሁ! ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ 14ኛው ሀብታም ነኝ! በእነዚህ ባሉኝ ነገሮች ሁሉ ሆነ በሀብቴ ተኩራርቼ አላውቅም:: በመሠረቱ አንድ ሰው ባለው ሀብት ሊኮራ ሆነ ሊመፃደቅ አይገባውም! ቢበዛ ሊደሰት ይገባው ይሆናል እንጂ... ለማንኛውም ዛሬ በመሀከላችሁ አንድ ትልቅ እንግዳ አለ፡፡ ይህ ታላቅ እንግዳ የኔ ጓደኛ ነበር:: ከሁለተኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል አብረን ተምረናል:: አንድ ጊዜ የዕረፍት ሰዓት ላይ ጠራኝ፡-

'ስምህ ማን ነው'

'አቤንኤዘር'

'ማለቱ ትርጉሙን ታውቀዋለህ '

'አላውቅም'



t.me/OLDBOOKSPDF

'እናትና አባትህ አልነገሩህም '

'ሞተዋል! ጎረቤት ነው የሚያሳድገኝ '

'አይዞህ ! ትላንት ማታ ስለ እኔ እና ስለ አንተ ህልም አይቻለሁ:: ለእናቴ ስነግራት ፍቺውን ነገረችኝ:: ለማንም ተማሪ የማትናገር ከሆነ ህልሙን እነግርሀለሁ'

'አልናገርም '

'ኢየሱስ ይሙት በል '

'ምን እሱ ቢሞትም ይነሳ የለ !

'እሺ እኔ ልሙት በል'

'እኔ ልሙት'

'ዛሬ ሁለታችንም ምንም ነን! በተለይ አንተ ምንም የለህም ! ጌታ ግን አንተን ከፍ ያደርግሀል! ለራስህ ብቻ ሳትሆን ለብዙዎች ትተርፋለህ! በኢትዮጵያ ውስጥ ስማቸው ከሚጠሩት ሀብታሞች መሀከል አንደኛው ትሆናለህ! ጠንክረህ ተማር! ማንኛውንም ስራ ሳትንቅ ስራ! የምታገኘውን ገንዘብ በአግባቡ ተጠቀምበት! በምንም ተዓምር ተስፋ እንዳትቆርጥ.... ይህን ነገር እናቴ እንድነግርህ ነግራኛለች'

' ጥሩ ነው:: ያልከኝን አልረሳም! አንተስ ምን ትሆናለህ?'

' ጠቅላይ ሚኒስቴር'

' ከባድ ህልም ነው'

" ይህን ነገር ሰምቼ ወደ ቤት ስመለስ እግሬን ጠርሙስ ቆረጠኝ:: ለመጀመሪያ ጊዜ ጫማ ያደረኩት አንድ ደግ ሰው ሰጥቶኝ ዘጠነኛ ክፍል ስገባ ነበር:: ለማንኛውም የተከበራችሁ እንግዶች ውድ መምህራን፣ ጋዜጠኞች፣ ባለሀብቶች ፣ ክት/ት ሚኒስቴር የመጣችሁ እንግዶች .... ታሪኬን ላሳጥረውና ለኔ ሕይወት መሳካት ትልቅ ሚና የነበራት ሚስቴ ሲልቪያ ነበረች፤ በነገራችን ላይ ባለቤቴ በድንገት ከሞተች በኋላ እሷን ለማስታወስ እጅግ ውብ የሆነችውን ልጄን ስም መጀመሪያ ቃል ኪዳን የነበረ ቢሆንም አሁን ግን በእናቷ ስም ሲልቪያ እየተባለች ትጠራለች:: ለእኔና መምህር ቀቁ መገናኘትም ትልቁን ሚና የወሰደችው ይቺው ብቸኛ ውብ ልጄ ሲልቪያ ናት::



t.me/OLDBOOKSPDF

ባለቤቴ 'ሀብታም ማለት ብዙ ሚሊየን አልያም ቢሊየን ብር ያለው ሳይሆን ጥሩ ነገር ማድረግ የሚችል ሰው ነው' ትል ነበር:: የዘወትር ህልሙዋ በኢትዮጵያ ውስጥ እጅግ ዘመናዊ ት/ቤት መገንባት ነበር :: አንድ ጠዋት 'ምን እንደምመኝ ታውቃለህ ' አለችኝ

' ንገሪኝ' አልኩዋት::

'ህያ ሺ ሰው የሚይዝ ስታዲየውም፣ እጅግ ዘመናዊ ከፍሎች፣ እጅግ ዘመናዊ ወንበሮች ፣ እጅግ ዘመናዊ መፀዳጃ ቤቶች፣ እጅግ ዘመናዊ መኝታ ቤቶች፣ የትያትር መለማመጃ መድረክ ያለው፣ ሲኒማ ቤት ያለው፣ ዘመናዊ የውበት ሳሎኖች ያሉት ፣ እጅግ ያማረ ውብ ግቢ ያለው ልክ እንደ አምስት ኮከብ ሆቴል አምስት ኮከብ የሆነ በኢትዮጵያ ሳይሆን በአፍሪካ ምድር የተለየ ዘመናዊ ት/ቤት መገንባት ! በዚያ ዘመናዊ ት/ቤት ውስጥ ቢበዛ በአንድ ክፍል ውስጥ 20 ተማሪዎችን ብቻ የሚያስተምር ሁለት ሺ ተማሪዎችን የሚይዝ! ለኢትዮጵያ ለውጥ የሚተጉ! ታላላቅ ደራሲዎች፣ መሪዎች ፣ ፕሮፌሰሮች፣ ስፖርተኞች፣ ሙዚቀኞች፣ ዘማሪዎች፣ መምህራኖች፣ የሀይማኖት አዋቂዎች ... ከምንም በላይ በዓለም ላይ የኢትዮጵያን ስም ከፍ ከፍ የሚያደርጉ ደም ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ተማሪዎችን ማፍራት ነው:: ...' ትል ነበር :: የሚገርማችሁ ሀብታችን እየበዛ ሲመጣ ባለቤቴ የተለያዩ ሀገራት እየዞረች ውድ ናቸው የሚባሉትን ት/ቤቶች ትጎበኝ ነበር:: የዘወትር ህልሙዋ ይህን ት/ቤት ስለመገንባት ማውራት ነበር:: ባለቤቴ ለዚህ ት/ቤት ግንባታ የሚሆን ቦታ አለ ተብላ ለማየት ስትሄድ ነበር መኪናዋን እያሽከረከረች መንገድ ውስጥ የገባችን ህፃን ልጅ ለማትረፍ ስትጥር መኪናዋ ተጋጭታ ሕይወቱዋ ያለፈው::"

" ይህን የሚስቴን ህልም እውን ለማድረግ ጥረት ላይ እያለው ህልሜን ይበልጥ ያቀጣጠለው ሰው! መምህር ቀቁ የኔን ህልም የሚጋራ ሀሳብ ይዞ ሲመጣ የተሰማኝን ደስታ በቃላት ለመግለጽ በጣም ተቸግሬ ነበር:: ት/ቤቱ ከተጀመረበት እና ለዛሬዋ የምርቃት ቀን እስከደረሰበት የነበረኝን ደስታ ለመናገር እቸገራለሁ:: ለኔ በሕይወት ዘመኔ ከሠራዋቸው ትልቅ ስራዎች ይህ ት/ቤት ግንባር ቀደሙ ነው:: ይህ ሲባል ግን ለዚህ እጅግ ዘመናዊ ት/ቤት የሚወጣው አጠቃላይ ወጪ 100 ሚሊየን ብር ታስቦ የነበረ ሲሆን አጠቃላይ ወጪው ግን 900 ሚሊየን ብር ነው፣ የኔ ድርሻ ከዚህ ውስጥ 60% ገደማ ነው::"



t.me/OLDBOOKSPDF

ሌሎች ባለሀብቶችም ለዚህ ት/ቤት መሳካት ትልቅ ድርሻ አላቸው:: ሁሉንም በአቢሲኒያ በከፍታ ት/ቤት ስም አመሰግናለሁ:: የኔ የወደፊት እቅድ ይህን መሰል እጅግ ዘመናዊ ተማሪዎችን በየወሩ ከፍተኛ ገንዘብ እያስከፈለ ሳይሆን እየከፈላቸው የሚያስተምር! ባለአምስት ኮከብ አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ት/ቤት በሌሎች ትላልቅ የኢትዮጵያ ከተሞች መክፈት ሳይሆን ይህን ት/ቤት ወደ ዝነኛ ዩኒቨርሲቲ ማሳደግ ነው:: የባለቤቴን ህልም ማሳካት ነው:: ውድ እና የተከበራችሁ እንግዶቻችን አሁን አንድ ትልቅ እንግዳ በመሀከላችን ይገኛሉ! አጠር ያለ ንግግር ያደርጉልናል... በድጋሚ ጥሪያችንን አክብራችሁ ስለመጣችሁ በጣም አመሠግናለሁ"

ግርማ ሞገስ ያላቸው፤ እጅግ በጣም ቸር ባለሀብት ናቸው፤ የሚባሉት የሲልቪቢያ አባት አቶ አቤንኤዘር በሚያምር ፈገግታ ተሞልቶው ከመድረኩ ወደ ተዘጋጀላቸው ወንበር ላይ አመሩ:: በዘመን መልኩ በተሰራው የት/ቤቱ አዳራሽ ውስጥ በርካታ ጥሪ የተደረገላቸው ጋዜጠኞች፤ ልዩ ልዩ እንግዶች... ባጠቃላይ 800 ሰዎች በተዋበው ዘመናዊ አዳራሽ ውስጥ ተቀምጠዋል:: ከፊት ለፊት ወንበር ሲልቪቢያ፤ መምህር ቀቁ፤ የት/ቤቱ ዋና ዋና አስተዳደሮች፤ ከመላው ኢትዮጵያ በብቃታቸው የተመረጡ ምርጥ መምህራን ፤ የት/ቤቱ ምግብ ባለሙያዎች፤ የንፅህና ባለሙያዎች ፤ ወዘተ ተቀምጠዋል:: ከሲልቪቢያ አጠገብ መምህር ቀቁ ከመምህር ቀቁ አጠገብ መምህር ሰለሞን የተቀመጠ ሲሆን መጀመሪያ ከሰው የአቶ አቤን ኤዘር ወንበር አጠገብ አንደኛው ወንበር ላይ 'ተይዟል' የሚል ፅሁፍ ቢኖርበትም የተቀመጠበት ሰው ግን የለም ... ይህ ወንበር ለማርያ ሙሴ የተዘጋጀ ነበር:: ማርያ ግን ከኢጣሊያ እስካሁን አልተመለሰችም...

አቶ አቤንኤዘር የተነሱበት ወንበር ላይ ደርሰው እስከሚቀመጡ ድረስ የ799 ሰው ታላቅ ጭብጨባ ተቀበላቸው:: ልክ ወንበራቸው ላይ እንደተቀመጡ ቆፍጣናው የመድረክ አስተዋዋቂ መድረኩ ላይ ወጣ:: " የተከበራችሁ እንግዶች ሰስት ፕሮግራሞች ናቸው የሚቀሩን እጃችሁ ላይ ያለውን የፕሮግራም ዝርዝር ወረቀት መመልከት ትችላላችሁ:: አሁን አንድ እጅግ ትልቅ እንግዳ አጠር ያለ ንግግር ያደርጋሉ፤ ከእርሳቸው ንግግር በመቀጠል አስደሳች የሆነው ክፍል ሁለት የጉብኝት ሥነ ሥርዓት ይከናወናል::



t.me/OLDBOOKSPDF

እንግዲህ ቅድም ት/ቤቱን ስትገቡ ሁላችሁም ማለት ይቻላል ስትደነቁ ነበር፡፡ ትምህርት ቤት ነው አለም አቀፍ ብቃቱን የጠበቀ ሆቴል ነው? የተሰራው ስትሉ ነበር ... የት/ቤቱን ዘመናዊ የላውንደሪ አገልግሎት ፤ ዘመናዊ መማሪያ ክፍሎች ፡ ዘመናዊ ወንበሮች፡ የመምህራን አስገራሚውን ማረፍያ፡ የአስተዳደር ቢሮዎች፡ ውበት ያላቸውን መፀዳጃ ቤቶች፡ የተማሪዎችን መመገቢያ እና መኝታ ቤቶች፡ የት/ቤቱን ሆስፒታል... አይታቹሀል ... ያላያችሁት ለሁሉም እንደ ምርጫቸው የሚስተናገዱበትን አራት የእምነት ቤቶች፡ የአትክልት ቦታዎች እንዲሁም ከምንም በላይ እጅግ ዘመናዊ ወንበሮች የተገጠሙለትን ደረጃውን የጠበቀውን 20ሺ ሰው የሚያስተናግደውን አቢሲኒያ ስታዲየውምን አልተመለከታችሁም! ይህ ዘመናዊ ስታዲየውም ለስብከት አገልግሎት ፤ ለሙዚቃ ዝግጅቶች፡ ለሠርግ እና ለእግር ኳስ ጨዋታዎች እየተከራየ ለት/ቤቱ የገቢ ምንጭ ከመሆኑ ባሻገር ዋነኛ አላማው በዚህ ት/ቤት ውስጥ የሚማሩ ብቃት ያላቸውን ተተኪ እግር ኳስ ተጫዋቾች እና ሯጮች ማፍራት ነው፡፡ የመጨረሻው ፕሮግራማችን በእለቱ ትልቅ እንግዳ የባንዲራ መስቀል ሥነ ሥርዓት ተደርጎ ይጠናቀቃል ! የተከበራችሁ እንግዶቻችን የዕለቱ ትልቅ እንግዳችን ወደ መድረኩ እየመጡ ስለሆነ በጭብጨባ ከተቀመጣችሁበት ተነስታችሁ እንድትቀበሉልን ከይቅርታ ጋር እጠይቃለሁ..."

ጭብጨባው ቀለጠ፡፡ የእለቱ ትልቅ እንግዳ መድረኩ ላይ ወጥተው የመነጋገሪያ ሳጥኑ ጋር ደርሰው እስከሚቆሙ በተዋበው አዳራሽ ውስጥ ያለው ሁሉ ተገረመ... ጉዳዩን የማያውቁት ውብ ሲልቪያ እና መምህር ቀቁ ራሳቸው በግራ መጋባት እና በግርምት እርስ በእርስ ተያዩ... የእለቱ እንግዳ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስቴር... ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ አንድ ጠቅላይ ሚኒስቴር ይህን መሰል አምስት ኮከብ ት/ቤት ሲያስመርቅ የመጀመሪያው ነው ... በት/ቤቱ ምርቃት ላይ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ይገኛሉ ብሎ ያሰበ አንድም እንግዳ እንኳን አልነበረም... ለዚህም ይመስላል ሁሉም በታላቅ ዝምታ ተዋጠ፡፡ አስራ ስምንት የሚሆኑ ፈርጠም ፈርጠም ያለ ሰውነት ያላቸው የጠቅላይ ሚኒስቴሩ ስውር ጠባቂዎች ወሳኝ ወሳኝ የሚባሉ ቦታዎች ላይ " ጋዜጠኛ" የሚል ወረቀት አንገታቸው



t.me/OLDBOOKSPDF

ላይ እንጠልጥለው የአዳራሹን ሁኔታ በከፍተኛ ትኩረት እየተከታተሉ ነው… ጠቅላይ ሚኒስቴሩ በፈገግታ ታጅበው ንግግር ጀመሩ፡፡

- በቅድሚያ የተከበራችሁ እንግዶች የልጅነት ጓደኛዬን ጌታ ሀልሙን እውን ስላደረገለት ክብር ለጌታ ይድረሰው ! ቅድም ሲነግራችሁ የነበረው ታሪክ የኔ ነው፡፡ ከአቢንኤዘር ጋር አራት ዓመት አብረን ተምረናል፡፡ ከዚያ ተለያየን ዛሬ ደግሞ ይህን በመሰል ትልቅ ፕሮግራም ላይ ከአቢንኤዘር ጋር በመገናኘቴ ደስታዬ ወደር የለውም፡፡ ይህ ሁሉ የጌታ ፍቃድ እና ድንቅ ስራ ነው፡፡ እኛ ከጣርን፣ ከለፋን ጌታ ይረዳናል፡፡ እንኳኑ ይከፈትላቹኋል ተባለ እንጂ በር ላይ ቁሙ ይከፈትላቹኋል አልተባለም፡፡ የተከበራችሁ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች በብቃታችሁ የተነሳ ተመርጣችሁ የመጣችሁ ምርጥ አስተማሪዎች ፤ ከተለያዩ የግል ሆነ የመንግስት ድርጅቶች ተወክላችሁ ወሬ ለመለቃቀም የመጣችሁ ጋዜጠኞች፣ ከፍተኛ የት/ት ሚኒስቴር ባለስልጣናት ፤ ልጆቻችሁ በዚህ ድንቅ ት/ ቤት እንዲማሩላችሁ በከፍተኛ ጥንቃቄ የተመረጣችሁ ወላጆች ፤ የተለያያችሁ ባለሀብቶች… ባጠቃላይ ከቡራን እና ከቡራት እንግዶች እንኳን በዚህ መሰል ምረቃ ላይ ስለተገናኘን እና ስለመጣችሁ በጣም አመሠግናለሁ፡፡ አቶ አቢንኤዘር ፤ መምህር ቀቄ፣ የskylight K ዋና ኃላፊ፣ ባይሻ ህንፃ ተቋራጭ፣ A.M.K.W የግል እርዳታ ተቋም… ባጠቃላይ በዚህ ት/ቤት ግንባታ ላይ አሻራችሁን ያሳረፋችሁ በሙሉ ለትውልድ የሚሆን ታሪካዊ ቅርፅ ስለሰራችሁ ልትኮሩ ይገባል፡፡ ት/ቤቱን በከፍተኛ ግርምት እየዞርኩ ተመልክቻለሁ! ቅድም እንደተባለው ት/ቤት ሳይሆን ባለአምስት ኮከብ ሆቴል ውስጥ ያለው ያህል ነው የተሰማኝ! በጣም ያምራል! መቼም ተማሪዎች በየዕለቱ መንፈሳቸው እየታደሰ እንደሚማሩ እምነት አለኝ! ት/ቤቱ በ60 ምርጥ መምህራን ፤ በ4 የሳይኮሎጂስት ባለሙያዎች ፤ በ15 አስተዳደሮች ፤ በ8 የጥበቃ አባላት፣ በ18 የምግብ ባለሙያዎች፣ በ14 ተተኪ ተጠባባቂ መምህራን … በሌሎችም ያልጠቀስኩላችሁ ባለሙያዎች ባጠቃላይ 256 ሰዎች አሉት፡፡ እንግዲህ ለ256 ሰዎች የሥራ እድል ተፈጠረ ማለት ነው፡፡ ከዚያም በላይ ለነገዋ ባለተስፋ ሀገር ኢትዮጵያ መመኪያ የሚሆኑ ድንቅ ተማሪዎችን ት/ቤቱ ያፈራል የሚል ፅኑ እምነት አለኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

" መንግስትም ይህን መሰል የተቀደሰ ሀሳብ ያላቸውን ባለሀብቶች ከመደገፍ እና ሞራል ከመስጠት ወደ ኋላ አይልም:: ለዚህም ነው ከሶስት ዓመት በፊት አቶ አቤንኤዘር እና መምህር ቀቂ ሀሳባቸውን አቅርበው የመሬት ጥያቄ ሲያነሱ ያለ እንዳች ጣጣ እና ዙሪያ ጥምጥም በ24 ሰዓት ውስጥ ይህ ውብ ት/ቤት የተሰራበት ግዙፍ ቦታ በነፃ የሰጣቸው:: ወደፊትም ይህን መሰል ለህዝብ የሚሆን ታሪካዊ ሥራ ለሚሠሩ ግለሰቦች ሆነ ባለሀብቶች የመንግስት ድጋፍ በፍፁም አይለያቸውም:: ለሀገራችን ኢትዮጵያ አጅግ ከሚያስፈልጉዋት ነገሮች አንዱ የተማረ ሰው ሃይል ነው:: ኢትዮጵያ ትልቅ ራዕይ አላት:: ይህን ራዕይ ለማሳካት ደግሞ አቢሲኒያ በከፍታን የመሠሉ ት/ቤቶችን መክፈት ተወዳዳሪ የሌለው ነገር ነው:: እውነቱን ለመናገር እዚህ ት/ቤት ያየሁት ነገር ሁሉ በእነዚህ ሰዎች ኩራት እንዲሰማኝ አድርጎኛል:: ከዚህ ት/ቤት ወደፊት የሚወጡትን በታላቅ ጉንታቄ እየተኮተኮቱ የሚያድጉ ተማሪዎችን ሳስብ ልቤ በሀሴት ይሞላል! የኢትዮጵያ ዘመን እንደ መጣ ይሰማኛል:: ት/ቤቱ እንደ ስያሜው ኢትዮጵያን በከፍታ ላይ የሚያስቀምጡዋትን ተማሪዎች እንደሚያፈራ ታላቅ እምነት አለኝ! ባጠቃላይ ይህን ትልቅ ራዕይ ያለውን ት/ቤት እንድመርቅ ስለጠሩኝ እና እድሉን ስለሰጡኝ ደስታዬ ወደር የለውም! ስላዳመጣችሁኝ ሁላችሁንም ከልብ አመሠግናለሁ:: አገራችንን ኢትዮጵያን እግዚአብሔር ይባርካት! ንግግሬን የምቋጨው አንድ ታሪክ ነግሬያችሁ ነው"

" እንዲት ኢትዮጵያዊት አንድም ቀን እንኳ ሳታቋርጥ ጠዋት ጠዋት ለእግዜር ጥያቄ ታቀርባለች... እግዜር ሆይ ኢትዮጵያ እና እስራኤል ቅዱስ ህዝቦቼ የሚኖሩባቸው ናቸው እያልክ! በኢትዮጵያ ህዝብ ደስ ይለኛል እያልክ! ኢትዮጵያ የሚለውን ስም ከማንም በላይ 40 ጊዜያት በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲጠቀስ አድርገህ... እኮ ለምን በኢትዮጵያ ላይ ዘወትር ግጭት! ርሀብ! ድህነት ! ዘረኝነት! ሙስና! ጦርነት ! መሀይምነት! ኃላቀርነት፣ ችግር ... ችግር... እዚህ ችግር... እዛም ችግር.... ችግር... የችግር አረንቋ ውስጥ ከተትከን ! እኮ ለምን ? እያለች ዘወትር ትጠይቃለች ከ18 ዓመቱዋ እስከ 28 ዓመቱዋ ለ10 ዓመታት ሳታቋርጥ ጠየቀች:: ታዲያ አንድ ጠዋት እግዜር መጣ:: እንደተለመደው ጠይቃ ስትጨርስ



t.me/OLDBOOKSPDF

እግዜር '10 ዓመት ሙሉ ይህን ነገር ከምትናገሪ ለምን ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ችግሮች አንዱን ብቻ እንኳ አቅምሽ የፈቀደውን ለመፍታት ጥረት አታደርጊም ?' አላት!! እንግዲህ ለእናንተም ማስተላለፍ የምፈልገው ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው ችግር ማውራት ሳይሆን ችግሩን ለመፍታት የበኩላችሁን ጥረት ማድረግ ነው! ኢትዮጵያ በዚህን ወቅት የምትፈልገውም ስለችግር የሚፈተፍተውን የተማረ ይሁን ያልተማረ ኢትዮጵያዊ ሳይሆን ስለችግሩ መፍትሔ ያለውን እና የግሉን ጥረት የሚያደርግን ግለሰብ ነው:: ወደ ፊት ከዚህ የአንድ ዓመት እቅድ ሳይሆን የአስራ ሁለት ዓመታት ግዙፍ ለኢትዮጵያ ሀገራችን እውነተኛ ታላቅ ለውጥ የሚያመጣ እቅድ ይዞ ከተነሳው ከአቢሲኒያ በከፍታ ት/ቤት የሚወጡ ተማሪዎች የኢትዮጵያን ችግር የሚፈቱ እና የአገር ፍቅር ልባቸው ውስጥ የሚቃጠል ተማሪዎች እንደሚሆኑ እምነቴ የበዛ ነው:: ለኔም ለእናንተም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማስተዋሉን ይስጠን:: በጣም አመሠግናለሁ"

ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ከነበሩበት ወንበር ላይ ተመልሰው ሳይቀመጡ በአስተናባሪዎች እየተመሩ ወደ ባንዲራ መስቀያው ማማ ላይ ሄዱ:: አዳራሹ ውስጥ የነበረው ህዝብ በእርጋታ ተከተላቸው....

ከሀያ ሰምንት ደቂቃዎች በኋላ ሁሉ ነገር ተዘጋጀ:: በእለቱ ድምቀት እንዲሰጡ የተመረጡት የፖሊስ ማርሽ ባንድ ሙዚቃ አቅራቢዎች ትምህርት ቤቱ የሚለውን ተወዳጅ ዜማ ከተጫወቱ በኋላ የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙርን አቀረቡ:: በጠቅላይ ሚኒስቴሩ አማካኝነት የኢትዮጵያ ባንዲራ አረንጓዴ! ቢጫ! ቀዩ! እርማ ከአቢሲኒያ ት/ቤት ላይ ተሰቀለ:: በንፋሱ የተነሳ ከግራ ቀኝ ይውለበለብ ጀመረ... በቦታው የነበረው ህዝብ በአንድነት ታላቅ ጭብጨባ አሰማ! ከእቶ አቢንኤዘር እና መምህር ተቱ ላይ የእንባ ዘለላ ጠብ ... ጠብ... አለ:: (ነገሩ ደስታ ስሜትን ያፈነቅልና ያስለቅሳል...)

* * *

እነሆ በስንት ጉጉት ሲጠበቅ የነበረው እጅግ የተለየው አቢሲኒያ በከፍታ ት/ቤት በታላቅ ድምቀት የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር በተገኙበት ሰኔ 28/2005ዓ.ም ተመረቀ::



t.me/OLDBOOKSPDF

በአካባቢው የሚንቀሳቀሱትን አዕዋፋት እንኳን ሲከታተሉ የነበሩት የጠቅላይ ሚኒስቱሩ ስውር የልዩ ሀይል ጥበቃዎች ጠቅላይ ሚኒስቴሩን በስውር እንዳመጧቸው በስውር ከቦታው ይዘው ተሰወሩ፡፡ የተቀሩት እንግዶች ወደ ጉብኝት ሥነ ሥርዓቱ ማገምራት ያዙ...

•  •  •

እጅግ ውብት የፈሰሰባት አንዲት ወጣት በህዝቡ መሀከል እየተሹለከለከች መምህር ቀቁ ወዳለበት ተጠጋች፡፡ መምህር ቀቁን ለማግኘት ሶስት ሰዓት ሙሉ ሳትሰለች በተጠንቀቅ እየተከታተለችው ነበር፡፡ አስደንጋጭ ውብት አላት፡፡ አረማመዷዋ የተለየ ግርማ ሞገስ አለው፡፡ የሰውነት አወቃቀሩዋ አማላይ ነው፡፡ በዘመናዊ መልኩ የተሰራ የሀገር ባህል ልብስ ለብሳለች... እንደምንም ብላ እጁዋን በመስደድ የመምህር ቀቁን ጅርባ ነካችው፡፡ መምህር ቀቁ ዞረ፡፡ አያት፡፡ በውበቷ ተደነቀ፡፡ ሁሊ እንደተደነቀ ነው፡፡ ምክኒያቱን ባይረዳውም ውብት ያላቸው ሴቶችን ሁሌ እንደተመለከተ ነው፡፡ ይቺ ደግሞ ቁርጥ ሱዛንን የመሰለች ስለ ነበረች ልቡ ድንገት ሱዛንን አስታወሰና ከው አለ... ከፊት ለፊቱ የቆመችው ውብ ወጣት ሳትጨናንቅ በእጁዋ ይዛ የነበረውን ጥቅል አበባ አያቀበለችው " ታላቁ ህልምህ እውን ሆኖ ስላየሁት እጅግ በጣም ተደስቻለሁ! አንተንም እንኳን ደስ አለህ"

" በጣም አመሰግናለሁ" አላት እቅፍ አበባውን እየተቀበላት፡፡

" አዲስ አበባ አንድ ሳምንት ብቻ ነው የምቆየው ስለዚህ ሐምሌ ሁለት ከጠዋቱ 4፡00 ላይ ሂልተን ሆቴል እጠብቅሀለሁ፡፡ ብቻህን ና! በድጋሚ ህልምህ ስለተሳካ እንኳን ደስ አለህ አላለሁ"

" በጣም ይቅርታ አላወኩሽም"

" ሐምሌ ሁለት 4፡00 ላይ እንገናኝ" ብላው ሄደች፡፡ ተሰወረች፡፡ መምህር ቀቁ ግራገባው ከራሱ ሀሊና ጋር መነታረክ ያዘ '... ማን ናት..ማን ነበረች?... ለምን ቀጠረችኝ...? ' መልሱ ግን በፍጥነት ሊመጣለት አልቻለም፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# 2

## ሰኔ 28/10/2005

### ከምሽቱ 1፡35

### እነ ሲልቪቪያ መኖሪያ ቤት

አቶ አቤንኤዘር ታላቁን ደስታቸውን እንደጨረሱ በቀጥታ ያመሩት ወደ ቦሌ አየር መንገድ ነው፡፡ ለአስቸኳይ ስራ ወደ አየርላንድ አምርተዋል፡፡ ለሸኘት ቦሌ ኤርፖርት የሄዱት መምህር ቀቁ እና ሲልቪቪያ በቀጥታ የመጡት ወደ ዘመናዊው የእነ ሲልቪቪያ መኖሪያ ቤት ነበር፡፡ ሁለቱም ሰውነታቸውን ታጠቡ፤ ቀለል ያለ ምግብ ተመገቡ... በአሁኑ ሰዓት እጅግ የሚያምረው ሳሎን ውስጥ ተቀምጠዋል...

" ዛሬ መቼም ጥለኸኝ አትሄድም እዚው እንደምታድር እርግጠኛ ነኝ" አለችው በፍቅር ዓይን እየተመለከተችው፡፡ ሲልቪቪያ፡፡

" በሕይወቴ እንደ ዛሬ ተደስቼ አላውቅም! ት/ቤቱን እንደምከፍተው እርግጠኛ ነበርኩ ግን ይሄን ያህል ውብ ሆኖ ባለአምስት ኮከብ ት/ቤት ይሆናል የሚል ግምት አልነበረኝም ለዚህ ሁሉ መሳካት ትልቅ ምስጋና የሚገባሽ አንቺ ነሽ፡፡ በአጋጣሚ ካንቺ ጋር ባልገናኝ አንቺ ከአባትሽ ጋር ባታስተዋውቂኝ ህልሜን ለማሳካት ረጅም ዘመናት ይፈጅብኝ ነበር፡፡ እውነቴን ነው በጣም ነው የማመሰግንሽ!!"

ድንገት ሳያስበው ዘላ ጥምጥም አለችበት፡፡ አቤት የሰውነት ጠረኑዋ! መዓዛው... ልብን የሚያሸብር አስደሳች መዓዛ... መምህር ቀቁ አንዳንድ ጊዜ በሲልቪቪያ ሁኔታ ግራ ይጋባል... ይደነግጣልም... ድንገት ዘላ ጥምጥም የምትልበት ሁኔታዋን ይፈራዋል... ሰውነቱን የሆነ ነገር ውርር ያደርገዋል፡፡ "አሁን እሱን ተውና ይልቅ ታድራለህ? አታድርም"?" አለችው፡፡

" በሚገባ እንጂ"

t.me/OLDBOOKSPDF

" በጣም አሪፍ! አሁን የምትወደውን ቀለል ያለ ወይን አመጣልሀለሁ! ስለደራሲው ትነግረኛለህ እኔ ደግሞ የጎልያድ ሳቅ ክፍል ሁለትን ስለ ጨረስኩ ታነብዋለህ... መጣሁ! ዘና በል" ብላው:: ሄደች:: መምህር ቀቁ አያት:: ድንገት የዘነኛው ሚኒሊክ ወስናቸው ድንቅ ሙዚቃ አንቃጨለበት! "

... ስለ ውበቷ ሳስብ ቀኑ መሽቶ ይነጋል ወሮች ሊሊት ሲንጫጩ ታዝበውኝ ይሆናል... ሲልቪያ ብዙም ሳትቆይ መምህር ቀቁ የሚወደውን ወይን ይዛለት መጣች:: በአነስተኛ ብርጭቆ ቀዳችለት ፣ ለራሷም ቀዳች... ለጤናችን ተባብለው ተጎነጩ:: ጠረጴዛው ስር የነበረውን አጀንዳ አወጣች:: የጎልያድ ሳቅ ክፍል ሁለት እና የኢየሱስ ሳቅ የፃፈችበት ማስታወሻ ደብተሯ ነው::

" ይህ የጎልያድ ሳቅ ክፍል ሁለት እና የኢየሱስ ሳቅ የፃፍኩበት ነው:: በነገራችን ላይ የጎልያድ ሳቅ ላይ በክፍል ሁለት እስከ ገጽ 28 ከጻፍኩ በኋላ ሀሳቤን ቀይሬው ሌላ ርዕስ በመስጠት ለየት ባለ አፃፃፍ የጎልያድን ታሪክ ፅፌዋለሁ"

" አልገባኝም"

" በክፍል አንድ ጎልያድ እጅግ በጣም አንባቢው ፣ አወዛጋቢው፣ ለፍላፊው ፣ ስለማንኛውም ነገር ብትጠይቀው ምላሽ የማያጣው ጎልያድ ብዙዎች ሲደነቁበት ስለፍልስፍና ፖለቲካው ፣ አግርኳሱ፣ ውበት፣ መፅሐፍ... የሚያስረዳው ... ሳያስበው በአሸዋሪያ ፍቅር የተያዘው በሌላ በኩል አሸዋሪያ ወደ ጎልያድ የቀረበችው ጓደኛዋ ዊንታዘር ጎልያድን አፍቅራ ለማስተዋወቅ በሚል የነበረ ሰበብ ቢሆንም በመጨረሻ ሁለቱም ሴቶች በጎልያድ ፍቅር ተይዘው እንደነበር አንብበሀል ... ታሪኩን በዚያው ቀጥዬ ነበር:: ሶስቱም ወጣቶች ከዩኒቨርሲቲ ተመርቀው ዳግም በሕይወት አጋጣሚ በስራ ጉዳይ ተገናኝተው .... ጎልያድ ከሁለቱ ሴቶች ማንን መምረጥ እንዳለበት ሲወዛገብ ... ሁለቱ ጓደኛሞችም በፍቅር የተነሳ ሲወዛገቡ... ባጠቃላይ ፍቅር ፍቅር የሚሸት መፅሐፍ አንበለው ታሪክ ነበረው:: እንዳልኩህ ወደ ሀያ ስምንት ገፅ ገደማ እንደፃፍኩ ድንገት ሌላ ሀሳብ መጣልኝ:: አሰብኩት:: በጣም ሳሰበው ወደድኩት:: ጎልያድን ጋዜጠኛ አደረኩት:: የራሱን FM ፕሮግራም ሰዓት



t.me/OLDBOOKSPDF

አስገዛሁት:: ጎልያድ አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል የሚል ፕሮግራም ይዞ በFM 66.6 ኩተፍ አለ:: ፃፍኩት ! በእርግጠኝነት ትወደዋለህ" አለችውና ጠረጴዛው ላይ አስቀመጠችለት::

" እስከማነበው ቸኩያለሁ! እንደ በቆጂው ፈረስ ዘና የሚያደርግ ምርጥ ታሪክ መሆን አለበት"

" በእርግጠኝነት ትወደዋለህ ይልቅ ስለደራሲው ንገረኝ! ለአራተኛ ጊዜ ተገናኝታችሁ ነበር ፤ ምን አወራልህ? ስለደራሲው ስትነግረኝ በጣም እደሰታለሁ! ሴት ልጅ በመስማት ወንድ ልጅ በማየት ፍቅር ይይዛቸዋል የሚባለው ትልቅ እውነት ነው:: አንተ የምታወራለት ደራሲ በሕይወት ቢኖር ኖሮ በእርግጠኝነት የኔባል ነበር የሚሆነው! ሕይወትን በቀላሉ የሚመለከት ቀና አመለካከት ያለው! ሕይወትን በማሰብና በምኞት ሳይሆን በተግባር የሚኖር አይነት ሰው ይመስለኛል! ተሳስቻለሁ?"

" ሙሉ ለሙሉ ልክ ነሽ?"

" በአራተኛው ቀጠሮ ምን አወራልህ?"

" እንደተለመደው ቻርሊ በጠዋት ቀስቅሶኝ በፍጥነት ቁርስ እንድበላ አዘዘኝ:: ከደራሲው ጋር ለመጨረሻ ጊዜ ትገናኛለህ ከዚህ በኋላ ወደ አርጀንቲና ስለሚያመራ አታገኘውምና ፍጠን ሲለኝ ሁለት የተዘበራረቀ ስሜት ነበር የተሰማኝ:: ሀዘን እና ደስታ! ስለማገኘው ተደሰትኩ... ስለማጣው ደግሞ አዘንኩ:: 5:40 ደቂቃ ላይ ተገናኘን:: እጅግ ጣፋጭ በልቼ የማላውቀውን ምሳ አበላኝ:: በእጁ ሁለት ግዙፍ የኢንግሊዝኛ መፅሐፎችን ይዞ ነበር:: የፍልስፍና ነበሩ:: አንደኛው የታላቁ ፈላስፋ የሶቅራጠስ ነበር ሁለተኛው የኮንፊሺየስ ታሪክን የሚያወራ መፅሐፍ ነበር::

" አርጀንቲና ልትሄድ እንደሆነ ቻርሊ ነገረኝ" አልኩት ወሬ ለመጀመር::

" እውነት ነው"

" የዩኒቨርሲቲ ትምህርትህን ሳትጨርስ? ወይስ እዛ ልትቀጥል አስበህ ነው?"

" የኢትዮጵያ ዲግሪ ውጪ ሀገር እምብዛም ተቀባይነት የለውም:: ካስቀጠሉኝም ከ High school ነው:: አንዳንድ ጊዜ አንድን ነገር ለማግኘት ሌላውን ማጣት አለብህ



t.me/OLDBOOKSPDF

በዚያ ላይ በምንታቸው እና በእውቀት እንኳ ከኔ ከማይሻሉ የዩኒቨርሲቲ አስተማሪዎቼ ተመርቄ ዲግሪ ያገኙ ከምል ቢቀርብኝ የተሻለ ነው:: የእውቀት ጥማቱ ስላለኝ በሚያከብሩኝ እና በማከብራቸው አስተማሪዎች ወደፊት አርጀንቲና ውስጥ መማሬ አይቀርም:: አንተም አስተማሪውን እየናከ አስተማሪውም አንተን እየናቀ የመማር ማስተማር ሂደቱ አሉታዊ ነው:: እነዚህን መፅሐፎች ወደፊት ካገኘሀቸው እንበባቸው ብዙ ነገር ትማርበታለህ! ስለ እውቀት ምንነት ሶቅራጠስ ይነግረሀል፤ ስለ ሕይወት ኮንፊሺየስ ብዙ ይነግርሀል:: እኔ ከሁለቱም መፅሐፎች አንዳንድ ታሪኮችን ልንገርህ ስለ ሶቅራጥስ ከዚህ በፊት ሰምተሀል?"

" በመጠኑ"

"ጥሩ ነው! በአቴና ከተማ እጅግ የሚከበር አንድ አዋቂ ... ጥበብ የተገለጠበት ነው የሚባል አንድ የተከበረ ሽማግሌ መምህር በጣም በርካታ ተማሪዎችን ሰብስቦ እያስተማረ ነበር:: ተማሪዎቹም በፀጥታ እያዳመጡት ነበር 'ዛሬ ስለ መልካም ነገር እና መጥፎ ነገር እናወራለን:: የትክክለኛ እና የጤነኛ ሰው መገለጫው የሚያደርገው መልካም ነገር ነው:: መልካም ነገር ያደረገ ሁሉ ትልቅ ሰው ነው::"

"ለምሳሌ አንድ ሰው ታሞ ብናውቀውም ባናውቀውም ወደ ሀኪም ከወሰድነው የመልካምነት ምልክት ነው:: ጠላታችን የሆነ ሰው ታሞ ከመንገድ ላይ ተመልክተነው በሀዘን ተውጠን ወደ ሀኪም ከወሰድነው የበለጠ የመልካምነት እና የጥሩነት መገለጫ ነው:: ቀጥሎ መልካምነትን እንዴት ማሻሻል እንችላለን የሚለውን እንመለከታለን ምክኒያቱም በሕይወታችን ውስጥ ትልቁ ቁም ነገር መልካም መሆን! አዋቂ መሆን! እና ሕይወትን ማወቅ ነው' እያለ ሳለ ሳይታሰብ የ12 ዓመቱ ሶቅራጠስ ከቦታው ደረሰ:: ከሶቅራጥስ አንዱ የተለየ ስጦታ ሰዎች የሚያወሩትን እጅግ ሩቅ ከሆነ ቦታ የከንፈራቸውን እንቅስቃሴ ብቻ በመመልከት መረዳት መቻሉ ነበር:: ከቦታው እንደ ደረሰ ከማማው ላይ የቆመውን የተከበረ ሽማግሌ መምህር እና ከስሩ ያሉትን በርካታ ሰዎች (ተማሪዎች) በግርምት እየተመለከተ " አቶሬ (መምህር) ይቅርታ ጥያቄ ማንሳት ይቻል ይሆን" ሲል



t.me/OLDBOOKSPDF

ሶች:: ከስፍራው የነበሩት 25 የ12 ዓመት ብላቴና የሆነውን ሶቅራጥስን ሲመለከቱ ተደነቁ:: በተለይ በጣም የሚያከብሩትን እና የሚፈሩትን አቶሬያቸውን ንግግር ስላቋረጣቸው ደነገጡ:: ሽማግሌው መምህር በመጠኑ እየተበሳጩ 'ጠይቅ! ምንድ ነው ጥያቄህ አንተ ትንሽ ብላቴና?' አሉት::

'ትልቅ ምስጋና አቀርባለሁ! እንደ ሰማሁት በሕይወታችን ውስጥ ትልቁ ቁም ነገር መልካም መሆን፣ አዋቂ መሆን፣ እና ሕይወትን ማወቅ ነው ብለዋል አይደለም መምህር?'

'ትክክል'

' ለመሆኑ ለእነዚህ ተማሪዎች መጀመሪያ ስለ እውቀት ምንነት... ስለ መልካምነት ምንነት... ስለ ሕይወት ምንነት አስረድተዋል?'

' አላስረዳሁም'

'ለምን አላስረዱም'

'አልጠየቁኝም'

' እህ ካልተጠየቁ አያስረዱዋቸውም ማለት ነውን? እሱም ይቅር ለመሆኑ እነዚህ ተማሪዎች እነዚህን ጥያቄዎች ለምን ያልጠየቁ ይመስሎታል'

' አላውቅም'

' ስለ ከባዶቹ እውቀት ፣ መልካምነት ፣ ሕይወት ካወቁ እንዴት ፊት ለፊትዎ የተቀመጡትን ተማሪዎች ማንነት ማንበብ አልቻሉም ? እንዴትስ የማያውቋዋቸውን ተማሪዎች ለማስተማር ይጥራሉ? ይሄም ይቅር ለመሆኑ እርሶን እነዚህ ተማሪዎች እንደ ሚፈሮት እና ጥያቄ መጠየቅ እንደሚፈሩ ያውቃሉ? ተማሪ አስተማሪውን ከፈራ አስተማሪው እያስተማረ ሳይሆን በተቀደደ በርሜል ውስጥ ውሃ እየጨመረ ያለ ሚስኪንን ሰው ይመስላል! ለመማር መጀመሪያ ነፃነት ያስፈልጋል እነዚህ ተማሪዎች ደግሞ ጨርሶ ነፃነት የላቸውም:: ሌላው ይቅርና አንድ ጥያቄ ብቻ ልጠይቆትና ልሂድ ለመሆኑ እርሶ አዋቂ ኖት'

' ይመስለኛል'



t.me/OLDBOOKSPDF

' ለመሆኑ አዋቂ ለመሆኑም ማስረጃዎ ምንድ ነው ወይም  አዋቂ ነኝ  የሚሉት አዋቂ ነኝ ስላሉ ነው ወይስ አዋቂ ኖት ስለተባሉ ነው? ለመሆኑ እውቀት ራሱ ምንድ ነው?'

" ትልቁ መምህር  የሚመልሱት ምላሽ  ስላልነበራቸው:: በዝምታ ከቆሙበት ማማ ላይ ወርደው ሄዱ::  ተማሪዎች ለትንሹ ሶቅራጠስ አጨበጨቡለት:: ትንሹ ሶቅራጠስ ግን ሁሉንም በትኩረት እየተመለከተ ' አሁን  ነፃናችሁ!  እውቀትን ፈልጉ!  ስለ እውቀት ከኔ ቀድማችሁ  ካወቃችሁ አደራ ትነግሩኛላችሁ'  በማለት ባሉበት ጥሎዋቸው ሄደ:: እንግዲህ በእነ ሶቅራጠስ ዘመን  የነበረው ክፍተት በዚህ ዘመን በኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ካለው ጋር ይመሳሰላል:: ተማሪው የውሸት ይማራል! አስተማሪውም የውሸት ያስተምራል:: አንድ ጊዜ አንድ መምህር ምን እንዳደረገ ታውቃለህ? 300 ገፅ ያለው መፅሐፍ ይዞ መጣ 'ይህን  መፅሐፍ በደንብ አንብቡ ሳምንት ፈተና አለ' ሲል ተናገረ እጄን አውጥቼ ጠየኩት 'በቃ ፈተናው ማንበብ ከዚያ መፈተን ነው! የዩኒቨርስቲ ት/ት ማለት በቃ ይሄ ነው?' አልኩት እየሳቀ 'ስማ ከፍ ያለች ሚስማር የመዶሻ ሲሳይ ትሆናለች' የሚለውን ተረት ታውቃለህ? የማዝህን ብቻ በዝምታ ፈፅም! ይህ ዩኒቨርሲቲ ነው! መብት ፡ ዲሞክራሲ አለኝ እያልክ እፈነዳለሁ ብትል የእንጀራ ገመድህ ይበጠሳል አለኝ:: በቃ እውቀት ማለት በኛ ዩኒቨርሲቲዎች ታነባለህ ትፈተናለህ! ከፈተናው በኋላ ያነበብከውን ትረሳዋለህ!! ማንበብ ⟶

መፈተን ⟶ መርሳት = Ø በቃ ስትመረቅ አዕምሮህ ውስጥ  የሚቀመጠው Ø ነው!

ምንም ነገር የለም! ትመረቃለህ:: ሥራ ፍለጋ ማስታወቂያ በማንበብ ጊዜህን እና ጫማህን ትጨርሳለህ... ይህን የመሰሉ ነገሮች ስመለከት ነው: በፍጥነት ወደ አርጀንቲና ለማምራት የወሰንኩት:: ለማንኛውም ስለ ኮንፊሽየስ ልንገርህ  ታላቁ የቻይና ፈላስፋ እና የለውጥ ምሳሌ ለመሆን የበቃው ኮንፊሺየስም ባንድ ወቅት በዝምታ ተቀምጦ እያሰበ የእርሱ ተማሪ ለመሆን ታላቅ ጉጉት ያላቸው ሶስት ተማሪዎች መጡ :: ከፊት ለፊቱ ቆሙ::" 'መምህር ሆይ አስተማሪያችን እንድትሆን እንፈልጋለን'  አሉት:: ታላቁ ኮንፊሺየስ ሶስቱንም ወጣቶች በትኩረት ተመለከታቸው:: ትዕግስታቸውን ለመፈተን ለግማሽ ሰዓት ያህል  ዝም አላቸው:: ወጣቶቹ በዝምታ  ታላቁ መምህር እንደበቱን እስኪከፍት ጠበቁት::  ታላቁ መምህርም



t.me/OLDBOOKSPDF

ከግማሽ ሰዓት በኋላ በትኩረት እየተመለከታቸው " ከኔ ምን ትሻላችሁ" አላቸው::

የመጀመሪያው " እውቀት እና ተግባርን"

ሁለተኛው " የሕይወትን ምንነት"

ሶስተኛው " እርሶ ለኔ አስፈላጊ ነው የሚሉትን ሁሉ"

" ታላቁ ኮንፊሺየስ ሶስቱን ወጣቶች በትኩረት እየተመለከተ ለሁለተኛው ወጣት የሕይወት ምንነት እኔ ጋር የለችም! ሕይወት ተግባር ናት ስለዚህ ከኔ ጋር የምታጠፋው ጊዜ የለምና ሂድ አለው ... ወደ ሶስተኛው ወጣት እየተመለከተ አንተም የምትፈልገውን ነገር በውል አታውቅምና ወደ ቤትህ ሂድ አለው! እውቀት ያለውን ወጣት እየተመለከተ 'አንተ ከኔ ጋር ትቆያለህ አብረን የእውቀትን ምንነት እና ተግባርን እንፈልጋለን' አለው ከዚህ የምንማረው ትልቅ ቁም ነገር በሕይወት ውስጥ በተለይ በአስተማሪና ተማሪዎች መሀከል ሊኖር የሚገባው ትልቅ ነገር ማሳወቅ ብቻ ሳይሆን እውቀትን በተግባር እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ማሳወቅ ነው:: ለዚህ ነው በኛ ሀገር የጋን ውስጥ መብራት የሚሉት ወይም ፈረንጆቹ ያወከውን ነገር እንዴት እንደምትጠቀምበት ካላወከው ከንቱ ነው የሚሉት:: በኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ያለው ትልቁ የብቃት መለኪያ ማንበብ ያነበብከውን መፈተን ነው! ይህ ደግሞ ለተማሪውም ለውጥ የለውም! ለሀገሪቱም ለውጥ አያመጣም:: ሀገሪቱ ለምትፈልገው ለውጥ ሆነ እድገት የኢትዮጵያ ወጣቶች የሚያስፈልጋቸው ማንበብ ⟶ መፈተን ⟶ መርሳት = Ø ሳይሆን በእውቀት እና ተግባር የታነፁ ተማሪ ዎችን! ወጣቶችን ነው! ብቻ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ እያሌ ችግሮች አሉ:: ችግር ደግሞ ጥሩ ነው:: በዓለማችን ላይ አሁን የምናያቸው ትላልቅ ሀገራት ሁሉ ትላንት ችግር ነበረባቸው:: በፈተና የተሞሉ ነበሩ:: ለለውጥ አንዱ ምርጥ ነገር ችግር ነው:: ለሚያጋጥምህ ችግር መፍትሔ ስትፈልግ ያኔ ለውጥ ይመጣል:: ለማንኛውም ዛሬ በመጨረሻ ቀጠሮዎችን ስለ ሰው ልጆች ባህሪያት እና ስለ ሀይማኖት ልነግርህ አስቤ ነበር:: ብዙ ሰዓት ስለሌለኝ በእነዚህ በሁለቱ ዙሪያ 20 ገፅ የሚሆን ማስታወሻ አዘጋጅቼልሃለሁ ቤትህ ዘና ብለህ በጥንቃቄ እንብባቸው! ከምንም በላይ በድርሰት ውስጥ ለመሳተፍ ስለ ሰው ልጆች ባህሪያት እና ስለሀይማኖት



t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ምንነት ማወቅ አለብህ፡፡ የሰው ልጆችን ባህሪያት ከለየህ የምትፅፈው ገፀባህሪ ምን አይነት አመለካከት አለው? ፍላጎቱ ምንድ ነው? በሕይወቱ ምን ምን ይፈልጋል? ምን ግጭት ይገጥመዋል? እምነቱ ምንድ ነው? ለምን አመነ? ወዘተ የሚለውን መለየት ትችላለህ ፡፡ ሁለት ሰዎች ተፋቀሩ ካልክ ለምን ተፋቀሩ? ፍቅር ምንድ ነው? ሁለቱ ሰዎች መሀከል ያለው የፍቅር አይነት ምንድ ነው? መሰል ጥያቄዎችን ማወቅ አለብህ! በድርሰት ውስጥ ለአንድ ድርሰት እጅግ አስፈላጊው ነገር የላላ ሳይሆን የጠበቀ ግጭት እና አፀመዋቅር በቅድሚያ ማዘጋጀት ነው፡፡ ምንግዜም ደግሞ ከመፃፍህ በፊት በቅድሚያ ምርጥ ሀሳብ ማግኘት አለብህ! ጥሩ ሀሳብ ካላገኘህ በተለይ አዲስ ሀሳብ ካልሆነ ባትፅፍ ይመረጣል፡፡ በተለይ ወደዳት ወደደችው... አይነት ፍሬፍስኪ ነገር መፃፍ የለብህም፡፡ ጠንካራ ስብዕና ሊኖርህ ይገባል! ለምትሰራው ወይም ለመስራት ለተዘጋጀኸው ነገር ታማኝ መሆን አለብህ! መነሻና መድረሻህን ቀድመህ ማወቅ አለብህ! ለማግኘት የምትፈልገውን ነገር እወቅ ያን የምትፈልገውን ነገር ካገኝህ በኋላ ምን እንደምትሰራበትም አስቀድመህ እወቅ፡፡ የዚያን ጊዜ ሕይወት ቀላል ትሆንልሀለች፡፡ ሕይወት ማለት ማሰብ አይደለችም፤ ሕይወት ማለት በ እውቀት መሞላት ማለት አይደለችም ፤ ሕይወት ግራ መጋባት ማለት አይደለም፤ ሕይወት ማለት በጥያቄ መሞላት አይደለም .... ሕይወት ማለት ማወቅ ማለት እና ያን ያወከውን ነገር በተግባር ማሳየት ማለት ነው፡፡ ከምንም በላይ በመጨረሻ የምትገርህ ነገር ምንም ነገር ከመስራትህ አስቀድመህ መወሰን ያለብህ ትልቅ ቁም ነገር የምትሰራውን ነገር በእርግጠኝነት እንደምታሳካው ካመንክ አድርገው ፡፡ መጠነኛ ጥርጣሬ እንኳን ካለህ በጭራሽ እንዳትሞክረው! አይሳካልህም ግራም ቀኝም ነፈሰ በሕይወትህ የሆነ ትልቅ ነገር ሳትሰራ እንዳትሞት!! በተረፈ በሥነ ፅሑፍ ውስጥ ከፍተኛ ሥራ ለመስራት ከፈለክ መፅሐፍ ቅዱስን በእርጋታ አንብብ! ግዕዝ ለመማር ሞክር በግዕዝ ቋንቋ የተፃፉ በርካታ ሥነ ፅሁፍን የሚያነቃቁ ግብዓቶችን ታገኛለህ! ከምንም በላይ ድርሰት መጨነቅ እና ራስን መጣል አይደለም፡፡ ይህን መሰል ስሜት ከፈጠረብህ በፍጥነት ትተህው ሌላ ሥራ መስራት አለብህ፡፡ ስላገኘሁህ በጣም ተደስቻለሁ ሌላው የፃፍከውን ፅሁፍ ሰው አንብቦ አስተያየት እንዲሰጥህ



t.me/OLDBOOKSPDF

ስትሰጥ ኮፒ አድርገህ ስጥ! ወይ ሊጠፉ አልያም ለትሰረቅ ትችላለህና' በማለት 4,000 ብር እና የታሸገ ፖስታ ሰጥቶኝ ግንባሬን ስሞኝ ለመጨረሻ ጊዜ ተለየኝ::"

"ቢታ"

" አለቀ! ከዚያ በኋላ ደራሲውን አላየሁትም! በሰጠኝ ብር ከቻርሊ ጋር መርካቶ ሄደን ለቅርብ ጓደኞቻችን በሙሉ አልባሳት ገዝተን ተመለስን! በተረፈው ብር ጠጣንበት ፣ በላንበት፣ ተደሰትንበት"

" ስለሰው ልጆች ባህሪያት እና ስለ ህይማኖት የሰጠህን ማስታወሻ መቼ አነበብከው"

"በሕይወቴ ከሠራሁት ስህተቶች መሀከል አንደኛው ይህ ጉዳይ ነው:: በሁለተኛው ቀን ደራሲው የሰጠኝን ማስታወሻ ላነበው ከመኝታ ቤታችን ጀርባ ባለው መናፈሻ ውስጥ ተቀመጥኩ:: ላነበው ፖስታውን ከፈትኩት:: በመሀከል ታሪኩ መጥቶ ጠራኝ:: በዕለቱ ቤት የመወልወል ተራ የኔ ነበር:: ቤቱን ከታሪኩ ጋር እየተሳሳቅን አፀዳነው:: በዕለቱ ዝናብ እየዘነበ ነበር:: ቤቱን አፅድተን ስንጨርስ ያደራሲው የሰጠኝ ማስታወሻ ትዝ አለኝና በድንጋጤ ወደ አስቀመጥኩበት ቦታ ሳመራ ወረቀቱ ሁሉ በሀይለኛው ዝናብ በስብሶ ከጥቅም ውጪ ሆኖ ነበር:: በጣም አዘንኩ:: ወደ ቢልጂየም ሄጄ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ እያለሁ እና ማንነቴን መፈለግ ስጀምር በእርግጠኝነት ደራሲ እሆናለሁ የሚለውን ምኞቴን በአራት ነጥብ ዘጋሁት::"

" ለምን? ከዚህ ውሳኔ ላይ ደረስክ"

"ትልቋን ሚና የተጫወተችው ያቺ ምርጥ ሴት ሰዛን ነበረች:: እንዴኔ ግን ድርሰት የሚሳካልህ አይመስለኝም ስለ ሕይወት ብዙ የማታውቀው ነገር አለ:: በተለይ ስለ ሴቶች ምንም ነገር አታውቅም እኔ የምመክርህ በአስተማሪነትህ ቀጥለህ በዓለማችን ላይ ድንቅ የሚባለውን ት/ቤት አከፍታለሁ የሚል ራዕይ አንግበህ ብትነሣ የሚሳካልህ ይመስለኛል ስትለኝ ለምን እንደሆነ ባላውቀውም ልቤ አመናት አለኝ:: አመንኩዋት! ደራሲ እሆናለሁ የሚለውን ሀሳቤን ወደ መቃብዕር ላኩት:: ነገ ወጣሁ:: ከዚህ በፊት እንደነገርኩሽ የአስተማሪውን ማስታወሻን የፃፍኩት የድርሰት ችሎታው ስላለኝ አይደለም... ውስጤ



t.me/OLDBOOKSPDF

የታጨቀውን ሀሳብ ለማስተንፈስ ብቻ ነው። ባጠቃላይ ከዶራሲው ጋር የነበረኝ ውይይት ይህን ይመስል ነበር"

" በጣም ደስ ይላል"

ዝም አላት። በአዕምሮው ላይ የምትመላለሰው ያቺ ውብ! ያቺ ቀና! ያቺ ሚስኪን! ያቺ የ9/ዘ ሰለባ! የሆነችው የተለየች ሴት ሱዛን ነበረች። ሕይወት እጅግ ድንቅ ከሆነች ወጣት ጋር አገናኘችው... በሞት ለየችው። 'ለነገሩ ይቺን ከመሰለች እግዜር ውበትን፣ ጥበብን፣ ማስተዋልን፣ ቀናነትን ሞልቶባት ከፈጠራት ድንቅ ሴት ጋር ለሁለት ሰዓት ራሱ ማውራት በቂ ነው ' አለ ለህሊናው። የመምህር ቀቁን በሀሳብ መንገድ ያጤነችው ውቡዋ ሲልቪያ በፈገግታ ተሞልታ "መኝታ ቤቱ በሚገባ ተዘጋጅቶልሀል! መተኛት ትችላለህ! ቀኑን ሙሉ ስትራወጥ ስለ ነበር ያወጣኸውን ጉልበት ለመመለስ እንቅልፍ መተኛት አስፈላጊ ነው" በማለት መምህር ቀቁ ምንም ሳይናገር ከተቀመጠበት ወንበር ላይ ተነስታ እቅፍ አድርጋ ስማው ተሰናበተችው ። መምህር ቀቁ ብዙም ሳይቆይ ወደ ተዘጋጀለት የተዋበ መኝታ ቤት ገባ። አልጋው ውስጥ አልባሳቱን አውልቆ ዘለቀ። ለመተኛት ሞከረ። እንቅልፍ ግን የለም! በሕይወቱ የዛሬዋ ነሀሴ 28 ትልቅ የደስታው ቀን ናት! ለዘመናት ሲመኘው የነበረው ምኞቱ! የዘመናት ህልሙ! እውን የሆነበት ቀን ዛሬ ነችና! በደስታው የተነሳ እንቅልፍ ጠፋ!

ድንገት የሲልቪያ አዲስ የሰጠችው FM66.6 የተሰኘውን የጎልያድን ታሪክ አስታወሰና ወደ ሳሎን አምርቶ ከጠረጴዛው ላይ የሲልቪያን የማስታወሻ አጀንዳ ይዞ ተመለሠ። አልጋው ላይ ወጣ። ትራሱን አስተካከለ። ተመቻችቶ ተቀመጠ።

FM66.6ትን ማንበብ ጀመረ።

* * *

ሲልቪያ ከግራ ቀኝ ተገላበጠች። እንቅልፍ ጠፋ! ማሰብ ገባች። ከሁለት ሳምንት በፊት ከባለሀብቱ አባቱዋ ጋር ባቦጋያ የግል ሪዞልታቸው ውስጥ በሚገኘው ምርጥ ቤታቸው ውስጥ ያወሩት ነገር ትዝ አላት። አባቷ በዕለቱ በጣም ተጨንቀው ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF

'የእኔ ትልቁ ምኞት ምን እንደ ነበር ታውቂያለሽ? ከት/ቤቱ ምርቃት ጋር ማርያ እና የመምህር ቀቁ ጋብቻን በዕለቱ የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጭምር በተገኙበት በታላቅ ድምቀት እንዲከናወን ነበር ማርያ ሳምንት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ኢጣሊያ ውስጥ የቀራትን ጣጣ ጨርሼ እመለሳለሁ ብላ ነበር የሄደችው ግና ከሰባ አምስት ቀናት በላይ ሆናት! ስልኩዋ አይሠራም! ወይ አትደውልም! ወይ አልመጣችም... ምን እንደዋጣት አልታወቀም:: በጣም ግራ ነው የገባኝ የሆነ ችግር ውስጥ ሳትሆን ትቀራለች? ምን ተሻለ ትያለሽ... መቼም መምህር ቀቁም ጭንቀት ውስጥ ሳይሆን አይቀርም?'

' እውነቱን ለመናገር እኔም በጣም ተጨንቄያለሁ:: በተለይ ማርያ ላይ የሆነችግር ደርሶባት ይህ የፍቅር ግንኙነቱ የሚበላሽ ከሆነ ለመምህር ቀቁ ትልቅ አሰቃያሚ ጠባሳ ነው የሚሆንበት:: ምክኒያቱም ከዚህ በፊት ሁለቱን ፍቅረኞቹን ስላጣ ... ጥሩ ነገር አይፈጠርም! እንዳኔ በጣም የተሻለው ነገር ለምን ተጨማሪ አንድ ሳምንት እንታገስምና አንተ ራስህ ኢጣሊያ ሄደህ ጉዳዩን አጣርተህ አትመለስም?'

'ትክክለኛ ሀሳብ! አመሠግናለሁ ልጄ! አንቺ ግን ብቸኝነት እንዳያጠቃው በደንብ ተንከባከቢው'

' ችግር የለም ባቢ! ለኔ ከመምህር ቀቁ ጋር ማውራት እድሜ የመጨመር ያህል ነው! ካልተቀየምከኝ ካንተ ጋር ብዙ ሰዓት ተቀምጦ ከማውራት ከእርሱ ጋር 10 ደቂቃ ማውራት የበለጠ ደስታ ይሰጠኛል:: ዋናው መፀለይ ያለብን ማርያን እግዜር ደህና እንዲያደርግልን ነው'

'ልክ ነሽ ልጄ'

ሲልቪቪያ ከአልጋዋ ላይ ሳትነሳ ስለ መምህር ቀቁ... ስለ አክስቷ ልጅ ማርያ ... ማውጠንጠን ያዘች::



t.me/OLDBOOKSPDF

**ማስታወሻ፡-** ከአዲስ አበባ እስከ ታሪካዊት ከተማ ደብረታቦር ርቀቱ 666 ኪሌ ሜትር ነው! እነሆ...

# FM 66.6

“ አፍ

ሲከፈት ጭንቅላት

ይታያል”



t.me/OLDBOOKSPDF

# የFM66.6

መግቢያ ...............................................................................

...........................................................................................................

.................................................... ነው።

"እንሰዳደብ....."



t.me/OLDBOOKSPDF

# ክፍል ሀ

## " እንሰዳደብ..."

## የካቲት 20/2005

## FM66.6 ዋና ስቱዲዮ ሀ

" ጤናይ ይስጥልኝ የተከበራችሁ አድማጮች! ዝነኛው ! ተወዳጁ! ተደማጩ! አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል ፕሮግራሜ እነሆ ጀመረ... እንደ ተለመደው በየመሀሉ የእናንተን አዕምሮ ዘና የሚያደርጉ ምርጥ ምርጥ ሙዚቃዎችን ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጪው ይገርላችሁ መጥቻለሁ... ከ 8-9:20 ደቂቃ ከዚህ ከ FM66.6 እናንተን እያስተናገድኩ የምቆየው ዝነኛው ጎልያድ ነኝ!! የተከበራችሁ አድማጮቼ ለዛሬ ለውይይት የተመረጠው ርዕስ

'እንሰዳደብ' የተሰኘ ነው:: እስቲ ብዙ ከምቀባጥርባችሁ በጣም ተወዳጅ የሆነውን የStevie wonderን you are the sunshine of my life የተሰኘውን ምርጥ ሙዚቃ እንኮምኩም"

> You are the sunshine of my life
> That's why I'll always by around,
> You are the apple of my eye,
> Forever you'll stay in my heart
> I fell like this is the beginning,
> Though I've loved you for a million years

" አድማጮች ተመልሼ መጥቻለሁ ! ድንገት FM66.6 ትን አሁን ለከፈታችሁ ለዛሬ የመረጥኩላችሁ ርዕስ እንሰዳደብ የሚል ነው... እንግዲህ ከአሁኑ ደቂቃ ጀምሮ ያቆሰላችሁን! ያናደዳችሁን! ያበሳጫችሁን... ቆሽታችሁን የቆሰለውን ሰው ... ነገር... በዚህ



t.me/OLDBOOKSPDF

ከ20 ሚሊዮን ህዝብ በላይ በሚሰማው አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል ፕሮግራም ላይ መሳደብ ይችላሉ....በ 0911 04 89 ** ይደውሉ... ስድቦትን በአጭር የፅሁፍ መልዕክት ለማስተላለፍ የምትፈልጉ ከሆነ ደግሞ በ 777 ላይ SMS ይላኩልኝ ታዲያ ለሚልኩት መልዕክት ሁለት ብር ይቆነደዳሉ ! ውድ አድማጮቼ እንደተለመደው ጫቲንም ቅሚ... ሺሻዬንም ወስጄ በሞቅታ እያስተናገድኳችሁ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ከሀያ ደቂቃ ከተከበራችሁ አድማጮቼ ጋር የምዘልቀው ዝነኛው ጎልያድ ነኝ... ለዛሬ የተመረጠው ርዕስ እንሰዳደብ ነው... ደወል ደወል አድርጉ... አ! ከአሁኑ ሁለቱም ስልኮች መጥራት ጀምረዋል ስለዚህ አንድ ማስታወቂያ እንስማና የመጀመሪያውን ተሳዳቢ በአየር ላይ አውለዋለሁ! FM66.6"

<u>ሊንዳ የውበት ሳሎን</u>

በአይነቱ የተለየው የውበት ሳሎናችን ለወንዶችም ለሴቶችም የተለየ አገልግሎት ይሰጣል! ከሌላው ፀጉር ቤት ለየት የሚያደርገን

- በነፃ ጭገር መላጨት
- መጠጥ በነፃ መስጠት
- ደንበኛ ንጉስ ነው ማለት

በዚያ ላይ የውበት ሳሎናችን ትልቁ አላማ ገንዘብን ማፈስ ሳይሆን የእናንተን ደስታ ማርካት ነው! ይምጡ በውበቱ ላይ ውበት እንደፋለን! በተለይ መልከ ጥፉ ነኝ ብለው የሚያምን ካለ/ካለች በእርግጠኝነት ውበት አላብሰን በራስ መተማመናቸውን ጨምረን ለመመለስ በዓለም ላይ ዝነኛ ስመጥር የሆኑ ሁለት ሳይኮሎጂስቶች በነፃ ምክር እንዲሰጦዎት አዘጋጅተናል! ሊንዳ! የውበት ጓዳ! እንገኛለን ጎጃም በረንዳ !!



t.me/OLDBOOKSPDF

" የተከበራችሁ አድማጮች ተመልሼ መጥቻለሁ ... የመጀመሪያ ደዋይም መስመር ላይ ገብቷል ሀሎ"

" ሀሎ"

" ማን ልበል? ከየት ነው?"

" ማንደፍሮ ነኝ ከመርካቶ ነው የምደውለው ባነሳኸው ርዕስ ጉዳይ ላይ ሀሳቤን ለመስጠት ነው?

" በጣም ጥሩ ! ማንን ነው መሳደብ የምትፈልገው?"

" በጣም ብዙ ናቸው..."

" ማንደፍሮ ብዙ አድማጮች እንዳንተ ለመሳደብ በወረፋ ላይ ስለሆኑ አንድ ብቻ መርጠህ መስመሩን ለሌላ ተሳዳቢ ልቀቅ"

" እሺ ጎልያድ... በቃ ፍቅረኛዬን ልሳደብ"

" ማን ናት? ለምንድነው የምትሰድባት?"

" ገሊላ ትባላለች እዚህ መርካቶ ዕቃ ልትገዛ ሱቄ ውስጥ መጥታ ነው የጠበሰችኝ ሁለት ዓመት ቆይተን አሁን ሌላ ፍቅረኛ እንዳላት ነገረችኝ ስለዚህ ያንተን ተወዳጅ ፕሮግራም ስለምትሰማ ልሰድባት ፈልጌ ነው"

" ቀጥል እሺ"

" ገሊላ እወድሽ ነበር አሁን ግን ጠላሁሽ ስለዚህ አንቺ ጥቁር ድመት አድሜሽ ይጠር ! መኪና ይግጭሽ! አዲስ ፍቅረኛሽ ደብድቦ ያባርሽ! ልጅ አትውለጂ! የኔን ሕይወት እንደበጠበጥሽው ያንቺም ይበጥበጥ! በልልኝ ይበቃኛል"

" እሺ ማንደፍሮ ገሊላ እንደሰማች ተስፋ አደርጋለሁ መልካም ቀን ይሁንልህ አድማጮች በ777 ላይ SMS ላኩ በ0911 04 89 ** ... ደውሉ ጣቢያው FM66.6 ነው እናንተን እዚህ ሳሪስ ከሚገኘው የFM66.6 ዋና መስሪያ ቤት 6ተኛ ፎቅ ላይ እያስተናገድኳችሁ የምቆየው ዝነኛው ጎልያድ ነኝ:: የሁለተኛው ደዋይን ሀሳብ እንቀበል! ሀሎ ማን ልበል?"



t.me/OLDBOOKSPDF

" አቶ ከተማ ሜኔ"

" ማንን ነው የሚሳደበት"

" እናንተን! FM ሬዲዮኖችን በሙሉ! እንዴ ፈርሀ እግዜር የጠፋበት ጊዜ ላይ እኮ ነን በተለይ ሙዚቃ እና ስፖርት አዘጋጅ የሆኑ ሁለት ጅብ ጋዜጠኞች አሉ፡፡ የመሲ እድሜ ስንት ነው? ከባርሴ እና ማንቼ ማን ያሸንፋል? ባላቶሊን ይወዱታል? የሩኒ ሚስት ስሙዋ ማን ነው? የመሰሉ ተራ ወሬዎችን እያነሱ በህዝቡ ይጫወታሉ! ህዝቡም ራሱ ሞኝ ነው፡፡ ለአሸናፊው ትልቅ በግ! ሱፍ ልብስ ! አሜሪካ ደርሶ መልስ ትኬት ! ቪላ ቤት... ልዩ ሽልማት አዘጋጅተናል እያሉ SMS ላኩልን እያሉ ህዝቡ ተሸውዶ ሲልክ ከሞባይሉ ላይ በትንሹ ሁለት ጊዜ ከላከ 4 ብር ይበሉታል! ሆዳሞች ናቸው፡፡ ሌላው መሳደብ የምፈልገው እኔ ያኔ ሎሬት የሚባል ገጣሚ ጓደኛ አለኝ የሚገርምህ የማጥም ተሰጠው ድንቅ ነው፡፡ ለዚህ ምስኪን ልጅ በደካማ ጎኑ እየተጠቀሙ ለሜት፡ ለሲጋራ እና ሴት እያዘጋጁለት የማይረባ 100 ብር እየሰጡት ስንቶች ዝነኛ ሙዚቀኞች ተጫውቱበት መሰለህ! የሚገርምህ ባለው ልዩ ተሰጥአው ተጠቅሞ ሁለት ኩርቱ ፈስታል ሙሉ የሙዚቃ ግጥሞች ነበሩት... ቢያንስ ስሙን እንኳ የሚፅፉ መሰለህ? የራሳቸውን ስም ያሰፍራሉ! ሌላው ጊዜ እንዳልሻማብህ ፈልጌ ነው እንጂ አንድ ዝነኛ ደራሲም አለ ስሙን እየሸጠ የሚበላም"

" አልገባኝም አቶ ከተማ"

" ወይ ጎልያድ! ጀማሪ ፀሐፊዎች በሱስም ከመፅሐፍ ነጋዴዎች ጋር ይደራደሩና በስሙ ያሳትማሉ፡፡ ህዝቡ እሱ የደረሰው እየመሰላቸው ተሸውደው ይገዛሉ ... ኧረ ስንት ጉድ አለ ... ብቻ ሁሉንም አድማያችሁን እምላክ ያሳጥረው! የምታገኙት ብር አይጥቀማችሁ በልልኝ! በጣም አመሰግናለሁ እንድተነፍስ ስላደረከኝ"

" የተከበራችሁ አድማጮች አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል እንደ ቀጠለ ነው አሁን ደግሞ የብዙነሽ በቀለን ጣፋጭ ሙዚቃ እንስማና ሰስተኛውን ተሳዳቢ በአየር ላይ እስገባለሁ! FM66.6"



t.me/OLDBOOKSPDF

……  የእናት ውለታዋን ሳወሳ እወዳለሁ
ደግነቷ ብዙ መሆኑን አውቃለሁ
ወላጅ እናት አኮ ፍፁም በመንፈሷ
ልጇን ትወዳለች አብልጣ ከራሷ
ዘጠኝ ወር በሆዷ ደግሞም በጀርባዋ
ጡቷን እያጠባች እኔን ማሳደጓ
ዘወትር ይሰማኛል የእማዬ ድካሟ
ችላ በማሳደግ በሴትነት አቅሟ…

" እያዳመጣችሁት ያላችሁት በFM66.6 ላይ የሚተላለፈውን አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል የተሰኘውን ተወዳጅ ፐሮግራምን ነው፤ ሶስተኛው ደዋይ መስመር ላይ ይገኛል ሀሎ ማን ልበል?"

" ወ/ሮ ብርቄ ነኝ ከሰፈረገነት"

" እሺ ወ/ሮ ብርቄ ማንን ለመሳደብ ነው?"

" ለቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስቴር 400 ምርጥ ስድቦች ነበሩኝ ግን በኛ ሀገር ሙት ወቃሽ አታድርገኝ ይባላልና ትቼዋለሁ ለማንኛውም የእሳቸው ምስል ያለበትን ባነር በብዛት በመላው ሀገሪቱ ተለጥፈዋል ሀገሪቱ ዲሞክራሲያዊ ሀገር ነች እያልን የኮምኒስት ስርዓት ለምን እናራምዳለን በዚያ ላይ ለአንድ ትልቅ ባነር 40ሺ ብር ከምናወጣ ምነው ልብ ካለን በእሳቸው ስም ለአንድ ት/ቤት የ40 ሺ ብር መፅሐፍ በስማቸው ገዝተን ብንሰጥ … ለማንኛውም እንተን እመሠግናለሁ"

"መልካም ቀን ወ/ሮ ብርቄ! አድማጮች FM66.6ትን ነው እያዳመጣችሁ ያላችሁት የዛሬው ርዕሳችን እንሰዳደብ ነው! በ0911 04 89 ** ደውሉ በ777 ላይSMSላኩ ሌላ ደዋይ መስመር ላይ ይገኛል ሀሎ ማን ልበል?"



t.me/OLDBOOKSPDF

" ጋሽ ከቤ ከአለላ"

" እንዴ ጋሽ ከቤ ወሬኛው እንዴት ኖት ሥራ ጥሩ ነው?"

" ጥሩ ነው ጎልያድ*... ተመስገን ነው"

" ማንን ነው መሳደብ የሚፈልጉት?"

" ጊዜ እሻማብሀለሁ እንጂ እኛ ሀገር የማይሰደብ የለም:: ት/ቤቶች ፤ ሙዚቀኞቻችን፣ ስፖርት ፌዴሬሽን ፤ በተለይ በትራፊክ ፖሊሶች ዝርፊያ እና ያለ ምክኒያት ብር እምጣ አለበለዚያ እፅፍብሀለሁ እየተባሉ ሥራቸውን እምርረው በርካታ ሹፌሮች ስራውን አቁመዋል! ትራፊክ ፖሊሶች ሁሌ ጮማ ይቆርጣሉ፣ መጠጣቸውን ያንደቀድቁታል ይህ ብር ከየት የመጣ መስለህ? ሆስፒታሎችን፣ ETVን ፤ ደራሲዎቻችንን ከሁሉም እንደው FM66.6 ይዘጋብሀል የመናገር ነፃነት በህገመንግስቱ እንጂ በተግባር የለም ብዬ ፈርቼ ነው እንጂ መንግስትን ሙልጭ አድርጌ መሳደብ እፈልግ ነበር ብቻ ብዙ የሚሰደቡ አሉ"

"ብዙ ደሞዮች ስላሉ አንዱን ብቻ ይምረጡና ይሳደቡ"

" ብቻ ለዛሬ መሳደብ የምፈልገው የሥነ-ፅሁፍ ሥራ የሚያዘጋጁትን ነው:: እኔ ብዙ ዓመት መፅሔቶችን ፤ መፅሐፍትን፣ እና ጋዜጦችን እነባለሁ:: እየሆነ የመጣው ግን ሁሉ ነገር ቁልቁለት መጓዝ ነው በተለይ ደራሲዎቻችን መፃፍ ማዘጋጀት ያለባቸው ለህዝቡ ምን ያስፈልገዋል ብለው ለውጥ ለማምጣት መፃፍ እንጂ ትርኪምርኪውን በመፃፍ ከህዝቡ ገንዘብ ለመሰብሰብ መሆን የለበትም! አሁን አሁንማ የተያያዙት ስታይል ጋዜጣና መፅሔት ላይ የዛሬ ሀያ ዓመት የፃፉትን ፅሁፍ እያሰባሰቡ አሳትሞ ብር መሰብሰብ ነው... የህዝቡን ደካማጎን ተጠቅሞ የሆይ ሆይ ፅሑፍ እያዘጋጁ ብር መጋጥ ትልቅ ውርደት ነው ... በዚያ ላይ አንዱ ጥቁር ድመት ብሎ በመፃፍ ከተሸጠለት ሌላው ነጭ ድመት ብሎ ይፅፋል... በዚህን ጊዜ ተደስተህ መልሰህ የምታነበው መፅሐፍ የለም! በተለይ መፅሔቶችንማ ተወው ትርኪምርኪ እና የሰፈር አሉባልታ ይዘው እኮ ነው ብር የሚዘርፉት... ጋዜጦችም ያው ናቸው:: ብቻ ሁሉንም የማትረቡ! ህብረተሰቡን ለመለወጥ ሳይሆን ከርሳችሁን ብቻ ለመሙላት የቆማችሁ ከንቱዎች ናችሁ በልልኝ"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እሺ ጋሽ ከቤ መልካም ቀን ይሁንሎት"

"ላንተም ይሁንልህ የኔ ልጅ"

• እያዳመጣችሁት ያላችሁት እፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል የተሰኘውን ዝነኛ የFM66.6 ፕሮግራም ነው:: በ777 ላይ SMS ላኩ በ 0911 04 89 ** ላይ ደውሉ:: አሁን ደግሞ በሙዚቃ ዘና እንበል በየካቲት 7/1945 የተወለደው በዓለማችን ላይ በየሀያ ሴኮንዱ ከዓለማችን በአንዱ ቦታ ስሙ የሚጠቀሰው ቦብ ማርሌይ ነው:: በነገራችን ላይ የቦብ ማርሌይ ሌላ ስሙ "ብርሃነ መስቀል" ነው:: ላማንኛውም ሙዚቃውን እንኮምኩም!!"

> Buffalo soldier, Dreadlock Rasta
>
> There was a buffalo soldier
>
> In the heart of America
>
> Stolen from Africa, brought to America


## ዘኒ ሀኒ አልጋ ቤት

እጅግ ዘመናዊ ከፍሎች አሉን ... አልጋ ቤታችን ለየት የሚያደርገው ወንዱ ሴት ሴቷም ወንድ ይዞ መምጣት አትችልም ለሴቱዋ እጅግ ብቃት ያለው ወንድ! ለወንዱም ውበት የፈሰሰባት ሴጋ ወጣት በአልጋ ቤታችን ውስጥ ያገኛሉ! ያስታውሱ ወንዱም ሆነች ሴቱዋ በታይላንድ የሁለት ዓመት የወሲብ ስልጠና ወስደው የመጡ ናቸው:: ለሁሉ ነገር የሚከፍሉት 700 ብር ብቻ ነው:: ዘኒ ሀኒ አልጋ ቤት ይምጡ መንፈስዎትን አድሰው ይመለሳሉ! በተለይ ከፍቅረኛዎ ጋር ተጣልተው ከሆነ ተጨማሪ ምርቃት አሎት! በወሲብ ለመደሰት ዘኒ ሀኒ አልጋ ቤት!!!




t.me/OLDBOOKSPDF

" እያዳመጣችሁት ያላችሁት FM66.6 አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል የተሰኘውን ዝነኛ ተወዳጅ ፕሮግራም ነው:: እናንተን እያስተናገድኩ ያለሁት ዝነኛው ጎልያድ ነኝ! ጥሪ ልቀበል ሀሎ ማን ልበል?"

" T.K ነኝ ከጣሊያን ሰፈር"

"እሺ T.K ማንን ለመሳደብ ነው?"

" ፍቅረኛዬን"

" ለምን?"

"ጎልያድ ሙት ነው የምልህ ለፍቅረኛዬ ብዬ ያልሆንኩት ነገር የለም:: ስድስት ዓመት በፍቅር ቆይተናል:: ድንግልናዬን የወሰደው እሱ ነው ግን እኔን እንደ ሸንኮራ አገዳ ከመጠጠኝ በኋላ ጣለኝ"

" ምን አደረገሽ "

" እንዴ ጎልያድ! ልጅ ከሌላ ሴት ወልዷል፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከምትማር ተማሪ ጋር በፍቅር ከንፍ ብሏል .... እንደሰለቸሁት ነገረኝ ... ብቻ ሕይወቴን ስለተጫወትከባት እኔ ላንተ የምመኘው በቁምህ ሞተህ ማየት ነው! ... ድፍት ያድርግህ ! እንቅልፍህ ይጥፋ! የዘራኸውን ከፋት መልሰህ እጨድ በልልኝ"

" እሺ T.K የሳይኮሎጂስት ባለሙያ የምትፈልጊ ከሆነ በውስጥ ስልክ ደውይልኝ አገናኝሻለሁ!! አድማጮች አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል እንደቀጠለ ነው ከFM66.6 እያስተናገድኳችሁ ያለሁት ጎልያድ ነኝ በ777 ላይ SMS ላኩ በ 0911 04 89 ** ላይ ደወል ደወል አድርጉ ማህሙድ አህመድ ይቀጥላል ...."

> ትዝታሽ ዘወትር ወደ እኔ እየመጣ
> እሮይ የምልበት ሕይወቴ ጊዜ አጣ
> የትዝታ ስሜት ልብ ላይ ነዳጅ
> አይጠፋም ምንግዜም ይዳፈናል እንጂ
> እንዳላንጎራጉር ምዬ ተገዝቼ
> ታዲያ እንዴት ያስችለኝ ትዝታን ሰምቼ



t.me/OLDBOOKSPDF

" ውድ አድማጮች ተመልሼ መጥቻለሁ! FM66.6 አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል ለዛሬ የተመረጠው ርዕስ እንስዳደብ ነው... በነገራችን ላይ አንዳንድ ጥናቶችን ሳነብ መሳደብ ራሱ ጤንነት ነው በተለይ ስትበሳጩ፣ ባፈቀራችሁት ግለሰብ ስትካዱ፣ እሪ ብላችሁ በጣም ብትጮሁ አልያም ብዙ ደቂቃ ብታለቅሱ በጣም ምርጥ እንደሆነ በጥናቶች ተረጋግጧል! በሌላ በኩል ንዴትን በውስጥ አምቆ ማስቀመጥ በሰውነታችን ውስጥ ፈንጂ እንደመትከል ይቆጠራል ይላሉ የጥናቱ ባለሙያዎች ለማንኛውም አንድ ስልክ ላንሳ ሀሎ ማን ልበል?"

" Sweet"

" ከየት ነው ስዊት ?"

" እንዴ? ትላንት ማታ አብረን ወሲብ አድርገን ነበር እኮ! ረሳኸን አድናቂህ ነኝ ብዬህ ጥፈራ ቤት ማታ ተዋውቀን ነበር Sweet ነኝ"

" አ! ሞት ይርሳኝ ምን አባከሽ የማወጣቸው ሴቶች እኮ በዝተውብኝ ... ለማንኛውም ማንን ለመሳደብ ነው?"

" አይ ለመሳደብ አይደለም ድምጽህን ስሰማ ናፍቀኸኝ ነው ! ማታ ልጠብቅህ ትመጣለህ እዛ ቤት ወይስ ሌላ ቤት አለች?"

" ማታ... እርግጠኛ አይደለሁም መልካም ጊዜ ይሁንልሽ ቻው... አድማጮች ስዊት ነበረች ማታ ፀዳያለ ጊዜ ነበር ያሳለፍነው ለማንኛውም ሌላ ስልክ ላንሳ ሀሎ ማን ልበል?"

" 50 አለቃ መከተ ከ50ቀተኛ ከፍለ ጦር"

" እንዴት ኖት 50 አለቃ ?"

" ደህና ነኝ! ያንተ ፕሮግራም አያመልጠኝም በጣም ነው የሚመቸኝ በርታ በዚሁ መቀጠል ነው"

"እመሠግናለሁ 50 አለቃ ታዲያ ማንን ለመሳደብ ፈልገው ነው?"

" አንዳንድ በቅቧታ እርባና የሌለው ቱልቱላ የሚያስላልፉትን ጋዜጠኛ መሰል አውቀት ያጠራቸውን ፀሐፊዎች ነው! ምሽት ይሆን ጫት ሲበሉ እያደሩ ማታ በሀልማቸው ያዩትን ጠዋት ይፅፉሉ! የጉድ ዘመን ላይ ደረስን እኮ ጎልያድ!!"



t.me/OLDBOOKSPDF

## "50 አለቃ ግልፅ ቢያደርጉት?"

"ጎልያድዬ ምን መሰለህ አንድ መፅሔት እጄ ላይ አለ 'ግብፅ ኢትዮጵያን ልትደበድ በመዘጋጀቷ ኢትዮጵያዊን ስጋት ላይ ናቸው' ይላል:: ምን አባቱ ይሄ የማይረባ ተራ አውቃ አልባ ጋዜጠኛ! ስለ ኢትዮጵያዊያን ወኔ እና የሀገር ፍቅር የጠለቀ የባንዲራ ፍቅር ቢያውቅ ይህን አይፅፍም ነበር! ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት ግብፅ ጦሩዋን ብታጠናክር ፣ ግብፅ ከኤርትራ ጋር ሴራ ብትጠነስስ...ኢትዮጵያ ላይ አንድ ፀጉር እንኳ ከጥቁርነት ወደ ነጭነት አይለወጥም በእርግጠኝነት የምነግርህ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ለግብፅ ብቻዋን አይደለም እስራኤል ራሱ ፊስ ፊስ ሊያደርግ የሚያስችል ብቃት ላይ ትገኛለች! እጅግ ብቃት ያላቸው ሰውር ሰላዮች፣ የደህንነት አባላት፣ ብቃት ያላቸው በምድር ይሁን በሰማይ ላይ ሀገራቸውን የሚያኮሩ ኮማንዶዎች አሉዋት... ታንክ፣ ፈንጂ፣ ሚሳኤል፣ ፀረሚሳኤል፣ ከቀላል እስከ ከባድ መሳሪያዎች... በራሳችን ልጆች ራሳችን እየሰራን ነው:: ከዚህ በኋላ ከማንም ፈረንጅ ሀገር ከአሜሪካ ፣ ራሺያ፣ ፈረንሳይ... ወዘተ መግዛት ተረት ሆኗል! በቅርቡ መሸጥ ይጀመራል... ብቻ ለህዝብ የማይነገር ሥራ በሚስጢር እየተሰራ ነው:: ያው በFm 66.6 ላይ ማውራት ሚስጢር ማውጣት ስለሚሆን ነው፤ ስለዚህ ለህዝቡ መናገር የምፈልገው እንኳን ግብፅን አሜሪካን፣ እስራኤልን፣ ቻይናን፣ ሩሲያን የመሳሰሉት ትላልቅ ሀገራት ራሳቸው ማንነታችን ላይ አፍ እንከፍታለን ቢሉ ዝም ጭጭ ነው የምናደርጋቸው! አለም እንዲያከብርህ አኮ የግድ ስላለህ የጦር ብቃት ሆነ መሳሪያ ለህዝብህ መዶስኮር የለብህም! ለማንኛውም ህዝቡ ላይ ያልሆነ ሽብር እና ጦርነት የሚያውጁ ጋዜጠኛ መሳይ ሜት ቃሚ ጋዜጠኞች! እተላዎች ናችሁ በልልኝ! መረጃ ስለሌላችሁ ነገር ገንዘብ ለማግኘት ብቻ የሰፈር አሉባልታ እና ቡና ላይ የሰማችሁትን ሁሉ እየፃፋችሁ ህዝቡ ላይ ሽብር አትፍጠሩ በላቸው! ለማንኛውም ጎልያድ የሌላ ደዋይ ደቂቃ እንዳልሻማብህ አመሰግናለሁ"

" ያሉት ግነት እና ውሸት ካልሆነ መልካም ነው፤ እንደው አለቃ አንድ ጥያቄ ላንሳሎትና እያድርገውና ሞቅ ያለ ችግር ቢፈጠር የመከላከያ ሠራዊቱ እንደ ግብዖች ለህዝቡ መከታ በመሆን ከህዝቡ ጋር ይቆማል ወይስ ለመንገ ሰት ጥብቅና ይቆማል?"



t.me/OLDBOOKSPDF

" ልጅ ጎልያድ ከባድ ጥያቄ ስለሆነ ከይቅርታ ጋር ይለፈኝ"

" አድማጮች እየሰማችሁት ያላችሁት በዝነኛው ጎልያድ የሚዘጋጀውን እፍ ሲከፈት ሞንቃላት ይታያል የተሰኘውን ከ FM66.6 ጋር በመተባበር የሚቀርበውን ፕሮግራም ነው! ለጆግ ዝነኛ የሆነችውን ተደናቂ ድምፃዊት Celinedion 'my heart will Go on' የተሰኘውን ምርጥ ዜማ እንስማና ለዛሬው ካለኝ ሰዓት አንፃር አንድ ደዋይ አስገብቼ እንሰነባበታለን"

…. Every night in my dreams
I see you , I feel you
That is how I know you, go on.
Far across the distance
And spaces between us
You have come to show you, go on
Near, far, wherever you are

" ተመልሼ መጥቻለሁ … እያዳመጣችሁት ያላችሁት FM66.6 ነው አድማጮች በጣም ትንሽ ደቂቃ ስለቀረኝ የመጨረሻ ደዋይ መስመር ላይ ይገኛል! ሀሎ ማን ልበል?"

" በንቱ እባላለሁ"

" ከየት ነው በንቱ?"

" ከናዝሬት 04 ቀበሌ"

"ማንን ነው የምትሳደቢው?"

" በዚህ ከተማ ውስጥ የሚገኙትን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ነው"



t.me/OLDBOOKSPDF

" አንዴ ጎልያድ! እኔ ለስምንት ዓመት ሽርሙጥናን ነው የሠራሁት የሚገርምህ በወር ውስጥ እነሰ ከተባለ ከ40 ሰው ጋር እማግጥ ነበር፡፡ ዘንድሮ ግን በወር ሁለት ወንድ እንኳ አጥቼ የምበላው ሆነ ለቤት ኪራይ የምከፍለውን አጥቻለሁ! እነዚህ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ሁሉ ስራችንን ተሻሙብን! ማታ ማታ በየመንገዱ፣ በየቡና ቤቱ ያሉት እነሱ ብቻ ናቸው ምናባታቸው እዚህ ዩኒቨርሲቲ የመጡት እውቀት ወስደው ተመርቀው ነገ ትልቅ ለመሆን አይደለም እንዴ!?" ታዲያ እነሱም ከትልቁ ዩኒቨርሲቲ ገብተው የእኛን እስጠሊታ እና አስቸጋሪ የቤተኛ አዳሪነት ሥራ ከተሻሙብን ምን ይባላል? እና ጎልያድዬ አርፋችሁ ተማሩ አለበለዚያ ወንዶች ቀጥረን እናስቀጠቅጣቹዋለን በልልኝ!! በነገራችን ላይ ጎልያድዬ ወደ ናዝሬት ስትመጣ ደውልልኝ እንከባከብሀለሁ! አመሠግናለሁ"

" እኔም ስለሰጠሸኝ ሀሳብ አመሰግናለሁ መልካም ጊዜ ይሁንልሽ በነገራችን ላይ ከዚህ ስራ መልቀቅ የምትፈልጊ ከሆነ በውስጥ ስልክ ደውይና የአንድ መሰሪያ ቤት አድራሻ ውሰጂ ስልጠና እና ስራ ይሰጡሻል... የተከበራችሁ አድማጮች ለዛሬ የነበረን ቆይታ እዚህ ላይ ይጠናቀቃል ነገ በተመሳሳይ ሰዓት ሌላ ርዕስ በመያዝ እመለሳለሁ! የደወላችሁልኝ ሆነ መስመሩ ለተያዘባችሁ እንዲሁም በ777 ላይ SMS በመላክ ሁለት ብር ለላካችሁልኝ ሁሉ እጅግ አመሠግናለሁ! የምስናበታችሁ ኢትዮጵያ በዓለም ህዝብ ስሙዋ እንዲጠራ ካደረጉዋት የጥበብ ሰዎች መሀከል Emilia (Hanna) ትጠቀሳለች በተለይ አይኖቹዋን በጣም ነው የምወዳቸው ለማንኛውም ተወዳጅ ሙዚቃዋን ' Big Big world' ን እናዳምጥ ... ሠናይ ጊዜ!!"

I'm a big , big girl in a big, big world
It's not a big, big thing if you leave me
But I do, do feel that I do, do
Will miss you much
Miss you much
I can see the First leaf falling
It's all yellow and nice
It's so very cold outside


t.me/OLDBOOKSPDF

# ክፍል ለ

## ወይ

## የመጀመሪያ ፍቅር

## ጣጣ



t.me/OLDBOOKSPDF

"... How on earth can you explain in terms of chemistry and phys ics so important a biological phenomenon as first love? put your hand on a stove for a minute and it seems like an hour. Sit with that special girl for an hour and it seems like a minute" (Abert Ein stein)

# ክፍል ለ

## የካቲት 21/2005

## FM66.6 ዋና ስቱዲዮ ሀ



t.me/OLDBOOKSPDF

• የአለማችን ዝነኛ ደራሲ ሲድኒ ሽልደን ሀብት ማግኘት የለማኝ ምኞት ነው፤ ፍቅርን መኘት ግን የንጉስ ህልም ነው ሲል ታላቁ ብራህማ ደግሞ አንድ ወንድ እንዲት ሴትን ሲያፈቅር ያቺም ያንን ወንድ ስታፈቅር መላዕክት ከሰማየሰማያት ወርደው በጎጆአቸው እየኖሩ የደስታ መዝሙራቸውን ያንቆረቁራሉ... ፍቅር በልብ ውስጥ የሚነድ ጭስ አልባ እሳት ነው... ፍቅርን የምንገዛው በጥሩ ፍቅር ነው ... Love is only the dirty trick played on us to a chive continuation of the species .... ከፀሐይ ብርሃን ቀጥሎ እ/ር የሰጠን ታላቅ ነገር አለ እሱም ፍቅር ነው... ለፍቅር ያልተገዛ ልብ ድንጋያማ ነው... Love is a deep felling inside us that makes us want to do good things for others people. We show that we love others when we have a good felling to word them.... አስገራሚዋ ምድራችን ከተፈጠረች ጀምሮ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዝነኛ ፀሐፊዎች ፡ዝነኛ መሪዎች፡ የሥነጥበብ ባለሙያዎች ፡ የኪነጥበብ ባለሙያዎች ፡ አለምን ያስደነቁ ፈላስፎች... ብቻ አርቲስት! ወጣት! ሽማግሌ ! ወታደር! ወዘደር! አስተማሪ! ተማሪ! ሌባ! ሸርሙጣ! ሹፌር!... ሁሉም የፍቅር ፍቺ አስቀምጧል:: ዛሬም እያስቀመጡ ናቸው፤ ወደ ፊትም ማስቀመጣቸው አይቀርም:: በአለማችን ላይ በየአንድ ሴኮንዱ የሚጠራው ቃል ምንድ ነው ካላችሁ በእርግጠኝነት መልሱ ፍቅር ነው"

" የተከበራችሁ አድማጮች ዛሬ በፍቅር ዙሪያ በተነገሩ አባባሎች የጀመርኩት የዛሬው የውይይት ርዕሳችን በፍቅር ዙሪያ ስለሆነ ነው:: የናንተው ዝነኛ ጋዜጠኛ ጎልያድ ነኝ ባላችሁበት ቦታ ሁሉ FM66.6 አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያልን ፕሮግራም ለመረጣችሁ ሁሉ አመሠግናለሁ!! እንደተለመደው ዛሬም ጣፋጭ ጣፋጭ ሙዚቃዎችን በየመሀከሉ አስደምጣችሁአለሁ! ለዛሬ እንግዲህ የተመረጠው የውይይት ርዕስ የመጀመሪያ ፍቅር ጣጣ የሚል ርዕስ ነው! የተከበራችሁ አድማጮቼ የመጀመሪያ ፍቅር ወቅት ያጋጠማችሁን ነገሮች አጋሩን! እያዳመጣችሁት ያላችሁት FM66.6 ነው መጀመሪያ ማስታወቂያ እንሰማና ቀጥሎ የጥሲን ተወዳጅ የፍቅር ሙዚቃ ሰምተን ከመጀመሪያው ደዋይ ጋር እንገናኛለን ፕሮግራሙ



t.me/OLDBOOKSPDF

አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል ከFM66.6 ጋር በመተባበር የሚቀርብ ለየት ያለ ሳምንታዊ ፕሮግራም ነው:: በ0911 04 89 ** አልያም በ777 ላይ SMS ላኩልኝ! ሁለት ብር ላጥ ይደረግባቹሀል:: ዘና በሉ ጎልያድ ነኝ!!"

## አልብድ ዴዜ!

አንድ ሚሊየን ኮፒ በኢትዮጵያ የመፅሐፍ ሽያጭ ታሪክ በመሸጥ ታሪክ ያስመዘገበው ዝነኛው! አነጋጋሪው! አወዛጋቢው ደራሲ. አልብድ ዴዜ የተሰኘ እጅግ አስደማሚ የወሲብ መፅሐፍ በሚደንቅ አፃፃፍ ለውድ አንባቢያን ይዞ ከተፍ አለ! አልብድ ዴዜን ሲያነቡ በእውን ወሲብ እያደረጉ ያሉ ያህል ይሰሞታል በዚህ መፅሐፍ ዙሪያ ዝነኛ በጂዎች እና ሸርሙጣዎች አስተያየታቸውን አስፍረውበታል... ይህ ድንቅ የዘመኑ መፅሐፍ ሳያልቅቦት በ45 ብር ብቻ ይግዙት! ወሲብ ያልጀመሩ ወሲብ ይጀምሩበታል... ወሲብ ላይ ያሉ ይበልጥ ዙሩን ያከሩበታል... በተለይ ያገቡ ከትዳራቸው ውጪ በጥበብ እንዴት ዝሙተኛ መሆን እንደሚችሉ ያስተምራል ባጠቃላይ የወሲብ ችግርዎ ቁልፍ አልብድ ዴዜ ነውና አሁኑኑ ገዝተው ፍስሐ ያግኙበት!!

.... አልረሳህ አለኝ ተቀብሮ ከአንጀቴ

አንቺ የሌለሽበት የፍቅር አመቤቴ

እንኳን ቆሜ ብቀበርም

እኔ ያላንቺ ከቶ አልኖርም...

" ተመልሼ መጥቻለሁ አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል! FM66.6 ትን ነው እያዳመጣችሁ ያላችሁት የዛሬው ርዕሳችን የመጀመሪያ ፍቅር ጣጣ የሚል ነው:: ፕሮግራሙን እየመራው ከአናንተ ጋር የምቆየው ዝነኛው ጎልያድ ነኝ... የመጀመሪያው ደዋይ በስልክ መስመራችን ላይ ይገኛል! ሀሎ ማን ልበል?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"የሺ-ፐላ ነኝ"

" ከየት ነው የሺ-ፐላ"

" ከፈረንሳይ ለጋሲዮን"

"ዛሬ የምናወራበት ርዕስ የመጀመሪያ የፍቅር ጣጣ የሚል ነው ምንድ ነው የምትለን?"

" የመጀመሪያ ነገር ሁሉ ፈተና ይበዛበታል በተለይ የመጀመሪያ ፍቅር በጣም አስቸጋሪ ነው የኔን ሕይወት በጣም ያበላሸውም የመጀመሪያ ፍቅር ነው... ነገሩ እንዴት መሰለህ እኔ ስራዬ ካሜራማን ነኝ እና ባንድ የሠርግ ቀረፃ ወቅት የሙሽሪትን ታናሽ እህት አይቼ ልቤ ቀለጠች! ሳላጣራውና ብዙም ሳልቸገር ተግባባን እጅግ ውብ ልጅ ነበረች! ሳቂታ! ተግባቢ! አዋቂ! የምይዘውን የምጨብጠውን አጣሁ ስራዬን ትቼ ከእሱዋ ጋር 24 ሰዓት ፊልም ቤቶች 24 ሰዓት መዝናኛ ቦታዎች! 24ሰዓት እሷን ለማስደሰት እና ለመሳብ ጥረት እያደረኩ አስር ዓመት ለፍቼ ያጠራቀምኩትን 44ሺ ብር በስድስት ወራት ውስጥ አጨረስኩት! ይህም ያንሰሀል ሲለኝ 28ሺ ብር ብድር ጠየቀችኝ ሳላንገራግር ከባንክ አውጥቼ ሰጠኋት በሳምንቱ መጨረሻ መርዶ ተነገረኝ ባህሬን ሄዳለች ተባልኩ"

" ከዚያስ"

" አለቀ በቃ!! በእርግጥ ብዙ ተጎድቻለሁ እርሷን ለመርሳት መጠጥ፤ ሲጋራ፤ ጫት፤ ጀምሬ ነበር:: ቀስ ብዬ ሳስተውል ግን የምጎዳው ራሴን መሆኑ ሲገባኝ ራሴን አፅናንቼ ወደ ስራዬ ተመለስኩ:: በዚህ አጋጣሚ የፍቅር ሕይወት ውስጥ ላልገቡ ሰዎች የምመክረው በኔ የግል ጥናት የደረስኩበት 98.5% የመጀመሪያ ፍቅር ሊሳካ ስለማይችል ራሳችሁን አሳምኑ! ሙሉ ለሙሉ ራሳችሁን ለፍቅር አሳልፋችሁ አትስጡ በልልኝ በእርግጥ ፍቅር ውስጥ ስንገባ ትለየናለች/ ይለየናል ብለን ማሰብ ቢያስቸግርም በጣም ላለመጎዳት ግን አስቀድማችሁ ተዘጋጁ በልልኝ::"

" የሺ-ፐላ ከፈረንሳይ! አመሠግናለሁ አድማጮች ሁለቱም ስልኮች በጥሪ እየተጨናነቁ ናቸው:: የሁለተኛውን ደዋይ ጥሪ ልቀበል ሀሎ ማን ልበል?"

" እከሱማዊት አባላለሁ ከየረር ነው የምደውለው"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እሺ አከሱማዊት ያንቺስ የመጀመሪያ ፍቅር ጣጣ ምን ይመስል ነበር?"

" በነገራችን ላይ የመጀመሪያው ደዋይ 98.5% የመጀመሪያ ፍቅር አይሳካም ባለው ሀሳብ በጣም ነው የምስማማው! የሚገርምህ የመጀመሪያ ፍቅር የያዘኝ በ16 ዓመቴ ነበር:: ያፈቀርኩት ልጅ ሰቀ ነጋዴ ነበር:: እሱን ለማየት በየአንድ ሰዓት ልዩነት ነበር ሱቁ የምመላለሰው.... ታዲያ በሁለተኛው ወር እሱም ባነና ተግባባን ስልክ ተለዋውጠን ማታ ከ4ሰዓት እስከ 6 ሰዓት ደውዬ አዋራዋለሁ! ጠዋት ነግቶ አይኑን እስከ ማየው እንዴት ይጨንቀኛል መሰለህ? በተለይ ስልኩን ዘግቶ ሳላናግረው ካደርኩማ ሌሊቱን ሙሉ ሳለቅስ ነበር የማድረው እጅግ በጣም ተበሳጭቼ የሱን ዓይን ሳይ በሀሴት እሞላለሁ ሀይለኛ የመራብ ስሜት ተሰምቶኝ እሱን ሳይ እጠግባለሁ ታዲያ ሱቃቸው ሄጄ ከወጣት ሴት ጋር አይደለም ከሆነች አሮጊት ጋር እንኳ ሲሳሳቅ ካየሁት እጅግ በጣም በቅናት እበሳጭና ላልነግረው ቤቴ ገብቼ አለቅስ ነበር::"

" አከሱማዊት ላቋርጥሽና በእድሜ አኩያ ነበራችሁ?"

" ኧረ በስምንት ዓመት ይበልጠኝ ነበር"

"ከዚያስ ምን ተፈጠረ?"

" ባመቱ የወሲብ ጥያቄ አነሳ"

"ምን አደረግሽ"

"ምን ነካህ በዚያን ወቅት እንኳን እንቢልለው ቆርጠሽ እኔ ጋር ይቀመጥልሽ ቢለኝ ራሱ ደስተኛ ነበርኩ::የጥምቀት በዓል ከተራ ጊዜ ቤተክርስቲያን እድራሰሁ ብዬ ዋሽቼ ከእርሱ ጋር አደርን ! ድንግሌን አስረከብኩት! ከዚያማ ተወው ማፍቀሬ ይበልጥ ተንቦገቦገ! ያለ እርሱ ምንም ነገር ማሰብ አልቻልኩም! ት/ቤት ሄጄ መማር ሆነ ማጥናት አልቻልኩም! አቃተኝ!! ራሴን መቆጣጠር አቃተኝ! አብዛኛውን ሰዓት ከእርሱ ጋር ስለ ማሳለፍ እና ስለማላጠና ዩኒቨርሲቲ የመግባት ሀሳቤ ሳይሳካ ቀረ...በወቅቱ ከእርሱ ጋር በፍቅር ታውሬ ስለ ነበር ምንም ነገር አልመሰለኝም ነበር:: ለሰባት ዓመት እስከሚበቃው ከተጫወተብኝ በኋላ ቀይ



t.me/OLDBOOKSPDF

ካርድ ሰጠኝ! ተለያየን... የመጀመሪያ ፍቅር ጣጣ ግን እጅግ በጣም አስቸጋሪ እና የማይረሳ ነው"

" ለምን ተለያያችሁ?"

" ከእርሱ ጋር በእድሜ እቻ የሆነችው ፍቅረኛ እንዳለችው ደረስኩበት!"

" አሁን ምን እየሰራሽ ነው?"

" አስተናጋጅ ነኝ! ከዚያ በኋላ ለመማር ጥሬ ነበር ግን ሀሳቤን መሰብሰብ ስላልቻልኩ አልተሳካልኝም በዚህ አጋጣሚ ለሴት እህቶቼ የምመክረው በጣም የፈጠነ ፍቅር የውሸት ነውና እንደኔ ሕይወታችሁ እንዳይበላሽ ተጠንቀቁ ነው የምላቸው:: በዚህ አጋጣሚ ልጅ ሁሉ አርግዤ አስወርጃለሁ:: ሁሌ ኮንዶም እንጠቀም ነበር አንድ ጊዜ ግን ፍቅራችን ይበልጥ እንዲጣፍጥ ለምን በመላጣው ወሲብ አናደርግም ብሎኝ የወር አበባ ቀናትን ቆጥረን ወሲብ አደረግን! የወር አበባዬ ደረቅ የሚሆንበት ቀናት ነበር! ግን ጉድ ሆኛለሁ::"

" አከሱማዊት ከየረር ስለ ደወልሽና ሀሳብሽን ስላካፈልሽኝ በጣም አመሠግናለሁ! አይዞሽ በርቺ! እያዳመጣችሁ ያላችሁት FM66.6 አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል የተሰኘውን ፕሮግራም ነው:: እያስተናገድኳችሁ ያለሁት ዝነኛው ጎልያድ ነኝ! በ0911 04 89 ** ደውሉ! በ777 SMS ላኩ! ከአንድ ሙዚቃ በኋላ ሌላ አድማጭ በመያዝ እመለሳለሁ እጅግ ተደናቂው ብላቴናው አወዛጋቢው ዝነኛው ቴዲ አፍሮ ይቀጥላል! በነገራችን ላይ በቃሊቲ አስር ጊዜው በርካታ ጊዜያትን ጠይቄዋለሁ! ቴዲ ይሄኔ ረስቶኝ ይሆናል ... ለማንኛውም ወደ ሙዚቃው ...

> ኸረ ባላውቅሽ ... ከምጨነቅ አንቺን ወድጄ
> ኖሬ በደላኝ ገና ለኔ ምኑን አውቄ
> ... ፍቅርን ልቻለው ደግሞ በምን ጉልበቴ
> አቤት እያልኩኝ ሁሌ ለአመቤቴ ...



t.me/OLDBOOKSPDF

" አጅግ ብዙ ሰዎች የሚያነሱት ጥያቄ አፍቅረን ያፈቀርነው ሰው ሲለየን፣ አፍቅረን እንቢ ስንባል፣ አፍቅረን ያፈቀርነውን ግለሰብ ለመጠየቅ የሚያስፈራን፣ አፍቅረን ያፈቀርነውን ሰው ስንመለከት... ብቻ የተለየ ስሜት የተለየ ሀሴት ለምን ፍቅር ይፈጥርብናል? የሚል ጥያቄ ያነሳሉ ሳይንስቶች ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት አደረጉ:: ፍቅር በያዛቸው በርካታ አፍቃሪዎች ላይ ባደረጉት ጥናት ፍቅር ሲይዘን በሰውነታችን ውስጥ ዶፖሚን የተባለ ንጥረ ነገር በፍጥነት ይመረትና በመላ ሰውነታችን ላይ ይሰራጫል:: ይህ ኬሚካል ወደ አዕምሮ ክፍላችንም በማምራት የአንጎል ክፍላችንን በቁጥጥሩ ሥር ያደርገዋል ታዲያ በቀላሉ ሰውነታችንን የተቆጣጠረው ኬሚካል ከሰውነታችን በተለይ ካፈቀርነው ሰው ብንለያይ በቀላሉ ውጣ ለማለት ከቶ አይቻልም! ያፈቀርነው ሰው ሲለየን በዶፖሚን የተነሳ ይበልጥ የፍቅር ስሜት ይፈጥርብናል! ሱስ ይሆናል:: በቀላል ምሳሌ የሲጋራ፣ የመጠጥ፣ የጫት፣ የወሲብ ሱስ የተጠናወታቸው ሰዎች ከሱሳቸው በአንድ አፍታ መላቀቅ እንደማይችሉ ሁሉ ውስጣችን የተፈጠረው የፍቅር ስሜትም ዶፓሚን የተሰኘውን ኬሚካል ባንድ ጊዜ ለማውጣት አይቻልም! ጊዜ ይፈልጋል! ለፈተና ይዳርገናል በዚህ ኬሚካል የተነሳ ነው እንግዲህ የተለያዩ ስሜቶች የሚሰሙን... የደስታም ... የሀዘንም ... ያፈቀርነውን ሰው ለናይ መደሰት! መደናገጥ! ላለመለየት መፈለግ! ስንለየው ደግሞ ይበልጥ መፈለግ! የቅናት ስሜት.. ወዘተ መሠል ስሜቶችን ይፈጥርብናል ይላሉ የጥናቱ ባለቤቶች! አድማጮች አንድ ማስታወቂያ ላሰማችሁና ከአንድ ደዋይ ጋር እመለሳለሁ:: FM66.6 በማዳመጥ ላይ ናችሁ የዕለቱ ርዕስ የመጀመሪያ ፍቅር ጣጣ ነው ... ዘና በሉ በ777 ላይ SMS ላኩ በ0911 04 89 ** ላይ ደውሉ"



t.me/OLDBOOKSPDF

## ሁላላ ነብስ በላ

በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነው ሁላላ ነብስ በላ! ጠላት አሎት? በፍቅር፣ በገንዘብ፣ በሥራ፣ አልያም በሌላ ከእርሱ ጋር ጠላት ያፈሩትን ሰው እኛ ጋር መጥተው አድራሻውን እና ምስሉ ፡ ብቻ ያምጡልን ... እርሶ በፈለጉት መሰረት ገለነው እንቀብረዋለን !! እንደ ሀንዶች ሬሳው ይቃጠልም ካሉ በቁም እናቃጥለዋለን ... ያስታወሱ በስራችን ላይ ብዙዎችን አኮርተናል! እኛ ጋር ይምጡና ጠላቶዎን እንግደልሎ! ያስታውሱ ይህን የኛን ማስታወቂያ ድንገት ጠላትዎ ቀድሞ ከሰማ እኛ ጋር ቢመጣ እርሶን ስራችን ነውና እንገድሎታለን ስለዚህ ሳይቀደሙ ይቅደሙ! ጊዜ ወርቅ ነው ይሉ የለ አበው? ሁላላ ነብስ በላ!

" አድማጮቻችን የሁላላ ነብስ በላን ማስታወቂያ ነበር ያዳመጣችሁት FM66.6 አሁንም እንደቀጠለ ነው:: ደዋይ የስልክ መስመር ላይ ገብቷል ሀሎ ማን ልበል?"

" ኤርሚያስ ከቂራ"

" አሺ ኤርሚያስ የመጀመሪያ ፍቅር ጣጣ ላይ እያወራን ነው የአንተ ገጠመኝ ምንድ ነው?"

"Love don't cost a thing የሚል ፊልም ካየሁ በኃላ ልጅቷ ቁርጥ እሷን የመሰለች ነች አስደማሚ የውበት እመቤት ነበረች! በውበቷ የተነሳ ነበር የተጠመድኩት



t.me/OLDBOOKSPDF

ግዮን ሆቴል ለመጀመሪያ ጊዜ ያየኋት የቴዲ አፍሮ የሙዚቃ ኮንሰርት ላይ ነበር:: አቢት ፈገግታ! አቢት የዳንስ ብቃት ... በግራም በቀኝም ብዬ ተዋወቅን... ከዚያ ተወው በቀን ጊዜ መደዋወል ነው... እስከ ሌሊቱ ስምንት ሰዓት በልክ እናወራለን"

" ምን ነበር የምታወሩት?"

" ምን አውቃለሁ! ማውራቴን እንጂ ስለማወራው ነገር አላስታውስም ለኔ ትልቅ ደስታ የሚሰጠኝ ድምጿዋን እና ትንፋሹዋን መስማት ነው በእርግጥ በብዛት የምናወራው ነገር ትርኪምርኪ ነው፤ ግን ፍቅር ሲይዝህ የፍቅረኛህ ፈስ እንኳ እንደ ሽቶ ይሸትሀል ይባል የለ? ሁትኩስ ፍቅር ሁለት ወር ከቆየን በኋላ ጥያቄ አነሳች"

" የምን ጥያቄ?"

" የምትወደኝ ከሆነ መስቀል አደባባይ እጠብቅሀለሁ ራቁትህን እወድሻለሁ የሚል ትልቅ ባነር አሰርተህ ይዘህ ና አለችኝ"

" ዋው መቼም እየቀለደች ነበር?"

" ወይ ቀልድ 100% የምሩዋን ነበር"

" እናስ?"

" እንቢ የሚል ልብ አልነበረኝም! በፍቅሩዋ በጣም ሰክሬ ነበር ነገሩን ለጓደኞቼ እና ለቤተሰብ ስነግራቸው ባለማመን ሳቁብኝ እኔ ግን ባለችኝ ቀን እና ሰዓት ትልቅ 'ሊናዬ እወድሻለሁ' የሚል ባነር አሰርቼ መስቀል አደባባይ አመራሁ:: ሰው ለጉድ ነበር የሚመለከተኝ ... ከቦታው ስደርስ እቅፍ አድርጋ ሳመችኝ ... ለየት ያለ ፀባይ ነበራት ፊልም ቤት ስንገባ ሆን ብቻ ሰው የበዛበት ቦታ ውስጥ ስንሆን ሊናዬ እወድሻለሁ ብለህ ጩህልኝ ትላለች! እጮህላታለሁ አንድ ምሽት ከሌሊቱ 6 ላይ ደወለች የኔ ቤት ቁራ ነው የሱዋ ቤት አውቶቢስ ተራ ነው አሁኑኑ ካልመጣህ ነገ አታገኘኝም አለች:: የተወሰነ መንገድ በላዳ የተወሰነ መንገድ በሩጫ ሄጄ ደረስኩላት ግጥም አድርጋ ከንፈሬን ሳመችኝ:: ምነው ስላት እንደምትወደኝ ለማወቅ ነው አለችኝ:: በጣም ሳስታውሰው የሚደንቀኝ ግን አንድ ጊዜ ጠጅ ቤት ካልወሰድከኝ ሞቼ እገኛለሁ አለች:: ወሰድኳት ጠጣን:: በመሀከል ልብሶችህን

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ለቀሀ እወድሻለሁ ካላልከኝ ራሴን እጠፋለሁ አለች! ግጥም አድርጌ ራቁቴን ሆንኩኝ! ... ደ ተያዘብኝ አብድ ናችው ተባልን! ብቻ ብዙ ጣጣ አሳይታኛለች ምን ዋጋ አለው? ያ ... ሪኛ ተዓምራዊ ውበቷ ጉድ ሠራኝ አንድ ዝነኛ ፓይለት ጠብሶዋት ተለይታኛለች! ...ጀመሪያ ፍቅር አለደሳችም ነው:: የማይረሳ ጠባሳም አስቀምጦልህ ይሄዳል"

"ለየት ያለ ፀባይ ነው ያላት ለማንኛውም ኤርሚያስ ከቁራ ሰላካፈልከን የመጀመሪያ ...ር ጣጣህ እናመሠግናለን... ወድ አድማጮች FM66.6 አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል ...ሮግራም አሁንም እንደቀጠለ ነው:: አሁ፡ አሁን ደግሞ በ james Blunt ሙዚቃ ፈታ ...ነበል ይሀን ዝነኛ የጥበብ ሰው ኢንግሊዛዊያን በጣም ይወዱታል ይህ ሙዚቃ አሁን ለደወለው የቁራው ኤርሚያስ መታሰቢያ ይሁን!"

| |
|---|
| ...... You touched by heart you touched my soul.<br>You changed my life and all my goals<br>And love is blind and that I knew when<br>My heart was blinded by you,<br>I've kissed your lips and held you head<br>Shared your dreams and shared your bed... |

* አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል ከ FM66.6 ጋር በመተባበር የሚቀርብ ተወዳጅ ፕሮግራም ነው :: ውድ አድማጮቻችን ስለ ፍቅር አይነቶች ማወቅ ከፈለጉ በተለይ የተወለዱበትን ወር ካወቁ በምን አይነት ፍቅር ሊያዙ እንደሚችሉ፣ ሊደርስበት የሚችለውን ጣጣ ለማወቅ ከፈለጉ ኢያሪኮ 888 መጽሐፍ ገፅ 128-132 ያንብቡ! ስለፍቅር የተፃፈውን አስገራሚውን ያፈቀሩትን ግለሰብ ልብ ማንበቢያ የፍቅር አስገራሚ ቀመር ማንበብ ከፈለጉ ደግሞ ዘና የሚያደርገውን "አዳምና ሔዋን/ ለሚስቴ ባል ፍለጋ/ የተሰኘውን የአዙርማን አወዛጋቢ መፅሐፍ ያንበቡ እኔ ባነበባችሁ ደስ ይለኝ ነበር ግን ሰዓት ስለሌለኝ ነው ለማንኛውም

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

መስመር ላይ ደዋይ አለ:: ሀሎ ማን ልበል?"

" ቃል ኪዳን"

" ከየት ነው ቃልኪዳን?"

" ከአስኮ መዳኒዓለም"

" የመጀመሪያ የፍቅር ገጠመኝሽ ወይም ጣጣሽ ምን ይመስላል?"

" ለመጀመሪያ ጊዜ ፍቅር የያዘኝ በ18 ዓመቴ ነበር ያፈቀርኩት ሰው የተለየ ግርማ ሞገስ ነበረው ታውቃለህ በፊት መፅሐፍ ሳነብ ፣ ፊልም ስመለከት ሳላስበው የወደፊት ባሌ በማለት በምናቤ ስዕል ሰዬ ነበር ያን ሰው የመሰለ ነበር ድንገት እኛ ቤት ተከራይቶ የገባው:: ለማመን ተቸግሬ ነበር:: ሶስት ወር ተሰቃይቼ አራተኛው ወር ላይ ዛሬ ልንገረው ነገ ልንገረው እያልኩ ፍቅረኛው ከውጪ ሀገር መጣች:: እንዴት እንዳዘንኩ ልነግርህ አልችልም! ሁሉ ነገር ጨልሞብኝ ነበር! በረኪና ሁሉ ልጠጣ አቅጄ ነበር"

" ቀጥሎ ምን አደረግሽ?"

" ምን አደርጋለሁ ያው ፍቅር ሲይዝህ የበታችነት ይሰማሀል፣ ያፈቀርከው ሰው ያንተ ጌታ ነው፣ ያፈቀርከውን ሰው ቶሎ ቶሎ እየው የሚል ስሜት ይፈጠርብሀል ሰለሱ ላለማሰብ በጣም ብዙ ጥሬ ነበር ግን አልቻልኩም በቃ ፍቅረኛው ወይ ትከዳዋለች ወይ ትሞታለች ከዚያ የኔ ይሆናል እያልኩ ራሴን እፅናና ነበር ... በመሀከል ሚስቱ የኔን ሁኔታ እና እንቅስቃሴ አወቀችና በፍጥነት ከቤታችን ውጣ! ያኔ ይበልጥ በጣም ተጎዳሁ! ከ6ወር በኋላ ለማመን እስከሚቸግረኝ ድረስ ያፈቀርኩት ሰው ቤታችን ድረስ መጣ:: በደስታ ሳላስበው አቀፍኩት፣ አወራን:: ከፍቅረኛው እንደተጣላ ነገረኝ:: በሁለተኛው ቀን የተከራየው ቤት ወሰደኝ:: ከብረንፅናዬን ሰጠሁት:: ላሳጥረውና ለአንድ ዓመት በደስታ ኖርኩኝ ምን ዋጋ አለው እርሱ የፈለገኝ ለወሲብ ብቻ ነበር:: ከፍቅረኛዬ ተለያይቻለሁ ያለው ውሸቱን ነበር ... አሁን በጣም የሚቆጨኝ ለሱ ስል ከዩኒቨርሲቲ መቅረቴ ነው:: ብቻ ብዙ ጠባሳ ነው ያሳደረብኝ በዚህ አጋጣሚ ለሴት እህቶቼ የምመክራቸው አባካችሁ የሚቻላችሁ ከሆነ ለወሲብ አትቸኩሉ የሚል ነው"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

" በጣም አመሰግናለሁ ቃልኪዳን መልካም ጊዜ ይሁንልሽ አድማጮች ሌላ ደዋይ መስመር ላይ ገብቷል:: ሀሎ ማን ልበል?"

" ስሜ ይቅር ስለ ወንድሜ ማውራት እችላለሁ?"

" በሚገባ ቀጥል"

" ከሁለት ዓመት በፊት ወንድሜ ከሥራ ሲመጣ እንዲት የተቀበች ሴት ሊፍት ሰጣቸው! ተዋወቁ መደዋል ጀመሩ! በጣም የተቀበች ሴት ነበረች:: በወሩ መጨረሻ ውጪ አደረ:: ጠዋት ሲመጣ የሰማውትን ማመን አቃተኝ .... መድሀኒት አድርጋበት ... የሆነ የተዋበ ግቢ ውስጥ ወስዳው ለሁለት ወንዶት አስደፍራው ነበር:: አሁን ስጠይቅ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ 'ቡኒ እርግቦች ' በሚል መጠሪያ የሚጠሩ ስራቸው ወንድ ልጅን እያጠመዱ ለግብረሰዶማዊያን ማስረከብ ነው:: በዚህ አጋጣሚ ሴቶች ሆኑ ወንዶች ማንም ግለሰብ በነገራችን ላይ ወንድሜ ራሱን ሰቅሎ ከሞተ ወር ሊፍት ሲሰጣቸው መጠንቀቅ አለባቸው፤ ሆኖታል!"

" ስለሰጠኸኝ መረጃ በአድማጮች ስም በጣም አመሰግናለሁ መልካም ጊዜ ይሁንልህ! አድማጮቻችን የዝነኛውን Stevie wonder ተወዳጅ ዜማ እንስማና የመጨረሻ ሁለት ደዋዮች እንዲሁም አንድ ዝነኛ ሳይኮሎጂስት በአየር ላይ ይውላሉ! የምታዳምጡት FM66.6 ትን ነው::"

እያስተናገድኳችሁ ያለሁት ዝነኛው ጎልያድ ነኝ"

....

I just called to say I love you
I just called to say how much I care
I just called to say I love you
And I mean it from the bottom of my heart
No summer's high
No warm July
No harvest moon to light one
Tender august night ...

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

"ሀሎ ማን ልበል?"

"ሶስና"

" ከየት ነው ሶስና?"

"ሾላ ገበያ"

" እሺ የመጀመሪያ የፍቅር ጣጣሽ ምን ይመስል ነበር?"

" በጣም አሪፍ ነበር! በብዛት የምሰማው ሆነ የማየው አብዛኛው ሰው በመጀመሪያ ፍቅር ተጎዳሁ ሲል ነው እኔን ያጋጠመኝ ግን ጥሩ ነው:: ያፈቀርኩት ሰው በጣም የተማረ ነበር:: ፍቅር ሲይዘኝ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩ:: ሁሉ ነገር ከአቅሜ በላይ ሲሆንብኝ ደብዳቤ ሰጠሁት:: ጠራኝ:: በአክብሮት አናገረኝ:: ማፍቀር ጥሩ እና የጤንነት ምልክት ነው ከኔ ጋር በፍቅር መቆየት ከፈለግሽ ሁለት ነገር ካንቺ ይጠበቃል! ይሄን ውፍረትሽን ቀንሺ! አሁን ከባድ ፈተና ስላለብሽ በደንብ አንብቢና ዩኒቨርሲቲ ግቢ! ዩኒቨርሲቲ መግባት ብቻ አይደለም ተመርቀሽ መውጣትም አለብሽ ይህን ሟሟላት ከቻልሽ እኔ ያንቺው ነኝ... እሱን እያሰብኩ ውፍረቴን ቀነስኩ :: ዩኒቨርሲቲ በጥሩ ውጤት ተመርቄ ወጣሁ:: የሚገርመው አንድ ቀን እንኳ ፀባዩ አልተለወጠብኝም ሁሌ ያበረታታኝ ነበር! ተመርቄ ስጨርስ 60ሺ ብር አስቀምጦልኝ ወደ እስራኤል ሄደ"

" ለምን?"

" በቃ የሱ አላማ ውፍረቴን እንድቀንስ እና ጎበዝ ተማሪ እንድሆንለት ብቻ ነበር ... የካንሰር ታማሚ ነበር:: በጣም ጥሩ ሰው ነበር በዚያን ሰዓት ቢፈልግ በእኔ ሕይወት መቀለድ ይችል ነበር:: አሁን በጣም የምበሳጨው ምነው አንድ ቀን እንኳ አብረን በተኛን እያልኩ ነው:: የሴትነት ክብሬን ብሰጠው ደስ ይለኝ ነበር!"

" ሶስና ከሾላ አመሰግናለሁ! አድማጮች ሌላ ደዋይ መስመር ላይ ይገኛል ሀሎ ማን ልበል?"

" ከድር ነኝ"

" ከድር ከየት ነው?"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

" እሺ ከድር ያንተ የመጀመሪያ የፍቅር ጣጣ ምን ይመስል ነበር?"

" የኔ ትንሽ ለየት ይላል! ለመጀመሪያ ጊዜ ፍቅር የያዘኝ የሀያ ዓመት ወጣት እያለሁ ነበር:: እኔ የግል ሥራ ነበር የምሠራው ት/ት ላይ ደካዛ ነበርኩኝ ያፈቀርኳት ወጣት ደግሞ አዋሳ ዩኒቨርሲቲ ትማር ነበር! እኔንጃ ብቻ ሳያት የምሆነውን ነበር የማጣው ሲብስብኝ ሰው ነገረልኝ:: አይመጥነኝም አለች:: ብዙ ጣርኩ ብዙ ሞከርኩ አልተሳካልኝም:: እሷም እኔን ተስፋ ለማስቆረጥ ፍቅረኛ ይዛ ሆን ብላ እኔ በምሠራበት ቦታ ይመላለሱ ገቡ:: በቅናት ተቃጠልኩ:: ከዚያ አንድ እሁድ ምን እንደነካኝ አላውቅም አሳቻ ቦታ ጠብቄ ቅጥቅጥ አድርጌ አስቀመጥኳት በጣም ተጎድታ ነበር:: በነጋታው ፖሊስ ያዘኝና አምስት ዓመት ማረሚያ ቤት ቆይቼ ወጥቻለሁ:: በዚህ አጋጣሚ ለአፍቃሪዎች የምመክረው አንድ ትልቅ ሀቅ እንዳለ እንዲያውቁ ነው:: እኛ ያፈቀርነው ሰው እኛን የግድ ማፍቀር አለበት የሚል አቋም መያዝ ጨለምተኝነት ነው! ስለዚህ በስሜት ተገፋፍተው ባፈቀሩት ሰው ላይ እንደኔ ጉዳት ማድረስ የለባቸውም ! አመሰግናለሁ"

" ከድር እኔም ስለደወልክልኝ ከልቤ አመሰግናለሁ! አድማጮች ብዙ ደቂቃ ስለሌለን በቀጥታ ወደ ዝነኛው ሳይኮሎጂስት አበራ ፋንታሁን እናምራ! ሀሎ አቶ አበራ እንዴት ነህ?"

" ፈጣሪ የተመሰገነ ይሁን"

" በቅድሚያ በአድማጮች ስም ስለ ደወልክልኝ በጣም ነው የማመሰግነው እንግዲህ ስለ ፍቅር በተለይ ስለ የመጀመሪያ ፍቅር ጣጣ እያወራን ነበር ካለኝ ደቂቃ አንፃር የተወሰኑ ጥያቄዎች አሉኝ ልቀጥል አቶ አበራ?"

" ቀጥል ... ቀጥል"

" ከፍቅር ራሱ እንጀምርና ፍቅርን እንዴት መግለፅ ይቻላል?"

" በእርግጥ ሁሉንም ሊያስማማ የሚችል የፍቅር ፍቺ እስካሁን አልተገኘም ባጠቃላይ ግን አነቃቂ ስሜት፣ ሀይለኛ ሞገድ፣ ጥሩ ነገር እንድንሠራ የሚያነሳሳን፣ ሕይወት አሰልቺ እንዳትሆን የሚያደርግልን፣ ልዩ ስሜት እንዲሰማን የሚያደርገን፣ ከውጪ የሚመጣ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ሳይሆን በውስጣችን የሚገኝ ኬሚካል ነው ለማለት ይቻላል"

" አንዳንድ ሰዎች ፍቅር የሚባል የለም ይላሉ ሌሎች ደግሞ ፍቅር የሚባል አይዘኝም ይላሉ ይህን ሀሳብ እንዴት ትመለከተዋለህ?"

" አባባል ብቻ ነው:: አባባል ሁሉ ልክ ነው ማለት አይደለም! በጥናቶች እንደተረጋገጠው ይህን መሰል የሚናገሩ ግለሰቦች ከማንኛውም ሰው ይበልጥ ፍቅር ሲይዛቸው እንደሚሰቃዩ ባስ ሲልም ራሳቸውን ሲገድሉ እንደሚታዩ ለማረጋገጥ ተችሏል:: እዚህ ጋር መታወቅ ያለበት አስቀድሜ እንዳልኩት ፍቅር ከውጪ የሚመጣ ነገር አይደለም ከውስጣችን አውጥተን የምንሰጠው ነገር ነው:: ስለዚህ ፍቅር የለም የሚል ሰው በሌላ ቋንቋ እኔ በድን ነኝ እያለ ነው! በዚህ አጋጣሚ የፍቅር አይነቶችን በ13 ዘርፍ ከፍለን ነው የምናያቸው ሁሉንም በዝርዝር ለማስቀመጥ አሁን አስቸጋሪ ነው:: አንዳንድ ሰዎች ላይ "የማታ ፍቀር" የሚባል ነገር አለ:: እድሜያቸው በጣም ከገፉ በኋላ የፍቅር ስሜቱ የሚቀሰቅስባቸው ማለት ነው አንጂ 100% በፍቅር የማይያዝ ሰው በምድር ላይ የለም! አይኖርምም! እያንዳንዱ ሰው ከ13ቱ የፍቅር አይነቶች ውስጥ የግዴታ በአንደኛው ውስጥ መገኘቱ አይቀርም!"

" ወደ ዛሬው ርዕስ እንምጣና የመጀመሪያ ፍቅርን እንዴት መግለፅ ይቻላል?"

" ጥሩ ጥያቄ ነው:: የመጀመሪያ የሆኑ ነገሮች ሁሉ አስቸጋሪ ናቸው:: ያደናብራሉ፣ ግራ ያጋባሉ፣ ስሜትን ይረብሻሉ፣ ጥያቄ ይፈጥራሉ፣ የተለየ ስሜት ውስጥ ይከቱናል፣ ምክኒያቱም ከዚህ በፊት ይህን መሰል ነገር አጋጥሞን ስለማያውቅ! በመጠኑ ግራ መጋባቱ ያለ ነገር ነው:: ባጠቃላይ እንደ አስተሳሰባችን የመጀመሪያ ፍቅር ማርም ሬትም ሊሆን ይችላል:: ይህን አስቀድሞ ማወቅ አዋቂነት ነው::"

" እቶ አበራ የብዙዎች ችግር ካፈቀሩት ሰው ጋር መለየት መቻገር ነው:: በሌላ በኩል ያፈቀሩትን ለመጠየቅ በጣም የሚቸገሩ ሰዎችም አሉ:: ይህ ስሜት ከየት ይመጣል?"

" ይህ የሚመጣው በራስ ያለመተማመን፣ ለራስ ዝቅተኛ ውጤት መስጠት፣ ራስን እንደተራ ከመቁጠር የሚመጡ አሉታዊ ስሜቶች ናቸው:: If they are not positive

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

thinkers ሁሉን ነገር የሚመለከቱት በአሉታዊ መንገድ ነው:: ወደ ፍቅር ስንገባ ፍቅር ህግ ባይኖረውም የራሱ ደንብ ግን አለው:: እኛ ያፈቀርነው ሰው እኛን ማፍቀር ግዴታ የለበትም እኔ ስላፈቀርኩት እሱም እኔን ማፍቀር አለበት ማለት አምባገነንነት እና በራስ ያለመተማመን ችግር ነው:: የተፈቀሩ ሰዎች ሲለያዩ ለምሳሌ DUMP የተደረገችው ሴት ከሆነች አዕምሮዋ መላልሶ የሚነግራት "ተናቅሽ አትረቢም ከንቱ ነሽ" የሚል ስሜት ነው:: በዚያ ላይ ከለመዱት ነገር መለየትም የራሱ የሆነ ፍርሀት ይፈጥራል:: ለምሳሌ ሁልጊዜ ጠዋት ቁርሱን ዘጠኝ ዳቦ መብላት የለመደ ሁለት ዳቦ ቢሰጠው አይረካም! ይበልጥ ይራባል! በፍቅር ስንያዝ ደግሞ ቅድም አንተም ለመግለፅ እንደሞከርከው ዶፓሚን የተባለው ንጥረ ነገር ፍቅር ሲይዘን በሰውነታችን ውስጥ በጣም ስለሚረጭ ያፈቀርነው ግለሰብ ከኛ ሲለየን ባርባር፣ ፍርሀት፣ ጭንቀት፣ ብቸኝነት፣ ግራ መጋባት ፣ የበታችነት ስሜት ለተወሰነ ጊዜ መፍጠሩ አይቀርም በተለይ ቅድም እንዳልከው ግለሰቡ በራስ የመተማመን ችግር ካለበት ችግሩ ይበልጥ ይባባሳል! እንዳልከው ብዙዎች አፍቅረው መጠየቅ የሚፈሩት ለራስ ካላቸው ንቀት አንዳንዴ ከፍተኛ ለራስ በሚሠጥ አጉል ክብርም ጭምር ጠይቄ እንቢ ብባል ወይም እባላለሁ በሚል ፍራቻ ለመጠየቅ ይፈራሉ በተለይ በፊት ፈሪ ከሆኑ ያፈቀሩትን ሰው ከሰው በላይ አስበልጠው የተለየ ፍጡር አድርገው ገና ሲመለከቱት ሁሉ ሰውነታቸው በላብ መጠመቅ ፣ መራድ፣ መደነባበር፣ ግራ መጋባት፣ በእጃቸው ዕቃ ይዘው ከነበሩ ሳያውቁት መጣል፣ ያፈቀሩትን ሰው ሲመለከቱ የልብ ትርታቸው ቶሎ ቶሎ መደለቅ፣ እንደበታቸው መዘጋት፣ የመሳሰሉት ስሜቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ:: ለዚህ መፍትሔው እንግዲህ ለራስ ያለንን ግምት መለወጥ ፣ እና ያፈቀርነውን ሰው ጠይቀን እንቢ ከተባልንም ራሱ በጣም አመስግነን መሄድ ነው እንጂ ሙጭጭ ማለት ጠቀሜታ የለውም:: በእርግጠኝነት ማወቅ ያለብን እኛን የሚያፈቅረን ሰው እንዳለ ማወቅ ነው"

" በዚህ አጋጣሚ አቶ አበራ ለምሳሌ አንድ ወንድ ከአንዲት ሴት ጋር ለአምስት ዓመት ሲጠናኑ ቆይተው ወንዱ እንደማትስማማው ሲያውቅ ማለቴ If she is not his type እንደማትሆነው ነገራት እንበል፣ ልጅቷ ራሷን ብትገድል ተጠያቂው ማን ነው?"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

" እንዳልኩህ ነው ከእውነታ አንፃር የምንነጋገር ከሆነ ጥፋተኛዋ ወጣቷ ናት በራስ መተማመን ወይም ለራሱዋ ጥሩ ግምት ቢኖራት በእርግጥ ካፈቀሩት መለየት ለተወሰነ ጊዜ ቢያስቸግርም ሌላ አፍቃሪ ለኔ አለ ብላ ብታምን ራሷን አታጠፋም ነበር:: በፍቅር ላይ ትልቁን ሚና የሚጫወተው ለራስ የሚሰጥ ግምት ፣ ቆና የመሆን እና ካለመሆን ጋር በተያያዘ ነው በዚህ አጋጣሚ ለተፈቃሪዎች የምመክረው የፈለገውን ያህል ብንፋቀር መለየት በተለያየ ነገር እንዳለ አስቀድሞ ማሰብ... ከሌላ ሰው ጋር ወደ ፍቀር ከእንደገና ልንገባ እንደምንችል ማወቅ ለወሲብ አለመቸኮል... በተለይ ከፍቅረኛችን ስንለያይ ወዲያው በንዴት ሌላ ፍቅረኛ ቢያንስ እስከ ስድስት ወራት መያዝ የለባቸውም"

" አቶ አበራ የመጨረሻ ጥያቄ ፍቅር እና ቅናት ግንኙነት አላቸው? ያፈቀረ ሰው መቅናት አለበት፣ ካልቀና አላፈቀረም ማለት ነው የሚሉ አሉ ምን ትላለህ?"

" ግንኙነት የላቸውም ለማለት አይቻልም:: ይህ እንግዲህ ከራሳችን አመለካከት ጋር ቀጥታ ግንኙነት አለው:: ራሱን የሚያምን አፍቃሪ ተፈቃሪውንም ያምናል:: በሌላ በኩል የተገናኘንበት መንገድም ለቅናቱ ወሳኝ ሚና ይጫወታል:: ለምሳሌ አንድ ወንድ ታክሲ ውስጥ አንዲት ወጣትን ቢጠብሳት ያቺ ወጣት ፍቅረኛዋ ታክሲ ውስጥ ከሴት ጋር ሲያወራ ስታይ ልትቀና ትችላለች፣ መጠጥ ቤት የተዋወቁ ለየብቻቸው መጠጥ ቤት ቢሄዱ ቅናት ሊፈጠር ይችላል ... ለሥራ ክፍለ ሀገር ሄዶ የተዋወቁ ያ ሰው ሌላ ቦታ ለሥራ ቢሄድ ሌላ ሴት ጋር ልትሄድ ነው በሚል ቅናት ሊፈጠር ይችላል:: ባጠቃላይ ያልበዛ ከሆነ ቅናት ሊፈጠር ይችላል እንደተባለውም የፍቅር መገለጫም ሊሆን ይችላል:: ይህ ማለት ግን አልቀናም ማለት አላፈቀረም ማለት ግን አይደለም! በዚህ አጋጣሚ ወንዶች ከማርስ ሴቶች ከቬነስ የሚባለውን ምርጥ መፅሐፍ እንዳያነቡ ጋብዛለኝ! በተለይ የመጀመሪያ ፍቅር ቅድም እንዳልኩት ሬትም ማርም ሊሆን ይችላል:: ለማንኛውም በድንገት ፍቅረኛችን ከኛ ቢለየን ብዙ ጉዳት እንዳይደርስብን የሚከተሉትን ተግባሮች ማከናወን ጥሩ ነው"

i. ለብቻ ሆኖ ቢያንስ ለ45 ደቂቃ ስቅስቅ ብሎ ማልቀስ ... የሚሰባበሩ ዕቃዎች ካለ መሰባበር

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

2. ለአንድ ሰዓት ያህል በቀዝቃዛ ውሃ ውስጥ ተቀምጦ መቆዘም

3. ያፈቀርነውን ግለሰብ የሚያስታውሱንን ማንኛውንም ነገሮች ማስወገድ ፎቶ፣ ስጦታ፣ ስልክ፣ face book ላይ ካለ block this person የሚለውን መጫን ..

4. ፍቅር ነክ ሙዚቃዎችን መሸሽ

5. ራስን ከወትሮው ይበልጥ በስራ መወጠር... ብዙ ሰዓት ለብቻ እያሰቡ አለመቀመጥ!

6. ውስጣችን ያለውን ስሜት በጣም ለምንቀርበው ሰው በዝርዝር ማውራት ፣ ማማከር ታዲያ የምናማክረው ሰው በእውቀት፣ በልምድ እና በአስተሳሰብ ከኛ የተሻለ መሆኑን ማረጋገጥ ! እውር እውርን ...

7. እንደ እምነታችን የእምነት ቦታዎች ሄዶ ለፈጣሪ መናዘዝ

8. በምንም ተዓምር ለመርሳት ተብሎ መጠጥ፣ ጫት፣ ሲጋራ፣ ጭፈራ ቤት፣ ቶሎ ሌላ ፍቅረኛ ከመያዝ መቆጠብ...

9. በእርግጠኝነት አንዱ በር ሲዘጋ ሌላው ይከፈታልና ሌላ ፍቅረኛ እንደሚኖረን ማወቅ... በራስ መተማመን

10. በምንም ተዓምር ለገንዘብ፣ ለጊዜያዊ ስሜት (ወሲብ) ፣ ለበቀል፣ ለማማረጥ ብለው ፍቅር ውስጥ እንዳይገቡ.."

" አቶ አበራ ለዛሬው በጣም አመሠግናለሁ ሌላ ጊዜ በስፋት ሙያዊ ምክርህን ትሰጠናለህ፣ የተከበራችሁ አድማጮች አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል! ከFM66.6 ጋር በመተባበር የሚቀርበው የዛሬው ፕሮግራም እዚህ ላይ ተጠናቋል:: በ0911 04 89 ** ላይ የደወላችሁ ሆነ በ777 ላይ SMS በመላክ 2 ብር ለሰጣችሁኝ አድማጮቼ ሁሉ በጣም አመሠግናለሁ! በጥሌ ሙዚቃ እንሰያይ ሰናይ ጊዜ! ኀልያድ ነበርኩ... በዚህ አጋጣሚ ከፍቅር ጋር በተያያዘ ችግር ውስጥ ያላችሁና የባለሙያ ምክር የምትፈልጉ ካላችሁ በ0911 04 89 65 ላይ ብትደውሉ በተለይ ደግሞ አጭር የፅሁፍ መልዕክት /SMS/ ብትልኩ ከአቶ አበራ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ፉንታሁን ጋር አገናኛቹዋለሁ! ወደ ጥሌ ዜማ.."

... ከሰው ተራ አውጥቶ ያረገኝ ብቸኛ
አውቃለሁ ፍቅርሽ ነው ይሄ መዘዘኛ
ነጭናጫ ያረገኝ ተቆጪ በቶሎ
ያው ያንቺ ፍቅር ነው ሌላ ማን ተብሎ
ስምቼ እንዳልሰማው ያረገኝ ፍቅርሽ ነው
አንድ በይ አንቺዬ አረምነው ምነው?...

## ምርቃት

" How to get over your first love: 13 steps' በሚል ምርጥ ሀሳቦችን ያንብቡ ... በጣም ይጠቀማሉ ... ሙሉ መረጃዎን Google ላይ " First love" በመፃፍ ማንበብ ይችላሉ ... ከመጀመሪያ ፍቅር ጋር የተያያዙ አባባሎች ... ገጠመኝ... ምክሮችንም ... ሁሉ ያነባሉ ...

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

# ክፍል ሐ

# “ ስለ ወሲብ እናውራ”

የካቲት 22/2005

ስለወሲብ እናውራ

FM66.6

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

" የተከበራችሁ አድማጮች የዕለተ ሐሙስ የካቲት 22 አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል ፕሮግራም እነሆ ጀመረ! ለዛሬ የተመረጠው ርዕስ ስለ ወሲብ እናውራ የሚል ነው... በዓለማችን ላይ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው አምስት ነገሮች አሉ:: ፍቅር፣ ብር፣ ስልጣን፣ ወሲብ እና እምነት ናቸው! እነዚህ አምስት ሀይላት እንግዲህ ዓለማችን ላይ ትላንትም ዛሬም ወደ ፊትም የውዝግብ መንስኤ ሆነው ይቀጥላሉ ... በቅርቡ የወጡ ጥናቶች የሚያሳዩት በዓለም ላይ ከፍተኛ ወጪ የሚወጣበት ሆነ ገቢ የሚታፈስበት ወሲብ እንደሆነ ያትታል... በወሲብ ዙሪያ ከ5475000 በላይ መፅሐፎች በኢንግሊዝኛ ቋንቋ ብቻ እስካሁን ተፅፈዋል! በርከት ያሉትም በኛ ሀገር ቋንቋ ተተርጉመው ለጉድ ተሸጠዋል... እየተሸጡም ይገኛሉ:: (ሶስት አብይ የወሲብ ዘርፎች አሉ:: ከ426 በላይ የወሲብ አይነቶች አሉ:: ወሳኝ የሚባሉትን 26ቱን የወሲብ አይነቶችን ለማወቅ ጉጉት ከተፈጠረበት ኢያሪኮ 999 መፅሐፍ ገፅ 42-49 ያንብቡ) ለማንኛውም የተከበራችሁ አድማጮች እጅግ በጣም የተወሳሰበ ማህበራዊ ቀውስ ውስጥ እየከተተን ያለ ጉዳይ ነውና ዛሬ ስለ ወሲብ እናወራለን በ0911 04 89 ** ላይ ደውሉ በ777 ላይ SMS ላኩ ታዲያ ሁለት ብር መቆንደዳችሁን እንዳትረሱ ! ከማስታወቂያ እና ከ Limp bilkit ሙዚቃ መልስ የመጀመሪያ ደዋይ በአየር ላይ አውላለሁ እስከ መጨረሻው እናንተን የተከበራችሁ አድማጮቹን እያስተናገድኩ የምቆየው ዝነኛው ጎልያድ ነኝ... አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል ጀምሯ"

## ሻማከ ማሳጅ

እጅግ በጣም ዘምና በተሰራው ቢላ በታችን ውስጥ እጅግ ውበት ባላቸው ሴጋ ወጣቶች የማሳጅ አገልግሎት እንሰጣለን! ከሌሎች ማሳጅ ቤቶች ሻማከ ማሳጅን ልዩ የሚያደርገው ገላዎትን በውብ ወጣት ሴቶች ይታጠባሉ! 100 ብር ብቻ በመክፈል እንደ ሌላው ማሳጅ ቤቶች extra ሳይጠየቁ የወሲብ ስሜቶዎንም በነፃ ከእንዷዋ ውብ ወጣት ጋር ያደርጋሉ!
ልበ እስከሚጠፋ ረከተው ይወጣሉ ...
አድራሻችን አዲሱ በሌ ድልድይ አጠገብ
ሻማከ ማሳጅ የደስታ ደጅ!!

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

> ....
> It's a fucked up world; we're a fucked up place
> Everybody judged by their fucked up face
> Fucked up dreams; fucked up life
> A fucked up kid with a fucked up knife
> Fucked up moms and fucked up dads
> And a fucked up cop with a fucked badge
> With a fucked up job with fucked up pay...

" እያዳመጣችሁት ያላችሁት አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል የተሰኘውን ፕሮግራም FM66.6 ጋር በመተባበር የሚቀርበውን ነው:: የመጀመሪያው ደዋይ መስመር ላይ ነው ሀሎ ማን ልበል ?"

"አቶ አቻም ያለህ ከኢቃቂ 08 ቀበሌ"

" እሺ አቶ አቻምየለህ የዛሬው ርዕሳችን ስለ ወሲብ እናውራ የሚል ነው! የእርሶ ሀሳብ ምንድ ነው?"

"እውነቱን ለመናገር ወሲብ ተፈጥሮአዊ ነው:: ወሲብ የተቀደሰ የፈጣሪ ስጦታ ነው:: ወሲብ መኝታው ቅዱስ ነው:: ይሄ ምንም ጥርጥር የለውም! ሰው ከተፈጥሮ ውጪ ለመሆን አይችልም ተፈጥሮን በተለይ ስሜታችንን ግን መግዛት እንችላለን! በአሁኑ ዘመን ግን ስሜታችን በጣም እየገዛን ነው:: እውነቱን ነው የምልህ እኔ የእግዜርን ቃል ስለማከብርና የተቀደሰ ዘር እንዲኖረኝ ወሲብ ለመጀመሪያ ጊዜ ያደረኩት ሚስቴን ሳገባ ነበር:: እስከዛሬም የሌላ ሴት ገላ ነክቼ አላውቅም:: እኔ ለወጣቱ መምከር የምፈልገው ከጋብቻ በፊት እንምከከር ወይም ወሲብ ፍቅራችንን ያጠናክራል በሚል የተሳሳተ መረጃ ወሲብ ማድረግ የለባቸውም!! በተጨማሪ ትልቁ ስህተት ከብዙ ሰው ጋር ወሲብ ማድረግ ችሎታን ያዳብራል የሚል አመለካከት አለ ይህ ትልቅ ስህተት ነው:: በተ[illegible] ብዙ ሰው መማገጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ይበልጥ የወሲብ ችሎታን ከማዳበር ይልቅ አርካታ ቢስ እንደሚያደርግ የብዙ ባለሙያዎች ጥናት አረጋግጧል! ባጠቃላይ ለወጣቶች የምመክረው እባካችሁ የፈጣሪ መቀመጫ የሆነውን የተከበረውን ሰውነታችሁን ከምታገቡት ሰው ውጪ እንደ ሴተኛ አዳሪ አታርክሱት ነው፤ የእግዚአብሔርን ቃል አክብረው ተጋብተው በጋብቻቸው ጊዜ የወሲብ አለመጣጣም ቢፈጠር እንኳ ለአምላካቸው ቢፀልዩ ታላቁ ፈጣሪያችን እንኳን የወሲብ ችግርን መፍታት ቀርቶ የሞተን እንኳ ያስነሳል:: ሴይጣን የሰው ልጅን ከሚፈትንባቸው መንገዶች ዋነኛው ወሲብ ነው ለዛ እኮ ነው ታላቁ ጠቢቡ ሰለሞን ያን ሁሉ ጥበቡን ያጣው በምንድ ነው? በወሲብ አይደለምን? ለማንኛውም አመሠግናለሁ"

" እኔም አቶ አቻምየለህ ስለሰጡኝ ሀሳብ በጣም አመሠግናለሁ! አድማጮች ሌላ አድማጭ መስመር ላይ ይገኛል:: ሀሎ ማን ልበል?"

"ዱናሚስ በዓሉ"

" ዱና ሚስ ከየት ነው?"

" ከሰበታ አራዳ"

" ፍቅረኛ አለህ?"

" አለኝ"

" ስንት ዓመት ሆናችሁ?"

" ዓመት ከአራት ወር"

" ወሲብ አድርጋቹኋል?"

" 58 ጊዜ አንሶላ ተጋፈናል! ወሲብ ስናደርግ እንመዘግበዋለን"

" ብዙዎች ከጋብቻ በፊት ወሲብ ማድረግ ለትዳር ዘለቄታዊነት ጥሩ አይደለም! ቅድመ ወሲብ እንደ ዝሙት ይቆጠራል! ከጋብቻ በፊት ቀድሞ በወሲብ መርካት የማግባት ፍላጎትን ይቀንሳል ይላሉ ምን ትላለህ?"

" ወሬኛ በላቸው!! እኛ ሀገር ትልቁ ችግር ምን እንደሆነ ታውቃለህ? ማድረግ ያቃተንን ነገር አድርጉ ብሎ መምከር ነው! አባባል ብቻ አድርጌ ነው የምወስደው አግብቼያት

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ወሲብ ላይ ቀሰስተኛ ሆና ከምንፋታ ቀድመን ተፈታትነን ካልተመቻቸን መለየት ነው:: እውነቱን ለመናገር አብዛኛው ሽማግሌ በየሽርሙጣ ቤቱ የሚገኘው ፡ ለሥራ ከፍለ ሀገር ነኝ ብሎ ከሌላ ሴት ጋር የሚማግጠው (ሁሉንም ማለቴ ግን አይደለም) ከተጋቡ በወሩ የሚፋቱት በወሲብ ዙሪያ ግልፅነት ስለሌለ እኮ ነው:: እኔ ገና ነገ እግብቼያት ወሲብ እናደርጋለን ብዬ እያሰብኩ ልፈንዳ እንጴ? የሌላ ሰው ሰዓት ካልተሻማው አንድ እውነተኛ ነገር ልንገርህ" " እሳጥረው እሺ"

"አመሰግናለሁ ያዕቆብ የሚባል ጓደኛ አለኝ በጣም የሚወዳት ልጅ ነበረችው:: ወሲብ ሲጠይቃት ከጋብቻ በፊት አንገቴ ይታረዳል አለች:: ውይ የኔ ቆንጆ ልፈትንሽ ነበር እንጂ ከመጋባታችን በፊት ወሲብ መጀመር አልፈልግም አላት:: የሚገርምህ እየተደበቀ ከሴተኛ አዳሪ ጋር ይወጣ ነበር:: ሌላ ሴት ጠብሶ በሳምንት ሁለት ቀን ይወጣ ነበር ብቻ ልጁ ትንሽ ቆንጆ እና ገንዘብ ስላለው ይጨፈጭፍ ነበር... ከሶስት ዓመት የፍቅር ቆይታ በኋላ ተጋቡ:: ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አስጠላችው:: ወሲብ ላይ እሱ ዲግሪ አለው እሷ ሰርተፍኬት ናት! አንድ ዓመት ለማስለመድ ጥረት አደረገ እርሷ አልቻለችም! ተፋቱ! የሁለቱም ሕይወት ተበላሸ.. ስለዚህ ለኔ ሰዎቹ የሚሉትን አልቀበልም! ከቻልክ ኮተታም ነገር ናችሁ በልልኝ"

" ዱናሚስ ከሰበታ አመሠግናለሁ"

" እኔም አመሠግናለሁ ... አድማጮች ሌላ ደዋይ መስመር ላይ ገብቷል:: ሀሎ ማን ልበል?"

" ዘውዲቱ በላይነህ"

" ከየት ነው ዘውዲቱ?"

" ከአየር ጤና"

" ስንት ዓመትሽ ነው?"

" 22 ዓመቴ ነው"

" ፍቅረኛ አለሽ?"

" ነበረኝ የወሲብ ጥያቄ ሲያነሳ ጊዜ ተወያይተን በመፋታት ተስማምተን ነበር አልተሳካም

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ተለያየን  እኔ ከጋብቻ በፊት ወሲብ አላደርግም የሚል አቋም ላይ ነኝ! ለሴት እህቶቼ የምመክረው ቅድመ ወሲብ ባያደርጉ ነው:: ሙሉ ለሙሉ ተጎጂው እኛው ሴቶች ነን ማርገዝ አለ፤ በሽታ አለ በዚያ ላይ በብዙ ሴት ጓደኞቼ ያየሁት እና የነገሩኝ ወንዶች ወሲብ ካደረጉ በኋላ ፍቅራቸው የመቀዛቀዝ!! እና የመናቅ ስሜት ይንፀባረቅባቸዋል በዚህ አጋጣሚ እኔ እንደ ሀሳብ  የማነሳው በመንግስት ደረጃ ከ18 ዓመት በታች ከሆነች ሴት ጋር ወሲብ ማድረግ ወንጀል ነው የሚለው በወረቀት ብቻ ሳይሆን በተግባር ውሎ ይህን ድርጊት የሚፈፅሙት ላይ ክስ ቢመሠረት ጥሩ ነው:: አልጋ ቤቶች ራሱ ከ18 ዓመት በታች የሆነችን ሴት ማሳደር የለባቸውም የሚል ሀሳቤ ለመሰንዘር ነው"

" እናመሰግናለን! ኢድማጮች አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል ከ FM66.6 ጋር በመተባበር የሚቀርበው ተወዳጅ ፕሮግራም እንደቀጠለ ነው:: እየተወያየን ያለነው ስለ ወሲብ እናውራ የሚል ነው 0911 04 89 ** ላይ ደውሉ በ777 ላይ SMS ላኩልኝ አንድ ሙዚቃ እንስማና እንመለሳለን"

... Totoos on her ass take one  
Dame Grease, we got'em baby  
Got these niggaz  
Got the whole game tryna take  
Up down A1 pac ....  
Fuck this shit ....

" ኢድማጮች ተመልሼ መጥቻለሁ! ሁለቱም ስልኮች እየጠሩ ናቸው:: በርከት ያሉ መልዕክቶችም በ777 SMS ላይ እየመጡ ናቸው:: FM66.6 እንደቀጠለ ነው:: እያስተናገድኳችሁ ያለሁት ዝነኛው ኀልያድ ነኝ! ሀሎ ማን ልበል?"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

" ኤፍሬም"

" ከየት ነው ኤፍሬም?"

" 4 ኪሎ "

" ስለ ወሲብ እያወራን ነው ያንተ ሀሳብስ ምንድ ነው?"

" 30 ዓመቴ ነው በትዳር ውስጥ ነው ያለሁት:: እውነቱን ለመናገር ከጋብቻ በፊት ከበርካታ ሴቶች ጋር ወሲብ አድርጌያለሁ:: ሚስት አግብቼ ለተወሰነ ጊዜ በጣም ተቸግሬ ነበር ስለዚህ እኔ መናገር የምፈልገው ሶስት ነገሮች አሉ:: የመጀመሪያው የወሲብ ፊልሞችን በተመለከተ ነው:: የወሲብ ፊልም ላይ የሚታየው ትዕይንት ሁሉ የካሜራ ጥበብ እና የመድሀኒት ሀይል እንጂ እውነት እንዳልሆነ ማወቅ አለባቸው:: ወንዶቹ ሳይረጩ ለረጅም ደቂቃ የሚቆዩት ፣ ሴቶች ለማስመሰል የሚጮሁት... ሁሉም ነገር እንደ ፊልም በጥበብ የሚቀናበር ስለሆነ እንዳይሸወዱ ነው:: ሁለተኛው በተለይ ለተማሪዎች ወሲብ የት/ት ሰዓትን በጣም ስለሚሻማ ወደ ወሲብ እንዳይገቡ መጠንቀቅ አለባቸው:: የመጨረሻው ሀሳቤ የግል ሕይወቴን ሌላው እንዲማርበት በግልጽ የምናገረው ከብዙ ሴተኛ አዳሪዎች ጋር አድሬያለሁ! እነሱ ጋር ሳገኝ የነበረው እርካታ ሚስቴ አልሰጠችኝም:: ቆይቼ የተረዳሁት ግን ችግሩ የሚስቴ አይደለም:: ሚስቴ ከኔ ሌላ ከሌላ ሰው ጋር ወሲብ አድርጋ አታውቅም:: ሴተኛ አዳሪ ጋር ስንወጣ ሴተኛ አዳሪዎቹ ወንዱን ለማጥመድ እና ደንበኛቸው ለማድረግ ማንኛውንም የወሲብ አይነት ይፈፅማሉ! ወንዱን እስረኛቸው ለማድረግ ልቡ እስከሚጠፋ ያረኩታል ስለዚህ ይህን ያላገቡ ወጣቶች የትዳር ሕይወታቸው እንዳይበጠበጥ በማስተዋል መሄድ አለባቸው የሚል ሀሳብ አለኝ አመሰግናለሁ"

" ኤፍሬም ከ 4 ኪሎ ስለሰጠኸኝ ሀሳብ በጣም እመሰግናለሁ! አድማጮች አንድ ደዋይ መስመር ላይ አለች ሀሎ ማን ልበል?"

" ቤዛዊት"

" ከየት ነው ቤዛዊት?"

" ጀሞ"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

"እንዴ ስልክ መስራት ጀመረ እንዴ?" Net work የለም ብዙ ሰዎች ይላሉ ..."

" የመጨረሻ ፎቅ ላይ ወጥቼ ነው የምደውልልህ"

" እሺ. ሀሳብሽ ምንድ ነው?"

" የኔ ሕይወት የተበላሸው በወሲብ የተነሳ ነው"

" እንዴት?"

" አስራ አንደኛ ክፍል እያለሁ አንድ የጎረቤት ልጅ ነበር አብረን እናጠና ነበር ከዚያ ከመላመድ ፍቅር ውስጥ ገባን፤ አንድ ጊዜ እያጠናን ሳናስበው ወደ ወሲብ ውስጥ ዘለቅን፡ የወር አበባዬ ቀረ አደርግነው ድንግሌን ወሰደው ያቺ አጋጣሚ ግን ሕይወቴን ቀየረች:: ልጅ በልጅነት! ሕይወቴ ሁሉ ተበላሸ:: ለማስወጣት ሞከርኩ ከአቅም በላይ ነው ተባለ:: ልጅ በልጅነት! ሕይወቴ ሁሉ ተበላሸ:: በዚህ አጋጣሚ ለሴቶች ማስተላለፍ የምፈልገው ከምታፈቅሩት ሰው ጋር ባዶ ቤት ውስጥ አትቀመጡ የሚል እና በወሲብ ዙሪያ በግልፅነት ማውራት አለባቸው ቅድም የደወለው ደዋይ ልክ ነው ብዙ ሰዎች አውቃለሁ ከፍቅረኛቸው ጋር ላለ መለያየት እና በግልፅነት ወሲብ ለመጠየቅ ፈርተው ከሌላ ሰው ጋር ወሲብ የሚፈፅሙ አሉ ስለዚህ በወሲብ ዙሪያ በግልፅነት ተወያይተው ውሳኔ ላይ መድረስ አለባቸው ወሲብ ለማድረግ ከተስማሙ ደግሞ እጅግ ጥንቃቄ ቢያደርጉ የሚል ምክር ለመስጠት ነው! እንደኔ ሕይወታቸው እንዳይበላሽ"

" ቤዛዊት በጣም አመሰግናለሁ! FM66.6 ትን ነው እያዳመጣችሁ ያላችሁት እፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል የሚለውን ፕሮግራም ነው ... እያስተናገድኳችሁ ያለሁት ኀልያድ ነኝ እንድ ማስታወቂያ እና ሙዚቃ ሰምተን እንመለስ ... ጆኒ ራጋ ሽፍታው ልቡ ...


## ቤልጉቤት ኮንደም

ቤልጉቤት የወንዶች አስገራሚ ኮንዶም መጣልዎ! ምሁራን ተጨንቀው ተጠበው የሰሩት አስገራሚ ኮንዶም፡ ቤልጉቤት ኮንዶም ቁላዎን ለ40 ደቂቃ ገትሮ ያቆማል! በተለይ ወሲብ የሚያደርጉዋት ሴት የHIV በሽተኛ ከሆነች ቤልጉቤት ኮንዶም ገና ወደ ሴቱዋ ጭን ሲጠጋ ቀለሙን ይለውጣል! በተጨማሪ ቤልጉቤት ኮንዶም ምንም ጉዳት የለውም! ዋጋው 26 ብር ነው! ቤልጉቤት የዘመኑ ድንቅ ኮንዶም ሌላው ቢቀር ለግርማ ሞገሱ ሲሉ ብቻ ኮንዶሙን ገዝተው ይያዙ! ቤልጉቤት ይለማል ሀቢት!


t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

"አድማጮች ተመለሼ መጥቻለሁ! ከወሲብ ጋር በተያያዘ በርካታ ጥያቄዎች ይኖራቹኋል በተለይ ከወሲብ ጋር በተያያዘ የግል ችግር ካላችሁ በ777 ላይ SMS ላኩ ከባለሙያ ጋር አገናኛቹዋለሁ! ከወሲብ ጋር በተያያዘ ምርጥ የኢንግሊዝኛ መፅሐፎችን ማንበብ ከፈለጋችሁ Google ላይ Sex books ብላችሁ ብትጎለጉሉ ታገኛላችሁ በተለይ ከወሲብ ጋር የግል ማንኛውንም ጥያቄዎች ካሉዋችሁ www. How to have a sex.com (amazon.com) ላይ ብትገቡ ምርጥ ምርጥ መፅሐፍቶችን ታገኛላችሁ! ማስታወስ ያለበት አንድ ቁም ነገር ለማንኛውም የወሲብ ችግርዎ በግል ከሚጨነቁ ሳይፈሩ ባለሙያን ማማከር ይጠበቅበታል!! ለማንኛውም አንድ አድማጭ አየር ላይ እናውል ሀሎ ማን ልበል?"

"ከአውቶቢስ ተራ ገተኛ ነው ስሜ ይቅር"

"እሺ ስለወሲብ እያወራን ነው ያንተ ሀሳብ ምንድ ነው?"

"ከወሲብ ጋር ግንኙነት ያላቸውን አባባሎች ለመናገር ነው"

"ቀጥል እሺ"

"አመሠግናለሁ! ተበዳ ያለው እምስ ከጎንደር አዲስ አበባ ይመጣል ... እያንዳንዱ እምስ ጫፉ ላይ የሚገባበት ቂላ ተፅፏል... አንድ እምስን ያስከፋ ዘጠኝ እምስ ይሸሸዋል... ሴት ልጅን ራቁቷን በዓለም ላይ እምስና ቂላ ለአንድ ደቂቃ እንኳን ተለያይተው አያውቁም ... ሴት ልጅን ራቁቷን አይቶ ቁላው ያልቆመ ወንድ ስልብ ብቻ ነው...የአዋቂ ስራ አፐል ቁርስ ምሳ ጥብስ ራት እምስ ነው አይበቃህም?"

"ይበቃል! ስራህ ምንድ ነው?"

"ማጣበስ"

"ማለት?"

"የHigh school ተማሪዎችን ከባለሀብቶች ጋር እያገናኘሁ ኮሚሽን መቀበል! በተለይ ድንግል ከሆነች ጥሩ ዝግ ነው የምዘጋው በርካታ ደንበኞች አሉኝ"

"ይሄ ነገር ጥሩ ነው ትላለህ? ሴት ተማሪዎች ትምህርታቸውን በሚገባ እንዳይማሩ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

አንቅፋት አይፈጥርባቸውም?"

" እኔምን አደረኩ? ተስማምተው ለብራቸው ሲሉ እንጂ ማን አስገደዳቸው በዚያ ላይ ይዋል ይደር እንጂ አህያ የጅብ ናት እውነቱን እናውራ እስቲ የተማሩትስ ለመሆኑ ከዩኒቨርሲቲዎች ተመርቀው የካፍቴሪያ ወንበሮችን ከማሞቅ የዘለለ ለአገሪቱዋ ምን ፈየዱ?"

" ከርዕስ ጉዳዩ እንዳንወጣ እኔ ያልኩህ ከ18 ዓመት በታች ከሆነች ሴት ጋር ወሲብ ማድረግ እኮ ወንጀል ነው ያሳስራል ነው?"

" ወይ ጎልያድ! አንተ ሚስኪን ጋዜጠኛ ነህ! ቱልቱላ ነው ባከህ ዞር ብሎ የሚመለከት የለም ! በዚያ ላይ ደንበኞቼ ወሲብ የሚያደርጉት ቤታቸው ወስደው ነው! እንዴ አውቶቢስ ተራ መሸት ሲል እስቲ ና የ14 እና 15 ዓመት እድሜ ያላቸው ሴተኛ አዳሪዎች እኮ ሺ ይሆናሉ ምነው በከተማችን ውስጥ ባሉት ስንት ታዋቂ ሆቴሎች ውስጥ ያሉትን ትናንሽ ሴቶች መንግስት ለምን አላባረራቸውም ለአፍሪካ ስብሰባ እያሉ በየዓመቱ እየመጡ ስንት ህፃናትን እየበዱ አይደለም የሚሄዱት? እኔ ራሴ ብዙ ፈረንጅ ደንበኞች አሉኝ!.. ኧረ በናትህ ይደብራል ብዬ ነው እንጂ ብዙ ዘግናኝ ጉድ እነግርህ ነበር..."

" ስለሰጠሀኝ ሀሳብ አመሰግናለሁ"

" ይመችህ ቻው"

" እድማጮች የምታዳምጡት አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል የተሰኘውን ፕሮግራም ከ FM66.6 ጋር በመተባበር የሚቀርበውን ነው እናንተን እያስተናገድኩ ያለሁት ዝነኛው ጎልያድ ነኝ! አንድ የዝነኛውን የታደሰ አለሙን በጣም ጣፋጭ የሠርግ ሙዚቃ እንስማና የመጨረሻ ደዋይ በአየር ላይ እስገባለሁ! ተወዳጁ ታደሰ አለሙ ይቀጥላል ! ነብሱን ይማረውና ታደሰ አለሙ በሠርግ ዘፈኖች ላይ ቆመጥ የነበረ የጥበብ ሰው ነበር"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

...

ሙሽሪት ሙሽራው እንኳን ደስ ያላችሁ
የአብርሃም የሳራ ይሁን ጋብቻችሁ
ሁለቱም ተለዩ ከእናት ከአባታቸው
ትዳር መሠረቱ አንድ ሆነ ቤታቸው
እንዲህ ነው እንዲህ ነው ጋብቻ
ወረት ያልዳሰሰው ...
የአብርሃም የአብርሃም የሳራን
ፍቅርን ያወረሰው
ለሰው ልጅ ለትውልድ ለታሪክ ጋብቻ መሪ ነው
ትዳርን -ትዳርን መመስረት ለኑሮ ሕይወት ነው

"እ! እሪፍ የሠርግ ሙዚቃ እንደ ነበር ተስፋ አደርጋለሁ:: በወሲብ ዙሪያ ለበርካታ ዓመታት ጥናት ያደረጉት የዓለማችን ዝነኛ ደራሲ እና የሥነ ወሲብ አማካሪ ፈረንሳዊ ዥንቬን ሎሬንዞ የሚከተሉትን አስር ነጥቦች በወሲብ ዙሪያ ያስቀምጣሉ

- ለጤናማ ሕይወት የቀን ወሲብ ባያደርጉ ይመረጣል
- በወሲብ ደስተኛ ለመሆን ከበርካታ ሰዎች ጋር መማገጥ ሳይሆን አንድ የወሲብ አጋር ብቻ መምረጥ ጥበብ ነው
- በዕድሜ በጣም ከሚበልጡት አልያም ከሚያንሱት ሰው ጋር ወሲብ ባይፈፅሙ ይመረጣል
- ለወሲብ ተብለው የሚዘጋጁ አነቃቂ መጠጦች ሆኑ መድሐኒቶች ከጥቅማቸው ይልቅ ጉዳታቸው በጣሙን ያመዝናልና አይጠቀሙ
- ወሲብ ሙሉ ለሙሉ የአዕምሮ ስራ ነው ለወሲብ ጤናማ አመለካከት ከሌሎት ደካማ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

የወሲብ ሕይወት ይኖሮታል

- በወሲብ ጊዜ የፍቅረኛንም ስሜት እንጂ የራስዎን ስሜት ብቻ ለማርካት እንደራስ ወዳድ ሰው አይሁኑ
- ተማሪ ሆናችሁ ወሲብ ባትጀምሩ እጅግ ይመረጣል። በተለይ በ2006 ወሲብ ማድረግ ለተማሪዎች ጭንቀት እና ውጥረትን ስለሚቀንስ ሳያበዙ ይመከራሉ ተብሎ ይፋ የሆነው ጥናት እጅግ ሀሰት ነው
- ወሲብ የአንድ ቀን ችሎታ ሳይሆን እንደ ባህር ዛፍ ቀስ በቀስ የሚያድግ ነው
- ከወሲብ በኋላ ምንግዜም ሰውነቶዎን መታጠብ እና ተመጣጣኝ እረፍት ማድረግዎን አይርሱ
- ለማንኛውም የወሲብ ችግርዎ ተመጣጣኝ መፍትሔ ስላለው የወሲብ ችግርዎን ለባለሙያ ከማማከር በፍርሀት ወደ ኋላ እንዳይሉ ... የሚል ምክሮችን አስቀምጠዋል! ለማንኛውም አድማጮች የመጨረሻውን ደዋይ ሀሳብ እናድምጥ ሀሎ ማን ልበል?"

" ብዙአየሁ"

" ከየት ነው ብዙአየሁ?"

" ከሸሮ ሜዳ"

" ስለ ወሲብ እያወራን ነው ያንቺ ሀሳብ ምንድ ነው?"

" አሁን 34 ዓመቴ ነው። እስከ 25 ዓመቴ አባቴ በጣም ይቆጣጠረኝ ነበር ልክ 12:00 ሲሆን ቤት መግባት አለብኝ። 85 ኪሎ ነኝ። በጣም አስጠሊታ ባልሆንም አላምርም አሁን ግራ የገባኝ ወንድ ልጅ እንዴት እንምጠይቅ ነው! በተለይ ወሲብ ለማድረግ በጣም እፈልጋለሁ ፤ ግን እስካሁን ማንም የጠየቀኝ የለም! እኔም ስለምፈራ ጠይቄ አላውቅም አሁን እናቴም አባቴም ስለሞቱ ተቆጣጣሪ የለብኝም"

" እሺ ብዙአየሁ ለወሲብ ከሆነ ችግር የለም ዛሬ ማታ ካንቺ ጋር እድራለሁ! ራስሽን አዘጋጂና ጠብቂኝ"

" አ! አምላኬ ተመስገን!! በጣም ነው የማመሠግነው ሸሮ ሜዳ ዘነቡ ሆቴል 12:00

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ላይ እጠብቅሀለሁ"

" ውድ አድማጮች አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል የዛሬው ፕሮግራም እዚህ ላይ ተጠናቀቀ! በነገራችን ላይ ለማንኛውም የግል ወሲባዊ ችግሮቻችሁ መጨነቅ ሳይሆን ፈረንሳዊ ደራሲ እንዳረጋገጡት ተመጣጣኝ መፍትሔ ስላለው ከባለሙያ ጋር በግልፅነት ምንም ሳይፈሩ መነጋገር ይኖርቦታል:: ለማንኛውም በ0911 04 89 ** አልያም 777 ላይ SMS ብታደርጉልኝ ከባለሙያ ጋር አስተዋውቃቹሀለሁ እስካሁን ከእናንተ ጋር የነበርኩት ዝነኛው ጎልያድ ነኝ! ሠናይ ጊዜ!!"

t.me/OLDBOOKSPDF


Scanned by CamScanner

# ክፍል መ

# “ ኢትዮጵያዊ ማንነታችን ”

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner




## ክፍል - መ

የካቲት 23/2005

## FM66.6

## ኢትዮጵያዊ ማንነታችን

… ኢትዮጵያ የኛ መመኪያ

እናት ሀገር ኢትዮጵያ

የሰው ዘር ትስስር ልዕልና ሀብት መቁጠሪያ

የነፃነት ምኩራብ የታሪክ መስፈሪያ

የእግዜር ብሩክ ምድር ቅድስት ኢትዮጵያ

የጥቁር ህዝብ ሁብር የማዕዘን ድንጋይ

የተጋድሎ አፅም መርህ የደም ፈሳሽ ብቃይ

የምድር ፍቅር ብስራት የመስዋዕት ሜዳ

የባህል ቅርፅ ቋንቋ ሰገነት

ኢትዮጵያ ሀገሬ ነሽ ....

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

* * *

ዋ... ያቺ አደዋ

(ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህን)

ዋ ...!

ዓድዋ ሩቅዋ

የዓለት ምሰሶ አድማስ ጥግዋ

ሰማይ ጠቀስ ጭጋግ ዳስዋ

ዓድዋ...

ባንቺ ሀልውና

በትዝታሽ ብፅዕና

በመስዋዕት ክንድሽ ዜና

አበው ታደሙ እንደገና

ዋ!

የኩሩ ትውልድ ቅርስዋ

የኢትዮጵያዊነት ምስክርዋ

ዓድዋ...

" የተከበራችሁ አድማጮች በመጀመሪያ የጥሌን ተወዳጅ ሙዚቃ ጋበዝኩ በመቀጠል የሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህንን አድዋ የተሰኘ ዝነኛ ግጥም በመጠኑ ቀነጨብኩ። ዛሬ እንግዲህ የካቲት 23 ነው ! ይቺ ቀን ደግሞ ለኢትዮጵያ ብሎም ለአፍሪካ ታላቅ የማትረሳ ቀን ናት። ታላቁ የአድዋ ድል የተጠናቀቀው በዛሬዋ ቀን ነበር። ለዓድዋ ጦርነት በመነሻነት የሚጠቀሱት ሶስት ግዙፍ ምክኒያቶች ቢኖሩም አድማጮች ቁጥር አንድ የሆነውን ምክኒያት ብቻ እነግራቹዋለሁ። በቁጥር አንድ የተቀመጠው የአንቀጽ 17 ጉዳይ ነው። በነገራችን ላይ ታላቁ አበበ ቢቂላ 17 ቁጥር ያለው መለዮ ለብሶ በማራቶን ታላቅ ገድል ሠርቷል! ለማንኛውም ሚያዚያ 25 ቀን 1881 ዓ.ም ኢትዮጵያ እና ጣሊያን የውጫሌ ውልን

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ተቀምጡ ! በዚህ ውል ውስጥ በ3ተኛው አንቀጽ የተገለፀውን ኮንት አንቶኔሊ ጋር እንዲታደስ ስምምነት ላይ ከደረሱ በኋላ ጣሊያኖች የታደሰውን ውል አፍርሰው እስከ መረብ መሬና በለስ ደረሰ ዘልቀው ሰንደቅ ዓላማቸውን በመትከላቸው ሲሆን በሁለተኛ ደረጃም የውጫሌው ውል 17ተኛው ክፍል የተገለፀውን ለመለወጥ ስምምነት ላይ የደረሱ ቢሆንም ኢጣሊያኖች ተግባራዊ ባለማድረጋቸው እንዲሁም ለአፄ ምኒልክ የከፋ የሆነባቸው የኢጣሊያኑ ጀኔራል ጋንዶልፍ ወደ መረብ መጥቶ ከእርሳቸው ዕውቅና ውጪ ከራስ መንገሻ ጋር የወዳጅነት ውል መዋዋላቸው ነበር! የተከበራችሁ አድማጮች ይቺ ጣጠኛ አንቀፅ ምን ትል ነበር የሚለውን ልንገራችሁ "የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከኤሮፓ ነገስታት ለሚፈልጉት ጉዳይ ሁሉ በኢጣሊያ መንግስት አጋዥነት መላላክ ይቻላቸዋል" የሚል የነበረ ሲሆን የኢጣሊያንኛው ትርጓሜው ግን "የኢትዮጵያ መንግስት ከውጭ ሀገር መንግስት ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት በኢጣሊያ መንግስት አማካይነት ማድረግ ይገባዋል" የሚል ነበር በነገራችን ላይ ይህ የተዛባ ትርጉም የያዘ አንቀፅ ሊታወቅ የቻለው በታላቁ እዕመ ጊዮርጊስ በተባሉ ቋንቋ አዋቂ ነበር:: እንግዲህ አድማጮች ስለ አድዋ በሰፋት ለማወቅ ከፈለጋችሁ የዘነኛውን ታሪክ ፀሐፊ ተክለ ጻዲቅ መኩሪያን መጽሐፍት አንብቡ! እላቹኋለሁ:: እኔ ሳልነግራችሁ የማላልፈው ቢኖር ኢጣሊያኖች እጅግ በጣም የሚጠሉት እና ሲሰሙ ውስጣቸው በንዴት የሚቃጠለው ነገር "አድዋ" የምትለዋን ቃል ነው! የሚገርማችሁ ነገር ታላቁ የአደዋ ድል 80ኛው ዓመት ሲከበር ኢጣሊያ አለኝ ብላ የምትመካባቸውን ጀኔራሎች ሰብሰባ እጅግ ሚስጢራዊ ስብሰባ በኢጣሊያ ፍሎሬንስ ከተማ አድርጋ ነበር:: በሚስጢራዊው ስብሰባ የኢትዮጵያ መሪ ጓድ ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃ/ማርያም ተገኝቶ ነበር:: ኢጣሊያ የአደዋ ድል እየተባለ የሚጠራውን ቀን ኢትዮጵያ እንዳታከብር 1,000,000 የእንግሊዝ ገንዘብ ለፕሬዝዳንት መንግስቱ በማቅረብ ተደራደረች! ጓድ መንግስቱ የኢጣሊያን ሀሳብ ከተገነዘበ በኋላ እየሳቀ "እኔ ጓድ መንግስቱ ኃ/ማርያም የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት ነኝ! ኢትዮጵያ ሀገሬ ለኔ ሁለመናዬ ናት! ኢትዮጵያ ሀገሬ ለኔ እስትንፋሴ ናት! ኢትዮጵያ ሀገሬ የጀግኖች ምድር ናት! ስልጣን ላይ ከወጣሁ ገና ሰስት ዓመት ሆነኝ አንድ መሪ ለአንድ ሀገር ምን ማለት እንደሆነ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ተረድቻለሁ! የኔ አያቶች እና ቅድመ አያቶች ደማቸውን አፍስሰው አጥንታቸውን ከስክሰው በዱር በገደሉ! እየተዋደቁ ! በረሀብ! በጠኔ! በችጋር! እየተሰቃዩ እናት የአንድ ዓመት ጡት በወጉ ጠብታ ያልጨረሰችውን ልጇዋን ከሀገር በላይ ምንም የለም በማለት ጥላት ተዋግታ! ሞታ! አባቶች ቅሌን ማቄን ጨርቄን ሳይሉ ሌት ተቀን ተዋግተው በዘመናዊ መሳሪያ እጅግ የተራቀቀውን የኢጣሊያን ማለቴ የእናንተን ጦር ልክ ታላቁ ጎልያድ በትንሹ የዳዊት ጠጠር እንደወደቀ ሁሉ እነሱም የእናንተን ታላቅ ወደር የማይገኝለት ጦርን በወኔና በሞራል ኢትዮጵያ ትቅደም በለው ንፍጥ በንፍጥ አድርገውት አሸነፉት! ለዓለም ህዝብ ሁሉ ለጦርነት ትልቁ ወሳኝ ነገር ዘመናዊ መሳሪያ ሳይሆን ወኔ እና የሀገር ፍቅር መሆኑን አስመሰከሩ! በዓለም ላይ እንደውሻ ትራፊ ፍርፋሪ የሚሰጣቸው የነበሩት ጥቁሮች በአድዋ ድል የተነሳ አንገታቸው ቀና አለ! የኢትዮጵያ ልጆች ዘላለማዊ ታሪክ ፃፉ!! አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀዩን ባንዲራ እጅግ ከፍ አድርገው አውለበለቡት!"

" እርግጥ አደዋ ምን ያክል ታላቅ ድል እንደሆነ በሌላ በኩል በየዓመቱ የአደዋ ድል ሲከበር እናንተ ኢጣሊያኖች አንገታችሁ እንደሚደፋ! እንዴት አንዲት ደሀ እና ጥቁር ህዝብ ያላት ሀገር እኛን ታሸንፋለች ብላችሁ እንደምትሸማቀቁ ይገባኛል! ለዚህም ነው ይህን ብዙ ገንዘብ ለድርድር ያቀረባችሁልኝ ! ያስቃል! በጣም ያስቃል! በሀገሬ በኢትዮጵያ አንድ አባባል አለ " የማይመስል ነገር ለአናትህ አትንገራት" ይላሉ:: ፈጣሪያችሁን ማመስገን ያለባችሁ ይህ ስብሰባ እንኳን ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተከናወነ ስለመሆኑ ነው! ይህን መሰል የጅል ተረት ነበር:: እንኳን የአደዋን ድል እንዳይከበር ቀኑን ላደበዝዘው ቀርቶ እዚህ ዘርፋችሁ ያመጣችሁትን ታላቅ ሐውልታችንን ወዳችሁ በግዳችሁ በኔ ዘመን ባትመልሱ እንኳ ከኔ በኋላ የመስሉ ነገሥት ኢትዮጵያን ተመልከተው ሲወጡ ንጉሱ ራሳቸው መርከባቸው ድረስ በመሄድ ሚስቶቻውን በማስወለቅ አጥበው ይሰጧቸው ነበር:: ለምን ካላችሁ የእምዬ ኢትዮጵያን አፈር ስብሰባውን ረግጠው ወጡ ታዲያ በዓመቱ ፀ1ኛው የአደዋ ድል የካቲት 23 ሲከበር

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ከራሽያ በርካታ ሮኬቶችን ፤መድፎችን፡ እና መሳሪያዎችን በማስመጣት በታላቅ ድምቀት ተከበረ!!"

" ለማንኛውም ወጣቶች የሀገራችሁን ታሪክ እወቁ! አደዋ ማለት እጅግ በጣም መኩሪያችን ነውና ባግባቡ አክብሩት! በታሪካችን እንኩራ! በኢትዮጵያንታችን እንመካ! እያደመጣችሁ ያላችሁት አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል በ FM66.6 ነው:: እያስተናገድኳችሁ ያለሁት ዝነኛው ጎልያድ ነኝ:: የዛሬው መወያያ ርዕሳችን ኢትዮጵያዊ ማንነታችን የሚል ነው! በ0911 04 89 ** እንዲሁም በ 777 ላይ SMS ላኩልኝ የጥሌ ዜማ ይቀጥላል በዚህ አጋጣሚ ጨዋታን ጨዋታ ያነሳልና የዝነኛውን የቦብ ማርሌይን ኢትዮጵያ ወሰዳችሁ ቅበሩኝ ኑዛዜ ተግባራዊ ለማድረግ ለጓድ መንግስቱ ባንድ ወቅት ሀሳቡ ቀርቦለት ነበር የጓድ መንግስቱ ምላሽ የሚከተለው ነበር:: "ምናልባት እንዳላችሁት የቦብን መቃብር ለማየት በሚመጡ ጎብኚዎች ኢትዮጵያ ብዙ ብር ታገኝ ይሆናል፤ ነገር ግን ብሩ ጥንቅር ብሎ ይቅር እንጂ የማንም ሀሺሽ አጫሽ አገሬ ኢትዮጵያ ላይ የሚቀበርበት ምክኒያት የለም" በማለት ተናግረው ነበር:: ወደ ጥሌ ዜማ እናምራ::

...የጥቁር ዘር እርማ ሰንደቅሽን ያመነ
ህብረት ያደመቀው በእምነት የጀገነ
በቃል ሰንሰለት ቅድመት ዜጋሽ የገነነ
የአንድነት አክብሮት የአትንኩኝ ባይነት
የጽድቅ ቋሚ መዝገብ ምንጭ ነሽ አብነት
ኢትዮጵያ እናት ሀገር ኢትዮጵያ ነሽ እውነት
በነፃነት በአንድነት ፈርጅሽ
ጠላትሽም ይወድቃል ከእጅሽ...

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

**ሱመያ**

ሱመያ በአይነቱ የተለየ አሠሪና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ! ኤጀንሲያችን ኩዌት፣ ሳውዲ፣ ባህሬን፣ ቤሩት፣ ግብፅ፣ የመን በነፃ ይልኮታል! በዚያ ላይ ለስድስት ወራት አስቀድመን ስለ ቋንቋ እና የቤት አያያዝ እናስለጥኖታለን ለዚህ ግን 400 ብር ይከፍላሉ!! ታዲያ በሚሠሩበት ቤት ወይ ተደፍረው! ወይ ከፎቅ ላይ ተወርውረው ወይ እጅግ ስራ በዝቶቦት ተሰላችተው ራስዎን ገለው ቢገኙ ሱመያ የተከበረዎን ሬሳዎትን ወደ ሀገሮ በክብር በመመለስ በክብር ይቀብሮታል! በክብር ባይኖሩም በክብር እንቀብሮታለን::

" አድማጮች በስልክ መስመራችን ላይ በጣም የተከበሩት ፕሮፌሰር እንዳልካቸው ወ/ሰንበት ይገኛሉ:: ሀሎ ፕሮፌሰር እንዴት ኖት? ስለደወሉልኝ በጣም አመሰግናለሁ! የዛሬ ርዕሳችን ኢትዮጵያዊ ማንነታችን የሚል ርዕስ ነው ያነሳሁት የእርስዎ ሀሳብ ምንድ ነው?"

" አመሰግናለሁ ያነሳኸው ርዕስ ስለሚመለከተኝ ነው የደወልኩት በኢትዮጵያ ላይ በርካታ የታሪክ እና የፖለቲካ መፅሐፍትን ፅፌያለሁ:: ችግሩ ህዝቡ ጠጠር ያለ ነገር ማንበብ አይወድም! የማይረባ የወሲብ እና የሰፈር ወሬ የያዙ መፅሐፍትን በውድ ዋጋ ገዝቶ ያነባል:: ይህ በጣም የሚደንቀኝ ነው! ወደ ርዕሱ ልመለስ እና የሚገርምህ የኢትዮጵያ ህዝብን ላለፉት 40 ዓመታት ለማጥናት ሞክርኩ! የህዝቡን መንፈስ ለመታዘብ ጣርኩ! ከሊቅ እስከ ደቂቅ ለመመርመር ጣርኩ የሚገርምህ ግን ያገኘሁት ፍሬ ነገር የለም"

" ምን ማለት ነው ፕሮፌሰር"

" ባጭሩ ስለ ኢትዮጵያ ህዝብ ማለት የምችለው ሁለት ቁም ነገር ብቻ ነው:: የመጀመሪያው ያለ ምንም ጥያቄ ህዝቡ በቃላት የማይገለጽ የሀገር ፍቅር አለው:: ኢትዮጵያ እና ኬኒያ ሊዋጉ ነው ቢባል አሜሪካ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ሁሉ ለሚሠራበት መስሪያ ቤት

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

የፍቃድ ደብዳቤ ያስገባል:: ምንድ ነው ቢሉት አገሬ ኢትዮጵያ ጎረቤታችን ኬንያ በጣም ስለተሳፈጠቻት አንድ ሀምሳ ኬኒያዊያንን ገድዬ እመጣለሁ ብሎ በኩራት ይናገራል! ፍቃድ ራሱ ቢከለከል ከእናት ሀገር ወዲያ ብሎ ይመጣል:: ሁለተኛው የተገነዘብኩት ቁም ነገር የኢትዮጵያ ህዝብ ወሽካታ እና ፈጠኛ ህዝብ ነው ! ባጭሩ ይህን ይመስላል:: በነገራችን ላይ ስለ ጓድ መንግስቱ ያቀረብከው ታሪክ ከዚህ በፊት አልሰማሁትም! አላነበብኩትም ያቀረብከው እውነተኛ ታሪክ ከሆነ የመረጃ ምንጩን ማጣቀስ አለብህ!"

" ፕሮፌሰር ከመሰናበታችን በፊት አንድ ጥያቄ ላንሳ?"

" ቀጥል"

" የኢትዮጵያ ህዝብን ለ40 ዓመታት አጥንተውት ያገኙት የህዝቡ ማንነት ወሽካታ እና ፈጠኛ ነው ብለዋል! በዚህ ነገር መነሻ ምክኒያቱ ምን ይመስሎታል ፕሮፌሰር?"

" በጣም ምርጥ ጥያቄ ነው ለሚቀጥሉት ሀያ ዓመታት ደግሞ ምክኒያቱን ለማግኘት ጥናት አደርጋለሁ:: ያኔ ለህዝቡ ይፋ አደርጋለሁ! ለጥናቴ ያስቀመጥኩት መንደርደሪያ ሀሳብ ግን ተማሪ አስተማሪውን ከመሰለ ህዝቡም መሪውን ይመስላል:: ወይም በመሪው ይወጣል:: በዚህ መሰረት ምናልባት ሲላቸው 44 ዓመታት ሲሻቸው 21 ዓመታት በስልጣን ላይ የቆዩት መሪዎችን መነሻ አድርጌያለሁ:: ለማንኛውም ትክክለኛው ምላሽ የሚታወቀው ከሀያ ዓመት በኋላ ነው"

" አመሰግናለሁ ፕሮፌሰር ጥሩ ጊዜ እመኝሎታለሁ:: አድማጮች ኢትዮጵያዊ ማንነታችን ለዛሬ የተመረጠው የመወያያ ርዕስ ነው:: እናተን እያስተናገድኩ የምቆየው ዝነኛው ጎልያድ ነኝ! አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል FM66.6 ! ንዋይ ደበበ ይቀጥላል...

> ... የዜማ የቅኔ የቀሳውስት ሀገር
> የቅዱስ ገዳማት የታቦታት ደብር
> ፋሲለደስ አክሱም የታሪክ ምስክር
> መስቀል ፅላታችን የእምነታችን ሚስጢር
> ገዳማት መስኪዱ ሀውልታችን ሳይቀር
> ሀገሬ ሰው ኧረ እንዴት ነው
>
> ወፍ አረዋቱ ኧረ እንዴት ነው?...

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

" እድማጮች ሁለቱም ስልኮች እየተጨናነቁ ናቸው:: አንድ ደዋይ በአየር ላይ ላውል ሀሎ ማን ልበል?"

" አቶ ይጥና ተፈሪ"

" አቶ ይጥና የዛሬውን የአደዋን ድል ቀንን በማስመልከት ኢትዮጵያዊ ማንነታችን ላይ እየተወያየን ነው የእርሶዎ ሀሳብ ምን ይመስላል?"

" እመሠግናለሁ የአደዋ ድልን አፍሪካዊያን ራሳቸው እንደነፃነት ቀናቸው ሲያከብሩት በተገባ ነበር! አልተረዱትም! ለነገሩ እንርሱ ቀርቶ የዚህ ዘመን ትውልድ ራሱችላ እያለው ነው:: መሠልጠን ማወቅ በስልጣኔ መራቀቅ ማለት የራስን ማንነት ባህል፣ ወግ፣ ታሪክ፣ እየረሱ አልያም እየናቁ ሳይሆን ትልቁ የስልጣኔ መገለጫ የራስን ማንነት እና ታሪክ ማክበር ነው:: ወደ ጥያቄህ ልመለስና all most 64 ዓመት እየሆነኝ ነው በእነዚህ ዘመናት ዕድሜ ዩኒቨርሲቲ ስለሆነ ብዙ ነገር ለመታዘብ ችያለሁ:: በርካታ ድንቅ የሚባሉ መልካም ነገሮች አሉን፤ በጣም ትንሽ እሉታዊ ነገሮችም አሉን ታዲያ እነዚህ ትንሽ አሉታዊ ነገሮች ማንነታችን ላይ ትልቅ ውዝግብ ፈጠሩብን:: ስለዚህ የተወዛገበ ማንነት አለብን"

" እንደው አቶ ይጥና እነዚህን ነገሮች በቃል ማስቀመጥ ይቻል ይሆን?"

" በመጠኑ ይቻላል! ስሜታዊነት ፣ የሀገር ፍቅር፣ ውሸት፣ ባዶጉራ፣ ባዶ ተስፋ እነዚህ ማንነታችንን ይገልጻሉ:: እኛ ሀገር ፈረንጅ ሲመጣ አክብረን እንቀበለዋለን ለፈረንጅ የምንሰጠውን ክብር ለራሳችን የለም! ሴንትራል የተባለ ትልቅ ሆቴል ስገባ ከኔ በፊት ያለው እርሱ ፈረንጅ ነው ፈረንጅ እንደ ሀበሻ ተንከል የለውም! አንተ አሸባሪ ብትሆንስ እሉኝ! ማንነታችን ላይ ትልቅ ጠባሳ ያስቀመጠው ውሸት ነው:: ከትንሽ እስከ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ የሚል ህዝብ ያለው! እንዴ ኢትዮጵያ ውስጥ እኮ ነው እየተራበ ውይ አሁን ነው የበላሁት ለመታየት ይጥራል! መንግስት ከጠዋት እስከ ማታ ውሸት ይነዛል! መንገድ ተሰራ ፣ ባቡር ተዘረጋ ልማቶች በየቦታው እየተፋጠኑ ናቸው... ቅጥፈት... እንዴ! እውነተኛ ስልጣኔ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ማለት እኮ ሰማይ ጠቀስ ፎቅ መገንባት ፤ መንገድ መስራት፣ ባቡር መዘርጋት፣ ወዘተ አይደለም! የእውነተኛ ስልጣኔ መገለጫ ቁሳዊ ለውጥ ሳይሆን የሰው ልጅን ማክበር ነው! እስራኤሎችን ለምን እንደምወዳቸው ታውቃለህ? ለአንድ እስራኤላዊ ዜግነት ያለው ሰው ያላቸውን ክብር ተወው! በቅርቡ ያደረጉትን መቼም ጋዜጠኛ ስለሆንክ ሰምተሀል? አንድ እስራኤላዊ ፍልስጤም ውስጥ ታግዶባቸው እሱን ለማስለቀቅ 500 መቶ ፍልስጤማዊያንን በመፍታት ነው የተቀያየሩት! የእኛ መንግስት ቢያውቅ እኮ ኢትዮጵያ ያፈራቻቸው ልጆቹዋ በየአረብ ሀገሩ እየሄዱ ሲሞቱ ዝም አይልም ነበር! የህዝብ ቁጥር በየጊዜው እያደገ የኑሮ ውድነቱ እንዳይባባስ እንደቻይና ከሁለት ልጅ በላይ መውለድ አይቻልም የሚል ማዕቀብ ያስቀምጥ ነበር... ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ እኮ ነው የ800 ብር ደሞዝተኛ እግዜር የከፈተውን ጉሮሮ እግዜር ይዘጋዋል በሚል አስራ ሁለት ልጅ የሚፈለፍለው ... ሌላው የሚገርመኝ ማንነታችን አንድ ሀብታም ሰው እጅግ የተቸገረ ወንድም እያለው እሱን ከመርዳት ይልቅ ከሴተኛ አዳሪ ጋር ተዝናንቶ ማደርን ያስቀድማል:: ለመድሐኒት መግዣ ስጠኝ ወይም እርዳኝ ያልከው ሰው እንቢ ይልህና መጠጥ ጋብዘኝ ስትለው በደስታ እሺ ይልሀል! ለማንኛውም እንዳላበዛብህ እንጂ እኛ ኢትዮጵያዊያን የተወዛገበ ማንነት የተጠናወተን ህዝቦች ነን! በተለይ አጉል ሽንገላ እንወዳለን! ስለጥሩ ነገር የሚያወራውን እንጂ ድክመታችንን የሚነግረንን ሰው አንወድም! ለዚህ ነው እንግዲህ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ዓለም በስልጣኔ እየገሰገሰች እኛ አሁንም ድረስ በቋንቋ እና በብሔር ልዩነት ... በስልጣኔ ጥማት የተነሳ እርስ በርስ እየተባላን ያለነው ለማንኛውም አመሠግናለሁ"

"እኔም አመሰግናለሁ ጋሽ ይጥና!

አድማጮች እፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል FM66.6 ትን ነው እያዳመጣችሁት ያላችሁት! የዛሬው የውይይት ርዕስ ኢትዮጵያዊ ማንነታችን የሚል ነው:: የብርሃኑ ተዘራን ሙዚቃ እና ማስታወቂያ ሰምተን እንመለስ"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

.... አገሬን አገሬን አይልም ወይ ሰው
ከፉ ሲናገሩት ሆድ እየባሰው
ዝናሽ የገነነ ስምሽ ከዓለም ዙሪያ
ጎልቶ ከከፍታ...
የጥቁር ፈርጥነሽ..
የነፃነት መውጫ ...
የአፍሪካ ውሊታ ...
የእሳት ውስጥ አበባ ሁሉም ይመኙሻል

## ኑኒ ሺሻና ጫት ቤት

ጭንቀት እና ውጥረቶዎን እኛ ጋር መጥተው ያራግፉ! ያሻዎትን የጫት አይነት እኛ ጋር በትኩስ ያገኛሉ! የሺሻችንን ልዩ መዓዛ ተዓምር ነው ይላሉ! ኑኒ ሺሻና ጫት ቤት የኢትዮጵያን ሀዳሴ ለማፋጠን ሲባል እና ኢትዮጵያችንን ቀዳሚ ሀገር ለማድረግ በማሰብ የተከፈተ እጅግ ዘመናዊ ሺሻ እና ጫት ቤት ነው! ይምጡ ዘና ብለው ይመለሳሉ! የእኛ እርካታ ገንዘብ ሳይሆን የእናንተን ደስታ ማስቀደም ነው! ኑኒ ሺሻና ጫት ቤት ! ይገኛል እውነተኛ ሀሴት!!!

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

" አድማጮች ከማስታወቂያው ተመልሼ መጥቻለሁ:: በ0911 04 89 ** ላይ ደውሉ በ777 ላይ SMS ላኩ አሁንም መስመር ላይ ደዋይ አለ ሀሎ ማን ልበል?"

" ወ/ሮ ኪዳን ነጋሽ"

" ከየት ነው ወ/ሮ ኪዳን?"

" ከመካኒሳ"

" የእርስዎ ሀሳብ ምንድ ነው በተነሳው ርዕስ ዙሪያ ?"

" እኔ በኢትዮጵያዊነታቸው በጣም ከሚኮሩት ሰዎች አንደኛዋ ነኝ:: ብዙ ሀገራትን ተመልክቻለሁ! ሁሉም የራሳቸው ማንነት እና መገለጫ አላቸው:: በእርግጥ አስቀድመን ማንሳት ያለብን ማንነት ምንድ ነው?' ማንነት በምን ይገለፃል?" መስፈርቱንስ ያስቀመጠው ማን ነው?' ወዘተ የሚል ጥያቄ ነው:: ሀብታም ስለሆንክ ጥሩ ማንነት ደሀ ስለሆንክ የረከሰ ማንነት ይኖርሃል ማለት ሙሉ ለሙሉ አይቻልም! ማንነት ባንድ ጊዜ የሚመጣ ከስተትም አይደለም! ዘመን የሚፈልግ ነው! እኔን ከሁሉም በላይ በጣም የሚያበሳጨኝ እግዜር በርካታ ወንዞች! ለምመሬት! ተስማሚ የአየር ንብረት! በርካታ ህዝቦች ሰጥቶን በሌላ በኩል ደግሞ ምድረበዳ ላይ የሰፈሩት እስራኤላዊያን ሀገራቸውን በልምላሜ ሲፈጥሩ እኛ አግራችን ስር ምግብ አስቀምጠን አንስተን ለምን መብላት እንዳልቻልን ይደንቀኛል! ምነው በከፊል የእስራኤላዊያንን ማንነት ቢሰጠን እያልኩ እመኛለሁ ባጠቃላይ ማንነታችንን በቃል ሆነ በዐ/ ነገር ማስቀመጥ በጣም እቸገራለሁ:: ከምንም በላይ አብሮ የመብላት ፣ የእቁብ፣ የእድር፣ የሠርግ፣ የለቅሶ፣ የመረዳዳት ባህላችንን ግን እጅግ እወደዋለሁ! እነዚህ የማንነታችን መገለጫዎች ጭምር ናቸው"

" ወ/ሮ ኪዳን ስለሰጡኝ ሀሳብ አመሰግናለሁ:: አድማጮች FM66.6 ትን ነው እያዳመጣችሁት ያላችሁት የእናተን ሀሳብ በመቀበል እያስተናገድኳችሁ ያለሁት ጎልያድ ነኝ የቴዲ አፍሮን ጥቁር ሰው ሙዚቃ እናዳምጥና የመጨረሻ እስተያየት በአየር ላይ እውላለሁ በ0911 04 89 65 ደውሉ በ777 ላይ SMS ላኩ! አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል! FM66.6"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

... ወደ አድዋ ሲሄድ ሚኒሊክ ኑ ካለ

ኧረ አይቀረም በማሪያም ስለማለ

ታዲያ ልጅሽ ሲጠራ ምን አለ

ወይ! ወይ ሳልለው ብቀር ያኔ ...

እኔን አልሆንም ነበር...

" በማዳመጥ ላይ የምትገኙት አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል የተሰኘውን ፐሮግራም ነው! እስቲ የተወሰኑ ሀገራት ስለ እኛ ኢትዮጵያዊያን የተናገሩትን አባባሎች ላንብብላችሁ

- ኬኒያዊያን :- እንደ ኢትዮጵያ ሚስኪን ህዝብ የለም ዳቦ ላይ ተቀምጠው ዳቦ ዘወትር ሲለምኑ ይደንቀናል
- ሚሊ:- ኢትዮጵያኖች ድከመትህን ይነግሩሀል፤ ድከመታቸውን ስትነግራቸው ግን አይሰሙህም
- አሜሪካዊያን :- ኢትዮጵያዊያን ድንቅ ህዝቦች ናቸው፤ ድንቅ መሪ ግን እስካሁን ባለማግኘታቸው መከራቸው በዝቷል
- የመናዊያን:- እግዜር ለእኛ ትንሽ ምድር እና ጭንቅላት ሰጠን፤ ለኢትዮጵያዊያን ሰፊ መሬት ሰጥቶ እንቅልፋም አድርጎ ፈጠራቸው! ለማኝ ህዝቦች!
- ፈረንሳዮች:- የኢትዮጵያ መሪዎች ሀገራችን ሲመጡ ልመና የሚል ቃል ትዝ ይለናል
- ህንዶች:- ፍቅር እና አብሮ መብላትን ያወረሰናቸው እኛ ነን ግን አልተጠቀሙበትም::
- ጀርመናዊያን:- እንዴ! ታላቋን ኢጣሊያንን ያስፈሩ የጀግና ህዝብ መኖሪያ ናቸው
- ግብፃዊያን:- አባብ እና ኢትዮጵያዊ መን[illegible] ቀድመህ ኢትዮጵያዊውን ግደል!

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ኢ-ጣሊያኖች ፡- ምትን እግዚሐብሔር ባይፈጥረው ኖሮ የሚፈጥሩት ኢትዮጵያዊያን ይሆኑ ነበር... አድማጮች ሁሉንም ለመጨረስ ጊዜው ስለማይበቃ ወደ መጨረሻው ደዋይ እናምራና የዛሬውን ውይይት እንጨርስ ሀሎ ማን ልበል?"

"አለበል"

" አለበል ከየት ነው?"

" ከ A.A.U"

" እሺ. ያንተ ሀሳብስ ምንድ ነው?"

" አመሰግናለሁ! ስልክህን በማግኘቴ በጣም ተደስቻለሁ! አድናቂህ ነኝ! ያንተ ፕሮግራም አያመልጠኝም! በኢትዮጵያዊ ማንነቴ በጣም ደስተኛ ነኝ:: ይህ ማለት ግን በሁሉ ነገር እደሰታለሁ ማለት አይደለም:: በዓለም ላይ ስለ ሀገራቸው ትእምክተኛ ህዝቦች ኢንግሊዞች ናቸው:: እኛ ኢትዮጵያዊያን የሀገር ፍቅር ያለን በነፃነታችን በጣም ስለምንኮራ ነው! ለማንም ፈረንጅ አልተገዛንም! ያለመገዛታችን ለሀገራችን ልዩ ቦታ እንድንሰጥ አድርጎናል የሚያሳዝነው ግን አንድ ሰው ከውጪ በሚላከለት ዶላር ብቻ እየኖረ አገሬን እውዳለሁ ቢል፣ ወጣቱ 20 ሰዓት ከሺሻ እና ጫት ቤት ተቀምጦ እየመረቀነ ኢትዮጵያን እወዳለሁ ቢል፣ ኢህአዴግ ለኢትዮጵያ የማውቀው እኔ ብቻ ነኝ ሌላው ቀንደኛ የኢትዮጵያ ጠላት ነውና ስልጣኔን መቼም አለቅም ሳሸንፍም 99% ተመርጬ ... አገሪቱ ውስጥ ታዛቢዎች ተደናግጠው ምርጫው ምርጫ ነው? የልጆች የዕቃዕቃ ጨዋታ ነው?" ቢሉም እኔ ብቻ ነኝ የኢትዮጵያን እድገት የማመጣው ቢል ... ደራሲው ፣ ሙዚቀኛው፣ ጋዜጠኛው፣ መፅሔት አዘጋጁ፣ የፊልም ፕሮውዲሰሩ ተራ እና ፍሬ ፍስኪ ስራ ለህዝብ እያቀረበ በገንዘብ ብቻ ኪሱን ለመሙላት ለሀገር ፋይዳ የሌለው ስራ እያዘጋጀ ኢትዮጵያን እወዳለሁ ቢል... ለኔ በጣም ትልቅ ስላቅ ነው! እኛ ኢትዮጵያዊያን ያለብን ትልቁ ችግርም ይሄው የተወዛገበ ማንነት ነው! ከትንሽ እስከ ትልቁ የፕሮፈሰርን አገላለፅ ልዋስና ወሸካታዎች ነን:: በተለይ ኢህአዴግ ራሱ ግራ ተጋብቶ ህዝቡን ግራ ባያጋባው የተሻለ ነው! ለኢትዮጵያ ስልጣኔ የሚያስፈልጋት የሚሸነግላት ሳይሆን ከነ አወዛጋቢው ባህሪው እንደ አፄ ቴዎድሮስ ለስልጣን

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ሳይሆን በሀገር ፍቅር እና ለኢትዮጵያ ፣ስልጣኔ ልቡ የተከፈተ ተስፈኛ መሪ ነው! ለነገሩ ከመንጋቱ በፊት ሁሌ ይጨልማል! ሊበጠስ የሚፈልግ ነገር ይከራል! ከለውጥ በፊት ሁሌ ታላቅ ጨለማ! ታላቅ ውዝግብ ታላቅ ግጭት ይፈጠራል... 'ለዚህም ነው ምንም ጨለማው ቢረዝምም መንጋቱ ግን ጨርሶ አይቀርም' ያለው የነፃነት አባቱ ኔልሰን ማንዴላ! ማንነታችንን በጅምላ ሳይሆን ከግለሰብ አንፃር ነው ያወራሁት! ያው የግለሰቦች ጥርቅም ነው ህዝብ የሚሆነው:: ባጠቃላይ የሰማይ እና የምድር የሚያክል ግዙፍ ልዩነት ያለባት ኢትዮጵያን ማንነት እንዲህ በቀላሉ በዐ/ነገር ማስቀመጥ የሚቻል አይመስለኝም በዚህ አጋጣሚ..."

" አለበል ስላቋረጥኩህ በጣም ይቅርታ! አድማጮች ለዛሬ ያለን ሰዓት እዚህ ላይ ያበቃል! ነገ በሌላ ፕሮግራም እንገናኛለን በርዕሱ ላይ ከጓደኛዋ ጋር ይወያዩበት! ይከራከሩበት.. ኢትዮጵያዊ ማንነታችንን እንዴት እንደሚገልፁት በ0911 04 89 ** ላይ SMS ይላኩ! በጣም የተሻለ ገለፃ ለላከ አድማጭ የ25 ብር አልያም የ100 ብር ካርድ ይላክለታል! ለማንኛውም እናንተን በማስተናገድ የቆየሁት ዝነኛው ጎልያድ ነበርኩኝ በ0911 04 89 ** ላይ ለደወላችሁ! ሞክራችሁ ለተያዘባችሁ በ777 ላይ SMS የላካችሁልኝ ውድ አድማጮቼን በሙሉ እጅግ አመሠግናለሁ ሠናይ ጊዜ!"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

# ክፍል ሠ

## “ ታምናላችሁ ?”

ምርቃት

ኦሪት ዘፀአት

32፡15÷35

ይመልከቱ...

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

# ክፍል ሠ

## የካቲት 24/2005

## FM 66.6 ዋና ቢሮ

"ታምናላችሁ?"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

• የየካቲት 24 አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል ፕሮግራም ጀመረ:: የተከበራችሁ አድማጮች የዛሬው የመወያያ ርዕሳችን ታምናላችሁ በሚል ርዕስ ቡዳ፣ ጥንቆልና ፣ ቡቄ፣ አቢያ፣ ዊች፣ ጁጁ፣ ሙጠምጢም ፣ ሟርት፣ እርግማን፣ ድግምት፣ ደብተራ ፣ መስተፋቅር፣ ቃልቻ፣ ውቃቤ፣ መተተኛ ፣ መፅሐፍ ገላጭ፣ ኮከብቆጣሪ፣ አስማት፣ አውሊያ፣ ዛር ... የሚባሉትን ነገሮች ታምናላችሁ ?" በሚል ሀሳብ እንለዋወጣለን በ0911 04 89 ** ላይ ደውሉ ጥያቄ ካላችሁም 777 ላይ SMS ላኩ፤ የዘማሪት ዘርፌ ከበደን መዝሙር እናደምጥና ከመጀመሪያው ሀሳብ ሰጪ ጋር እንመለሳለን ... ፕሮግራሙን እየመራሁ ያለሁት ዝነኛው ጎሊያድ ነኝ! ዘና በሉ!"

.... ምህረት የሚገባት ካላችሁማ

እኔ ነኝ ሰዎች ፋሀማ ...

ያልተማረች ሲሉኝ ሰምቻለሁ

ስድብና ንቀትን ጠግቤአለሁ

አዎን ይገባኛል ብዙ ነገር

ግን ሁሉን የሱ ፍቅር

በነበረ የቀረ ታሪክ አለኝ

አሁን ግን ይመስገን የጌታ ነኝ

ምህረት የተገባት ተብያለሁ

አልዘፍንም ለከብሩ እዘምራለሁ....

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

## ዛዳዲዮስ ትምሮ

በአፍሪካ ምድር የመጀመሪያ የሆነው ት/ቤታችን ስለ አሠራሩ፣ ስለወሲብ፣ ስለሰው አገዳደል ፤ ስለሙስና አሰራር፣ ስለግትርነት የስድስት ወራት የተለየ ስልጠና ይሠጣል! ያስታውሱ ስልጠናው በቃልብቻ ሳይሆን በተግባር ጭምር የተደገፈ ነው:: ዛዳዲዮስ ት/ቤት ከዚህ በፊት ብቃት ያላቸውን አውቅ የኢትዮጵያ ሙሰኞች፣ ሌቦች፣ አጭበርባሪዎች ፤ ምባይል ዘራፊዎች ያስመረቅን እኛ ነን!! መማር ዛዲዮስ ሕይወት ለማደስ !!!


" ከሙዚቃውና ከማስታወቂያው ተመልሰናል የመጀመሪያው አድማጭ በስልክ መስመር ላይ ይገኛል ሀሎ ማን ልበል?"

" ቢ.መ ነኝ"

" ከየት ነው?"

" ከቂርቆስ"

"እሺ ቢ.መ በተነሳው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ያንተ ሀሳብ ምንድ ነው?"

" በእርግጥ ብዙሰዎች ሲያወሩ እሰማለሁ ፤ እነዚህ ነገሮች ሊኖሩም ይችላሉ ለኔ ግን ትርጉም የላቸውም! አላምንበትም! እንደ ተረት ነው የምቆጥራቸው:: በእርግጥ በመፅሐፍ ቅዱስ ራሱ እነዚህ ነገሮች እንዳሉ በብሉኪዳን ሆነ በሀዲስ ኪዳን ይጠቀሳሉ! በተለይ እዮብ የተባለው በእግዜር እና በሴይጣን ውዝግብ ብዙ ተፈትኗል... ሴይጣን በእባብ ተመስሎ ክርስቶስን ራሱ ስገድልኝ ምድር የኔ ነች እሰጥሀለሁ ብሎታል! ቁም ነገሩ ግን እነዚህ ነገሮች ኖሩ አልኖሩ ሁሉ ነገር የእምነት ጉዳይ ስለሆነ እኔ ስለማላምንባቸው ኖሩ አልኖሩ በኔ ሕይወት ላይ ለውጥ የላቸውም! በእነዚህ ነገሮች በተለይ በጥንቆልና የሚያምኑ ሰዎች ራሱ ካሉ ለኔ ግራ የገባቸው እና ልባቸው የተደፈነባቸው ናቸው! አመሠግናለሁ"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

"እኔም አመሠግናለሁ ሁለተኛ ደዋይ መስመር ላይ ይገኛል ሀሎ ማን ልበል?"

• ቄስ ደጉዓለም ባንተ እባላለሁ"

• ቄስ ደጉዓለም ስለደወሉልኝ በጣም አመሠግናለሁ:: የእርስዎ ሀሳብስ በተነሳው ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ ምንድ ነው?"

• በመጀመሪያ ችሩ አምላካችን እውቀው ይሁን ሳያውቁት በእንደዚህ መሰል አምላክ የሚገረሩትው ነገሮች ውስጥ ለሚያልፈው ለዓለማዊ ሕይወት ሲሉ እጃቸውን ያጨማለቁትን መሀሪ እና ቸር የሆነው አምላካችን ማስተዋል ይስጣቸው! ልባቸውን ክፍት ያድርግላቸው… እንግዲህ አንተ ባነሳሀቸው ነገሮች ዙሪያ ለበርካታ ዓመታት ጥናት ሳደርግ እና መረጃ ሳሰባስብ ነበር! እነዚህ ነገሮች ራሳቸው የሴይጣን ከፍተኛ እሰራር ያለባቸው ነገሮች ናቸው:: ምድር የሰይጣን ናት ሴይጣን ደግሞ መልኩን እየቀያየረ ከሚገለፅባቸው ነገሮች መሀከል የተነሱት ነገሮች ናቸው:: እነዚህን ነገሮች ልናወግዛቸው ይገባል:: ለህዝቡ አስረግጬ የምናገረው ፊታችሁን ወደ አምላካችሁ መልሱ ዓለም ላይ ያለው ነገር ሁሉ ከንቱ ነው! ሁሉ ነገር ያልፋል! የእግዜር መንግስት ግን አታልፍም ስለዚህ ሰው ስጋውን ቢያተርፍ እና ነፍሱን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል? ስለዚህ ሰዎች ለሚፈልጉት ነገር ሁሉ ምላሹ ፈጣሪያቸው ጋር ስለሆነ ፊታቸውን እና ልባቸውን ወደ አምላክ ይመልሱ እላለሁ! እግዚአብሔር ኢትዮጵያን እና ህዝቦቿዋን ይባርክ"

• አመሰግናለሁ ቄስ ደጉዓለም እድማጮች አሁን ደግሞ የዘማሪት ቤተልሔም ተዘራን መዝሙር እንሰማና ውይይታችንን እንቀጥላለን"

> ቤትህን ሲሰራ የተመረጠው
> የተወደደ ጥበብ የሞላው
> ክብር ሲሆንለት ዝና ሲተርፈው
> ያባቶቼን አምላክ እንደማያውቀው
> ጣኦት አምልኮ ሞት ሆነ ፍፃሜው
> እድሜዬ ይለቅልኝ ቤትህ
> ህይወቱ ይመርልኝ ፊትህ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

"እያዳመጣችሁት ያላችሁት አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል የተሰኘውን ተወዳጅ የሬዲዮ ፕሮግራም በFM66.6 ላይ ነው! በ 0911 04 89 ** ደወልደወል አድርጉ ጥያቄም ካላችሁ በ777 ላይ SMS አድርጉ! አንድ አድማጭ መስመር ላይ አለ ሀሎ ማን ልበል?"

" ታምራት ሸዋንግዛው"

" ከየት ነው ታምራት?"

" ከአዲስ አበባ 79 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ከምትገኝ ከተማ "

" እሺ በተነሳው ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ ያንተ ሀሳብ ምንድ ነው?"

" እኔ ራሴ አዋቂ ነኝ"

" እ! ስለደወልክልኝ አመሠግናለሁ እስቲ ስለ ስራህ ንገረኝ?"

" አባቴ ከአባቱ ወረሰ እሱ ሲሞት እውቀቱን ለእኔ አወረሰኝ:: በዘራችን እየተላለፈ የመጣ ጥበብ ነው:: በነገራችን ላይ አባቴ ያወረሰኝ ጥበብ ላይ ተጨማሪ እውቀት ለመገብየት በእነዚህ ጥበባት በጣም ወደ ሚታወቁት ናይጀሪያ፣ ሱዳን፣ ህንድ፣ ቬትናም አምርቼ ጥበብ ጨምሬ መጥቻለሁ! በዚህ አጋጣሚ በበርካታ ሀገራት ለምሳሌ ያህል ደቡብ አፍሪካ፣ ናይጀሪያ ፣ ሱዳን፣ ማሊ ፣ ህንድ... በነፃነት በትልቅ ማስታወቂያ መለጠፍ ይቻላል በጋዜጦች ላይም ማስተዋወቅ ይቻላል ባጠቃላይ አሁን 256 የጥበብ አይነቶችን ተግባራዊ ማድረግ እችላለሁ"

" ታምራት ላቋርጥህና አንተ ጥበብ እያልክ የምትጠራውን ሰዎች ጥንቆልና ወዘተ የሚል ስያሜ ነው የሚሰጡት አንተ የምታስበው እንደ ጥበብ ነው? እንደ የሴይጣን መገለጫዎች?"

" ጥሩ ጥያቄ ነው! ጥበብ ነው ጥበቡን.ለተመረጡ ሰዎች የሚሰጠን አባታችን ሴይጣን ነው:: በሌላ ቋንቋ የሴይጣን አምልኮት ተከታይ ነኝ ማለት ነው"

" ስለ አሰራሩ አውጋኝ እስቲ"

" በጣም በርካታ ሰዎች እኔ ጋር ይመጣሉ! ዝነኛ ሙዚቀኞች፣ ዝነኛ አትሌቶች፣ ዝነኛ ደራሲዎች፣ ዝነኛ ባለስልጣናት ፣ ዝነኛ ነጋዴዎች ... ግለሰቦችም ይመጣሉ:: ያው

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

እንዳልኩህ 256 ጥበቦች ናቸው ያሉት ሁሉንም ለማስረዳት ጊዜ አይበቃንም ባጠቃላይ አ ገዝብ ነክ፣ ስልጣን ነክ፣ ፍቅር ነክ ፣ ወሲብ ነክ፣ ንግድ ነክ ፣ ትምህርት ነክ፣ ስራ ነክ እያልኩ በመከፈል እስተናግዳቸዋለሁ:: ለምሳሌ አንድ ነጋዴ መጥቶ ብዙ ብር እንዳገኝ ወይም ብዙ ደንበኛ እንዲኖረኝ አድርግ ይለኛል! አደርግለታለሁ:: ደራሲው የኔ መፅሐፍ ብቻ እንዲሸጥልኝ አድርግልኝ... ተማሪው ት/ት እንዲገባኝ አድርግልኝ... ባለስልጣኑ ስልጣኔን አራዝምልኝ.. እያሉ ይመጣሉ:: ይሠራላቸዋል:: ብቻ ማንም እኔ ጋር መጥቶ አይመለስም

• እስቸጋሪ ካልሆነ በምሳሌ ልታስረዳኝ ትችላለህ ታምራት?

• ችግር የለውም! ለምሳሌ ብዙ የሴተኛ አዳሪ ወይም ሽርሙጣዎች የሆኑ ደንበኞች አሉኝ:: ሁለት ጥበብ እሰጣቸዋለሁ የሚጨሱ የተለየ ዕጣን ወይም ሽቶ ይህ ማለት እጣኑን ሲያጨሱት ብዙ ደንበኛ ያመጣላቸዋል! ሽቶውን ተቀብተውት ያሸተተው ማንኛውም ወንድ ይከተላቸዋል ... ለተማሪዎች ት/ት ሳያጠኑ ፈተናውን እንዲያልፉ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ራሱ ገብተው ተመርቀው እንዲወጡ ማድረግ እችላለሁ:: በየወሩ የሚበሉት የተቀመመ ቅጠል ይሰጣቸዋል! አዲስ ቡና ቤት ... ምግብ ቤት ... ተማሪ ቤት ... ሥጋ ቤት ... ባጠቃላይ ንግድ ነክ የከፈቱ ሰዎች ገቢያቸው በወረፋ እንዲሆንላቸው አህያ ወይም ጥቁር ድመት ከነሕይወቱ ቤታቸው መግቢያ /ድርጅታቸው መግቢያ በር ሥር ስድስት ሜትር ቆፍረው እንዲቀብሩ አደርጋቸዋለሁ! ገበያው ይደራል! ሰዎችን ማፍዘዝ የሚፈልጉ ካሉም አንድ ሰውን ለ8 ሰዓት ያህል እንዲያፈዙት የሚያደርግ ጥበብ አለኝ::"

"በብዛት ለሌቦች የሚሠራ ነው፣ ሥጋ ቤት የሚሸጥ ከሆነ ቢላዋ ላይ ... ለትዳር ከሆነ ቀለበት ላይ.. ለግርማ ሞገስ ጥርስ ላይ ... እንዲፈራ ዓይኑ ላይ ብቻ እንዳልኩህ 256 ጥበቦችን እሰራለሁ! በብዛት መስተፋቅር ለማሠራት ይመጣሉ"

• አፍቅሮ የተቸገረ... ያፈቀራትን ለማግኘት ... ያፈቀረችውን ለማግኘት... ያፈቀራት ሴት ከድታው እንድታብድ .. ወዘተ ቀላል ምሳሌ ለመስጠት ለምሳሌ አንተ አንዲት ሴት አፍቅረህ ያንተ ማድረግ የምትፈልጋት ከሆነ ቁጭ የሚባል መፋቂያ ላይ እሠራልሀለሁ ወይም ልጅቷ የምትይዘው ሞባይል ላይ ... የፈለከው ነገር ላይ ይሠራልሀል.. ቤትህ ድረስ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ትመጣለች:: ከአርባ በላይ የዩኒቨርሲቲ ኃበዝ ተማሪዎችን አሳብዳቸው ተብዬ አሳብጃለሁ! ጓደኛዬ ወንድ እንዳይቀርባት፣ የጓደኛዬን ፍቅረኛ አሳብደው ብለውኝ ሴቶች ይመጣሉ:: አደርገዋለሁ:: 75% የኔ ደንበኛ ሴቶች ናቸው:: እስከ ሁለት ዓመት ባንተ ፍቅር እንድትታወር ማድረግ ይቻላል:: በተለይ ግድያ ነክ እና ሰው እንዲያብድ ማድረግ በጣም ተራ ጥበቦች ናቸው:: ሁሉንም አውርቼ አልጨርስም"

" ወደ አንተ ጋር ሲመጡ የሚያሟሉት ነገር ምንድ ነው?"

" ጥሩ ጥያቄ ነው! እኔም ሆንኩ ጥበቡን የሰጠኝ አባቴ ሴይጣን በሁለት ነገሮች እንደሰታለን! በመጀመሪያ ደንበኞችንን ማስደሰት እና የልቡን መሻት 100% መፈፀም ነው:: ከዚያ ከአምስት ዓመት በኋላ የሰጠነውን ደስታ መልሰን እንቀበላለን በኛ አሰራር ለአንድ ደንበኛችን የምንሰጠው ደስታ ለ5 ዓመት ብቻ ነው፤ ወደ እኔ ዘንድ ሲመጡ ስድስት ነገር መፈጸም ይጠበቅባቸዋል"

1. መጽሐፍ ቅዱስ ማቃጠል
2. የUSA አንድ ዶላር ከኪስ ውስጥ አለመለየት
3. ከሚያገኙት ነገር ፋብን ለኔ ለመስጠት ቃል ኪዳን መግባት
4. 666 ጊዜ መስገድ (በየወሩ ለአንድ ጊዜ)
5. እኔ ከማዛቸው ውጪ ሌላ ነገር ላለማከናወን ቃል ኪዳን መግባት
6. ተዘጋጅቶ የተቀመጠውን ደም መጠጣት ይህን ይመስላል"

" ለ5 ዓመት ብቻ ነው ስትለኝ"

" እኛ ጋር የማይጣስ ትልቅ ህግ አለን ያም የዘራኸውን ታጭዳለህ የሚል እና ደስታን መንጠቅ የሚሉ ናቸው:: አንድ ሰው የፈለገውን ነገር መጥቶ ሲጠይቀን እናሳካለታለን! ከአምስት ዓመት በኋላ ምናልባት ግን በሱ የተነሳ ብዙ ደንበኛ ካመጣ እስር ዓመት ይሆንለታል! የሰጠነውን ነገር በእርግጥ እንነሳውም ግን ሰላሙን እናሳጣዋለን! ያለመረጋጋት! ንጭንጭ! ግራ መጋባት! ተስፋቢስነት፣ ባዶነት እንሞላበታለን በተለይ በጣም የሚወደው ነገር ምን እንደሆን እናጠናና እሱን እንነጥቀዋለን በጣም የሚወዳት ልጅ ካለችው ገለሀት አንገጣ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

እንለየለን ወይም የሲቃይ ናዳ እናዘንብበታለን... ጤናውን እንነሳዋለን – የበሽታ መንፈስ እንለቅበታለን .. ሁሉ ነገር እንሰጠውና እርካታውን ግን እንወስድበታለን ሚስቱን በጣም የሚያፈቅራት ከሆነ እንገልበታለን! ባጭሩ ከንቱ እናደርገዋለን ለምሳሌ አንዲት ወጣት መጥታ አንድ ሰው ላይ መስተፋቅር ብታሠራ ከአምስት ዓመት በኋላ መልሰን እሷን እናስቃያታለን ሰው አሳብድልኝ የሚል ካለም ከአምስት ዓመት በኋላ ራሱ ያብዳል ወይም ልጅ ካለው እብድ ሆኖ እንዲወለድ እናደርገዋለን አብዛኛው የኛ ጥበብ ተጠቃሚዎች ዘወትር ደስታ ያሳቸው መሳይ ደስታቢሶች አድርገን እንፈጥራቸዋለን"

" ይህን ነገር ግን ደንበኞችህ ያውቃሉ ማለቴ አስቀድመህ ትነግራቸዋለህ?"

" መንገሩ አስፈላጊ አይደለም"

" የመጨረሻ ሶስት ጥያቄዎችን ላንሳልህ የመጀመሪያው እናንተ ጠንቋዮች ስትሞቱ ከሰውነታችሁ ውስጥ ትላትል ይወጣል፣ አባብ ይወጣል... ወዘተ ይባላል! እውነት ነው? ሁለተኛው አንተ የምትሰራው ጥንቆልና እንበለው ድግምት ሁሌ ይሠራል? የመጨረሻው የአሜሪካ ገንዘቡ ለምን አስፈለገ?"

" አሪፍ ጥያቄ ነው የጠየከው ጎልያድ! የምነግርህ አንድ ትልቅ እውነት አለ እሱም የኛ ጥበብ ሙሉ ለሙሉ የሚሠራው መሀከል ቤት ለሆነ ሰው ብቻ ነው፤ ይህ ምን ማለት ነው? ሶስት አይነት አማኞች አሉ

ሀ. 100% እግዚሐብሔርን የሚያምኑ

ለ. 100% እግዜርን የማያምኑ

ሐ. 50/50 % መሀከል ቤት ግራ ተጋብተው ያሉ! በዚህ መሠረት የኛ ጥበብ 100% "ለ" እና "ሐ" ላይ ያለ ጥያቄ ይሠራል! ቀላል ምሳሌ ለመስጠት በቅርቡ አንድ ሰው ግደልልኝ ብሎ ነግሮኝ የሞከርኩት ጥበብ ሁሉ አልሠራም! ምክኒያቱም ሰውየው"ሀ" ነበር፡፡ በሌላ በኩል ለምሳሌ አንተ እምነትህ "ሀ" ከሆነ አንዲት ሴተኛ አዳሪ አንተን ሽቶ ብትቀባ፣ ሽቶውን ተቀብታ ብታሽተው ወይም ሙሉ ሽቶውን ሁሉ ብትነሰንስብህ ለውጥ አያመጣም! ባጭሩ ሁሉ ነገር የማመን እና ያለማመን ጉዳይ ነው የሁለተኛው ጥያቄ መልስ ለኛ የጥበብ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

አባታችን ሴይጣን - ሉሲፈር ዋና መቀመጫ አሜሪካ ናት:: በእርግጥ የአሜሪካ ገንዘብ ላይ "we trust in God" የሚል ፅሁፍ አለ:: ይህ የኛ መግባቢያ code አልያም pass-word ልትለው ትችላለህ:: WE TRUST IN GOD የሚለው ትክክለኛ ፍቺ እኛ በእግዚሐብሔር እናምናለን ሳይሆን "GOD" የሚለው ቃል ሲተነተን

G= Gas

O = Oil

D = Devil . የሚል ፍቺ ይሠጣል:: ይህ ባይሆን አሜሪካ ገንዘቡዋ ላይ WE TRUST IN GOD እያለች ወንድ ለወንድ ጋብቻ፣ ሴት ለሴት ጋብቻ፣ ቁማር፣ ሴሰኝነት፣ ለእያንዳንዱ ግለሰብ መሳሪያ እንደ እስከርቢቶ መሸጥ ... የመሰሉትን ነገር አታከናውንም ነበር:: ህዝቡን አስሮ ለመያዝ God የሚለው ቃል መጠቀም ስላለባቸው ነው:: በዚያ ላይ አንድ ዶላሩ ላይ ከኔ እንዳያፈነግጡ አደግምበታለሁ ይህን ይመስላል"

" እንዱን ጥያቄ አልመለሰከልኝም ለማንኛውም ፤ በጣም ነው የማመሰግነው አቶ ታምራት ሸዋንግዛው ... አድማጮች በመዘመር ደግሞ ፈታ እንበል"

... ያላንተ ለኔ ማን ሊሆነኝ

ጌታ ሆይ ፍቅርህ ልቤን ነካኝ

ህግህ ነበር ያፈ መፍቻ

የማትቀየር አንተ ብቻ

ፀፀተኝ ዛሬ ያኛው ወራት

አንተን ሳላውቅ የኖርኩበት

ፍቅር ነህ ለካ ማር ወለላ

ምን ህይወት አለ ካንተ ሌላ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

"ለድማጮች እያዳመጣችሁት ያላችሁት አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል የተሰኘውን በየቀኑ የሚቀርብ ፕሮግራም ከFM66.6 ጋር በመተባበር የሚቀርበውን ነው እናንተን እያስተናገድኩኝ ያለሁት ዝነኛው ጎልያድ ነኝ! ቀደም ብለን የሰማነው መዝሙር የዘማሪት ምርትነሽ ጥላሁን ነበር... ማስታወቂያ እንሰማና አድማጭ አየር ላይ እናውላለን"

**ወለላ ጠጅ ቤት**

ወለላ ጠጅ ቤት እንደማንም ተራ ጠጅ ቤት ትላንት የተመሠረተ አይደለም! ወለላ ጠጅ ቤት 1889 የተከፈተ ታሪካዊ ጠጅ ቤት ነው ጠጃችንን እንኳን ጠጥተውት በሽታው ገና ይሰከራሉ! ጠጅ ቤታችንን ለየት የሚያደርገው ጠጥተው ከሰከሩ አልያም በምቅታ መቧቀስ ከፈለጉ 250 ካሬ.ሜ ግላጭ ሜዳ ከበርካታ ድንጋዮች ጋር አሰናድተናል ይምጡ!! ይጠጡ!! ይደባደቡ! የአንድ ብርሌ ዋጋ 18 ሽልንግ ብቻ ነው! የፍየል ጥብስም አለን!

" ሀሎ ማን ልበል"

" ካሰች"

" ካሰች ከየት ነው?"

" ከየሺ ደበሌ ሠፈር"

"እሺ ባነሳነው ሀሳብ ላይ የምትይው ምንድ ነው?"

" እይ ሀሳብ ለመስጠት ሳይሆን አሁን ከኔ በፊት የደወሉትን አዋቂ ስልክ ፈልጌ ነው"

" የጠንቋዩን ነው?"

" አዎ"

"ለምን?"

" እንዲረዱኝ"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

" ሲያወራ ግን በደንብ ሰምተሻል አይደለም ለ5 ዓመት ቢበዛ ለ10 ዓመት እንጂ ከዚያ በኋላ የሰቃይ ሕይወት ነው የማሳልፋቸው ነው ያለው"

" ሰምቻለሁ፡፡ እኔ አርባ ዓመት በስቃይ ከምኖር 5 ዓመት ዘናብዬ ኖሬ ብሞት እመርጣለሁ እናም ስልኩን ብትሠጠኝ ደስ ይለኛል፡፡

" ካሰች"

" አቤት"

" ጠንቋዩ ምን እንዲያደርግልሽ ነው የምትፈልጊው?"

" እናቴን እንዲገልልኝ"

" እናቴን? ለምን?"

" ነገሩ ምን መሰለህ..."

" ሀሎ ካሰች ... ሀሎ ካሰች ... ሀሎ አድማጮች የካሰች ስልክ ተቋርጧል፡፡ ካሰች መልሳ ከደወለች ሀሳቡዋን እንሰማለን! የተናገረችው ነገር ለኔ በጣም አስደንጋጭ ነው እናትን የመሠለችን ልዩ ፍጡርን ለማስገደል በጣም ይከብዳል! ለማንኛውም ሌላ አድማጭ መስመር ላይ ይገኛል ሀሎ ማን ልበል?"

" አቶ ደረሰ ኪ."

" ከየት ነው አቶ ደረሰ"

" ነዋሪነቴ ነቀምቴ ነው ሹፌር ነኝ፡፡ አንተ ባነሳሀቸው ነገሮች ላይ ሀሳቤን ለመስጠት ነው፡፡ ልቀጥል ጎልያድ?"

" ይቀጥሉ"

"አንድ ጊዜ ከአዲስ አበባ ደብረ ዘይት ስጓዝ ከምሽቱ 3፡44 ላይ መንገድ ላይ አንዲት የተዋበች ሴት አየሁ፡፡ ሸኝኝ ስትለኝ በእሺታ አስገባዋት፡፡ በጣም ነው የምታምረው፡፡ የተቀባችው ሽቶ መዓዛው ያስደንቃል! በጣም አጭር ቀሚስ አድርጋ ነበር፡፡ ደብረዘይት ልንደርስ ትንሽ ሲቀረን ካለው አለሙ ሆቴል ለማደር ተስማማንና ገባን፡፡ አልጋ ቤት ተከራየን፡፡ በሕይወቴ እንደሷ ያስደሰተችኝ ሴት የለችም! የወሲብ ንግስት ነበረች፡፡ ስንጨርስ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

በጣም ተደሰቼ ላመሥግናት ቀና ስል ፊቷ ወደ ፈረስ ፊት ተለውጧል:: በሩጫ ከክፍሉ ወጥቼ ጠፋሁ! አንድ ጊዜ ደግሞ ጅቡቲ መስመር አንድ ሰው ስራ ሰርቼለት 5000 ሺ ብር ሰጠኝ:: 50 ጊዜ ቆጥሬ ተቀብዬዋለሁ:: ከስምንት ደቂቃ በኋላ ግን ብሩ የለም! ሰልቦኝ ሄዷል:: አንገቴ ላይ መስቀል ካሰርኩ በኋላ ግን ማንም ሸውዶኝ አያውቅም።

"ስለዚህ አቶ ደረሰ በእነዚህ ነገሮች ያምናሉ ማለት ነው?"

"እግዚአብሔር አለ ብሎ የሚያምን ግለሰብ ሴይጣን የለም ቢል በእግዚአብሔር መኖር ራሱ እርግጠኛ አይደለም:: እግዚሐብሔር ካለ ሴይጣንም አለ! እኔ ሴይጣን ሆነ የመናፍስት አሰራር እንዳለ አውቄያለሁ:: መስቀሉ ግን ያድነኛል:: ቅድም መስመር ላይ ያስገባኸው ባለአውሊያ ጠንቋይ የተናገረው ነገር ትልቅ እውነት ነው:: አንድ ሰው ልብ ውስጥ እግዚአብሔር ካለ ለሴይጣን የሚሆን ቦታ የለውም! ሴይጣን ሆነ የመናፍስት አሰራር ቢኖርም ባይኖርም አይጨንቀኝም! ምክኒያቱም በእግዚአብሔር የሚመካ ሰው ምንም አይሆንም"

"አቶ ደረሰ ስለሰጡኝ ሀሳብ በጣም ነው የማመሠግነው:: እድማጮች ከአሰፋው መለሰ ቁ4 መዝሙር አንድ እናዳምጥና የመጨረሻ ደዋይ አየር ላይ አውላለሁ ለላ ጊዜ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የፈላስፋዎችን እና የሳይንስቶችን አስተያየት የሚነግሩንን ባለሙያዎች ከAAU እጋብዛለሁ... ወደ መዝሙሩ"

እንዳሰብኩት ሳይሆን እንዳሰበልኝ ነው
እግ/ር አርጎታል እንደተናገረው
አርገጠው ይለኛል ጠላቴን አዋርዶ
አሸፈተው ልቤን አሳይቶኝ ማዶ
ወጀቡን አይደለም ማዕበሉ ሚለኝን
ጌታን ነው [illegible] ተሻገር ያለኝን

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

" FM66.6 እፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል፡፡ የመጨረሻው ደዋይ መስመር ላይ ይገኛል
ሀሎ ማን ልበል?"

" መሰረት"

" ከየት ነው መሠረት በነገራችን ላይ መሠረት ለወንድም ለሴትም የሚሆን ስም ነው"

" ልክ ነው ግን ለሴት ይበልጥ ሙድ አለው፡፡ እኔ በርካታ አገራት በስራ ጉዳይ ዞሬያለሁ በእርግጥም እኔ አንተ ባነሳሀቸው ነገሮች አላምንም፡፡ ውጪ ሀገር በተለይ ካርታ አንባቢዎች ፣ ኮከብ ቆጣሪዎች ፣ ትንቢት ተናጋሪዎች፣ እስትሮቶች፣ በጣም ይታመናሉ፡፡ አንዲት ጓደኛ ነበረችኝ በየሳምንቱ የሚወጣውን ሆሮስኮፕ የምታነብ፣ ታምንበት ነበረች፡፡ አንድ ጊዜ ዛሬ ከቤት አትውጪ ከወጣሽ አደጋ ይደርስብሻል የሚል አነበበች፡፡ አልወጣም ብላ በስንት ጭቅጭቅ እኔና ባሉዋ ይዘናት ወጣን፡፡ በመኪና ተገጭታ ሞተች፡፡ በዚህ አጋጣሚ መናገር የምፈልገው ነ ው ልጅ የአስተሳሰቡ እና የሚያምነው ነበር እስረኛ እንደሆነ ነው፡፡ እኔ እነዚህን ነገሮች እንደ ብልጠት እና የማጭበርበሪያ ትረኮች ብቻ ነው የምመለከታቸው አመሠግናለሁ ጎልያድ!"

" እኔም አመሠግናለሁ! አድማጮች የዛሬው እዚህ ላይ ይጠናቀቃል በ0911 04 89 ** ላይ ለደወላችሁ ፣ SMS በመላክ ሁለት ብር ለሰጣችሁኝ ሁሉ የከበረ ምስጋና አቀርባለሁ! እስቲ እናንተም በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ከጓደኞችሁ ጋር ተወያዩበት! የደረሳችሁበትን ሀሳብ በአጭር የፅሑፍ መልዕክት ላኩልኝ! ነገ በጣም በጉጉት የምትጠብቁትን በወር አንድ ጊዜ የማቀርብላችሁን ምናባዊ ቃለ መጠይቅ በመያዝ እቀርባለሁ እስከ ነገ ሰናይ ጊዜ! ጎልያድ ነበርኩኝ! እስቴር ከበደ ትቀጥላለች"

## ደያስ ምግብ ቤት

በከተማችን ውስጥ ካሉ ትላልቅ ሆቴሎች ውስጥ ትርፍራፊ በመግዛት እንሸጣለን! ይምጡ በታላቅ ቅናሽ ያሻዎትን ምግብ ይመገቡ! ያሻዎትን ይጠጡ... ደያስ ምግብ ቤት! ለፍቅረኞች ልዩ ቅናሽ አለን! ለየት የሚያደርገን የዱቤ አገልግሎት በመስጠታችን ነው! ደያስ!!

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

እንግዲህ ጀመረኝ

መውደድህ ጀመረኝ

ደረሰ ሰዓቱ አንተን አንተን ሊለኝ

እንግዲህ ጀመረኝ

የማይሆንም አይሆንም የሚሆን ይሆናል

አወይ ልቤ ምኑ ሲጨነቅ ይኖራል

ማሰብ አይታከተኝ እንግዲህ ጀመረኝ

ናፍቆት አሰቃየኝ ወዳንተ እያሰኘኝ

የቤቴ የወለሉ ጣሪና ግድግዳው

ባንተ አምሳል ተሞላ አወይ የኔ እዳው

ልይዘው ብሞክር ልመልሰው ብጥር

ለካስ በሀሳብ ነው አወይ የኔ ነገር

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

# ክፍል ረ

# ምናባዊ ቃለ መጠይቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

# ክፍል - ረ

የካቲት 26/2005

ምናባዊ ቃለ መጠይቅ

ከ

አፄ ቴዎድሮስ ...

ጥላሁን ገሰሰ ...

በዓሉ ግርማ ...

መለስ ዜናዊ...

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

" የተከበራችሁ አድማጮች እፍ ሲከፈት ጭቅላት ይታያል FM66.6 የየካቲት 26 ፕሮግራሙ ጀምሯል:: የዛሬው ለየት ያለው እና በወር አንድ ጊዜ ብቻ የሚቀርበው ፕሮግራም ምናባዊ ቃለ መጠይቅ ከዝነኛ እና አነጋጋሪ ሰዎች ጋር የሚደረግበት ፕሮግራም ነው:: አድማጮች በነገራችን ላይ ሁለት ዜና አለኝ:: ጥሩና መጥፎ ዜና! ጥሩ ዜናው አራቱም ግለሰቦች ለቃለ መጠይቁ ፍቃደኛ መሆናቸው ሲሆን መጥፎ ዜናው ለቃለ መጠይቁ ፍቃድ የሰጡኝ አካል በመጀመሪያ ዙር ለእያንዳንዱ ሰው ከአምስት በላይ ጥያቄዎችን እንዳልጠይቅ ማዕቀብ ማስቀመጡ ነው:: ስለዚህ ውድ አድማጮች ለእያንዳንዱ ግለሰብ የማቀርብላቸው አምስት ጥያቄዎችን ብቻ ይሆናል ዛሬ በ 091104 89 ** ላይ መደወል አይቻልም! በSMS አስተያየት ብቻ መላክ ይቻላል፤ አንድ ማስታወቂያ ላሰማችሁና በቀጥታ ወደ ቃለመጠይቁ እመራለሁ::

## መይሳው ካሳ ዩኒቨርሲቲ

ዩኒቨርሲቲያችን ብዙ ለየት የሚያደርጉት ነገሮች አሉት! በጀግናው መይሳው ስም የተሰየመው ዩኒቨርሲቲያችን ሲመጡ በብቃት አስተምረን በብቃት እናስመርቃለን! የአንድ ዓመት የውትድርና ስልጠና እንሰጣለን! ከተመረቁ በኋላ በእርግጠኝነት ራሳችን ስራ በምርጥ ክፍያ እናስቀጥርታለን በራሱ የሚተማመን! ራዕይ ያለው! ቀና አሳቢ! በአዕምሮም በአካልም ዝግጁ ሆኖው ይመረቃሉ! መኝታ ቤታችን የሴት የወንድ የሚል ልዩነት የለውም በፍጥነት ይምጡ! ይመዝገቡ! በዩኒቨርሲቲያችን የሚሰጠው ዲግሪ በ148 ሀገራችን ተቀባይነት ያለው ነው! አጠቃላይ ወጪው እስከምርቃት ድረስ 1/2 ሚለየን የኢትዮጵያ ገንዘብ ብቻ ነው!! መይሳው ካሳ ዩኒቨርሲቲ-

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

" በሰልክ መስመራችን ላይ አፄ ቴዎድሮስ ይገኛል አስቀድሜ እንዳልኳችሁ የተሰጠኝ ደቂቃ በጣም ትንሽ ስለሆነ በቀጥታ ወደ ጥያቄ እመራለሁ! አፄ ቴዎድሮስ በፍቃደኝነት ከዘመናት በኋላ በ FM66.6 ላይ ለህዝቡ አስተያየት ለመስጠት ፍቃደኛ ስለሆንክ በጣም አመሰግናለሁ:: በቀጥታ ወደ መጀመሪያ ጥያቄ ነው የማመራው.. አፄ ቴዎድሮስ ነብሰበላ ነው በዚያው ልክ ለኢትዮጵያ አንድነት ታላቅ መስዋዕት የከፈለ ጀግና ንጉስ ነው ይሉሀል ምን ትላለህ ?"

" በመጀመሪያ ለኢትዮጵያ ህዝብ የከበረ ሠላምታ አቀርባለሁ:: እርግጥ የተባለው ነገር ዛሬ ላይ ሆነን ስናስበው እውነትነት ያለው ይመስላል በሌላ በኩል ወደ ኋላ ተጉዘን ያን ዘመን ላይ ተቀምጠን ስናስበው ደግሞ እኔ ያደረኩት ነገር ሁሉ ለኔ እውነትነት አለው:: ዘመኑ ዘመነ መሳፍንት ነበር! ኢትዮጵያ በየቦታው ስልጣን በሚፈልጉ መሪዎች እጅ ስር ነበረች! እኔ የወሰድኩትን እርምጃ የወሰድኩት በስሜታዊነት ተነስቼ አይደለም:: ቀኝ እና ግራ አማክሬ ... በዘመኑ የነበረው ህዝብ ከሰላማዊ ድርድር ይልቅ በጡንቻ የሚያምን አስተሳሰብ የነገሰበት ዘመን ነበር:: ስለዚህ እኔ ያደረኩት "ነብሰበላ" የሚል ማዕረግ የሚያስጠኝ ዛሬ ላይ ተቀምጠን ስናስበው ነው እንጂ እኛ በዘመነ መሳፍንት ዘመን ተቀምጠን ስንመዝነው ልክ ነበር:: እጅ የቆረጥኩትም ሆነ አሻፈረኝ ያሉትን የገደልኩት እንደ ሌሎች መሪዎች የግል ጥቅምን ለማስከበር እና የስልጣን ዘመኔን ለማራዘም ሳይሆን ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ ባለኝ ፅኑ እምነት ነበር:: በእርግጥ እኔም ለውጥን በፍጥነት በመፈለጌ እና ሁሉ ነገር በፍጥነት እንዲቀየር በመፈለጌ የተነሳ ጠላት በዝቶብኝ ነገሮች አልተሳኩም! ይልቅስ የሚገርመኝ እኔ አፄ ቴዎድሮስ ነብሰበላ ነህ ከተባልኩኝ ቢያንስ ከኔ በኋላ የመጡት መሪዎች የኔን ስህተት መድገም አልነበረባቸውም! ተመልከት እስቲ መቅደላ ድረስ ኢንግሊዞችን ስልጣን ለማግኘት ብሎ እየመራ ያመጣቸው ማን ነው ...? መንግስቱስ በቀይ ሽብር ስንቶችን አልጨረሰም? ... መለስስ በምርጫ 97 ላይ ምንድነው ያደረገው? እንግዲህ ነብሰ በላ መሪ ያልሆነውን ለኢትዮጵያ ህዝብ መተው የተሻለ ነው... ጥያቄው ግን እውነትነት አለው በዚያ ላይ መሪ ሰው ነው ሰው ደግሞ ስህተት አያጣውም! ችግሩ መሪ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

አልያም ታዋቂ ስትሆን ሰዎች አንተ ከሰራኸው 98 መልካም ነገሮች ይልቅ አንተ የሰራሀቸውን ሁለት ደካማ ነገሮች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ:: በዚያ ላይ የሁሉንም ሰው ፍላጎት መጠበቅ በጭራሽ አይቻልም"

" ሁለተኛው ጥያቄዬ ኢትዮጵያን ወደ 4749 ቀናት በመምራት በስልጣን ላይ ቆይተሀል እስቲ የኢትዮጵያን ህዝብ ግለፅ ቴዲ?"

" ልጅ ጎልያድ በኔ ጊዜ የነበረው የኢትዮጵያ ህዝብ በእርግጥ እንደ አሁኑ ዘጠና ሚሊዮን ህዝብ ገደማ አልነበረም:: በኔ ጊዜ ት/ት እና ዘመናዊነት አልተስፋፋም! በኔ ዘመን የነበረው የኢትዮጵያ መንፈስ እና የኔ ራዕይ በጣም ልዩነት ነበረው:: እኔ አንዲት ዘመናዊ አንድነት! ሰላም! ፍቅር! መተሳሰብ... የበዛባት እግዜርን የምታከብር ! የአፍሪቃ ታላቅ አገር ለመፍጠር ነበር:: ችግሩ በኔ ጊዜ የነበረው ህዝብ ገና ጥሬ ነበር! ሕይወት ማለት ለእነርሱ መብላት፣ መጠጣት፣ መተኛት _ ነበር ብቻ ... እኔ ህዝቡ መሀከል የበቀልኩ እብድ ነበርኩ:: የኔ እና የሶቅራጥስ ሕይወት በጣም ይመሳሰል ነበር:: የማልዋሸው ነገር ቢኖር በ13 ዓመቱ ወይም 4749 ቀናት የስልጣን ዘመኔ የኢትዮጵያ ህዝብ በምክኒያት ሳይሆን በስሜት የሚያምን ለውጥን በጣም የሚፈራ ህዝብ ነበር:: በሌላ በኩል ታላቅ የሀገር ፍቅር እና የባንዲራ ክብር ነበራቸው:: በዚህ ዘመን ስላለው እነ መለስ ዜናዊ ቢመልሱ የተሻለ ነው"

" አፄ ቴዎድሮስ ልበሙቅ ነው ይሉሀል! ልበሙቅ ባይሆን ራሱን መቅደላ ላይ አይገልም ነበር የሚሉ አሉ በሌላ በኩል እጁን ለነጭ ላለመስጠት እና ኢትዮጵያዊነት ወኔን ለመጠበቅ እና የጀግና ሞት ለመሞት ነው ይላሉ:: ምን ትላለህ?"

" ሰው የፈለገውን ሊል ይችላል:: እኔ የወሰንኩት ግን ዛሬም እስረግጬ የምነግርህ 100% ትክክለኛ ውሳኔ ነበር:: የሚያሳዝነው እና የሚያስደንቀው እኮ ማን ነው ኢንግሊዞችን እየመራ መቅደላ ድረስ ያመጣቸው የሚለው ጥያቄ ነው? የኔ ጠላት እኮ እንግሊዝ አይደለም! እሱ ነው ... ብቻ ተወው ልጅ ጎልያድ"

" አራተኛው ጥያቄ እንደሚታወቀው የመቅደላ ጦርነት ሊያልቅ አካባቢ የኢንግሊዙ ጄኔራል ናፒየር ጦርነቱ ሲጀምር "ድሉ የኛ ነውና እባኮት እጅዎን ይስጡ" ብሎ ሲልክብህ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

የአንተ ምላሽ "አከንዱ ላይ የነጭ እጅ አያርፍም! እሳት ነው ያቃጥልሀል" የሚል ምላሽ ሰጥተሽው ነበር:: እንዴት ነው ከጄኔራል ናፒየር ጋር ተገናኝታችሁ አውርታቹሀል ይባላል እውነት ነው?"

"ውሸት ነው:: በነገራችን ላይ እዚህ ለፍርድ እሰጣጥ እንዲመች ተብሎ ምድር ላይ በሰራነው ስራ መወቃቀስ፣ ሆነ መደናነቅ ፣ ይቅርታ መጠያየቅ... አይፈቀድም:: ባጭሩ አልተገናኘንም::"

"አፄ ቴዎድሮስ ለዛሬው የመጨረሻ ጥያቄ ሴባስቶፖልን በተመለከተ ነው:: ሴባስቶፖል የተባለው መድፍ ባንተ ቁራጥ ትዕዛዝ ሀገር ውስጥ በነበሩ የኢንግሊዝ ቄሶች ተሰርቶ አልቆ ወደ መቅደላ ተራራ ላይ ሲወጣ አንተ ራስህ ላብህን ጠብ እያደረክ ከሠራተኞች፣ አሽከሮች፣ ጀሌዎች ጋር ስትገፋ ነበር:: ይህ በጣም ደስ የሚል ምሳሌ ነው ግን የሴባስቶፖል መድፍ ተሞክሮ ሲሠራ በጣም ከመደሰትህ የተነሳ የሴባስቶፖልን አፈሙዝ በደስታ ስትስመው አፍህ /ከንፈርህ/ ተቃጠለ፣ ለምጥ መሰል ነገር አወጣብህ የሚባለውስ?"

"ቂ...ቂ...ቂ...ቂ.. በእርግጥ በደስታ ስሜዋለሁ:: እንደተባለው ግን አፈሙዙን አይደለም"

"አፄ ቴዎድሮስ በእውነት ስለነበረን ጊዜ እጅግ በጣም አመሠግናለሁ:: ሌላ ጊዜም አስፈቅጄ ክፍል ሁለት ቃለ መጠይቅ አደርግልሀለሁ:: በዚህ አጋጣሚ አድማጮች ለአፄ ቴዎድሮስ መጠይቅ የምትፈልጉዋቸውን ማንኛውንም ጥያቄዎች በ0911 04 89 ** ላይ SMS ላኩ... ብዙዎች የሚጠይቁዋቸው ጥያቄዎች ተመርጠው በክፍል ሁለት ቃለ መጠየቅ ለአፄ ቴዎድሮስ ይጠየቃሉ:: ለማንኛውም ውድ አድማጮች አጠር ያለ የመሸጋገሪያ ሙዚቃ እንስማና በቀጥታ ወደ ጥላሁን ገሰሰ እመራሁ"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ከመቅደላ ቢሰዋ ሕይወቱን
ብዙ ነበር የካሳ ምኞቱ
ለአንድ እናቱ ለአንድ እናቱ
ከአፄ ፋሲል እስከ ቴዎድሮስ
ያፈራችው ጎንደር ትወደስ…

… ….

የአገር አንድነት ሲነሳ
ስሙ አይረሳ የካሳ
የቋራ ካሳ ….

## አዜብ አፋቿ

መሀከል ፒያሳ ወደተከፈተው አዜብ አፋቿ ብቅ ይበሉ! እስከ መቼ ይጨቃጨቃሉ እስከ መቼስ ይነዛነዛሉ! የትዳር ሕይወትዎ ጨለማ ከሆነ የከፋ አደጋ ሳያጋጥሞት እኛ ጋር ይምጡ እናፋታዎታለን ! ልጆች ካሉ በጥሩ ዋጋ እንገዛታለን! ዋነኛው አላማችን እናንተን አፋተን ሠላማዊ ሕይወት እንዲኖሩ ነው! አዜብ አፋቿ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

"እድማጮች ወሬ ሳላበዛባችሁ ወደ ጥሌ መስመር ላይ ስለሆነ እመራለሁ:: ጥሌ በኢትዮጵያ ታሪክ ወደ 1.5 ሚሊየን ህዝብ የቀብር ስርዓትህ ላይ ተገኝቶ የቀበረህ ብቸኛ ባለ ሪከርድ ነህ! በወቅቱ ምን ተሰማህ?"

"በጣም የሚደንቅ ነው! የሚገርምህ እዚህ ስመጣ ራሱ ከኔ በላይ ታሪክ ለሀገራቸው የሠሩት ዝነኞች እነ ማሀትመ ጋንዲህ፣ አብረሃም ሊንከን፣ ማርቲን ሉተርና፣ ቼ ጉቬራ፣ ሆቺ ሚን፣ ማኦ ዜዱንግ... የመሰሉ ታላላቅ ሰዎች ራሱ ምን አይነት ሰው ቢሆን ነው 1.5 ሚሊየን ህዝብ የቀበረው በማለት አቀባበል አድርገውልኛል:: በዚህ አጋጣሚ ለኢትዮጵያ ህዝብ ምስጋናዬን ለማቅረብ ቃላት የለኝም:: እግዚሐብሔር ይስጥልኝ ከማለት ውጪ!!"

"ጥሌ ወደ ሁለተኛው ጥያቄ ላምራ ከብዙ ሴቶች ጋር ትማግጥ ነበር ይባላል ምን ትላለህ ጥሌ መዋሸት አይፈቀድም?"

"አይ ጎልያድ ! አሁንማ እዚህ መዋሸት፣ ማስመሰል፣ ይሉኝታ...ወዘተ የሚባል ነገር የለም:: ይህ ብዙ አያደንቅም ዝነኛ ስትሆን ከአህትህ ጋር ስትሄድ ራሱ ስም ይወጣልሀል... ለማንኛውም ወሬ ከማረዝምብህ በመጠኑ ልክ ሊሆን ይችላል ነገር ግን የተጠቀምከውን ቃል ግን አልወደድኩልህም ሚስት እኮ ከመሬት ተነስተህ አታገባም! መፈታተን ሊኖር ይችላል:: እስቲር አወቀ በቅርቡ የዘፈነችውን ትዳር ነከ ሙዚቃ አድምጥልኝ"

"እሺ ጥሌ .... ጥላሁን ገሰሰ በሕይወት ዘመኑ አንድ መፅሐፍ እንኳን አላነበበም ድምፅ እንጂ ባዶ ከበሮ ነው ይሉሀል ምን ትላለህ?"

"ቂ...ቂ...ቂ ...ቂ... እርግጥ ባነብ የተሻለ ነገር እሠራ ነበር ፤ ባነብ የተሻለ ማንነት ይኖረኝ ነበር!! የኔ ህይወት ሙሉ ለሙሉ የተሰጠው ለሙዚቃ ነበር:: ለኔ ሙዚቃ ገንዘብ ማግኛ ሳትሆን ሕይወቴ ነበረች!! እንደዘመኑ ሙዚቀኞች ጫጫታ እና አንድ ሳምንት ተደምጦ ለመጥፋት አልዘፍንም ነበር:: በዚህ አጋጣሚ ለዘመኑ ላሉት ሙዚቀኞች ባዶ ጭንቅላት እንዳይኖራችሁ እንብቡ እላለሁ! ማወቅ ያለብን መፅሐፍ ያነበበ ሁሉ አዋቂ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ያላነበበ መሀይም ነው ማለት ግን አይደለም"

" አመሰግናለሁ ጥሌ ባንተ ሕይወት ዙሪያ በተፃፈው መፅሐፍ ላይ በሆድ ይፍጀው ያለፍከው ታሪክ አለ:: ብዙዎች በዚህ ገለፃ ጥላሁን ፈሪ እና ድብቅ ነው ይላሉ::ባንተ ጉሮሮ ላይ ከፍተኛ አደጋ ያደረሰውን ግለሰብ እያወክ ለምን ለህዝቡ ማሳወቅ ፈራህ?"

" ልጅ ጎልያድ አንዳንዴ እኮ አንተ እና ፈጣሪ ብቻ የምታውቁት ሚስጢር ይኖራል:: ባለመናገሬ እኔ አልጎዳም ብናገር ግን የሚጎዳ ሰው አለ፤ ስለዚህ መምረጥ ነበረብኝ የመረጥኩት ደግሞ ለኔ ልክ ነበር ስለዚህ አሁንም ሆድ ይፍጀው እላለሁ"

" ጥሌ የመጨረሻ ጥያቄ አጠገብህ አፄ ቴዎድሮስ፣ ንጉስ ሐይለስላሴ ፣ በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ ተቀላቅለዋቸሁል! እንደው ጥሌ ከሶስቱ የማን አድናቂ ነህ? ባንተ አመለካከትስ ማን ነው ለኢትዮጵያ የተሻለ ነገር የሠራው? ጥሌ ሳትፈራቸው መልስ"

" አይ ልጅ ጎልያድ እዚህ መፍራት የሚባል ነገር የለም! እዚህ ይህ ዝነኛ ነው ይህ ፕሬዝዳንት ነው... ይህ ባለሀብት ነው... ወዘተ የሚባል የለም:: ሁላችንም እኩል ነን:: ሁላችንም ተራዎች ነን:: ላነሳኸው ጥያቄ ምላሽ መስጠት አልችልም ምክኒያቱም በተሰጠን ትዕዛዝ መሠረት ማድነቅ፣ መወቃቀስ ፣ መሰዳደብ ወዘተ ተከልክለናል መልሱ ግን ሼክ ሁሴን አሊ አላሙዲን ነው"

" እሺ ጥሌ በጣም ነው የማመሠግነው ሌላ ጊዜ በደንብ እስፈቅጄ በሰፊት እናወራለን! አድማጮች አንድ ማስታወቂያ እንስማና በቀጥታ የተመደበልኝ ደቂቃ በጣም አጭር ስለሆነ ወደ ዝነኛው በዓሉ ግርማ አመራለሁ! እያዳመጣችሁት ያላችሁት አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል የተሰኘውን ፕሮግራም በFM66.6 ላይ ነው... ማንኛውንም አስተያየት በ0911 04 89 ** አልያም በ777 ላይ በSMS ላኩልኝ..."

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

## FUN ZONE 1

እጅግ ወደተዋበው FUN ZONE 1 ይምጡ የውሸት እና የፊስ ውድድር አዘጋጅተናል! ለአሸናፊው 4000 ሺ ብር አዘጋጅተናል... በዚያ ላይ እናተን ለማዝናናት ሁለት የአስማት ትርሂት እና ትዕይንት የሚያሳዩ ህንዶችን አስመጥተናል...FUN ZONE 1

" ሀሎ በዓሉ ግርማ"

" ታዲያስ ልጅ ኅልያድ"

"በጣም ነው የማመሠግነው በዓሉ አንተ ራስህ ጋዜጠኛ ስለነበርክ መቼም የጋዜጠኛን ነገር ታውቃለህ የሰጡኝ ደቂቃ በጣም ጥቂት ስለሆነች በቀጥታ ወደ ጥያቄዬ ላምራ ሰዎች ሁሉ ጓሯ የሚጋቡበት ጥያቄ ኦሮማይን በመፃፍህ የተነሳ ጓድ መንግስቱ አስገደለው ይላሉ! በሌላ በኩል ፕሬዝዳንት መንግስቱ ሲጠየቅ በጭራሽ እኔ እንዲገደል አላደረኩትም ይላል! እውነታው የቱነው?"

"እውነታው እኔ መሞቴ ነው:: መሞቴን ደግሞ አውቀው ነበር:: ለምትወደው ነገር ስትል! ለጥበብ ስትል ስትሞት ክብር እንጂ ውርደት አይደለም! ብዙዎች ይህን ጥያቄ በቁጭት የሚያነሱት በዓሉ ግርማ በሕይወት ቢኖር ብዙ መፅሐፍትን ይፅፍልን ነበር ከማለት የተነሳ ነው:: ያለውን ራሱ መቼ አንብበው ጨረሱት? በቅርቡ ከስብሀትም ጋር በዚህ ጉዳይ ስናወራ ነበር ለማንኛውም ለምትወደው ነገር መሞት ክብር ነው እላለሁ እንጂ በኔ ጉዳይ ዙሪያ አይጨንቀኝም"

" ሁለተኛው ጥያቄ በመፅሐፍቶችህ ውስጥ ቆንጆ ገፀባህሪያትን ታበዛለህ ይህን የምታደርገው ቆንጆ ሴቶችን ስለምትወድ ነው ይባላል፤ እውነት ነው?"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

"በእርግጥ ማን ቆንጆን ይጠላል?" ስለ ቆንጅና ከጠቢቡ ሰለሞን ጋር ስናወራ ነበር ከአንድ ሺ ሴቶች ጋር ያስተኛው ውበት ነበር ... እኔ ግን ለቆንጆዎች የተለየ ቦታ ስለነበረኝ ሳይሆን በአጋጣሚ የተፈጠረ ጉዳይ ነው በዚህ ላይ ውበት አንፃራዊ ነች"

" አመሠግናለሁ ለኢትዮጵያ የተሻለ የሠራው መሪማን ነው? አፄቴዎድሮስ? ሐይለሥላሴ? መለስ ዜናዊ?" "አ! የኔ መልስ ከአንተ ምርጫ ውጪ ነው:: ሁሉም የራሳቸውን አሻራ ሁሉም የራሳቸውን ጠባሳ ለኢትዮጵያ ህዝብ ጥለው አልፈዋል:: በኔ አመለካከት አገሬ ኢትዮጵያ እስካሁን ምርጥ መሪ አላት የሚል ወይም አግኝታለች ለማለት አያስደፍረኝም:: እዚህ ከነአብርሃም ሊንከን፣ ጆርጅ ዋሽንግተን ፣ ማህተመ ጋህንዲ ጋር ሳወራ በኛ ሀገር መሪዎች አፍሬያለሁ:: ለማንኛውም ከሰስቱ የግድ አንዱን ምረጥ ካልከኝ ግን ለኔ የተሻለው ከነድክመቱ ጭምር አፄቴዎድሮስ ነው:: ህዝቡ አልተረዳውም እንጂ ውስጡ የነበረው ታላቅ እሳት " ሁሉም በአንድነት የሚኖሩባት ህዝቦቿዋ በዘር በቋንቋ... የማይበሉባት ታላቂቷን ኢትዮጵያን መፍጠር የሚል ራዕይ ነበር፤ ችግሩ ግን ጥሩ አማካሪ አላገኘም! ከህዝቡ ጋር እንዴት መዋሀድ እንዳለበት አልተገነዘበም ነበር"

" እንደ አንተ ደራሲ ለመሆን ለሚፈልጉ ወጣቶች ያለህ ምክር ምንድ ነው?"

" እህ ደራሲው የሚለውን መፅሐፌን ያንብቡ! ከዚያ በተረፈ ፈሪሰው ከሆኑ በጭራሽ ወደ ሥነ ፅሁፍ እንዳይገቡ ንገርልኝ የሰዎችን ንግግር ፣ ሁኔታ፣ ማንነት፣ ተፈጥሮን፣ የተፈጥሮን አካሄድ በሚገባ ያጤኑ ፣ ከምንም በላይ ጥሩ አድማጭ እና ጥሩ አንባቢ ይሁኑ"

" ለዛሬው የመጨረሻ ጥያቄዬ ባሁኑ ወቅት ስላለው የኢትዮጵያ ሥነ ፅሁፍ ምን ትላለህ?"

" ጥሩ ጥያቄ ነው! ሥነ ፅሁፍ ከዘመኑ ጋር ትጓዛለች:: እኔ የሪያሊዝም አፃፃፍ አድናቂ ስለሆንኩኝ ባለው የሕይወት ከስተት ላይ ተመስርተው የሚፅፉትን የሥነ ፅሁፍ ስራዎችን እንጂ ምናባዊ ፈጠራዎችን ብዙም አላደንቅም:: በጣም አሲደሳቹ ዜና ሰምኑን ወደኛ የመጡ ሰዎች እንደነገሩኝ በተለይ ከሰባህት ጋር በርካታ መፅሐፍት እየወጡ እንዳሉ ሰምቻለሁ:: እኔ ሁሉንም በርቱ ለማለት እፈልጋለሁ:: እዚህ ... ፈጽኖቅ ሆነ መወቀስ አይቻልም

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

የሚል ህግ ስላለ ነው"

"በጣም አመሠግናለሁ በዓሉ ግርማ ! አድማጮች የምታዳምጡት አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል የተሰኘውን ፕሮግራም በFM66.6 ፕሮግራም ላይ ነው:: ፕሮግራሙን እየመራሁ ያለሁት ጎልያድ ነኝ:: አንድ ሶስት ደቂቃ ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ የስልክ መስመር ላይ እስከ ሚገባልኝ አንድ ማስታወቂያ እና አጠር ያለ ሙዚቃ ላሰማችሁና ተመልሼ እመጣለሁ::"

## ቃና ቂና ባንክ ቤት

ባንክ ቤታችን በአንድ ቢሊየን ብር የተቋቋመ እጅግ ዘመናዊ ባንክ ቤት ነው:: የ24 ሰዓት አገልግሎት እንሰጣለን ባንክ ቤታችንን ከሌላው ባንክ ቤት ለየት የሚያደርገው የወለድ መጠኑ 9.60 መሆኑ ነው! ከዚህም በተጨማሪ ወደ ቃናቂና ባንክ ቤት ሲመጡ ጽድት ያለ ጣት የሚያስቆረጥም... ጠጅ እና በርገር እንጋብዞታለን አስተናጋጆቻችን በሙሉ ውበት የፈሰሰባቸው ወጣት እንስቶች ናቸው:: በዚያው ይጠብሳሉ ወይም ይጠበሳሉ ... ቃናቂና ባንክ ቤት

... ያስቀየምኩት ቢኖር የጠላኝ በቁሜ
ድምፄን ሰምቶ ያዝናል ለረገፈው አፅሜ
እኔን ለበደሉኝ ስርግለሁ ቂሜን
በእኔ የከፋችሁ ይቅር በሉት አፅሜን
ለቅርብ ወዳጄ ለሚወደኝማ
አይገደውም እንባ ትንፋሼን ሲሰማ ...

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

" አድማጮች ተመልሼ መጥቻለሁ በማዳመጥ ላይ ያላችሁት አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል የተሰኘውን ፕሮግራም በFM66.6 ላይ ነው አቶ መለስ ዜናዊ መስመር ላይ ይገኛሉ:: ሁሉ አቶ መለስ በቅድሚያ ለቃለ መጠይቁ ፍቃደኛ ስለሆንክ አመሠግናለሁ የተሰጠኝ ጊዜ በጣም አነስተኛ ስለሆነ እባክህ ለምጠይቅህ ጥያቄዎች ዙሪያ ጥምጥም እየዞርክ ደቂቃ እንዳትፈጅብኝ በቀጥታ ምላሹን ስለ ምትሰጠኝ አመሠግናለሁ:: የመጀመሪያ ጥያቄዬ ባንድ ወቅት ታሪክ ዳቦ አይደለም አይበላም! ባንዲራ ጨርቅ ነው! አክሱም ሐውልት ለደቡብ ህዝብ ምን ነው የሚል ነገር ተናግረህ ነበር ይባላል:: ይህን ነገር በተዕመለከተ ምን ትላለህ?"

" እኔም አመሠግናለሁ:: በተቻለኝ መጠን መልሱን ብቻ ለመመለስ ጥረት አደርጋለሁ:: በነገራችን ላይ ዙሪያ ጥምጥም እየዞርኩ ምላሴ እያበዛው የምናገረውን ነገር ቶሎ ስለማይረዱልኝ ነበር:: ለማንኛውም ወደ ጥያቄው ስመለስ በእርግጥ ታሪክ ዳቦ አይደለም አይበላም... አክሱም ሐውልት ለደቡብ ህዝብ ምን ነው ... ባንዲራ ጨርቅ ነው ስል እኔ ለማለት የፈለኩት ሌላ ሀሳብ ነው:: ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ከመስጠቴ በፊት የአንድ ንጉስ ታሪክን በምሳሌ ላሳይህ ..."

" አቶ መለሰ በጣም ይቅርታ ደቂቃ ስለሌለኝ በቀጥታ ወደ ሁለተኛው ጥያቄ አመራለሁ:: የአንተ አድናቂዎችህ ስሜታቸውን መቆጣጠር አቅቶዋቸው እስካሁን በደረሰኝ መረጃ መሰረት በብር ሲተመን 400 ሚሊየን ብር የሚጠጋ ባነሮች ፣ ማስታወቂያዎች፣ ፎቶዎች ፣ በየቦታው አሰለጥፈዋል ብዛት ያላቸው ሴቶችም የአንተን ምስል በሰውነታቸው ላይ ተነቅሰዋል... መንግስትም የከፍለ ዘመኑ ታላቅ መሪ ባስቀመጠልን ራዕይ ብቻ እንጓዛለን እያለ ነው:: ባጠቃላይ አንተን እንደ ሐይለስላሴ እንድትመለክ ጥረቶች እየተከናወኑ ነው ይህን ጉዳይ እንዴት ትመለከተዋለህ?"

" እኔ ቴዎድሮስ ያጋጠመው ችግር ነው እኔም ያጋጠመኝ:: ይህ ትልቅ ክፍተት ነው:: የኢትዮጵያ ህዝብ ያጣውን ነገር ይወዳል፤ በቁምህ ሳይሆን ስትሞት ክብር ይሰጥሀል እንጂ እኔ እንደ ማንኛውም ሰው ሟች ነኝ፤ ሞትኩኝም:: አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ሆይ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ሀገሬታ ማብዛት አላዋቂነት ነው:: ይህን የሚያደርጉት ግራ ከመጋባት የተነሳ ነው:: እኔ ማን ነኝ እና ነው ኢትዮጵያን የምታክል ታላቅ ሀገር በኔ ራዕይ ብቻ የምትመራው? ... እንኳን እኔ እነ ቹ ጉቬቫራ፣ ጁሊየስ ኔሬሬ፣ ጃሞኬኒያታ፣ አብርሃም ሊንከን እንኳን እንደኔ ወሬ አላበዙላቸውም:: እንዳልከው በሰውነታቸው ላይ የኔን ምስል የተነቀሱ ሴቶች ግላዊ መብታቸው ነው:: ሰውነታቸው ላይ የኔን ምስል መነቀስ አይደለም ዶታቸውንም የመቀየር መብት አላቸው! ለኔ ሙቀት አይፈጥርብኝም፤ አንተን እንደ ሀይለስላሴ ለማድረግ ያልከው ቡግም ያስቃል .. በዚህ ዘመን ስልጣኔ ይህ ነገር ይሳካል ብለህ አትጠብቅ! ሌላው የምነግርህ ነገር ኢትዮጵያን ስሜታዊ ህዝቦች ነን:: አሁን የምታየው በየቦታው የተሰቀሉ ፎቶችም፣ የመለስ ራዕይን ብቻ የሚሉት ሁሉ በቅርቡ ይጠፋሉ! እስቲ አንድ ሁለት ምሳሌ ብቻ ላንሳልህ ለቶ አበራ ሞላ ኢትዮጵያን እናፅዳ ብሎ ሲያውጅ ህዝቡ ሆብሎ ተነሳ! ለወረት ተረባረበ! ባመቱ ራሱ ባፀዳው ቦታ ላይ ራሱ መፀዳዳት ጀመረ! ጥላሁን ሲሞት ሺ ቃልኪዳን ህዝቡ ገባ በዓመቱ ጥላሁን የሚባል መኖሩ ራሱ ተረሳ! ወረት በጣም ያጠቃናል:: ስለዚህ እኔን የማያደንቁ ሰዎች ብዙም ሊጨነቁ አይገባም:: በተረፈ እኔ ስሜ ዘወትር እንዲነሳ ፤ ምስሌ እንዲለጠፍልኝ... ታላቁ መሪ እንዲሉኝ.. እንዲዘፈንልኝ ... የመሰሉ ቱልቱላዎች ለኔ ከንቱ ናቸው:: ለአድናቂዎቼ ማስተላለፍ የምፈልገው ማድነቅ በቱልቱላ ሳይሆን በተግባር መገለፅ አለበት ... የተግባር ሰው ደግሞ በቱልቱላ አይታሠርም .. አጉል ጫጫታችሁን ተውና ለኢትዮጵያ ለውጥ የራሳችሁን ድርሻ ተወጡ በልልኝ ! ኢትዮጵያ በዚህን ሰዓት የምትፈልገው ወሬ ሳይሆን ተግባር ነው በልልኝ"

" ወደ ሰስተኛው ጥያቄ አመራለሁ:: ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ጥሩ መሪ ነበር፤ ችግር የነበረው ከታች ያሉት በሚፈጥሩት ክፍተት ነበር ይላሉ፤ የተቀሩት ደግሞ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያ መቼም የማትወጣው ፈንጂ ቀብሮባት የሄደ DOUBLE –FACE MAN ነበር ይላሉ አንተ ምን ትላለህ?"

" ልጅ ኅሊያድ እንዴት እንደምመልስልህ አላውቅም:: እዚህ ግለሰቦችን ማድነቅም መውቀስም ክልክል ነው:: በዚያ ላይ አሁን ራሴን እንደፖለቲከኛ መቁጠር ሆነ ማሰብ .

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

እንዲሁም የዲፕሎማሲ ቋንቋ መጠቀም ትችለሁ:: ባጠቃላይ ግን በተቻለኝ መጠን ያለኝን እውቀት ለኢትዮጵያ ለመስጠት ጥረት አድርጌያለሁ:: ፖለቲካ እንደምናስበው ቀላል ነገር አይደለም:: ፖለቲከኛ ስትሆን ልታሟላቸው የሚገቡ ስብህናዎች ይኖራሉ:: መዋሸት ካለብህ ትዋሻለህ! መግደል ካለብህ ትገላለህ ሆኖ አንድ ዓመት በስልጣን ላይ ስቆይ ሀሉ ነገር አልጋ ባልጋ ነበር ማለት አይቻልም ለሀገር ጥቅም ሲባል ጥሩውንም መጥፎውንም ነገር አድርጌ ሊሆን ይችላል:: እየሀ አሁን ልዋሽህ አልችልም:: ያደረኩት ነገር እንደ ፖለቲከኛነት ልክ ነው፤ እንደ ግለሰብ ሳስበው ግን ተቃራኒውን ሊሆን ይችላል:: አንዳንዴ ሁሉ ነገር ፍፁም እንዲሆን ከመፈለግ ... እኔ ያልኩት ብቻ ልክ ነው ብሎ ከማሰብ ከሚመጣ ግትርነት... ትሳሳታለህ - ወይም ስህተት ትሠራ ይሆናል ባጠቃላይ ልጅ ኀልያድ ፖለቲከኛነት ቀላል ነገር አይደለም! እንደነገርኩህ መውቀስም ማድነቅም እዚህ ክልክል ስለሆነ በዝርዝር መናገር አልችልም:: ምናልባት ሁለተኛው ቃለ መጠይቅ ላይ አስፈቅጄ እሺ ካሉኝ አብራራለሁ"

" እመሀማናለሁ አራተኛው ጥያቄዬ አሁን የምታስብበት ረጅም ሰዓት አለህና በጣም የምትበሳጭበት ነገር ምንድ ነው?"

" ጥሩ ጥያቄ ነው:: መበሳጨት ሳይሆን ቢሆኑ ደስ የሚሉኝ ሶስት ነገሮች ልንገርህ የመጀመሪያው 15 ቀናት የፈጀው የተንዛዛው የቀብር ሥነስርዓቴ ነው! በእነዚያ ቀናት ስንት መሠራት የነበረበት ሥራ ተስተጓጎለ መሰለህ! በጣም አላስፈላጊ ነገር ነበር:: በመጠኑ ያሳቀኝ ብሡ ሰዎች ቤተመንግስት የመጡት ባንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ብለው በሕይወት እጋጣሚ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከፈተውን የቤተመንግስት ግቢ ለማየትም ነበር:: በግዴታ የመጡም ነበሩ ..."

" ሁለተኛው ነገር ስልጣን አለመልቀቄ ነው:: ሁሉንም የኢትዮጵያ መሪዎችን ተመልከት ቴዲ ተገድሎ.. ለዬሚኒልክ ሞቶ ... ኃይለስላሴ ሞቶ ... መንግስቱ ተሰዶ ... እኔ ሞቼ አስበኋል? አንዳችን እንኳ ስልጣን በቃኝ ብለን ለኢትዮጵያ ህዝብ መልቀቅን በተግባር አላይተን አናውቅም! በተለይ እኔ ይህን ተግባር ፈፅሜ ቢሆን ኖሮ እርግጥ ለኔ ትርጉም ባይሰጠኝም አሁን የሚያወሩት ቱልቱላ በመጠኑ ልክ ነው እልህ ነበር ... ሶስተኛው እንደ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ምላቷከኝ ሳይሆን እንደ አንድ ግለሰብ መኖር እፈልግ ነበር፡፡ አንድ ትልቅ ምኞት ነበረኝ፡፡ ስልጣኔን ለቅቄ እንደማንኛውም ተራ ዜጋ፣ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ፣ በአገሬ ከህዝቡ ጋር ሳልቀላቀል፣ አዲስ አበባ ስታዲየውም ሚስማር ተራ ጉበኛ ከቡና ደጋፊዎች ጋር ሳልጨፍር ፣ ሲኒማ ቤት ተሰልፌ ትኬት ቆርጬ ፊልም ሳልመለከት፣ ጎንደር ሄጄ የጥምቀት በዓልን ሳልመለከት፣ ሳልመው የነበረውን ቤተመፅሐፍት ሳልከፍት፣ የጀመርኩትን ትልቅ መፅሐፍ ሳልጨርስ ... ከልጆቼ ጋር ተያይዘን በአገራችን በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ ሳንፈላሰስ መሞቴ ..."

• የመጨረሻ ጥያቄ ላንሳ በአሁኑ ሰዓት ያለው ውዝግብ ግማሹ መለስ የከፍለ ዘመኑ የኢትዮጵያ መሪ ነው ሲል ሌላው መለስ ኢትዮጵያ ላይ ፈንጂ ቀብሮ የሄደ ነው ይላል – አንተስ ይህን ጉዳይ እንዴት ትመለከተዋለህ ... በነገራችን ላይ ደቂቃ እልቋል እየተባልኩ ስለሆነ በፍጥነት መልስልኝ"

• ትልቁ ቁም ነገር ይሄ አይደለም ትልቁ ቁም ነገር እለም በስልጣኔ የትደርሳለች? ኢትዮጵያ የት ትገኛለች? የሚል ጥያቄ ማንሳት ነው፡፡ ባለ አዕምሮ የሆነ ሰው ቁጭ ብሎ ባልሆነ ነገር ላይ አያወራም ባልሆነ ነገር ላይ አይከራከርም! ቁጭ ብለው ጫት እየቃሙ፣ መጠጥ ከአቅም በላይ እየጠጡ ስለ እኔ መለስ ቢወዛገቡ ለኢትዮጵያ የሚፈይዱት ነገር የለም፡፡ ፈንጂ ተቀብሯል ካሉ ያለበትን ቦታ መፈለግ እና ማምከን ነው! ስህተት ካለ ስለ ስህተቱ ማውራት ሳይሆን ማቃናት አልያም የሚቃናበትን ዘዴ መጠቆም ነው እኔ እኮ ሰው ነበርኩኝ መላዕክ አልነበርኩም... በሌላ በኩል በቀላል ምሳሌ እኮ ብናየው የከፍለ ዘመኑ መሪ ብሆን እኮ ይህን የመሠሉ ተቃራኒ ንግግሮች አትሰማም ነበር፡፡ ህንድ ሀገር ሄደህ ማሀተማ ጋንዲ ብትል ህዝቡ ሁሉ ጣንድነት ድንቅ መሪ ይለህል እንጂ የከፍለ ዘመኑ የህንድ መሪ የሚል ጨለምተኛነት ያዘለ ንግግር አይነገርም! አሜሪካ ሄደህ አብርሃም ሊንከን ብትል ህዝቡ ሁሉ ድንቅ መሪ ነው ይልሀል እንጂ ሁለት የተቃረነ ሀሳብ አትሰማም... ሁለት ተቃራኒ ሀሳብ በኔ ዙሪያ ለምን መጣ የሚለውን በጊዜ ሂደት ታሪክ የሚፈታው ይሆናል፡፡ እስረግጬ መናገር የምፈልገው ግን የኢትዮጵያ ህዝብን ከልቤ እንደምወድ ነው! ክርክሩን ለታሪክ ባለሙያዎች

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ተውትና ወጣቶች ሆይ አባካችሁ ወሬያችሁን ቆጠብ አድርጉና ለኢትዮጵያ የሆነ ነገ ለመሥራት ጣሩ በልልኝ:: ለኢትዮጵያ የምመኝላት የስልጣን ጥማት የሌለው፣ ማስተዋል የታደለ፣ እንደ ማሀትማ ጋንዲሂ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ባንድነት የሚያወድሰውን መሪ ነው:: ስለፍቅር የሚሰብክ መሪ ፣ አስመሳይ እና ወገንተኛ ያልሆነ ... የተቀባ መሪ የኢትዮጵያ አምላክ እንዲሰጣት ነው"

" አቶ መለሰ በጣም አመሠግናለሁ! በሁለተኛው ቃለመጠይቅ አድናቂዎችህ ሆነ ተቃዋሚዎችህ የሚያነሱትን ከበድ ከበድ ያሉ ጥያቄዎችን እያነሳልን ብዙ እንጨዋወታለን! አድማጮች እያዳመጣችሁት የነበረው አፍ ሲከፈት ጭንቅላት ይታያል የተሰኘውን ፕሮግራም በFM66.6 ላይ ነበር:: ለመለስ ዜናዊ ሆነ ለሌሎቹም በከፍል ሁለት እንድጠይቅላችሁ የምትፈልጉትን ጥያቄዎች ካላችሁ ጥያቄዎቻችሁን በSMS ላኩልኝ! እናተን እያስተናገድኳችሁ የነበርኩት ኅልያድ ነበርኩ:: ሠናይ ጊዜ ይሁንላችሁ"

## የ FM66.6

መውጪያ .................................................................................................................................................................................

.........................................................................................................................................................................................................

....ነው::

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

# ክፍል

# 3

## ሰኔ 29/10/2005

## ከጠዋቱ 4፡55

መምህር ቀቁ እየተገረመ፣ እየሳቀ፣ ራሱን በጥያቄ እየወጠረም የሲልቪቪያ ሶስተኛ ድርሰት የሆነውን FM66.6 ትን ሲያነብ ሳያስበው ሌሊቱ ተጋመሰ:: ከምሽቱ 8፡45 ገደማ እንቅልፍ ወሰደው:: ጠዋት ተነስቶ ሰዓቱን ሲመለከት ከጠዋቱ 4፡55 ደቂቃ መሆኑን ሲመለከት እጅግ በጣም ደነገጠ:: የሳምንቱ ቀናት በሙሉ በቀጠሮ ተይዘዋል:: በፍጥነት ተነስቶ ታጠበ:: ቁርሱን በፍጥነት ተመገበ::

" በእውነት መግቢያና መውጫ ባይኖረውም የተለየ ሥራ ነው የሠራሽው ሲልቪ! አስቸኳይ ቀጠሮ ስላለኝ ስመለስ ስለ FM66.6 በደንብ እናወራለን:: በተለይ ክፍል ሁለትን ለማንበብ እፈልጋለሁ::" ብሏት በፍጥነት ወደ መኪናው አመራ:: ማስታወሻ ደብተሩን ተመለከተ::

- ሰኔ 29 = 6፡01 ደቂቃ ላይ ከኢትዮጵያ ጋር የሚያሳብደውን መፅሐፍ ፍለጋ...
- ሰኔ 30 = ከ4-6 ሰዓት ከውጪ የመጡ እንግዶችን አቢሲኒያ በከፍታን ማስጎብኘት ..
- ሐምሌ 1 = ከጠዋት 3፡30 - 5፡45 አቢሲኒያ ት/ቤት የተማሪዎች አቀባበል ላይ መገኘት ...
- ሐምሌ 2 = ከጠዋቱ 4፡00 ሂልተን ሆቴል ... ከዚያች ወጣት ጋር .. መገናኘት
- ሐምሌ 3 ... ሐምሌ 4...

* * *

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ከመላው ኢትዮጵያ ለተመረጡት 60 ምርጥ መምህራን ሰኔ 22 የትውውቅ እና የአቢሲኒያ በከፍታ ት/ቤት ራዕይ እና ተልዕኮ በስፋት በፕሮጀክተር በታገዘ ማብራሪያ በት/ቤቱ ከፍተኛ አስተዳደሮች እስከ ሚደረግላቸው ድረስ ሁሉም የነበራቸው ግንዛቤ አንድ ነበር:: ምንም እንኳ አቢሲኒያ በከፍታ ት/ቤት በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካም በዓለምም ጭምር እጅግ ዘመናዊ ሁሉ ነገር የተሟላለት ባለአምስት ኮከብ ***** ትቤት ቢሆንም የመማር ማስተማር ፕራቱን በጠበቀ መልኩ ከ1ኛ-12ተኛ ክፍል ያሉትን ተማሪዎች ተቀብሎ በአግባቡ በእውቀትም በኢትዮጵያዊ ወግና ስነ ስርዓት ፣ እላማ ያላቸው፣ ከሴብ የፀዱ፣ ለኢትዮጵያ ታላቅ ሠኪታ የሚሆኑ ተማሪዎችን እያዘጋጀ ለዩኒቨርሲቲ ያበቃል የሚል ግምት ነበራቸው...

ሰኔ 22 የት/ቤቱን ራዕይ እና ተልዕኮ የት/ቤቱ ከፍተኛ አመራር የሆኑት እና በባለሀብቱ አቶ አቢንኤዘር ከፍተኛ ውትወታ ከአሜሪካ እውቀታቸውን ለእናት ሀገራቸው ኢትዮጵያ ለመስጠት ወስነው የመጡት የ44 ዓመቱ ዝነኛው ዶክተር ዝናህብዙ ወርቁ መግለጫ ሲሰጣቸው ነው:: ዶክተር ዝናህብዙ በአሜሪካ እና ኢንግሊዝ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ታላቅ ክብር እና ስኬት ያላቸው ከፍተኛ ጭንቅላት ያላቸው ኢትዮጵያዊ ናቸው:: የባለሀብቱን አቢንኤዘርን የአቢሲኒያ በከፍታ ት/ቤት እቅድን ሲሰሙ ለማመን ተቸግረው ብዙ ካውጠነጠኑ በኋላ ግን በአሜሪካ እና ኢንግሊዝ ዩኒቨርሲቲ ያላቸውን ዝና.. ስኬት ...ክብር .. በወር ሳይሆን ለሁለት ሰዓት ብቻ የሚከፈላቸውን 46ሺ ዶላር 'ባፍንጫዬ ይውጣ!! ከአቢሲኒያ በከፍታ ት/ቤት ራዕይ እና ተልዕኮ ውስጥ ጠካተት መቻሌ ለኔ ትልቅ ደስታ እና የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ነው' በማለት ወሰኑ፤ በጣም አስገራሚው ነገር ግን ከባለቤታቸው እና ልጆቻቸው የመጣው አስደንጋጭ ውሳኔ ነበር:: ዶክተር ዝናህብዙ ወርቁ ታላቁን የአቢሲኒያ በከፍታ ት/ቤትን ራዕይ እና ተልዕኮ ሲነግራቸው ከባለቤታቸው ጋር ለሁለት ቀናት ከፍተኛ ክርክር ገጠሙ:: በመጨረሻ ባለቤታቸው ወ/ሮ ዝናሽ ግዛቸው ውሳኔያቸውን አሳወቁ:: 'የዘር ፣ የቋንቋ፣ የፖለቲካ፣ አንድ ፓርቲ ብቻ ለዘመናት እንደ ግል ንብረቱ በሚመራት ዲሞክራሲ በወረቀት ብቻ ያለባት ሁሌ የችግር እና የጦርነት ምሳሌ የሆነች

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ኢትዮጵያ ውስጥ አንገቴ ቢቆረጥ ተመልሼ አልሄድም!! ስለዚህ የመጨረሻ ውሳኔዬ ወይ ኢትዮጵያን ወይ እናን ምረጥ ! ሌላ ዝባዝንኬ የለም

የዶክተር ዝናህ ብዙ ወርቁ ምርጫ ኢትዮጵያ ነበር:: ኢትዮጵያን መምረጥ! ለሀገራቸው ለኢትዮጵያ ያላቸውን እውቀት መስጠት! የአቢሲኒያ በከፍታ ት/ቤትን በከፍተኛ አመራር መምራት እና የት/ቤቱን ራዕይ እና ተልዕኮ እውን ማድረግ..!! መወሰን በጣም አስቸጋሪ ቢሆንባቸውም ! መቼም ከሚስትም ከልጅም ሀገር ትበልጣለች! በማለት በመጨረሻ ወሰኑ::

ሰኔ 22 ዶክተር ዝናህብዙ ከመላው ኢትዮጵያ የተመረጡትን ምርጥ እስተማሪዎች ሲመለከቱ ሀሴት ተሰማቸው ... ት/ቤቱን እየተዘዋወሩ ሲጎበኙ ... ስለት/ቤቱ 100 % እንዳች አንኳን ሳይቀር (ሚስጢር) ሲነገራቸው ሀሴት ይበልጥ ተሰማቸው...

በተለይ ለት/ቤቱ 'የህዝብ ግንኙነት' በሚል ማዕረግ የተመረጡትን መምህር ቀቁን እና መምህር ሰለሞንን እጅግ አስቸጋሪ የነበረው ለት/ቤቱ የሚያስፈልጉትን 500 ተማሪዎችን ቢታላቅ ጥንቃቄ ቤተሰቦችን አሳምነው እና ወላጅ አልባ ታዳጊዎችን ከየህፃናት ማሳደጊያው በመምረጣቸው አደነቋቸው::

"... በሀገሬ ምድር ተመልሼ ለሀገሬ ኢትዮጵያ ያለኝን እውቀት ለመስጠት በመቻሌ የኢትዮጵያ አምላክ የተመሠገነ ይሁን:: ያለፉትን ሀያ ዓመታት በአሜሪካ እና ኢንግሊዝ የዓለማችን ዝነኛ ዩኒቨርሲቲዎች ለበርካታ ተማሪዎች እውቀቴን ሰጥቻለሁ:: በዚህ ትልቅ ደስታ ይሰማኛል! በዓለም ላይ እውቀትን ከማካፈል የበለጠ ምንም ደስ የሚል ነገር የለም! ከምንም በላይ ግን ለሀገሬ ኢትዮጵያ ያለኝን እውቀት ለመስጠት ወደ ሀገር ቤት በመመለሴ እጅግ ሀሴት ይፈጥርብኛል"

" ውድ ከመላው የኢትዮጵያ ከተሞች የተመረጣችሁ እስተማሪዎች አሁን የማወራው የአቢሲኒያ በከፍታ ት/ቤትን ራዕይ እና ተልዕኮ ነው:: ታዲያ ከዚህ በኋላ የማወራው ሁሉ ለእናንተ እስከ ዛሬ ተደብቆ የነበረውን ሚስጢር ነው:: እርግጥ አቢሲኒያ በከፍታ ት/ቤት "ት/ቤት" የሚል ስያሜ ቢሰጠውም፤ ምንም እንኳን የመጀመሪያውን የመማር ማስተማር ሂደት በሚመጣው አዲስ ዓመት 2006 መስከረም ወር የመጀመሪያ

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

ሳምንት ላይ ብንጀምርም ... የሚኖሩት ተማሪዎች ብዛት 500 ናቸው:: እነዚህ 500 ተማሪዎች መምረጥ እጅግ አስቸጋሪ የነበረ ቢሆንም የት/ቤቱ የህዝብ ግንኙነት የሆኑት መምህር ቀቁ እና መምህር ስለሞን በብቃት ስለተወጡት በዚህ አጋጣሚ በድጋሚ ላደንቃቸው እና ላመሰግናቸው እወዳለሁ:: እነዚህ 500 ተማሪዎች እድሜያቸው በሙሉ 12 ናቸው:: 300 ወንዶች እና 200 ሴቶች ናቸው:: ሁሉም አስፈላጊውን ሥነ ምግባር ያሟሉ፣ መካከለኛ እና ፈጣን ጭንቅላት ያላቸው ናቸው:: የተዘጋጀላቸውን አስቸጋሪ ፈተና 80%-100% መልሰው ያለፉ ናቸው:: እነዚህን 500 ተማሪዎች ይዘን የኢትዮጵያን ታላቅነት ለማብሰር ታላቅ ስራ ከፊታችን ባሉት ተከታታይ 12 ዓመቶች!! እንሠራለን:: በመጪው ዓመት እነዚህ ተማሪዎችን በልዩ ት/ት ማስተማር የምንጀምረው ከአምስተኛ ክፍል ነው! ስለዚህ በ2006 ት/ቤታችን ውስጥ የሚሠጠው የተለየ የ5ተኛ ክፍል ት/ት ብቻ ነው... እነዚህ ተማሪዎችን በልዩ የማስተማር ጥበብ እየመራን ከሰባት ዓመት በኋላ በ2013...12ተኛ ክፍል እናደርሳቸዋለን ... ወደ ተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ጨርሶ እንልካቸውም:: እነሱ 12ተኛ ክፍል እስከሚደርሱ ይህ ት/ቤት በ2014 ዓለም አቀፍ ጥራቱን የጠበቀ ዩኒቨርሲቲ ይሆናል:: በነገራችን ላይ ውድ መምህራን ስለ ዩኒቨርስቲዎች ከተነሳ የተወሰኑ መረጃዎችን ልንገራችሁ... በዓለማችን ላይ ምርጥ ዩኒቨርሲቲዎችን ለመገምገም የሚቀመጡ 30 ወሳኝ የመገምገሚያ መስፈርቶች አሉ:: እነዚህ እጅግ ወሳኝ መስፈርቶችን አሟልተዋል የተባሉ በዓለማችን ላይ የሚገኙ 400 ምርጥ ዩኒቨርሲቲዎች አሉ:: የሚገርማችሁ አለማችን ላይ አሉ ከተባሉት 400 ምርጥ ዩኒቨርሲቲዎች ከአፍሪካችን የ400 ሰንጠረዥ ውስጥ የገቡት ሶስት ዩኒቨርስቲዎች ብቻ ናቸው::

- በ103ተኛ ደረጃ—university of cape town (ደቡብ አፍሪካ)
- በ275ተኛ ደረጃ— university of Witwatersrand (ደቡብ አፍሪካ)
- በ 320ኛ ደረጃ— Alexandria University—(ግብፅ) አፍሪካን ያስጠሩ ስለት ዩኒቨርሲቲዎች ናቸው:: በጣም የሚገርመው ነገር ከ1ኛ-30ኛ ባለው ደረጃ ብቻ ታላቋ አሜሪካ 22 ዩኒቨርሲቲዎችን አስመዝግባለች:: ከአንድ እስከ አምስት ያሉትን ብቻ ልንገራችሁ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

1. California Institute of technology (አሜሪካ )
2. Stanford university (አሜሪካ)
3. Harvard university (አሜሪካ )
4. University oxford (ኢንግሊዝ )
5. Princeton university (አሜሪካ )

በዓለማችን ላይ ያሉትን አስር ድንቅ ዩኒቨርሲቲዎች በሚገባ ተመልክቻለሁ:: በኢትዮጵያ ውስጥ አፍሪካን ያስጠሩዋትን ሶስት ምርጥ ዩኒቨርሲቲዎችንም አይቻለሁ:: በኢትዮጵያ ውስጥ ትልቅ ነው የሚባለው እና በአፍሪካ ጭምር የመጀመሪያ የሆነው ታሪኩ ዩኒቨርሲቲ የሆነው ግእዝስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንኳን ከ400ዎቹ የዓለማችን ዩኒቨርስቲዎች መደዳ ሲጠቀስ ቁርቶ ከተቀመጡት 30 ወሳኝ መስፈርቶች የሚያሟላው እጅግ በጣም ጥቂቶቹን ብቻ ነው:: ለማንኛውም ልነግራችሁ የምፈልገው የአቢሲኒያ በከፍታ ከ2017-2028 ዓ.ም ከትልቁ ራዕይ እና ተልዕኮ ውስጥ አንደኛው "አቢሲኒያ በከፍታ ዩኒቨርሲቲ" የሚለውን ስም ከዓለማችን 400 ምርጥ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ እንዲካተት ማድረግ ነው:: በዚህ አጋጣሚ የዓለማችን ምርጥ 10 ዩኒቨርሲቲዎች ዙሪያ የሚያውጠነጥን የዶክመንተሪ ፊልም አለኝ፤ አንድ ቀን ሰብሰብ ብለን በህብረት በት/ቤታችን ዘመናዊ ፊልም ማሳያ ውስጥ እናየዋለን በጣም ዘና ትሉበታላችሁ _ ለማንኛውም የዚህ ት/ቤት ራዕይ ከዚህ ት/ቤት ውስጥ ምርጥ ደራሲያን ፣ ምርጥ ጋዜጠኞች፤ ምርጥ መምህራን ፣ ምርጥ የጥበብ ሰዎች ፣... ከሁሉም በተለይ ምርጥ አምስት ጠቅላይ ሚኒስትሮችን እና 45 ታላላቅ የፖለቲካ ሰዎችን ማብቃት ነው!! በዚህ መሠረት ለሚቀጥሉት 12ዓመቶች ወይም ባጠቃላይ እስከ ምርቃታቸው2017 ድረስ ይህ ት/ቤት ከእነዚህ ተማሪዎች ውጪ አንድም ተማሪ አይቀበልም... የመጀመሪያው ትልቅ ስኬት በ2017 ሲጠናቀቅ በድጋሚ ሌሎች 500 ተማሪዎችን ለሁለተኛው ዙር ታላቅ ሀገራዊ ስልጠና ይመርጣል..."

ዶክተር ዝናህ ብዙ ወርቁ አሰልቺ ያልሆነ ባቢ ንግግራቸውን ለመምህራን አቀረቡ:: ዝርዝር አስፈላጊ ነገሮችን አስረዱ...ንግግራቸውን ሲጨርሱ መላው ምርጥ መምህራን ከወንበራቸው ተነስተው በአድናቆት አጨበጨቡ:: ከሁሉም ያስገረማቸው የመጨረሻው የዶክተር ዝናህብዙ ወርቁ ንግግር ነው::

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

"... እንግዲህ ስኬታማ ለመሆን ብዙ መስራት አለብን:: እኛ ሀገር ትልቁ ችግር ትንሽ ነገር ሠርተን የሠማይ ያክል እጋነን ማውራት ነው! እኛ ት/ቤት ይህ ነገር አይደገምም!! የእናንተን የሙያ ብቃት ለመጨመር በየሰስት ወሩ የተለየ ስልጠና በታላላቅ ምሁራን እንግሊዝ፣ አሜሪካ፣ ፈረንሳይ፣ እና ጃፓን ድረስ እየሄዳችሁ እጅግ ወሳኝ የሆኑ ስልጠናዎችን ትወስዳላችሁ! ሁልጊዜም ሁላችሁም በለውጥ መስመር ውስጥ ናችሁ! ከእናንተ በተጨማሪ ለዚህ የት/ቤቱ ታላቅ ራዕይ እና ተልዕኮ ስኬታማ መሆን በሚቀጥሉት 12 ዓመታት

ከሀገር ውስጥም ከውጪ ሀገራትም ለተማሪዎቻችን ስኬታማ ለመሆን እውቀታቸውን ፣ ልምዳቸውን፣ ምክራቸውን፣ ሀሳባቸውን... የሚሰጡልን በሁሉም የሥራ እና የእውቀት መስክ ያሉ 1444 ባለሙያዎችን እንጠቀማለን! በተረፈ በእጃችሁ ላይ የደረሱትን የአቢሲኒያ በከፍታ ት/ቤት ልዩ ተልዕኮ የሚለውን መፅሔት አንብቡ ፤ ፤ታዲያ በጣም የማስጠንቀቃችሁ ነገር ይህን የት/ቤቱን ሰስተኛ ከፍተኛ ሚስጢር የያዘ መፅሔት ሁለተኛ ወገን እጅ ላይ እንዳይገባ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረጋችሁን እንዳትረሱ!! ምሳ ከበላን በኋላ የቃለ መሀላ ስነ ሥርዓት በዋናው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ሰላለን ልክ 8:30 ደቂቃ ሲል እንገናኛለን:: በጣም አመሠግናለሁ:: እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርካት! እኛንም ይባርከን!! መልካም ምሳ ይሁንላችሁ!!"

* * *

በእርግጥ ሁሉም በጣም ተደስተዋል:: እንደ መምህርት ኢትዮጵያ የተደሰተ ግን የለም:: ከዚህ ታላቅ ራዕይ እና ተልዕኮ ካለው ት/ቤት ለመስራት በመቻሏ እጅግ ተደስታለች:: ማታ ባለቤቷ ስለ ት/ቤቱ ሲጠይቃት መንገር ያለባትን ብቻ ነገረችው እንጂ ስለ አቢሲኒያ በከፍታ ራዕይ እና ተልዕኮ እንዳች የነገረችው ፤ ሹክ ያለችው ነገር የለም! የገባችውን ቃል ኪዳን ለመጠበቅ 100% ወስናለች:: አሁንም ስለ አቢሲኒያ በከፍታ ት/ቤት ተልዕኮ እና ስለወደፊቷ ኢትዮጵያ እያሰበች ተቀምጣለች:: ብዙም ሳትቀመጥ በሰዓቱ መምህር ቀፀ በፈገግታ ተሞልቶ መጣ:: እየተሳሳቁ ምሳቸውን ተመገቡ:: ልክ ሰባት ሲሆን ቀጠሮዋቸውን በማክበር ወደ ወመሽ የመፅሐፍ መደብር አመሩ:: ብዙም ሳይቸገሩ የወመሽ መፅሐፍ መሸጫ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

መደብር ጋር ደረሱ:: ከመኪናቸው ወርደው መፅሐፍ ቤቱ ጋር ሲደርሱ በተለይ ኢትዮጵያ ደነገጠች:: ወመሽ በፈገግታ ተሞልቶ መፅሐፍ ቤቱ በራፍ ላይ ተቀምጧል:: መፅሐፍ ቤቱ ላይ ግን ኢትዮጵያ ያነበበችው ነገር አስገረማት "ታሽጓል" የሚል ጽሁፍ ተለጥፏል:: ኢትዮጵያ ግራ እንደተጋባች ወመሽን እና መምህር ቀቁን አስተዋወቀቻቸው... ሠላምታ ተለዋወጡ:: በፍጥነት "ይህ ፅሁፍ ምንድ ነው?" አለችው::

"ምን ባክሽ ትላንት ጠዋት አሸጉብኝ" አለ ወመሽ ብዙም ሳይጨናነቅ::

"ምን ተፈጠረ?"

"በዚው የሱቁ ቀለም የተነሳ"

መምህር ቀቁ የ፦ ወመሽን እና የኢትዮጵያን ንግግርን በዝምታ ይከታተላል፤ ያዳምጣል...

"አልገባኝም"

"ያው እንደምታውቂው እና እንደምታይው የዚህ መፅሐፍ ቤት ቀለም የኢትዮጵያ ባንዲራን ቀለም የያዘ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ቀለማትን በመጠቀም የተቀባ ነው:: እነሱ የሚሉት 'አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ቀለም መቀባት መብትህ ነው፤ ነገር ግን መሀከሉ ላይ የኮከብ ምልክቱን ካላስገባህ መብትህ አይደለም ስለዚህ በሶስት ቀናት ውስጥ ኮከብ መሀከሉ ላይ ጨምር' አሉኝ:: እንዚ አልኳቸው አሸጉት! የቀበሌው ዋና አስተዳደር ጋር ይግባኝ ብያለሁ:: ሐምሌ 4 ቀጠሮ አለኝ:: ስለዚህ ያ መፅሐፍም ያለው ውስጥ ነው:: ስለዚህ እስከ ሐምሌ 4 ታገሱኝ:: ጉዳዩ በሠላም ባያልቅ ራሱ በምናቃት የድብቅ በር ገብቼ አውጥቼ እሰጣቹኋለሁ፤ ለዛሬው በቃሌ ባለመገኘቴ በጣም ይቅርታ"

መምህር ቀቁ እና ኢትዮጵያ ከወመሽ ጋር ለተወሰኑ ደቂቃዎች አውርተው የሚያሳብደውን መፅሐፍ ወመሽ በእርግጠኝነት ለመምህር ቀቁ በ13,000 ሺ ብር ለመሸጥ ወስኖ ተለያዩ:: መምህር ቀቁ ኢትዮጵያን ቤቷ ካደረሳት በኋላ በቀጥታ ወደ አቢሲኒያ በከፍታ ት/ቤት መኪናዋን አሽከረከራት:: ከመኪናው ውስጥ የዝነኛው Don Williams ሙዚቃ እየተንቆረቆረ ነው...

... Don't you believe I've tried long enough

Don't you just believe it's time

Don't you believe I've gone far enough

Don't you just believe it's time...

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

# ክፍል 4

## ሐምሌ 2/11/2005
## ሂልተን ሆቴል

መምህር ቀቁ ከማርያ ዜና በስተቀር ያሰባቸው ነገሮች ሁሉ እልጋ ባልጋ እየሆኑለት ስለሆነ ደስታው ጨምሯል:: ጳጉሜ ሁለት ከጠዋቱ 4-6 ሰዓት ለት/ቤቱ ስኬት ከፍተኛ እርዳታ ያደረጉ እና ለማድረግ ቃል የገቡ እንግዶችን አቢሲኒያ በከፍታ ት/ቤትን በሚገባ ከመምህር ሰለሞን ጋር አስጎበኙ... ሁሉም በሚገባ ተደስተው ነበር :: ጳጉሜ ሶስት ከጠዋቱ 3፡30-5፡45 ደቂቃ ለ500ዎቹ የተመረጡ ተማሪዎች ሞቅ ደመቅ ያለ የአቀባበል ስነስርዓት እና የመኝታ ቤታቸው ቁልፍ ተሰጣቸው ... ከሞግዚቶች ጋር ተዋወቁ... ስለሚጠበቅባቸው ህግና ደንብ መጠነኛ ማብራሪያ ተደረገላቸው:: ለአስር ተማሪዎች የተመደቡት ሁለት ሁሉን ነገር የሚከታተሉ ሞግዚቶች ናቸው... መምህር ቀቁ ሁሉ ነገር እንዳሰበው ሳይሆን እጅግ ካሰበው በላይ እየተሳካለት ስለመጣ እጅግ ደስታው ጨምሯል:: ምሽት ብቻውን ሲሆን ሶስት ወራት ሙሉ ድምጽዋ የጠፋውን ፍቅረኛውን ማርያን ሲያስብ ደግሞ በመጠኑ ይጨነቃል... እሷንም እንደ እየሩሳሌም ፤ እንደ ሱዛን ... አጣት ይሆን እያለ በውስጡ ያብሰለስላል... ይህን ጭንቀቱን ግን ለማንም ሰው አልተነፈሰም ፤ ደስተኛ መስሎ ለመታየት ብቻ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል::

ስለ ማሪያ እያውጠነጠነ በተቀጠረበት ሰዓት 4፡00 ሲል ሂልተን ሆቴል ደረሰ:: ለመኪናው ምቹ ቦታ ፈልጎ ካቆመ በኋላ ብዙም ሳይቸገር የመዋኛ ስፍራው ጋር የቀጠረችውን አስደማሚ ውበት ያላትን ወጣት ተመለከታት:: በፈገግታ ተሞልታ ከተቀመጠችበት በመነሳት ተቀበለችው::

" ዳግም ስለተገናኘን በጣም ተደስቻለሁ፤ ከምንም በላይ ደግሞ ያሰብከው የተለየ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ትንቢት ስኬታማ ስለሆንልህ በእውነት ከልቤ በጣም ተደስቻለሁ:: በቀደም እንደጠፋሁብህ ገብቶኛል:: በጣም ተለውጫለሁ! ማከዳ ሰለሞን ነኝ"

"እንዴ?" በማለት መምህር ቀቄ ስለዘነጋት እያዘነ ከተቀመጠበት ተነስቶ አቅፎ ሳማት:: ትንቢተኛዋን ማከዳ ሰለሞንን::

"በእውነት በጣም ይቅርታ አንቺን ጨርሶ መዘንጋት አልነበረብኝም ግን እውነቱን ለመናገር በጣም ተለውጠሻል:: ለዚያ ነው የጠፋሽብኝ! አ! በእውነት እኔም ዳግም ስለተገናኘን እጅግ በጣም ተደስቻለሁ"

"እኔም ደስ ብሎኛል"

ትንቢተኛዋ ወጣት እና መምህር ቀቄ ብዙ ነገር ተጨዋወቱ:: መረጃ ተለዋወጡ:: የማከዳ ሰለሞን ሕይወት በአሁኑ ሰዓት በመልካም ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አስረዳችው:: በመጨረሻ ወደ ዋናው ቁም ነገር ገባች::

" ወረቀቱ ደረሰህ? በሚገባ ፈታኸው?"

" ደርሶኛል... ትንሽ አስቸጋሪ ነው::"

አንቺ ያልሽው 17 ትንቢቶች እንዳሉበት ነው:: እኔ ለማግኘት የቻልኩት አስር ትንቢቶችን ነው:: በዚያ ላይ የመለስ ዜናዊ የስልጣን ቆይታ አማርኛ አስተማሪው 29 ዓመት አለኝ ስልሽ ትልቅ ስህተት እንደሆነ ተናግረሽ ነበር:: ያንቺ የትንቢት ወረቀት ላይ ያለውን ስንፈታው ደግሞ ያገኘሁት 25ዓመት ይላል... ነብሳቸውን ይማርና አቶ መለስ ዜናዊ ደግሞ የሞቱት በ21 ዓመት የስልጣን ቆይታ ነው:: በዚህ መሠረት ያንቺም ትንቢት ልክ አይደለም ማለት ነው!! በዚያ ላይ ከመለስ በኋላ የስልጣን ወንበሩን የተቀበሉት አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ናቸው:: በእርግጥ ኃይለማርያም የሚል ስም አባት ባይኖረውም በስንት ጥረት አግንቼያለሁ:: የሌሎች ስድስት መሪዎችንም ሙሉ ስም ፤ በስልጣን ላይ የሚቆዩበትን ዘመን ብዛት፣ ወዘተም አግኝቼያለሁ:: ነገር ግን ማን ከማን ቀጥሎ እንደሚመጣ በግልፅ የሰጠኝ ወረቀት አያብራራም እንዴት አየሽው?"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

... ቀጥሎ ያለውን ማብራሪያ ከማንበብዎ በፊት ደብልጥ ግልፅ እንዲሆንሎት ከአቶ መለስ ዜናዊ ሞት በፊት ለህትመት የበቃውን ኢያሪኮ 777 ገጽ 146 (በ2004 ጥቅምት) በተለይ ኢያሪኮ 888 ገፅ 170-172 ያለውን ይመልከቱ ........

" በመጀመሪያ አንድ የሀገር ትንቢትን የያዘ ወረቀት እንደዚሁ በቀላሉ መፍታት ከተቻለማ ተራ ነገር ይሆናል፤ በዚያ ላይ እኔ እጅግ በጣም በጥንቃቄ ስለሞላሁት እናተም በጥንቃቄ እና በትዕግስት ብትፈቱት ትንቢቱ ልክ ነው:: ትልቅ ችግር የፈጠረባችሁ የትንቢት መንሻ ቁልፉ ዐ/ ነገሩን አለማግኘታችሁ ነው:: በዚያ ላይ እኔ የተጠቀምኩት የአማርኛ የፊደል ገበታ ሁሉንም ድምፆችን የያዘውን እንጂ ዲቃላ ፊደላትን የሚዘል፣ ሞክሼ ፊደላትን የሚዘል ከሆነ የሚመጣው ውጤት የተሳሳተ ነው:: ሀለሐመሠረሰ.. ፐፀ የሚለውን የፊደል ገበታ ከተጠቀማችሁ ውጤቱ ልክ ነው:: እኔ እኮ ያኔም ቢሆን 29 ዓመት የአማርኛ አስተማሪህ አሉኝ ስትለኝ ልክ አይደሉም ብያለሁ:: አንተ እና ሰለሞን ያገኛችሁት "25" የሚል ከሆነ አራቱን ዓመት የሚገዛው አሁን እንደምናየው በመንፈስ ይሆናል ማለት ነው:: ምክንያቱም አንድ አገር የቀድሞዋን መሪ ራዕይ ብቻ ያለ አንዳች ለውጥ እንከተላለን ካሉት በእርግጥም ያመሪ በተዘዋዋሪ አሁንም በስልጣን ላይ ነው ማለት ይሆናል:: ይህን ለቀልድ አልኩህ እንጂ አውነታውን እንመልከት ... ምናልባት ያኔ በችኮላ ስፅፍ ተሳስቼ ካልሆነ እርግጠኛ ነኝ 17ቱ ትንቢቶች ልክ ናቸው፤ ለማንኛውም እስቲ አብረን እንፍታው" በማለት ይዞ የነበረውን ወረቀት ጠረጴዛው ላይ ዘረጋቸው:: መምህር ቀቁ ወጣቷን ውብ ማከዳ ሰለሞንን በትኩረት ይከታተላት ገባ::

" ተመልከት የትንቢት መፍቻ መስመሮቹን ወደጎን ... ወደታች ... ወይም Horizontal line...vertical line ... including diagonal line ... በትኩረት

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

... ልዩ ምልክት የተደረገበት ነው ... እስቲ
ለይተን እንፍታው 29/29/230/204/20/46/326/314/45/ = ይህን ቁጥር የእንትሪክስ (*) ምልክት ያለበትን ትተን በጥንቃቄ በፊደላት እናስቀምጠው ... ተመልከት... በዚህ መሠረት

2929 = 2929

230 = የ

204 = ዓ


20 = ለ

46 = ም

326= ፍ

314= ጿ

45 = ሜ ... በዚህ መሰረት ያው እንደሰማነው ፈረንጆቹ የዓለም ማብቂያ በ2012 ነው እያሉ ሲቀባጥሩ ነበር:: የዓለም ማብቂያ ግን በ 2929 ይሆናል ማለት ነው:: ገና በጣም ብዙ ዘመናት ይቀራል... ይህን የመፍቻ ዐ/ነገር ይዘን እስቲ አንተ ተሳስቷል ያልከውን የአቶ መለስን ጉዳይ እንመልከት ምን ግዜም ከመፍቻ ዐ/ነገሩ አራት ወደ ላይ አልያም አራት ወደታች ስትጓዝ




t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

(+4 አልያም-4) የመፍቻ ዘዴው ነው:: ይህን ሰለሞን ሳይነግርህ አይቀርም:: ይህን ዘዴ ካልተጠቀማችሁ በዚህ የተነሳ ልዩነት ሊመጣም ይችላል:: ለማንኛውም አራት ወደታች ስንጓዝ ያለው ቁጥር የሚከተለው ነው::

40/20/76/215/144/193/25*/100/24/= ይህን ቁጥር አስቲ በፊደል እንተካው

40 = መ

20 = ለ

76 = ሰ

215= ዜ

144 = ና

193= ዊ

25* = 25

100 = ሰ

24 = ል

አየህ የተሸወዳችሁትን "25*" ከመፍቻ ዐ/ነገሩ ወይም የአቶ መለስ ስም ያለበት ሰንጠረዥ ከመፍቻው ስንት መስመር ይርቃል? እንቁጠረው 1 ...2...3...4 መስመር ወደታች ይርቃል ... በዚህ መሰረት (25* "4" መስመር ) = 25-4 መስመር = 21 ዓመት ! ታዲያ ምን ላይ ነው የተሳሳትኩት መምህር ቀቁ? በዚህ ምሳሌ 17ቱን ትንቢቶች በጥንቃቄ ስራቸው ሲሆን ወደ ዲያጎናል ከሆነ ግን ምንም ነገር ለውጥ አይደረግበትም !! በተረፈ 17ቱን ትንቢቶች ስትጓዝ ( + or -) የሚለውን በቀላሉ ለማግኘት ቀላሉ ዘዴ ሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ቁጥሮች ሁሉ በፊደል መተካት ... ማስታወስ ያለብህ ከመፍቻ መስመሩ ወደታች ወይም ወደላይ ከዚያ አያጋጠሙ ማንበብ ነው"

" አ! በጣም ነው የማመሠግነው ሌላውን ሰኔ ተይው እኔ ቤቴ እመራመርበታለሁ! በእርግጠኝነት ግን ሰለሞን ይህን ህግ አልነገረኝም:: አሁንም ግልፅ ያልሆነልኝ ቅደም ተከተሉን እንዴት አውቃለሁ? ማን ከማን ቀጥሎ እንደሚመጣ"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

" በአጭሩ የስልጣን ዘመናቸው እያነሰ ይመጣል ... በጣም ትልቅ ዘመን የሚገዛው መጨረሻ ላይ ይሆናል ሌላ ጥያቄ አለህ?"

" ይበቃኛል! እንዳልሽው ትንቢቱን ለመፍታት እኔ መልፋት አለብኝ በቀላሉ ከነገርሽኝ እንደተራ ነገር እንዳልቆጥረው ወደ አንቺ የግል ጥያቄ ላምራ"

" በመጠኑ ይቻላል"

" አሁን ሕይወት እንዴት ናት?"

" እንደነገርኩህ ነው:: የተወሰነ ጊዜ እሰቃያለሁ ከዚያ ችግሬ ሁሉ ተቀርፎ ሁሉ ነገር ይስተካከላል:: ስለ እኔ ምንም እንዳትጨነቅ"

" የአንቺና የሰለሞን ጉዳይስ?"

" ያው በፊት እንደነገርኩህ በ40 ዓመቴ እሞታለሁ:: ከመሞቴ በፊት የተወሰኑ የደስታ ዘመናትን ከሰለሞን ጋር እኖራለሁ:: ይህ ከመሆኑ በፊት ግን እንደነገርኩህ ሰለሞን ሚስት ይገባል:: አምስት ዓመት በሠላም ኖረው ልነግርህ በማልችለው ወይም በማልፈልገው ችግር ይለያያሉ:: ከዚያ በኋላ ነው እኔ በሰለሞን ሕይወት ውስጥ የምመጣው"

" ይህን ነገር ቀድመን ካወቅነው እንዳይሆን ማድረግ አይቻልም"

" በተዓምር"

" ያሳዝናል"

" ለሁሉም ጊዜ አለው:: በዚያ ላይ መሆን ያለበት ሁሉ መሆን ካለበት የፈለገውን ያህል ብትዘል ለማስቆም አይቻልም! ይልቅ ትላንት አቢሲኒያ ት/ቤትን በተመለከተ ሁለት ነገር አይቻለሁ:: አንዱ ጥሩ ዜና ነው አንዱ መጥሮ ዜና ነው:: ለማንም የማትናገር ከሆነ እነግርሀለሁ"

" አትጠራጠሪ"

" ስቀልድህ ነው እንጂ አምንሀለሁ:: በመጀመሪያ ይህን ት/ቤት መንግስት በስውር እንተንም ሆነ ት/ቤቱን ስለሚከታተል እንዳች የሚፈጠር ነገር ስለሌለ ምንም ነገር እንዳትጨናነቅ! እልፎ እልፎ አንተንም ስትንቀሳቀስ ስለሚከታተሉ እንዳትወዘገብ:: የምባይል

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ስልከህን ስለሚጠልፉት የምታወራው ሆነ TEXT ከጻፍከ በኮድ አድርገው ወይም ዉርስ አትጠቀም:: ጥሩ ዜናው በእርግጠኝነት የአቢሲኒያ ት/ቤት ራዕይ እና ተልዕኮ እናንተ ከምታስቡት በላይ ስኬታማ ይሆናል! የአቢሲኒያ በከፍታ ት/ቤት ተማሪዎች ኢትዮጵያን በታላቅ ከፍታ ላይ ያስቀምጡዋታል!! የኢትዮጵያ የስኬት እና የሀያልነት ዘመን ፊጣ እንዲሆን ያደርጋሉ.. በጣም ጥሩ ያልሆነ ዜናው በአቢሲኒያ በከፍታ አንድ መምህር በገዛዘ ታውሮ አልያም ማደንዘዣ ተደርጎበት በግብፆች እና በኢትዮጵያዊያን ራሳቸው በስልጣን ፍለጋ የት/ቤቱ ራዕይ እንዳይሳካ በሰኔ28,2014 የአቢሲኒያ ት/ቤት በከፍታ ወደ ዩኒቨርሲቲ መለወጥ ብስራት እና አስረኛ ዓመት ክብረ በዓል ላይ ትልቅ ውድመት ለማድረስ ፈንጂ ታጥቆው ት/ቤቱ ውስጥ በመግባት ታላቅ ውድመት ሊያደርስ ያቅዳል:: ስለዚህ ት/ቤቱን ለመታደግ ትልቅ ውሳኔ ሰኔ 27,2014 ላይ አንድ ቀን ሲቀረው ማድረግ አለባችሁ ማለት ነው"

መምህር ቀቁ እውነት የሆነ ያህል ደነገጠ ...በትኩረት ትንቢተኛዋን ማክዳ ሰለሞን እየተመለከተ...

" ምንድነው የሚደረገው?"

" ማንንም ሳይሰማ አንተ እና ዶ/ር ዝናህ ብዙ ወርቁ መምህሩን ለፖሊስ አሳልፎ መስጠት መሰል ነገር ሳታስቡ... ምክኒያቱም በመጠኑ የተወሰኑ የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት እጃቸው ስላለበት ለውጥ ስለሌለው መግደል አለባችሁ! ካልሞተ ብዙ መረጃ ያሾልከባቹኋል"

" ምን ... መግደል!? እየቀለድሽ መሆን አለበት ማክዳ?"

" በኔ ሕይወት ውስጥ ለቀልድ የሚሆን ቦታ የለም:: እርግጥ ነገሩ አስቸጋሪ ነው! የሰው ሕይወት ማጥፋትን የሚያክል አስቸጋሪ ነገር የለም:: እናንተ ግን ይህን ሰው የምትገድሉት ለተራ ጥቅም ሳይሆን ለኢትዮጵያ ብላችሁ ነው! 500 ድንቅ ጭንቅላት ያላቸውን ተማሪዎች ለመታደግ ነው:: ይህን የመምረጥ ጉዳይ የሁለታችሁ ነው... ለማንኛውም ሰው "ይድነቃቸው ፈይሳ ዛይ" ይባላል:: ት/ቤቱ ውስጥ የሚቀጠረው ግን በሌላ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ም ነው! ስለዚህ ከ2010 በኋላ የምትቀጥሩዋቸውን አስተማሪዎች እጅግ በጣም ማሰለል አለባችሁ:: ለነገሩ ነገሩን በስለላ ሰዎች ቀድሞ የሚሰሙት ዶክተር ዝናህብዙ ወርቁ ናቸው"

መምህር ቀቄ በዝምታ ብዙ ቆየ:: በመጨረሻ ትንቢተኛዋን ወጣት እየተመለከተ "ያልገባኝ ነገር እሺ...ይህን ሰውዬ አስቀድመን ካወቅነው እና ከገደልነው ችግሩ ይቀረፋል! ታዲያ ለምን የሰለሞንን ጉዳይ አስቀድመን ካወቅን ቀድመን አናስተካከለውም?"

" በዓለማችን ላይ ብዙ ሚስጢሮች አሉ!! ለማንኛውም ስለነበረን ጊዜ በጣም አመሰግናለሁ:: ስለተገናኘንም በጣም ተደስቻለሁ! ዳግም መገናኘት ሲኖርብን እንገናኛለን! ስለመንከኝ በጣም አመሰግናለሁ:: ያወራነውን ነገር ሁሉ የነገርኩህ ሚስጢር እንደምትጠብቅ ስለተማመንኩብህ ነው"

ትንቢተኛዋ ወጣት ማከዳ ሰለሞን ሰዓቷ በፍጥነት ተመለከተች:: በፈገግታ ተሞልታ ተነሳች::

"ትንሽ አትቆይም"

" ይበቃኛል"

" እሺ መኪና ስለያዝኩ የት ላድርስሽ?"

" በጭራሽ! ብቻዬን ነው የምሄደው"

*　　*　　*

በሞቀ ምስጋና ተለያዩ:: መምህር ቀቄ በገረሜታ ከነበረበት ወንበር ላይ ተቀምጦ ያውጠነጥን ገባ:: በተለይ በሕይወቱ የሰው ልጅ ሕይወት ሊጠፋ እንደሚችል ሲያስብ ዘገነነው ... 'እውነቷን ነው ... ስሁሉም ጊዜ አለው ብላ የለ?... እስቲ ጊዜው ይድረስና ሁሉንም ጊዜው ይፈታዋል...'

መምህር ቀቄ ከራሱ ጋር እያወራ በመሀከል ሲልቪያ ትዝ አለችውና ሥራ ከሌላት ሂልተን ነኝ ነይ ሊላት ለመደወል ሞባይሉን ከኪሱ ሲያወጣ ሲዘጋጅ ... አንድ የሆቴሉ ወጣት አስተናጋጅ እየተምዘገዘገ መምህር ቀቄ ያለበት ቦታ መጥቶ የታጠፈች ወረቀት ዘረጋለት::

" እዚህ ጋር ተቀምጣ የነበረችው ወጣት ናት ስጠው ያለችኝ"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

" አመሰግናለሁ" ብሎ ተቀበለው:: ምባይሉን አስቀመጠውና የታጠፈችውን ወረቀት ገለጣት::

' ይህ ዛሬ ጠዋት

ያየሁት ትንቢት

ልክ ከሆነ ሌሎቹም

የነገርኩህ ትንቢቶች

ልክ ናቸው ማለት ነው ...!

ፍቅረኛህ ማርያ በኢጣሊያ

እስር ቤት ውስጥ ናት ... አደራ

ለማንም እንዳትናገር ... ሁሉንም

ጊዜ ይፈታዋል'

መምህር ቀቁ በጣም ገረመው:: ' ትንቢተኛዋ ወጣት ስለማርያ የምታውቅበት አንዳች መንገድ የለም ... እስር ቤት ?? እስር ቤት ምን ሆና ይሆን ... ጥያቄ እንዳላነሳባት ነው በወረቀት የላከችልኝ? ወይ ጉድ ' ከራሱ ጋር እያወራ ወረቀቷን ኪሱ ውስጥ ከተታት ' ቃል ቃል ነው! ለማንም አልናገርም ለነገሩ አቶ አቤን ኤዘር ኢጣሊያ ለመሄድ ወስነዋል... ስለዚህ ሁሉ ነገር ያኔ ይታወቃል? እንዴ ማርያን ከልቤ አልወዳትም ማለት ነው? ለምን ውስጤ አልተጨናነቀም ... ለምን በጣም አልደነገጥኩም ... ወይስ በሠላም እንደምትመጣ ስድስተኛ ስሜቴ ነግሮኝ ነው...'

"መምህር ቀቁን ከሀሳብ የገታው የሞባይሉ ጥሪ ነው:: አነሳው :: ሲልቪያ ናት::

" ልደውልልሽ እያሰብኩ"

" ቀጠሮህን ጨረስክ"

" ብቻዬን ነኝ"

" ሠላማዊ ቀጠሮ ነበር?"

" ሠላማዊ ነው"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

"እኔማ የምስራች ልነግርህ ነው የደወልኩት"

"ምስር እንብላ ምን ተገኘ ባክሽ?"

"መጀመሪያ ምሳ ለመጋበዝ ከዚያ ፊልም ልናይ ምሽት እኛ ቤት ለማደር ቃል ግባ"

"ግድ ነው እንጂ ስለ FM66.6 መቼ አወራን ... ቃል"

"ከኢጣሊያ ኤምባሲ አሁን ለባቢ ተደውሎለት እንደ ነበር ደውሎ ነገረኝ፤ በጣም በፍጥነት ወደ ኢጣሊያ ማምራት አለበት ... ማርያ እስር ቤት ናት ... ለማንኛውም ጠብቀኝ ለመጣ በሰፋት እናወራለን ... ማወቅ ያለብህ ግን ማርያ ሙሉ ለሙሉ ደህና ነች"

"የት ነው ያለሽው መጥቼ ልውሰድሽ"

"አትጨነቅ! እኔ ራሴ በፍጥነት እየመጣሁ ነው:: እስከዛሬ መልካም ጊዜ ይሁንልህ"

"ላንቺም መልካም ጊዜ"

መምህር ቀቁ በጣም በረጅሙ ተነፈሰ ... ኪሱ ውስጥ ያስቀመጣትን ወረቀት አውጥቶ አነበባትና ቀዶ ጣላት ... በትንቢተኛዋ ወጣት ማከዳ ስለምን ተገረመ:: ራሱን በጥያቄ ወጠረም::

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

# ክፍል 5

## ሐምሌ 4/11/2005
## ኢጣሊያ- ከምሽቱ 2፡30 ደቂቃ

አጅግ ግዙፍ የሆነው እስር ቤት የሚገኘው ኢጣሊያ እለኝ ብላ ከምትመካባቸው ዩኒቨርሲቲዎቿ ውስጥ በኢጣሊያ የዩኒቨርሲቲ ደረጃ 5ተኛ ደረጃ የተሰጠው እና በ1343 ዓ.ም የተመሠረተው universita degli studi di pisa, Lungarno pacinotti, 43 pisa የሚገኘው 500 ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ አጅግ ዘመናዊው ልዩ እስር ቤት "ናዚዎች ጨካኝ ናቸው በእርግጠኝነት ግን ጭካኔን የተማሩት ከኢጣሊያ እስር ቤቶች በተለይ በ 1406 ከተመሠረተው D.K 1406 እስር ቤት ውስጥ ነው" ይላሉ፡፡ በዓለማችን ላይ ከሚገኙት እስር ቤቶች ውስጥ ከፍተኛ ጭካኔ የተሞላበት በሚል መስፈርት D.K 1406 ግንባር ቀደሙ ነው .. በተለይ ከ1939-1945 የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅቶች እስር ቤቱ ውስጥ የገባ ማንኛውም ተጠርጣሪ ሆነ ወንጀለኛ መጫወቻ ነበር...

ወንድ እስረኞች ይደፈራሉ ... እርስ በርሳቸው ግብረሰዶም እንዲፈጽሙ ይታዘዛሉ .. በረዶ ላይ ይተኛሉ .. ግውላ ላይ በርከት ያሉ መርፌዎች ይሰኩና በቂጣቸው እንዲቀመጡበት ይታዘዛሉ ... ስለት ባለው ነገር ሰውነታቸው ይቆራረጣል ... የራሳቸውን ዓይነ ምድር እንዲበሉ .. ሽንታቸውን እንዲጠጡ ይደረጉ ነበር .. በተለይ በሴቶች ላይ የሚደርሰውን በደል ለመግለፅ በጣም ያስፈራል ... ቁጥራቸው አስራ ሁለት በሚደርሱ ሰዎች ይደፈራሉ .. ፀጉር መላጨት .. ጡት መቁረጥ .. የእጅና የእግር ጥፍር መንቀል .. ጥርስ ማውለቅ ... ብልታቸው ውስጥ ብረታ ብረት ማስገባት .. አንድ አይናቸውን ማውጣት .. ጤነኛ ኩላሊት ካላቸው አውጥቶ መሸጥ ... የመሰሉት በመጠኑ ይጠቀሳሉ ...ለዚያውም እነዚህ ቀላል የሚባሉ ድርጊቶች ናቸው .. ሰዎች ሲሞቱ ይጠበሳሉ ... ታሳሪዎች ካልበሉ ራሳቸው ይጠበሳሉ .. ብቻ ይቅር ...

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ዘግናኝ ነውና...

ረጅም እድሜ ለዓለም እቀፍ የሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች ይግባና ... በስንት ክርክር ከ1999 ወዲህ በእስር ቤቱ መጠነኛ ለውጥ እየመጣ ነው... እጅግ ብዙዎች በዚህ ንዝበ ቢላ" በተሰኘ አሰቃቂ ድርጊት የሚፈፀምበት እስር ቤት ውስጥ ታስረዋል ... ሞተዋል .. እንግሊዞች .. አሜሪካ... ራሺያ ... ማሊ ... ኬኒያ ... ብራዚል... ብቻ በደፈናው ይህን ግዙፍ እስር ቤት የ 152 ሀገራት ዜጎች በተለያዩ ጊዜያት ታስረውበታል ... ሁሉም ለማለት ይቻላል ሞተዋል .. በእድል በጣት የሚቆጠሩ የተፈቱትም አብደዋል ... ለሁለተኛ ጊዜ ከኢትዮጵያ በእስር ቤቱ ጥቁር መዝገብ ውስጥ ስሟ የተፃፈው ማርያ ሙሴ ሆነች ... እጅግ በጣም ረጅም ከሆነው መግቢያ በር ላይ " WCH" የሚል ትልቅ ጽሁፍ በወርቅማ ቀለም ያለው ብረት ተቀርፆ ተሰጥፎ ይታያል !! ..."እንኳን ወደ ሲኦል መጡ" ማለት ነው ፍቺው ... እጅግ በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ ትርጉሙን ያውቁታል ... ማርያ ሙሴ ! ከታሪካዊት ሀገር ኢትዮጵያ! ጣሊያንን በአድዋ ድል ካሸነፈችው ኢትዮጵያ... ምድር! በእስር ቤቱ ታሪክ ቁጥር አንድ ላይ የተፃፈችው እስረኛ ሰሚራ ሙሀመድ የተሰማትን ስሜት ማርያ ሙሴም ገና በሩ ተከፍቶ ግቢውን ስትመለከተው ... አንዳች የሆነ ነገር ሰውነቷን ወረራት ... ደም ደም ሸተታት ...

* * *

አባቷ ዝነኛ አርበኛ ናቸው! እናቷም ስመጥር ነጋዴ ... ከሁለቱ ጥምረት ውበት የፈሰሰበት ሰሚራ መሀከል መርካቶ ተወለደች:: ሰሚራ ፈጣሪ ውበትን ብቻ አልነበረም የሰጣት እውቀት እና ጉልበትን ጭምር ! ገና የአራተኛ ክፍል ተማሪ ሆና የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ለሆነው ታላቅ ወንድሟ የቤት ሥራ የምትሠራው ያለ አንዳች ስህተት ሰሚራ ነበረች ... የእንግሊዝኛ ፣ የአማርኛ፣ የትግርኛ፣ የኦሮምኛ ብቃቷን ለመናገር በጣም ይከብድ ነበር ... የሰፈሯ ጓደኞች ሰሚራን " ሰሚራ ግራኝ መሀመድ" ይሏት ነበር ... እጅግ የተለየ ጥንካሬ ነበራት... ከሰባት ወንዶች ጋር ተደባድባ ወጥ በወጥ አድርጋቸው ፣ ሸንት በሸንት አድርጋቸው መሬት ላይ ሁሉንም እንከባለቻቸው አባቷ ሰሚራ መሀመድ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ከሁሉም በላይ እጅግ የተለየ የሂሳብ ችሎታ ነበራት ... በአስር ሴኮንድ ውስጥ ማንኛውንም የሂሳብ ጥያቄ ትመልስ ነበር ...

" ሰሚራ"

" አቤት"

" 200x920 ስንት ነው በፍጥነት መልሺ"

" ውይ ቀላል ነው! 184000 ነዋ"

" እሺ 1231x689 ስንት ነው?"

"848159 ነዋ"

" እሺ 446.5x184 ስንት ነው?"

" 82156 ነዋ"

ሌሎች ተማሪዎች ግራ የሚጋቡበትን የሂሳብ ... የኬሚስትሪ ... የፊዚክስ ... ትምህርቶች ለሠሚራ ተራ ነገር ነበሩ ... ገና የአስረኛ ክፍል ተማሪ እያለች እጅግ በጣም ግዙፍ እና አስቸጋሪ ቋንቋ ያላቸውን ዝነኛ የታሪክ ፣ የፍልስፍና፣ የፖለቲካ መፅሐፎችን አንብባ ያለ እንዳች ችግር ትረዳቸው ነበር ...

ውቧ ሠሚራ! የተለየ እውቀት የነበራት ሰሚራ ! አስገራሚ ጉልበት ልክ እንደ ግራኝ መሀመድ የነበራት ሰሚራ ... ሰዎችን ፣ ተማሪዎችን፣ አስተማሪዎችን እያስገረመች ... እያነጋገረች .. እውቀቷን ይበልጥ ተጠቅማበት እንድትመጣ እና ለሀገሯ ኢትዮጵያ ታላቅ ነገር እንድትሠራ በግርማዊ ቀዳማዊ የኢትዮጵያ ንጉስ ነገስት አፄ ሀይለ ስላሴ ትዕዛዝ መሠረት ቤተ መንግስት ታጅባ መጣች ...

ንጉሱ በግርምት ተመለከቷት! በተለይ የውበቷ ነገር አስደነቃቸው በልባቸው 'ንጉስ ሰለሞን የለም እንጂ በሕይወት ቢኖር አንቺንም አይቶ በውበትሽ ተማርኮ 1001ኛው ሚስቱ ያደርግሽ ነበር' አሉ ንጉሱ አድርገውት የማያውቁትን ለመጀመሪያ ጊዜ ከዙፋናቸው ላይ በመነሳት ጨበጧት! የወርቅ ሠዓት እጅዋ ላይ አሠሩላት ... በመጨረሻ " ስላንቺ ሁሉን ነገር ሰምተን ተደንቀናል! እግዚአብሔር ያለ አንዳች አላማ ይህን እውቀት አልሰጠሽም

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ለዚህ በዚህ እውቀትሽ ለኢትዮጵያ ትልቅ ነገር መስራት ስላሰብሽ ኢጣሊያ ሀገር ሄደሽ በፍተኛ ትምህርት ተምረሽ በመመለስ በእውቀትሽ ሀገርሽን እንድትጠቅሚ አስበናል ተምርቀሽ ስትመለሺ የመጀመሪያዋ ሴት የዩኒቨርሲቲ አስተማሪ እንድትሆኚ አስበናል? ምንድ ፍቃድ እንዴት ነው?"

ቆፍጣናዋ ሰሚራ አንዳች ሳታቅማማ በመጋቢት 22፡1956 ዓ.ም በታላቅ ሽኝት ወደ ኢጣሊያ አመራች:: በታላቅ አክብሮት ተቀበሏት:: አንድ ወር የፈጀ የጉብኝት ጉዞ በጣሊያን ተዘጋጀላት... ኢጣሊያን እስከ ሚበቃት ተመለከተቻት ... ታሪካዊ ቦታዎችን አየች.. ከምንም በላይ በሮም አደባባይ ታላቅ ታሪክ ያለውን የሀገሯ የአክሱም ሐውልትን ስትመለከት እንባ አቀረረች ... ሁሉ ነገር እንዳለቀ እንደ ኢትዮጵያዊያን አቆጣጠር መስከረም 28፡1959 እጅግ ፈታኝ የሆነውንና ብቃት የሚጠይቀውን ስምንት ዓመታት የሚፈጀውን ትምህርት ለመጀመር በኢጣሊያ ቁጥር አንድ ወደ ሆነው ታላቁ university of Roma ገባች:: ይህ ዝነኛ ዩኒቨርሲቲ በ 1303 ነበር የተመሠረተው.....

ለሰሚራ ሁሉ ነገር በጣም ቀላል ነበር ... በታላቅ ወኔ የሀገሯን ኢትዮጵያን ውለታዋን ለመክፈል ...የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊት በታላቁ university of Roma የተመረቀች ዶክተር ለመሆን ... ኢትዮጵያ ተመልሳ መጥታ የመጀመሪያዋ የዩኒቨርሲቲ መምህርት ለመሆን ... ከንጉሱ የተቀበለችውን ሀላፊነት ሳትዘነጋ ... እንቅልፍ ፈለጠኝ ሳትል ... በሚደንቅ ሞራል ሰባቱን ዓመታት በ 4.0 እየጨረሰች የዩኒቨርሲቲውን ምርጥ ሰቃይ ተማሪነት እየመራች አንድ ዓመት ሲቀራት ከሀገር ቤት መርዶ ደረሳት ... የምታደንቃቸው ታላቁ ንጉስ ከስልጣን ወንበራቸው ወረዱ... ታንቀው ሞቱ ... ወታደራዊ መንግስት ጓድ መንግስቱ ኃ/ማርያም ኢትዮጵያ ትቅደም ብሎ የስልጣን ዙፋኑን ተቆጣጠረ:: ተባለች ::

ሰሚራ ወኒ ... ሰሚራ ባለ እውቀቷ ... ሰሚራ የተለየ ጉልበት ያላት ... አዘነች ... በጣም አለቀሰች... ከሳምንት በኋላ ግን የምትወዳቸውን ንጉስ ቃል ለመጠበቅ አንድ ዓመት ብቻ የቀረውን ትምህርቷን ለመጨረስ ወሰነች...

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

እንደ ኢትዮጵያዊያን አቆጣጠር ሚያዚያ 24፣1967 እሁድ ጠዋት ለሰሚራ የቀን ጨለማ ነበረች... ለሁለት ዓመት በአስደማሚ ውበቷ የተነሳ ሲከታተላት የነበረው የከፍተኛ ባለስልጣን ልጅ የሆነው የኢጣሊያ ተወላጅ ቶሚ ማርሻል ዴልፔሮ በፍቅሯ ስክር ብሎ ሲደፍራት የሰሚራ መኖሪያ አፓርትመንት ውስጥ ከሁለት ጓደኞቹ ጋር መሳሪያ ይዞ መጣ ... ሀሳቡን ነገራት ...ሰሚራ ምንም ሳትደነግጥ እያሳሳቀች ... ሳያስቡት ሶስቱንም ወጣቶች በታላቅ ቡጢ እየነረተች ከመሬት ላይ እንደ ጭቃ ለጠፈቻቸው ... ሳይታሰብ የሰሚራ ቡጢ ከአቅም በላይ የሆነበት ቶሚ ማርሻል ዴልፔሮ ሞተ ...

ሰሚራ ተያዘች:: ለማስረዳት ሞከረች ... አንሰማሽም! አንቺ ጨካኝ ኢትዮጵያዊት ተባለች ... በሀገር ውስጥ በመንግስት ሽግግር ግራ የተጋባው የኢትዮጵያ ተወካይ ቆንስላ ጽ/ቤትም ከሰሚራ አጠገብ መሆን ሲገባው ጆሮ ዳባ ልበስ አለ... በዚያ ላይ በሰሚራ እጅ ህይወቱ የጠፋው የማንም ተራ ኢጣሊያዊ ልጅ ሳይሆን በውትድርና የመጨረሻ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ማዕረግ የተሰጣቸው የማርሻል ዴልፔሮ ልጅ ነውና ... ጉዳዩ በጣም አስቸጋሪ ነበር ...

(ለአጠቃላይ እውቀት)

ማርሻል

ጄነራል

↑

ሌ/ጄነራል

↑

ሜ/ጄነራል

↑

ብ/ጄነራል

↑

....እያለ ወደ ታች ይወርዳል...

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ያቺ ውብ ወጣት ... ያቺ የተለየ እውቀት የነበራት ወጣት ... ያቺ የተለየ ጉልበት የበራት ወጣት .. ያቺ ንጉሱ ራሳቸው ከዙፋናቸው ተነስተው በታላቅ አክብሮት የተቀበሏት ወጣት ... ያቺ ሰንት ተስፋ የነበራት ወጣት .. ያቺ የስንት ቋንቋ ብቃት የነበራት ወጣት...ያቺ አደባ አስቸጋሪ የማባዛት፣ የመደመር፣ የማካፈል፣ የመቀነስ ብዜቶችን ያለ አንዳች ስህተት በዐር ሴኮንዶች ብቻ ትመልስ የነበረች ወጣት ... ያቺ በ4.0 ሰባቱንም አመታት እያመጣች ለምረቅ ሰቃዩ ተማሪ ... ያቺ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ሀገራት ተማሪዎች ሁሉ በዘር እና ሰውን በቆዳ ቀለሙ በሚመዝኑባት ፤ ጥቁርን እንደ ሴይጣን እና ምናምንቴ የሚቆጥሩ ዘቀት ባለበት ኢጣሊያ ኢትዮጵያዊን ከማንም በላይ ጭንቅላት እንዳላቸው ያስመሰከረች ታላቅ ክብር ሊሰጣት የሚገባት ሰሚራ ራሷን ለመከላከል ባደረገችው ጥረት በፈጸመችው ያልታሰበ ድንገተኛ አደጋ ... በታላቅ ልብን የሚያሳዝን ፍርደ ገምድልነት ...48 ሰዓት ባልሞላት ጊዜ ውስጥ እንደ ዝንብ ተቆጥራ ወደ አሰቃቂው DK1406 ዘግናኝ እስር ቤት ሜይ 26፤1967 ተወረወረች!!

እንኳን ዘንቦብሽ እንዲሁም ጤዛ ነሽ እንዲሉ ... ለጥቁሮች ታላቅ ጥላቻ የነበራቸው ኢጣሊያኖች በሮም ጎዳናዎች ላይ እንዴት እንናቃለን በሚል ታላቅ የንዴት ተቃውሞ ወጡ... በዚህ ያላቸው ደግሞ የኢጣሊያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ነበሩ ... ብዙዎችም የያዙት KTMF...KTBF...BTBF... የሚሉ ባነሮችን ነበር በደፈናው ትርጉማቸው ነብሰ በላዋን ሴት በፍጥነት ግደሉ! ይህቺን ሸርሙጣ ሴት በፍጥነት ግደሉ! ... የሚሉ ነበር!! ያቺ ድንቅ ጭንቅላት ያላት! የመህከል መርካቶ ወጣት የሚያከብሯት ንጉሱ በመሞታቸው አለፈሩላትም ... ጓድ መንግስቱ ሰሚራ መሀመድ ስለምትባል ሴት ጨርሶ አልሰማም ... ምንም አላውቃት የሚላት ጠፍቶ ... ማርሻል ዴልፔሮን ለማስደሰት ሲባል ... ሠልፍ የወጡትን የኢጣሊያ ወጣቶች ለማስደሰት ሲባል ... የሞት ፍርድ ተፈረደባት!! ለዚያውም ስቃይ ተሠቃይታ እንድትሞት ...

ሰሚራ መሀመድ ወደ አሰቃቂው እስር ቤት! ዘብጥያ ... ስትገባ በወቅቱ የእስር

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ቤቱ ዋና አዛዥ የ38 ዓመቱ ሻለቃ አልበርቶኔ ግራምያዜ ነበር ... ይህ ሰው ደግሞ ቅፅል ስሙ ራሱ "ትልቁ ሴይጣን" ነበር:: ከምንም በላይ የሚያስደስተው ሰው ሲቃጠል ማሽተት... የሰው ልጅን በምላጭ መዘልዘል ... በጋለ ብረት ማቃጠል እና አይን ማውጣት የመሠሉት ናቸው:: ታላቅ ሴሰኛም ጭምር ነበር ... በአልበርቶኔ ግራምያዜ እጅ ብቻ የ484 ሰዎች ሕይወት በአሰቃቂ ሁኔታ አልፏል::

ሰሚራ መሀመድ አጠር ያለ ትዕዛዝ እስር ቤቱ ከገባች ከ44 ደቂቃ በኋላ ተሰጣት::

" አንቺ አረመኔ ሴት በፍጥነት ልብስሽን አውልቂ ለፍርድ አለቃችን ጋር ልትቀርቢ ነው!!"

ሻለቃ አልበርቶኔ ግራምያዜ ቢሮ ማንኛውም እስረኛ ወንድ ይሁን ሴት ሲቀርቡ ራቁታቸውን ነው... ሻለቃው ይመለከታቸውና ደስ ካሉት ወሲብ ይፈፅምባቸዋል... ሰሚራ መሀመድ አልባሳቷን ላለማውለቅ በጣም ጣረች ... ስቃይ ... ዱላ ... ሲበዛባት በተስፋ መቁረጥ አወለቀች ... ሻለቃ አልበርቶኔ ገና ሲመለከታት ከንፈሩን መጠጠ፤ ነከሰ... መላ ሰውነቱ በወሲብ ፍላጎት ተቃጠለ ... በሕይወት ዘመኑ እንደ ሰሚራ መሀመድን የመሠለች ውብ ሴት! እጅግ አስደናቂ የተስተካከለ የሰውነት አወቃቀር ...

"OMG ...SB" አለ ዓይኑ እስኪወጣ እየተመለከታት:: ሶስቱ ወታደሮች እንዲወጡ ምልክት ሰጣቸው... ወጡ:: ሰሚራ መሀመድ እና ሻለቃ አልበርቶኔ ብቻቸውን ቀሩ:: በክፍሉ ውስጥ ሶስት ስውር ካሜራዎች አሉ ...

ሻለቃ አልበርቶኔ ሰሚራ መሀመድን ለረጅም ደቂቃዎች በዝምታ ሲመለከታት ቆየና በመጨረሻ ወሰነ ... ከፊት ለፊቱ ያለውን ወንበር እያመለከታት ... በትህትና

" ተቀመጪ" አላት::

በዝምታ ተቀመጠች::

" ጉዳይሽን በሚገባ አይቸዋለሁ... እውነቱን ለመናገር ለኔ ያደረግሽው ነገር በጣም ተገቢ ነው! በሀት መሠረት መጠየቅ ካለባቸውም መጠየቅ የነበረባቸው አንቺ ቤት የመጡት ሶስቱ ወጣቶች ነበሩ... እኔ ልረዳሽ የምችለው አንድ ነገር ብቻ ነው"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ለሚራ የሻለቃውን አይኖች ለማንበብ ሞከረች:: በእርግጠኝነት እየዋሻት እንደሆነ ገባት፣ ለድስተኛ ሰሚራ! ደመነፍሷም ሹክ አላት ... እሷም ለመተወን አቀደች...

" በእውነት በጣም ነው የማመሠግነው! እንደ እርሶ ቀና አሳቢ ሰው በማግኘቴ!! ያሉት ሁሉ በጣም ሀቅ ነው!! እና በምን መልኩ ሊረዱኝ ይችላሉ ሻለቃ"

" ያንቺ ሕይወት ያለው በእኔና በፈጣሪ እጅ ላይ ብቻ ነው"

" የኔ ሕይወት ያለው እንኳ በፈጣሪ እጅ ላይ ነው! የኔ ሳይሆን የማናችንም ሕይወት ያለው በፈጣሪ እጅ ላይ ነው"

" ቀልደኛ ነሽ ... ጥሩ ነው... ለማንኛውም ምንም እንኳ እኔ ያንቺን ትክክለኛነት ብገነዘብም .. ከላይ የመጣልኝ የማይለወጥ ውሳኔ አንቺ እንድትገደይ ነው... እኔ ግን ላይሽ በጣም ደስ ስለአልሽኝ እና ንፁህ መሆንሽን ስላመንኩ! የውሸት ትሞቺያለሽ"

" አልገባኝም"

" ለህዝቡም! ለጋዜጠኞችም! ለልጁ አባትም ሌላ ሴት እናቃጥልና ተቃጠለች ብለን እናወራለን ... ታዲያ አንቺ የኔ ሚስት ለመሆን ከወሰንሽ ነው .. ማንም ላይነካሽ በሰውር ቤት ውስጥ እዚሁ እስር ቤት አብረን እንኖራለን ... የዚህን እስር ቤት አገልግሎት ስጨርስ ማንነትሽን ለውጠን አብረን ከዚህ እስር ቤት በድብቅ ትወጪና በነጻነት እንኖራለን! ምን አሰብሽ"

" በጣም አመሠግናለሁ! ከዚህ በላይ የተሻለ አማራጭ የለም!"

" አዋቂ ነሽ ... " ሻለቃው የሰሚራን አስደማሚ ጡቶች ሲመለከት ... ውብ ዳሌ ሲመለከት ... ራሱን መቆጣጠር አቃተው ... የወሲብ ፍላጎቱ መሀል እናቱ ላይ 360 ዲግሪ ዞረበት _ በፍጥነት ከወንበሩ ላይ ተነስቶ ወደ ሰሚራ መጣ ... ተጠጋት

" OMG ...SB" አለ ...

" አይዞሽ እኔ ሻለቃ አልበርቶኔ ግራምየዛኔ ከአጠገብሽ እያለሁ ምንም ነገር ባንቺ ላይ አይፈጠርም!! አሁን ነይ የመጀመሪያ ወሲባችንን እንፈፅም ! ነይ እንደሰት ..." እጇን ይዞ ኪሳቸው ክፍል ውስጥ አስገባት ... እንደመ[illegible] ... [illegible]ያንጠባጠበ ...

tme/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

የሀያ አምስት ዓመቷ ውብ ወጣት ሰሚራ ድንግል ነበረች:: ማንም የሀበሻ ወንድ ሆነ ... ማንም የኢጣሊያ ወንድ ያንአሰደናቂ አካሏን ለመንካት እድል አላገኘም ነበር ... "መጀመሪያ ትልቁን የሀገር ሀላፊነት ልወጣ! ጋብቻ ሆነ ወሲብ ከት/ት በኋላ ይደርሳል" በማለት ራሷን አሳምና ስለነበር .. ጨዋ ነበረች! ድንግል ነበረች! ክፍሉን በሚገባ አማተረች... ብረት የሚባል ሆነ መሳሪያ የሚባል ነገር የለም ... የመጨረሻ ውሳኔዋን ወሰነች:: ምንም ድንግል ብትሆን ምንም ወሲብ ባታደርግ ... ስለ ወሲብ በርካታ ነገሮችን ታውቃለች ... ሰምታለች .. አንብባለች ... የሻለቃውን የክብር አልባሳት በፍጥነት እያወለቀችለት ከመሬት ላይ ጣለችው ዘላ ተጠመጠመችበት ... ሻለቃው ሳያስበው ማጅራቱ ላይ እጅግ ከባድ ቡጢ አሳረፈችበት ... ደግማ ደጋግማ ነረተችው .. ቡቴሲታ አዞረችበት ... በሚደንቅ ፍጥነት የሻለቃውን ሱሪ ቀዳ ... ቀበቶውን አውጥታ አነቀችው ... ገደለችው .. ወደ ዋናው ቢሮ አመራች ሻለቃው ከተቀመጠበት ወንበር ጋር የነበረውን ጠረጴዛ ከፈተች ... ሽጉጥ አየች ! በጣም ተደሰተች!!

ጠረጴዛው ላይ የተቀመጠው አጀንዳ ላይ የሚከተለውን ፅሁፍ አሠፈረች

"..... ሰሚራ መሀመድ

ሚያዚያ ...1967 E.C

ተመርቄ ኢትዮጵያ ተመልሼ ... የመጀመሪያዋ የዩኒቨርሲቲ አስተማሪ ሆኜ ... ያለኝን እውቀት ለሀገሬ ለመስጠት ... ይህ ነበር የኔ ትልቁ አላማ ... አንዳንዴ ሕይወት እኛ ባሰብነው መንገድ ሳይሆን የራሷ እኛ የማንረዳው መንገድ አላት ... አጼ ቴዎድሮስ በክብር መሞትን አስተምረውኛልና ... እኔም ቢያንስ በክብር ልሙት ... እማማ ኢትዮጵያ የገባሁትን ቃል ኪዳን ባለመጠበቄ ይቅርታ አድርጊልኝ ... የኢትዮጵያ አምላክ ይቅር በለኝ ... ኢትዮጵያ ከልቤ አፈቅርሻለሁ!

ሰሚራ መሀመድ..."

ሰሚራ መሀመድ ራሷን ገደለች !!

ይህ የሰሚራ መሀመድ የመጨረሻ ደብዳቤ ! የሰንበት ቃል...

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ከD.K1406 አሰር ቤት ቤተመጽሐፍ ውስጥ በክብር ተሰጥፎ ይገኛል – የሰሜራ አስከሬን ሀገሯ ኢትዮጵያ መጥቶ የተወለደችበት መሀል መርካቶ እንዳይቀበር – ኢቃፐነውታል...

* * *

ማርያ ሙሴ ሁሉ ነገር ትዝ ሲላት ይደንቃታል ...በሀልም ዓለም ውስጥ ያለች ያህል ይሰማታል ... ከኢትዮጵያ ስትወጣ የነበራት እቅድ ኢጣሊያ ውስጥ ያላትን ንብረቶች እና ጣጣዎች ጨርሳ ቢበዛ በሁለተኛው ሳምንት ኢትዮጵያ መመለስ ... ከዚያ ከመምህር ቀቁ ጋር የጀመረችውን የፍቅር ህሁ... ማፋፋም! ግና ከኢትዮጵያ በሌ አየር መንገድ የተነሳው በይንግ 787 የኢጣሊያ መሬትን ከረገጠ ከ15 ደቂቃ በኋላ ማርያን እጅግ ፍጥነት በተሞላበት ሁኔታ እየጣደፉዋት ጥቁር መርቸዲስ ውስጥ አስገቧት ... ከሁለት ሰዓት ጉዞ በኋላ ... ሁሉ ነገር ሲነገራት በግርምት ሳቀች:: የኢጣሊያ ልዩ ስለላ አባላት እጅግ በደስታ ተሞሉ ... ያስቸገረችው ቀንደኛዋ ለስድስት ዓመት ስሟን እና መልኳን እየቀያየረች የአሸባሪዎች ተላላኪ ተያዘች

የሚል ዜና ምስሏን እና ፎቶዋን ሳይጨምር የኢጣሊያ ቁጥር አንድ ተነባቢ ጋዜጣ የሆነው ዴይሊ ሮማ ታይምስ ዜናውን አራገበው ... ማርያ ከማንም ሰው ጋር በስልክ ይሁን በአካል እንዳትገናኝ ተወሰነ ..የ24 ሰዓት ጥብቅ ክትትል እንዲደረግባት ከፍተኛ ትዕዛዝ ተላለፈ.. ማርያ ሙሴ ተጨነቀች፤ ለመነች፤ እጅግ ንፁህ ሰው እንደሆነች ተናገረች፤ ተናዘዘች ... በመሀከል መሰላቸት ጀመረች... ቀን ቀንን እየወለደ ሲመጣ ያመጣላት ለውጥ ግን የለም:: ማሰብ ብቻ መሆኑን ተረዳች:: እርግጥ በሰዓቱ ያላት ብቸኛ አማራጭ ስለነገ ጥሩ ነገር ... ከማንም ሰው ጋር አትገናኝም:: 7 ትበላለች.ትታጠባለች ካሻት ዜና ትመለከታለች ፤ ነገር ግን ማውራት በሚሊዮን ህዝብ ባለባት ዓለማችን ላይ የምታዋራው አንድ እንኳ ሰው ናፈቃት! ናፈቃት.. ከሰው ጋር የማውራት ጥማት አቃጠላት ... በድብቅ ከሚራ 24 ሰዓት የሚከታተላት ልዩ መርማሪ ባላቶማሊ እጅግ ማስተዋል የተሞላበት መርማሪ ነው

"ይቺ ወጣት ላይ አንዳች ተጨባጭ መረጃ ሳይገኝ አንድ ነገር እንዳትንካ በጥንቃቄ ተንከባከቧት! ወንጀለኛዋ እርሷ ስለመሆኗ እርግጠኛ ስንሆን እሳት ውስጥ ጨምሯት

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

እናቃጥላታለን

--- አለ:: አንድ ሳምንት እንዳለፋት ፈተና ፈተናት:: ወደቀች:: ፈተናው ሆን ተብሎ ውሃ በብርጭቆ በእስር ቤቱ መስኮት ላይ አስገቡላት:: ጠጥታ አስቀመጠችው:: 'እርግጠኛ ነኝ ይች ወጣት አሸባሪ ብትሆን በፍጥነት ብርጭቆውን ሰባብራ አንገቷን በጥሳ ራሷን መሬ እንዳይገኝባት ትገድል ነበር!! ስለዚህ አሁንም እርግጠኛ በመሆን የምነግራችሁ ይቺ ወጣት ንፁህ ነች! ሊያም ከፍተኛ የማስመሰል ጥበብ አላት ... ቢሆንም ከኔ ትዕዛዝ ውጪ አንዳች ነገር እንዳይፈጸምባት አለ'

ማርያ ሙሴ አድለኛ ሆና ልዩ መርማሪ ባላቶማሊ ደረሳት እንጂ እስር ቤት ከገባች ከሁለት ደቂቃ በኋላ የጅምላ እጅግ አሰነዋሪ እና አሰቃቂ ወሲብ ይፈፀምባት ነበር - መፈጠሯን የሚያስረግማት ድርጊት ይፈፀምባት ነበር ... በሁለተኛው ወር መጨረሻ ልዩ መርማሪ ባላቶማሊ የድርጅቱን ህግ ጥሶ በድብቅ ኢጣሊያ ለሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ በማይታወቅ አድራሻ የማርያ ሙሴን ጉዳይ በኢሜይል ላከላቸው ...የኢትዮጵያ ኤምባሲ ጉዳዩን ለማጣራት በፍጥነት ወደ ከፍተኛ ልዩ መርማሪ እና በኢጣሊያ የኢትዮጵያ ተወካይ ወደ ሆነው የኢንተርፖል አባል ግለሰብ ጋር አመራ... በጉዳዩ ዙሪያ ከፍተኛ ውይይት ተጀመረ..15 ቀናት ቢፈጅም ግን አልተሳካም ... ድርድሩ እና ማጣራቱ ቀጠለ ... ውብ ግሮ ኢጣሊያ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ ዋና ተጠሪ በግሉ ለ18 ደቂቃዎች ሲያናግራት ኩራት ተሰማት! ጥሩ ጥሩውን ነገር እያሰበች ቀናቱን ገፋች ... በሶስተኛው ወር መጨረሻ ጉዳዩን ለማሳወቅ ለባለሀብቱ አቶ አቤንኤዘር ስልክ ተደወለ ... ባለሀብቱ አቶ አቤንኤዘር የ15 ሚሊዮን ብር ስምምነት ለመፈጸም አየርላንድ የነበራቸውን ፕሮግራም ሰርዘው ወደ ኢጣሊያ አመሩ..

እጅግ በጣም የሚደንቀው እና ለማመን የሚያስቸግረው ልክ በወርሃ ሚያዝ 13.8.58 (በወቅቱ የጃማይካ አገረ ገዥ ከቡር ዶላንድ ስንግስተር ይባሉ ነበር) አፄ ኃይለሥላሴ ዝናብ አጥተው ቢታላቅ ችግር ውስጥ የነበሩት የጃማይካ ህዝብን መሬት ገና ከአውሮፕላን አንድ እግራቸው ወጥቶ መሬቱን ሲነካው ታላቅ ዝናብ ዘንቦ አፄ ኃይለስላሴን

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ቃለ" እንዲሆኑ እንዳደረጋቸው ሁሉ ባለሀብቱ አቶ አቤንኤዘርም ኢጣሊያ ደርሰው ገና ከአውሮፕላን ወርደው እግራቸው መሬት እንደነካ " እጅግ ተፈላጊዋ አሸባሪ ብራዚል ውስጥ ስለተያዘች ኮድ 0064 በፍጥነት ትፈታ! ለተፈጠረው ትልቅ የስም እና የመልክ ፍፁም ተመሳሳይነት በሚገባ ተነግሮዋት ለኮድ 0064 የካሳ ግማሽ ሚሊየን ዶላር ይከፈላት" የሚል መልዕክት ለልዩ መርማሪ ባላቶማሊ ደረሰው ... ባለቶማሊ ዜናውን እና የሆነውን ነገር ሁሉ በዝርዝር አስረዳቸው ... አቶ አቤንኤዘር ራሳቸው የሁለቱን ሴቶች መመሳሰልን ሲመለከቱ በጣም ተደነቁ... ለማርያ ሙሴ እና ለባለሀብቱ አቶ አቤንኤዘር ከትልቅ ይቅርታ ጋር ነገራቸው ... በመጠኑ የከሳችውን ተወዳጇን ማርያን ሲመለከቱ በደስታ ተጠመጠሙባት ... ሁሉ ነገር ለማርያ ተነገራት...

" አይዞሽ የኔ ውብ ሁሉ ነገር ለበጎ ነው የሰው ልጅ በሕይወት ዘመኑ ብዙ ያልታሰበ ፈተና ያጋጥመዋል! ዋናው ቁም ነገር ይህ ለምን በኔ ላይ ሆነ ማለት ሳይሆን ፈተናውን በትዕግስት ለማለፍ ጥረት ማድረግ ነው!! በዚያ ላይ ሁሌ ጥሩ ነገር ብቻ ይግጠመኝ ማለት የተፈጥሮ ህግን አለማወቅ እና ሞኝነት ነው... በይ በፍጥነት ከዚህ ቦታ እንውጣ .. ጣጣችንን ጨርሰን በፍጥነት ወደ እማማ ሀገር ኢትዮጵያ እናምራ!!"

ማርያ ሙሴ መናገር ስላቃታት በዝምታ ... በደስታ ... ባለሀብቱ አቶ አቤንኤዘር ላይ ተጠምጥማ አለቀሰች ... አላወቀችም እንጂ ትልቅ ምስጋና ማቅረብ የነበረባት ለልዩ መርማሪ ባላቶማሊ ነበር ... ልዩ መርማሪ ባላቶማሊ በህግና በፍትህ በጣም የሚያምን አመዛዛኝ ሰው ነው ... በሌላ በኩል እንድታሳሪ ወንጀለኛ መሆኑ ከተረጋገጠ... ባላቶማሊ የሴይጣን መንፈስ ይጠናወተዋል .. አስቀድሞ የተጠቀሱትን አሰቃቂ ወንጀለኞች ላይ የሚከናወኑትን ድርጊቶች ይፈፅማል! እንዲፈፀም ያዛል ... እንደምንም ብሎ በክፍሉ ውስጥ ያሉትን ካሜራ እና ድምጽ ማስተላለፊያ ካጠፋቸው በኋላ በትኩረት ማርያ ሙሴን እና ባለሀብቱን አቶ አቤንኤዘርን እየተመለከተ

" እኔ በህግና በፍትህ በጣም አምናለሁ! ከዚህ ቀጥሎ ኢትዮጵያ ስትመለሱ ይህን ወረቀት ለመንግስት ሀላፊዎች በጥንቃቄ ስጡ! በእርግጠኝነት ይህ ጉዳይ አለም አቀፍ ፍርድ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ቤት የኢትዮጵያ መንግስት ጉዳዩን ቢያቀርበው ለኢትዮጵያ ከፍተኛ ካሳ ያስገኛል፡፡ ...
ይህን ወረቀት በከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረስ አለባችሁ!! ይህ ታላቅ የታፈነ ሚስጢር ...
ኢትዮጵያዊትን ማንነት የሚያሳይ ጉዳይ ነው! ሰሚራ መሀመድ ትባላለች.. ይህን ወረቀት ...
እጅ እንደተቀበላችሁ መናገር በጭራሽ አይኖርባቹሁም! ከዚህ በላይ መናገር አልችልም ...
በድጋሚ በእንቺ ላይ ስለደረሰው ስህተት እጅግ በጣም ትልቅ ይቅርታ እጠይቃለሁ .. በ...
አገራችሁ ግቡ!!"

"እናመሠግናለን"

* * *

ማርያ ሙሴ ከእስር ቤቱ እንደወጣች ለዘጠና ቀናት የናፈቀችውን ... ተመለከተች:: በደስታ መሬቱን ለመሳም ጎንበስ ስትል ባለሀብቱ አቶ ኤንጂነር ... ያዟት!!

"መሳም ካለብሽ የኢትዮጵያን መሬትን በሌ አየር መንገድ ስትደርሺ ነው ... ኢጣሊያ ነው!" ሲሉ ተናገሩ::

ማርያ ሙሴ ኢትዮጵያ ደርሳ የኢትዮጵያን መሬት እስከምትስም .. ... መምህር ቀቁን እስከምታየው ... ከሲልቪያ ጋር እስከምታወራ ... የኢትዮጵያ ... በጣም ናፈቃት! ሁሉ ነገር በሴኮንዶች ውስጥ ቢከናወን ተመኘች .. አዕምሮዋ ላይ ግ... ማዙፍ አባባል እንቃጨለ ...!!

"...ለሁሉም

ነገር

ጊዜ

አለው

በ

ጊዜ

ለኩሉ ...."



t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

# ክፍል 6

# ድህረ ታሪክ

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

- ... 'ለሁሉም ጊዜ አለው ... ለሀዘንም ጊዜ አለው ... ለደስታም ጊዜ አለው ... ለመ... ጊዜ አለው ... ለመራብም ጊዜ አለው ... በ ጊዜ ለኩሉ ...' እነሆ ሁሉ ነገር ጊዜውን ... ሆነ ... ማርያ ሙሴ እና ባለሀብቱ አቶ አቤንኤዘር ኢትዮጵያ ... ደረሱ ..........................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................

- የመምህር ቀቁ እና የማርያ የፍቅር ሀሁ እጅግ አጥር ምጥን ባለ የቀለበት ሥነ ሥርዓ... ተቀጣጠለ ..........................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................................

- መምህር ቀቁ የሚያሳብደውን THE VENTRILOQUISM OF LIFE የተሰኘ... መፅሐፍ በ 13,000 ሺ ብር ከወመሽ ገዛ ... መግዛት ብቻ አይደለም በሁኑ መሰረት እ... ጨረሰ ... በመጠኑ ቢወዛገብም እንደተባለው ግን ጨርሶ አላበደም ... ሁሉ ነገር ... የማሳመን እና ያለማሳመን ጉዳይ እንደሆነ ይበልጥ አረጋገጠ.... በእርግጥ ግን THE VENTRIOQUISM OF LIFE የተሰኘው መፅሐፍ ያለ ማስተዋል ከተነበበ ሰው... ፈጣሪ መፅሐፍ መሆኑን አስተዋለ!! በተለይ ፈሪ የሆነ ሰው፣ በህይወት የተወዛገበ ሰ... አግኝቶ ያጣሰው፣ በፍቅር የተወዛገበ ሰው፣ በፖለቲካ ናላው የዞረ ሰው ፤ በ... መተማመኑ አነስተኛ የሆነ ሰው ፤ ትንሽ እውቀት አደገኛ ናት እንደተባለ ትንሽ አው... ኖሮት ሁሉን ያወቀ ለመምሰል ጉራውን የሚነሰንስ ሰው! ካነበበው በእርግጠኝነት ማ... እንደማይቀር አረጋገጠ!! በከፍተኛ ጥንቃቄ በመፅሐፉ ዙሪያ ምርምር ለማካሄ... አስቀመጠው ..........................................................................................................................................................................................................................................................

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

- ወ/ሮ ሲልቪቪያ አቤንዜአር "የኢየሱስ ሣቅ" የሚል መፅሐፍ አዘጋጅታ የጨረሰች ቢሆንም በዚህ መፅሐፍ ውስጥ አጅግ አወዛጋቢ እና ቁጣ ሊያስነሳ የሚችል ፈጠራ ቀመስ ሀሳቦች ስለሚበዙበት አልተካተተም ..............................................................................................................................................................................................................................................

- ጋዜጠኛው ጎሊያድ ከአሸዋሪያ ሆነች ዊንታዘር ማንንም አልመረጠም ለዚህ የሚከተለውን ምክኒያት አስቀምጧል ከሁለት ጓደኛሞች አንደኛዋን አፍቅረህ ሌላኛዋ አንተን ካፈቀረች የተሻለው ምርጫ ሁለቱንም ትተህ ሌላ ፍቅረኛ መፈለግ ብቻ ነው...የጋዜጠኝነት ህይወቱን በ FM66.6 ቀጥሏል..............................................................................................................................................................................................................................................

- በአቢሲኒያ በከፍታ ት/ቤት ሁሉ ነገር በመልካም ፍሰት ላይ ይገኛል... ለት/ቤቱ መንግስት ከፍተኛ ግቢቃ ... እያደረገ ነው፤ መምህራን በታላቅ ወኔ ለማስተማር በዝግጅት ላይ ይገኛሉ ... ተማሪዎችም እውቀትን ለመቅሰም እየተዘጋጁ ናቸው..............................................................................................................................................................

ሕ

ይ

ወ

ት ... እንደቀጠለች ናት ! የኢያሪኮ ባቡርም ጉዞውን አጠናቋል...

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

- ሲልቪሺያ አቤንኤዘር አዲስ ከጀመረችው FM66.6 ከፍል ሁለት (ቅ
መፅሐፍ መግቢያ ላይ ያለውን እንቆጵ ቀንጭበን እንሰናበት ... ከኢያሪኮ 777... ኢ
888 ... ኢያሪኮ 999 ... አቢሲኒያ 24 ባቡር ውስጥ እንውጣ ...

* * *

... የሀያ አምስት ዓመቱ ወጣት ጎልያድ ሁሉንም ነገር በግርምት እየተመ
ነው:: የግቢው ፀጥታ ፣ ያለው ንፋስ፣ ታሪክ ... አስር ብር ከፍሎ በገዛት ወረቀት የጎበኛ
ቤተመዛግብትን ... የአለም ሰገድ ፋሲል ግንብን ... የአእላፍ ሰገድ ጻዲቁ ዮሐንስ ግንብ
የአድያም ሰገድ እያሱ ግንብን ... የመሲህ ሰገድ በካፋ ግንብን ... የእቴጌ ምንትዋብን ግንብ
ሁሉንም በእርጋታ ተመለከታቸው ... በእጁ ዳሰሳቸው ... በወቅቱ የነበሩት ዕቃዎች የት ደረሱ
ይሆን?... ይህ ቤተመንግስት ለፊልም እጅግ የሚያነሳሳ ነው... እንዴት የፊልም ባለሙያዎች
አልተመለከቱትም? ከ1632-1721 ዓ.ም ኢትዮጵያ ውስጥ ይህን የመሠለ የሥነ ህንፃ ጥበ
ከነበረ እንዴት ይህ ጥበብ ከትውልድ ወደ ትውልድ አልተላለፈም?.. የሆነ ቦታ ስለጫ
ተቆርጧል ማለት ነው ... ወሬያችንን ቁጭ ብለን ስንከካ! በታሪካችን አብዝተን ስንመፃ
አማራ ... ትግሬ..ኦሮሞ.. ቅብርጥሶ እያልን ስንነታረክ እና ስንባላ ... ውስጣችንን በውሸ
ሞልተን ... በውሸት ተወልደን ... በውሸት አድገን .. በውሸት ተምረን ... ፍቅራችን የውሸት
ስራችን የውሸት ... ነፃነታችን የውሸት ... አስተሳሰባችን የውሸት ... ማንነታችን የውሸ
ደስታና ሀዘናችን የውሸት ... ሁሉ ነገር ውሸት ... አከሱምን! ጀጎልን ... ላሊበላን ! ፋሲል
የኢትዮጵያ ድንቅ ልጆች በእርግጥ ከሠሩት ...? ያ እውቀት ... ያ ጥበብ ... ለምን አሁን ጠፋ
በመሀከል የሆነ ቦታ ለምን ቆመ?... ምንድ ነው የተደበቀው ሚስጢር ...??

በንጽህና የተያዘው ሳር ላይ ተቀመጠ ... በብዙ ጥያቄዎች ራሱን ወጠረ.. ከብዙ
ጥያቄዎች መሀከል ሶስት ጥያቄዎች በጣም ወጠሩት

ማን ነኝ...?

ለምን ተፈጠርኩኝ...?

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ለሀገሬ ምን መስራት አለብኝ ...?" ጎልያድ ድንገት ከተቀመጠበት ሳር ላይ ዘሎ ተነሳ!!
ለሳብሪው የኢትዮጵያ ቀደምት ነገስታት ቤተመንግስት ወጣ ... ለጥያቄዎች ምላሽ ፍለጋ ...

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

# እንደ መሠናበቻ ምርቃት

1. ከኢያሪኮ 777- አቢሲኒያ 24....
2. የዳዊት ወንጭፍ

t.me/OLDBOOKSPDF




Scanned by CamScanner

## 1. ከኢያሪኮ 777—አቢሲኒያ 24

- ይህ አቢሲኒያ 24 መፅሐፍ እስከታተመበት ድረስ ኢያሪኮ 777 ...888...999 ከተጠበቀው በላይ ብዙ ሺ ኮፒዎች ተሸጧል... ለአንባቢያን ከፍተኛ ምስጋና ይድረሳችው!!

---

- መጽሐፍቱ ለገበያ ከቀረቡበት ከ2004-2005 ዓ.ም በመፅሐፍቱ ዙሪያ ስልክ በመደዋል... SMS በመላክ ... በተለያዩ መፅሔቶች ላይ አስተያየቶች የተሰጡ ሲሆን እጅግ በጣም በርካታ አስተያየት የመጣው በ SMS ሲሆን በዚህ መልኩ ሊቀመጥ ይችላል ... " በርከት ላሉት በጣም እናመሠግናለን መፅሐፍቱን ስላነበቡ" የሚል ምላሽ ተልኳል... ለማኛችውም ...




t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

<u>መግለጫ</u> :-

1. 60% አድናቆት ... "በጣም ጥሩ ነው! ቀጥል ... ድንቅ ነው " የሚሉ
2. 20% "ስድቦች" የማይረባ ቆሻሻ መፅሐፍ ነው... ገንዘብ ለማግኘት ብቻ የተፃፈ ... ካነበብኳቸው ሁሉ የወረዳ ተራ መፅሐፍ ነው .... ደራሲ ለመባል ብቻ የተፃፈ መፅሐፍ ነው ..." የሚሉ ይበዛሉ ...
3. 10% ጥያቄዎች " ማን ነህ? እውነተኛ ስምህ ማን ነው? ... እውነት ታሪኩ ውስጥ እውነት አለ ... ይህን ነገር ዕፈህል ምን ማለት ነው ..." መሰል ጥያቄዎች
4. 5% መረጃ ለመስጠት " እዚህ ቦታ ተሳስተሀል አስተካክል ... ይህ ገጠመኝ አለኝ .. እኔም አንድ ታሪክ ላጫውትህ ..." የመሰሉ
5. 3% ዛቻ ለመስጠት!!

" ከኢህአዴግ ጋር ነህ? ከተቃዋሚዎች ጋር ... ስልክህ ተጠልፏል ... የማይገባህ ውስጥ ባትገባ ይሻልሀል ... አርፈህ ተቀመጥ" የመሰሉ ...

6. 2% መረጃ ለመጠየቅ ... ሁሉም ምስጋና ይድረሳቸው!!

- ከኢያሪኮ 777—አቢሲኒያ 24 ድረስ ለመፃፍ ግማሽ ደስታ ወረቀት ብቻ እና 70 ብር የማይደርስ ብዕር አገልግሎት ላይ ሲውል 75% የሚሆነው ተፅፎ ያለቀው ከጠዋቱ 3-5:30 ደቂቃ ባለው ጊዜ ሲሆን ፤ በተለይ እሁድ ቀን !! 25% በተለያዩ የጉዞ ቦታዎች የተፃፈ ነው...
- ለመፅሐፍቱ ሙቀት ለመፍጠር ምንም አይነት የተለየ ማስታወቂያ በሬዲዮ፣ በጋዜጦች፣ በመፅሔቶች አልተሠራም ... ቁም ነገር መፅሔት እና አዲስ ጉዳይ መፅሔት ግን ሁል ጊዜ የዜና ሽፋን ይሰጡ ነበር ... ለሁለቱም መፅሔቶች ምስጋና ይድረሳቸው!!
- ኢያሪኮ 777 እና 999 ላይ ያለው ወጣት ምስል "ወጣት መርዕድ ጥሩነህ" ሲባል በኢያሪኮ 888 ጊዜ ሠርግ ስለነበረበት እና ስላልተመቸው በመፅሐፉ ላይ ምስሉ የተተካው በወንድሙ ኪሩቤል ነው ... ሁለቱም ወጣቶች በግል መስሪያ ቤት ውስጥ የሚሠሩ ናቸው ... ለወንድ[illegible] ምስጋና ይድረሳቸው::

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

በመፅሐፍቱ ላይ "በር" በብዛት የተመረጠበት አላማ በተለይ በት/ቤቶች ዙሪያ መቅረፍ ያለባቸው በዝምታ "የለወጥ በሩ" ተዘግቶ የተቀመጡ ጉዳዮች ስላሉ ለለውጥ እንኳ በሩን አንክፈተው የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ ነው፤ በየመፅሐፍቱ ለማሳየት የተሞከሩ በርካታ ችግሮች ከመለስተኛ እስከ ዩኒቨርሲቲዎች ይገኛሉ.. በት/ት ስኬታማ ለመሆን እነዚህ ነገሮች መለወጥ አለባቸው ... ባጠቃላይ በደረቁ ሳይሆን ለማዝናናት እየተሞከረ ስለ ት/ቤቶች፣ አስተማሪዎች፣ ተማሪዎች ለማንሳት ጥረት ተደርጓል... የተሻለ እውቀት እና ችሎታ ያለው ደግሞ በስፋት ሊያነሳቸው ይችላል..

- ከኢያሪኮ 777 -አቢሲኒያ 24 የአፃፃፍ መንገዱ "70/30+ ግነት" 70% ምናባዊ ፈጠራ 30% ሀቅ + ግነት የሚል ሲሆን በተቻለ መጠን በየመፅሐፍቱ ውስጥ አዲስ የአፃፃፍ ስልት ለመፍጠር ጥረት ተደርጓል! በተለይ በመፅሐፍቱ ዙሪያ ገፀባህሪያት ራሳቸው ስለ መፅሐፍቱ አስተያየት እንዲሰጡ የተደረገበት አዲስ ያልተለመደ ስልት ብዙዎችን አወዛግቧል... በቃላት ምርጫ መዝገበ ቃል ላይ ያሉት" ስድ" "ጨዋ" የተባሉትን /መዝገበ ቃል ግን አይላቸውም" ሁሉ አገልግሎት ላይ ውለዋል ... በዚህም ብዙዎች ቃላቱን " አዘርግ" ራሱ የፈጠራቸው እስከሚመስላቸው ድረስ ... ለምን በሚል አረ ብለዋል...
- ከኢያሪኮ 777 –999 ብዙዎች ያነሱት ጥያቄ ለመሆኑ አዘርግ ማን ነው? ለምን መፅሐፉን አያስመርቅም? ለምን ለአንባቢዎቹ ራሱን አያስተዋውቅም? አዘርግ ፈሪ ስለሆነ ነው ራሱን የሚደብቀው ...ራሱን ታዋቂ ለማድረግ ስሙን ለምን ከዝነኞች ጋር ይቀላቅላል!? ስለራሱ መፅሐፍ ራሱ ለምን አስተያየት ይሠጣል?... የመሰሉ ብዙ ጥያቄዎች ይነሳሉ ... ወደፊትም ይነሱ ይሆናል ...!! ለሁሉም የተሻለው መልስ " አዘርግ አንድ ኢትዮጵያዊ ብቻ ነው... ይህ አጀግ በጣም በቂው ነው! በተረፈ ስም መትከል፣ ታዋቂ መሆን፣ ሙቀት መፍጠር ... ለአዘርግ ትርጉም የላቸውም፤ በጣም ባጠረ ቋንቋ አዘርግ ገፀባህሪ ነው!! ከገፀባህሪ በላይ መሆንን ጨርሶ አይሻም!! ይልቅ በርከት ያሉ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

መፅሐፍትን ለተከበሩት አንባቢዎች ለማድረስ ጥረቱን ይቀጥላል....በተለይ የሥነ ፅሁፍ ደንብና ሥርዓትን የማይከተል የራሱን ለየት ያለ አፃፃፍ ለመፍጠር ጥረቱን ይቀጥላል... ገፀባህሪው አዘርግ!!

" ከሚጥልህ መልካም ፈረስ

ይልቅ የሚሸከምህ አህያ ይሻላል"

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

# ምርቃት

# 2


## የዳዊት ወንጭፍ

**የኢትዮጵያ ህዝብ 12 ግዙፍ ድክመቶች**

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner




t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

ከፈሊጋችሁ በቅናት እርር! ድብን ቅጥል! ንድድ በሉ እንጂ እኔ ለኢትዮጵያ አንድ ታላቅ የምስራች ለማብሰር ጥረት ላይ ነኝ!! ደግሞ ኢትዮጵያ ስላችሁ ሚሰቴ_ ፍቅረኛዬ_ ምናምኔ አትምሰላችሁ ... ይቺ "ኢትዮጵያ" ለምንላት ሀገር ነው ... ሀሳቡ የመጣልኝ የፕሮፌሰርን (መስፍንን) "መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ" የሚለውን መፅሐፍ ካነበብኩ በኋላ ነው_ እሳቸው ምላሽ ሰጡለት ያሉትን የመክሸፍ ታሪክ መነሻ እና ብልሀቱን እነሆ መልስ ፍለጋ ታላቅ ጥረት አደረኩ... እነሆ ጥናቴ አልከሸፈምና የምስራቹን ለመላው የኢትዮጵያ ሚሊየን ህዝብ ላበስረው ነው...

ዳዊት ታረቀኝ ሁባንቻካ እባላለሁ ...ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ በ-PHARMACIST ከተመረኩ ሁለት ዓመት አለፈኝ:: አንድ ዓመት በመንግስት መስሪያ ቤት ሰራሁ፤ ከዚያ ከጠዋት እስከ ማታ "... የሰውየውን ራዕይ ብቻ እናሳካለን ... በምሳ ሰዓት ይሁን በሻይ ሰዓት መንግስትን የሚቃወም ማንኛውንም መፅሔት፤ጋዜጣ፤ መጽሐፍ ማንበብ ታላቅ ወንጀል ነው ..." እያሉ ቅብርጥሶ ሲያበዙ ሰለቸኝ፤ ሊያስታውከኝ ደረሰ ... በራሴ ፍቃድ ስራውን ተውኩት :: ለነገሩ የልጅነት ህልሜ ራሱ  በግል ይሁን በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ እየሠሩ ወር ጠብቆ ደሞዝተኛ መሆን አልነበረም:: የልጅነት ህልሜ አንድ የራሴ የሆነ ነገር መክፈት ነበር!! እናም አወጣሁ አወረድኩና ወንድሜን አሳምኜ (ቤተሰቦቻችን ሞተዋል) ወንድሜ የታክሲ ሹፌር ነው:: እርሱ ነው በውድ የግል ት/ቤት አስተምሮኝ ዩኒቨርሲቲ ስገባም በቂ ገንዘብ እየላከልኝ እንድመረቅ ያደረገኝ! እውነተኛ ወንድም!)

"ወንድሜ" አልኩት ስራ ባቆምኩ በአራተኛው ቀን::

" አቤት"

" አንድ ሀሳብ መጣልኝ"

" ምን?"

" የኔን ፀባይ እንደምታውቀው ያለሥራ መቀመጥ አልወድም:: በዚያ ላይ ማንኛውም ጤነኛ አዕምሮ እና አካል ያለው ግለሰብ ሳይሠራ መብላት ሀጢያት ነው! ስለዚህ ደግሞ በግል ይሁን በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሬ መስራት አልፈልግም! የልጅነት

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

ሀልሜም ይሄ አይደለም ስለዚህ ካለን በጣም ሰፊው ግቢያችን ላይ ለምን የተወሰነ ቦታ አ...
እንሸጥምና ሕይወታችንን አንለውጥም?"

አልኩት:: ወንድሜ ጥቂት ካሰበ በኋላ "ገንዘቡን ካገኘህ ያንተ ዓላማ እንደሚሳካ
እርግጠኛ ነህ?"

" 100% አትጠራጠር"

" ምርጥ ሀሳብ ነው! የተወሰነ ቦታ እንሸጥ! እኔም በለጠች እየጨቀጨቀችኝ ነው
የተወሰነ ገንዘብ ትሰጠኝና እንደነገሩ ሠርግ ቢጤ አዘጋጅተን እንጋባለን"

.... ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነበር የተወሰነ ቦታ ቆርሰን 2.5 ሚሊዮን ብር የሸጥ...
ሁለት ወር ከፍተኛ ጥናት አደረኩ ... የማውቃቸውን ዶክተሮች አማከርኩ... ለንግድ ...
ቦታ ፈለኩ ... ለገበያ ጥናት አንድ ወር ዘነበወርቅ ሰፈር በሚገኘው የአባታችን ጓደኛ መድኃ...
ቤት ተቀጥሬ ሠራሁ ... ከስድስት ወራት በኋላ በኔ ጥረት ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሰዎችም ...
" የዳዊት ወንጭፍ መድኃኒት ቤት" የተሰኘውን ድርጅቴን ከፈትኩ... የአራዳነቴ ብዛት ...
ሥጋ ቤት ፤ አዲስ ምግብ ቤት፡ አዲስ መፅሐፍ... ብቻ ነው ምርቃት የሚያስፈልገው እስከ...
መድኃኒት ቤትም ምርቃት ያስፈልገዋል በማለት ለማውቃቸው ሆነ ወንድሜ ለሚያውቃቸ...
ጓደኞቹ የመርቁልኝ ወረቀት በተንኩ... የተወሰኑ ሰዎች መጥተው ዶድራንት፡ ኮንዶም፡ የ...
ምታት መድኃኒት ፤ ሞዴስ... ገዙኝ:: ተደሰትኩ::

በሁለተኛው ወር መጨረሻ መድኃኒት ቤቴ ሞቅ ደመቅ ማለት ጀመረች፡
የሚረዳኝ /የምትረዳኝ ሠራተኛ ልቀጥር አልኩና የገበያ ጥናት ሳከናውን አብዛኛውን ሰ...
የገበያ ቀናት የሚባሉት እርብ፡ ቅዳሜ እና ሰኞ መሆናቸውን ስገነዘብ ለጊዜው ወጪ ለመቀነ...
ብቻዬን መስራት ጀመርኩ... ብዙ ሰዓት ስለምቀመጥ ለማንበብ እና ለመመራመር
አጋጣሚውን ተጠቀምኩበት ... በአራተኛው ወር መጀመሪያ ያላሰብኩት የቢዝነስ በር
ተከፈተልኝ... እውነቱን ለመናገር ሁለት ችግሮች አሉብኝ::

1. የወሲብ ቀበኛ ነኝ

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

2 ገንዘብ የሚያስገኝ ማንኛውንም ስራ መስራት እወዳለሁ:: ታዲያ ሰው መግደልን አይጨምርም::

# ዕለቱ ሮዕቡ ነበር

- ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት መድኃኒት ቤቱን ከፈትኩኝ
- ከጠዋቱ 2:00-2:30 ፅዳት አከናወንኩ፤ አዋራ አራገፍኩ ... ወለሉን ወለወልኩ..
- 3:30 ደቂቃ ላይ መከሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ የሚለውን የጀመርኩትን የፐሮፌሰርን መፅሐፍ ለማንበብ ወንበሬ ላይ ለመቀመጥ ስመቻች እንዴት የድንጋጤ ፊት የሚነበብባት ... ዋው ... በጣም የምታሻፍድ ... ውብ ቢጤ ልጅ መጣች! የሚደንቅ ተከለሰውነት አላት!

ከወንበሬ ተነሳሁ :: በፈገግታ ተሞላሁ::

"ታዲያስ?" አልኳት ድንጋጤዋ እንዲቀንስላት! በጣም እንደ ደነጠች ከፊቷ ላይ ይነበባል:: የፈጣሪ ያለህ ከናፍርቶቹዋ ግመጡኝ፤ ግመጡኝ ይላሉ.. ሳላስበው በአድናቆት ብዙ ቃላዬ በፍጥነት ተገተረ ... ውይ ...እንባቢያን ባለኩኝ አይደለም ይቅርታ .. ያው ችግሬን ነግሬያችሁ የለ?

" ላስ ... ችግር..ህ ነው"

" ምን ልርዳሽ የኔ እህት?"

" ችግር ውስጥ ነኝ"

"የምን ችግር?"

በጣም ደስ ከሚሉኝ ነገሮች እንደኛው የሰው ሚስጢር መስማት ነው! እናም ይቺ ውብ ልጅ ላይ የተፈጠረው ነገር ለመስማት ቋመጥኩ::

"የዘኛ ክፍል ተማሪ ነኝ... ትላንት Day party ነበረን ሙዚቃ እና መጠጥ ምናምን ነበር:: ከፍቅረኛዬ ጋር እየደነስን ነበር እየተሳሳምንም ነበር... ሳናስበው የሆነ ባዶ ክፍል ስናገኝ ወሲብ አደረግን ... ድንግል ነበርኩኝ" ብላ ዝም አለች:: በፍጥነት አዕምሮዬን አሰራሁት! እንደ ነገር ዘልዬ በመነሳት የመድኃኒት ቤቱን በር ቆለፍኩት "ዝግ ነው"

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

የሚለውን ፅሁፍ ሰቀልኩኝ ... ለውቧ ልጅ ወንበር ሰጠዋትና እንድትቀመጥ አደረግኋት ... ለፊቷ ተቀመጥኩኝ

"ስምሽ ማን ነው?"

"ዳናይት"

"ዳዊት እባላለሁ የዚህ መድኃኒት ቤት ባለቤት ነኝ:: ረጋ ብለሽ ንገሪኝ እኔ ... በምችለው ነገር ሁሉ ከአጠገብሽ ነኝ"

" Thank you! ቤት ገብቼ ማታ በቀዝቃዛ ውሃ ሰውነቴን ስታጠብ እና ... ለቀቅ ሲያደርገኝ ነው ያወኩት ብልቴ አካባቢ እና ፓንቴ በደም ተጨማልቆ ነበር ... ያደረግነው ያለ ኮንዶም ነበር:: እረግዛለሁ?"

" አ ታስታውሻለሽ ስንት ጊዜ ወሲብ እንዳደረጋችሁ?"

"አላስታውስም ለፍቅረኛዬ ጠዋት ስደውልለት ግን ወደ ሶስት ጊዜ ብሎኛል"

" ምንም ድንግል ብትሆኚ! የእርሱ ስፐርም እንቺ ማህፀን ውስጥ ከገባ እና ማህፀን ውስጥ እንቁላል ካለ ማርገዝሽ አይቀርም ..."

"የፈጣሪ ያለህ" አለችና በድንጋጤ ራሷን ያዘች:: ዘኛ ክፍል ሆና ይህን ባለማወቋ አዘንኩ:: በተለይ የ Biology አስተማሪዎች ስለ reproduction ሲያስተምሩ ሁሉን ነገር በጥንቃቄ እና በዝርዝር ቢያስረዱ ይቺ ልጅ አሁን ትቸገር ነበር?

"ብዙም አትጨነቂ! ዛሬ እዚህ መምጣትሽ በጣም ትልቅ ነገር ነው:: የተወሰኑ ቀናት ቆይተሽ ቢሆን ኖሮ ነበር ችግር የሚፈጠረው ... ዘኛ ክፍል ነኝ አልሺኝ አይደለም ዳናይት?"

" አዎ"

"የBiology አስተማሪዎቻችሁ ስለ ፓስትፒል (postpill) አላስተማሩቿችሁም?"

" አላስተማረንም"

" ማስተማር ነበረበት ለማንኛውም ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ-ሥጋ ግንኙነት በተደረገ 72 ሰዓታት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከተወሰደ ይህ መድኃኒት ያልተፈለገ ድንገተኛእርግዝናን ይከላከላል"

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

ባላሰበው ዘላ ተጠመጠመችብኝ ... ትንፋሿ በደስታ ቁርጥ ቁርጥ እያለ

"ገለ..ዘ.ሀ.ለ.ላ..ሬ..ማዝም ማለት ነው?"

" you are so Lucky! ወሲብ ካደረግሽ 72 ሰዓታት በኋላ ብትመጪ ኖሮ ጉድ ሆነሽ ነበር:: መድኃኒቱ ሰባት ብር ብቻ ነው ዛሬ ማታ 2:00 ላይ አንዱዋን ዋጪ ነገ ጠዋት በዛት ሆነ ደቂቃ ሳታዛንፊ ልክ 2:00 ሰዓት ሲል ሁለተኛውን መድኃኒት ዋጪያት ታዲያ ምናልባት ስፐርሙ ማህፀንሽ ውስጥ ካልገባ መድኃኒቱ በማህፀንሽ ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል!! በእርግጠኝነት ግን ሶስቴ ወሲብ ካደረጋችሁ መግባቱ አይቀርም! ስለዚህ መውሰድ ትችያለሽ"

" በጣም አመሰግናለሁ"

" ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለብሽ ታውቂያለሽ?"

" ማለት"

" ድንግል ነኝ አላልሽም"

"Yes"

" ስለ ድንግልነት የBiology አስተማሪሽ አላስተማረሽም?"

" ማለት"

" ድንግል የሆነች ሴት ወሲብ ስታደርግ ምን ማድረግ እንዳለባት ወይም ስለ Defloration አላስተማራችሁም?"

" በደንብ አላስተማረንም"

"Anyway, ድንግል የሆነች ሴት ለመጀመሪያ ጊዜ ወሲብ ስታደርግ ድንግልናዋን ታጣለች:: በተለይ ስሜት ውስጥ ሳትገባ ወሲብ የምታደርግ ከሆነ ከፍተኛ ህመም ሊሰማት ይችላል... መድማቱ እንዳለ ሆኖ ማለት ነው:: ታዲያ በሁለተኛው ወይም በሶስተኛው ቀን በድጋሚ ወሲብ ማድረግ ይኖርባታል! ያለበለዚያ ቆይታ ወሲብ ስታደርግ ከፍተኛ የሆነ ስቃይ ሊሰማት ይችላል! ስለዚህ አንቺም ከሁለት ቀን በኋላ ወሲብ ማድረግ ይጠበቅብሻል ... ግን

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

በጣም ህመም እንዳይሰማሽ በጣም ልምድ ያለው ሰው መፈለግ ይኖርብሻል ወይም
ለወሲብ ራሱን እንዲያዘጋጅ ንገሪው:: ደግሞ በኮንዶም ተጠቀሙ በድንገ ስጥም
postpill በቀናት ልዩነት ውስጥ መውሰድ አደጋው ላንቺ ከፍተኛ ነው ተናግሬ
ከፊቷ ላይ ድንጋጤ አነበብኩ::

" ምነው?"

" አይ እሱም እንደኔው ጀማሪ ነው"

" እ! እ...እ! ልምዱ ከሌለው ኮንዶም በደንብ ሳያጠልቅ ከቀረ እኮ አንቺ
ውስጥ ሊቀር ይችላል! ብልትሽ ውስጥ ኮንደሙ ጠለቀ ማለት ከፍተኛ ችግር ነው::
ኮንዶሙ ሊቀደድ ይችላል"

አስፈራራዋት:: አይኑዋ ፈጠጠ:: ወዲያው ተናገርኩ::

" ልጅ ዳናይት እኔ ልተባበርሽ እችላለሁ! ምናልባት ፍቅረኛሽ ሌላ
ከሚከትሽ"

"እ! እውነት በጣም አመሠግናለሁ"

የተወሰነ ነገር ነግሬያት ተለያየን:: በሶስተኛው ቀን 3:30 ላይ መጣች:: ሲደከመኝ
የምልበት ክፍል እና የመርፌ አገልግሎት ብቻ የምሰጥበት ክፍል ውስጥ
አስደሰትኩዋት! አሳበድኩዋት ! ዳናይት ጣማት መሰለኝ በሰባተኛው ቀን ተመልሳ መጣች
ዳግም አስደሰትኳት ... አሳበድኳት... ከዚያ በኋላ ጠፋች !! ግልግል::

## 3 ሳምንት አለፈ

ዕለተ ሐሙስ ጠዋት ... ፕሮፌሰሩ በመከሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ ያነሱት
እያንቃጨለብኝ ነው... ራሴን በጥያቄ እየወጠርኩት ነው...

እውን ትላንት የአክሱም ...የላሊበላ...የፋሲለደስ ... የመሰሉት የሀገር ግንባታ
ኢትዮጵያ ከነበራት ... ትላንት ይቺ ኢትዮጵያ የምንላት ሀገር ታላቅ ከነበረች ... ለብዙ
ሁሉ የምግብ እርዳታ ትሰጥ ነበር ከተባለ .. በስልጣኔ ቀድማ የባነነችው ኢትዮጵያ
ከተባለ ... ያ ትላንት የነበራት ምርጥ ታሪክ! ስልጣኔ! አንድነት! ፍቅር!

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

መተሳሰብ! ኢትዮጵያዊ ኩራት! ኢትዮጵያዊ ወኔ!... ለዚህ ትውልድ ሳይተላለፍ ለምን ከሸፈ? ...ፕሮፌሰሩ " ምቀኝነት" ብለዋል ... ሌላስ? ይቺ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር የምን በከፍታማማ ላይ መቀመጥ አቃታት?... ብዙ ነገሮች አዕምሮዬ ላይ ተመላለሱ:: በመጨረሻ የሚከተሉት ችግሮች አዕምሮዬ ላይ መጡ:: በኔ እይታ ኢትዮጵያዊያን በሁሉ ነገር የበለፀጉ በእነዚህ አስራ ሁለት ችግሮች የተነሳ ነው:: እነዚህ ችግሮች እስኪ ድረስ ይቺ ኢትዮጵያ የምንላት ሀገር እንኳን የተስፋይቱ ምድር ልትሆን ... ለማንኛውም አስራ ሁለቱን ዋና ችግሮች በዝርዝር ፃፍኳቸው

1. በወሬ A++ መሆን
2. በትንሽ ነገር መኩራራት
3. ሁነኛ እና እውነተኛ መሪ ማጣት
4. "እኔ ከሞትኩ ሥርዶ አይብቀል..." አመለካከት
5. ለትችት/ ለለውጥ/ ዝግ መሆን
6. በትንሽ እውቀት መመፃደቅ
7. ብሔር እና ብሔርተኝነት ... ቋንቋ
8. የፈረንጅ አምላኪነት
9. ባዶ ተስፈኝነት
10. ምቀኝነት! ጥገኝነት ጨለምተኝነት ! ጠባብነት
11. አከክልኝ ልከክልህ ባዮች መብዛት
12. ደካማ የሥራ ባህል

እንግዲህ ለሀገራችን ኢትዮጵያ ወደ ኋላ መቅረት ሆነ በሁሉ ነገር መከሸፍ በኔ እይታ ያስቀመጥኳቸው ከላይ ያሉት ችግሮች ናቸው:: በእርግጥ ሌሎች ችግሮች የሉም ማለቴ አይደለም... መቼም ለም መሬት ፣ብዛት ያላቸው ወንዞች .. ለኑሮ የሚመች የአየር ንብረት የተፈጥሮ ሀብት ... በርካታ ህዝብ ... አዋቂዎችና ጠቢባን .. እያለን ማለወጥ ሆነ ማደግ ካቃተን በእርግጠኝነት ማህበረሰባችን ላይ ከላይ ከጠቀስኳቸው ችግሮች ሌላ


t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ተጨማሪ በርካታ ችግሮች መኖራቸው የግድ ነው ... በኔ እይታ ዋነኛ ማነቆ የሚሆኑት ግን ከላይ ያሉት 12 ችግሮች ናቸው:: እስቲ በወፍ በረራ ልዘርዝራቸው .. እንመልከታቸው!!

## በወሬ A++ መሆን

"Actions speak Louder than words"

* ድርጊቶች ከቃላት በላይ ይናገራሉ!

በእርግጠኝነት በወሬ ሽልማት ቢኖር ዋንጫ የሚሰጣቸው ህዝቦች ኢትዮጵያዊያን እንሆን ነበር:: አብዛኛው ጊዜያችን የሚቃጠለው በፍሬፍስኪ ወሬ ነው... ተማሪው ወሬኛ_ አስተማሪዎች ወሬኛ... መሪዎቻችን ወሬኛ... ፀሐፊዎቻችን ወሬኛ... ኤፍኤምኦቻችን ወሬኛ...ሬዲዮኖች ወሬኛ... የሚወጡት ጋዜጦች ፣ መፅሔቶች ... መፅሐፎች ቴሌቪዥኑ ወሬኛ... አገሪቱ ሁሉ በወሬኛ ተወጥራለች! አገሪቱ ሁሉ በሀሜተኞች! በወሬኞች! በአለቅላቂዎች! እንቶፍንቶውን በሚቀባጥሩ ወሬኞች ተሞልታለች! መስሪያ ቤቶች፣ ት/ቤቶች_ ትላልቅ ድርጅቶች .. ባለስልጣናቱ ... ተቃዋሚዎች.. ብቻ ሁሉም ከጠዋት እስከ ማታ ወሬ ይዘራሉ ... ወሬ ያጭዳሉ.. አሉ.. ተባለ ..ይባላል...ሀሜት ... እነዚህ ሁሉ የተፈጠሩት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው!! ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች በየሻይ ቤቱ፣ በየካፍቴሪያው፣ ጫትቤቱ፣ መጠጥ ቤቱ ... ተቀምጠው የማይረባ ወሬ ይከካሉ.. የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በቤተመፅሐፍ ውስጥ ተቀምጠው የሚከኩት ወሬ ነው... በኛ ሀገር ባህል የሚሠራ ሳይሆን ትልቅ ክብር የሚሰጠው ወሬኛ ነው! በተለይ ቆሽቴን የሚበጥሰኝ ምንም የሚሠራው ስራ ሳይኖረው በሰው ላብ እየኖረ የሚሠራውን ሰው የሚያናንቅ እና የሚተች በዛኔ ነው!!... ብቻ በሀገሪቱ ወሬ A++ ላይ ደርሷል... በየቦታው ከትንሽ እስከ ትልቁ ቅድሚያ የሚሰጠው



t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ለሀሜት ፣ ቡጨቃ... ዝልዘላ.. ቆርጦ መቀጠል ... አሉባልታ .. እንጂ ስለውጥ እና ለኢትዮጵያ እድገት የሚጨነቅ የለምና ስለዚህ በወሬኛንታችን መከሸፍ ተፈጠረ!!... አንድ በሉ (1)

# በትንሽ ነገር መኩራራት

አብዛኛው ኢትዮጵያዊያን ህልማችን ትንሽ ነች፡፡ ለዚያውም ህልም ካለን ነው፡፡ ከHighschool –University በጣም የሚገርመኝ በጣም ጎበዝ የምላቸው ተማሪዎች ራሳቸው ህልማችሁ ምንድ ነው? ከአምስት ዓመት በኋላ የት ትደርሳላችሁ? ለኢትዮጵያ ምን ትሰራላችሁ.. ስላቸው መልስ አይሰጡኝም፡፡ በግልፅ የነቀመጡት ህልም የላቸውም፡፡ ራዕይ የላቸውም፡፡ ይህ ከግለሰቦች የሚጀምር ህልም አልባነት ወደ መንግስት ከፍ ይላል... አንድ ባለሱቅ መላ ሕይወቱን ያቺን ሱቅ አሻሽሎ ሌላ ሱቅ ካልከፈተ .. ህልም የለውም! አንዳንዴ ሳትብሉኝ የውሸት ከምር የሆነውን ETV ዜና ስመለከት በንዴት እቃጠላለሁ..." በእከሌ ወረዳ የተሠራው ድልድይ በዛሬው እለት ከፍተኛ ባለስልጣናት በተገኙበት በታላቅ ድምቀት ተመረቀ" እንዴ ለአንዲት ትልቅ ሀገር አንዲት የድልድይ ምረቃ አካብዶ ማሳየት በጣም ያሳፍራል... ይሄ በትንሽ ነገር መኩራራት ነው እንደ ዜና መቅረብ ያለበት "ኢትዮጵያ ውስጥ ነዳጅ በቁፋሮ ተገኘ ... ሁለት ቢሊዮን ብር የፈጀው የባቡር መንገድ ተጠናቆ... ተመረቀ.. የህዳሴው ግድብ ተጠናቆ ያለ እንዳች የፈረንጅ እርዳታ በራሳችን ታላቅ ጥረት ተሰርቶ ተመረቀ.. ለኢትዮጵያዊያን ታላቅ የለውጥ በር የሚከፍት ግኝት ይፋ ሆነ ... በኢትዮጵያ ታሪክ በጣም ዘመናዊ አለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ስታዲየውም ተገነባ..." አይነት ዜና መሆን አለበት እንጂ አንድ ኪሎ ሜትር መንገድ ተመረቀ አይነት ዜና ምን ያህል አገሪቱ በትንሽ ነገር እንደምትረካ ያሳያል ... ይህ ደግሞ በሽታ ነው!! ኢትዮጵያዊያን በትንሽ ነገር እንመካለን ያቺን ትንሽ ነገር መለወጥ እንፈልግም በቃኝ እንላለን! ህልማችን ትንሽ ናት! ራስን ለማፅናናት ሀብታም መሆን ሀጢያት ነው! ሀብታም ገነትን ከሚወርስ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ብትሾልክ ይሻላል... ሀብታም መሆን አንቅልፍ ማጣት ነው እያልን (እየተባልን እየተሰበክን) ባለችን ትንሽ ነገር እትል ተሸውደን ከሳሎን ቤት ይልቅ ማደቤት ውስጥ መኖርን

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

መርጠናል ... በተለይ ኢትዮጵያዊያን ሴቶች በጣም ያነዱኛል -ህልም የላቸውም! በዛ ቢባል ከዩኒቨርሲቲ መመረቅ → ባልማግባት → የቤት እመቤት መሆን → ተቀምጦ የባልን እጅ መጠበቅ →ወሬ መከካት ...!! ከወንዶች በጣም የተሻለውን ያላቸውን IQ ቢጠቀሙበት ለሀገሪቷ እንዴት በጠቀሙ ነበር:: እኔ በግሌ ለሴቶች የተለየ ጥላቻ የለኝም! ንቀትም የለኝም:: ወንድንም ሴትንም የፈጠራቸው እግዜር ነው:: እግዜር የፈጠረውን ነገር ማመዛዘን እና ማጣጣል ራሱ የአዕምሮ በሽታ ነው... እኔ እያልኩ ያለሁት አንድን ሰው መገመት ሆነ መወዳደር! ማክበር ሆነ መናቅ ያለብን በአስተሳሰቡ ነው! በዚህ መሰፈርት እኔ ለሴቶች ንቀት አለኝ በጣም ያበሳጩኛል! ለዘመናት የወንድ እጅ ጠባቂ መሆን ማብቃት አለበት! ለዘመናት ይቺን መሬት ያሽከረከሩዋት ወንዶች ናቸው አሁን ተራው የሴቶች መሆን አለበት! ወንድ በችሎት ሴት በማጀት የሚል አባባል ማብቃት አለበት ... በቃ ሴቶች እኔ እውነቱን ልንገራችሁ.. ምራል ጥበቃ ምናምን የሚባል ነገር አላውቅም! ነቃ በሉ! በቃላት ኳኳታ አትሸወዱ! እውቀታችሁን ተጠቀሙበት ! ከወንድ ጥገኝነት ውጡ! የወንዶች በአመለካከት ይሁን በገንዘብ የበላይ የመሆን ዘመን ማብቃት አለበት እንዴ እስከመቼ ወንዶች የፃፉትን መፅሐፍ.. ወንዶች ያዘጋጁትን ፊልም .. ወንዶች የሰፉትን አልባሳት .. ትጠቀማላችሁ ! በቃ የእናንተ ዘመንም ተራው አሁን ነው!! በዚህ አጋጣሚ ሴቶች እናተን የሚያነቃቃ እጅግ ምርጥ መፅሐፍ ነውና ግዙትና አንብቡት! ደራሲው Dr. Myles Munroe ሲሆን ርዕሱ Understanding the purpose and power of woman የተሰኘ ስለሴቶች ብቃት የሚያወራ መፅሐፍ ነው:: ግዙት አንብቡት ... እንዴ ስለ እናንተ ብቃት ለማወቅ ከፈለጋችሁ እንደው በእናታችሁ Google ላይ "A book written on Woman" የሚል search አድርጉ... ምን ያህል እግዜር በሰጣችሁ IQ እንዳልተጠቀማችሁ ይገባችሁል (ሴቶች በኋላ መልሰን እናወራለን) ብቻ ሀገሪቱ ውስጥ ከግለሰብ እስከ ማህበረሰብ እስከ ትልቁ ሀገር ድረስ በትንሽ ነገር በጣም እንኩራራለን! ህልማችን ትንሽ ነው! ተማረውም አስተማረውም ነጋዴውም .. የተማረውም ያልተማረውም.. ገበሬውም ህልማቸው ትንሽ ነው! ትልቅ ራዕይ የሚባል የለንም! ስለሌለችን

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

ትንሽ ነገር እያወራን ዘመናችን ያልቃል! ይህ ሚስኪን ህዝብ እየተራበ እኮ ነው እግዜርን የሚያመሰግነው! እግዜር ራሱ ከትብሎ የሚስቅብን ይመስለኛል::

መቼም ግለሰቦች ሆኑ ሀገሪቷ በትንሽ ነገር የምትኮራ ከሆነ እድገት ስልጣኔ ሰውጥ ትከሸፋለች! እነ አሜሪካ! እንግሊዝ! ስፔን! ጃፓን! እስራኤል ያደጉት ሀልማቸው ትልቅ ስለሆነ እና በትንሽ ነገር ስለማይረኩ እንዲሁም ያላቸውን ብቃት ስላመኑ ነው:: ኧረ እንደ ከUSA ሀገን በማደጎ ለመውሰድ የመጣ ጓደኛዬ ያለኝን ንግግር ልንገራችሁ " እስቲ ኢትዮጵያን ከአሜሪካ አንፃር አነፃፅርልኝ" አልኩት

"WHAT ! OMG!" ብሎ በጣም ደንግጦ ከቆየ በኋላ የሚከተለውን አለኝ በአማርኛ ስተረጉመው እንዲህ የሚል ፍቺ ነበረው::

" ብርሃንን ከጨለማ የማነፃፀር ያክል ነው! አሁን አገራችሁ ኢትዮጵያ ያላት እድገት ስልጣኔ የኑሮ ዘይቤ... ከአንድ መካከለኛ የአሜሪካ ስቴት ጋር እንኳን አይወዳደርም! ገና ብዙ ነገር መስራት አለባችሁ! ኢትዮጵያ ከአሜሪካ አንፃር ገና ገጠርናት! ገና ዳዴ እያለች የምትገኝ ነጠር! ህዝቡ ጠንክሮ ከመስራት ይልቅ ወሬ እና እንቅልፍ ያበዛል "... ይሆን እያሰላሰልኩ እያለሁ ነበር ሁለተኛዋ ችግረኛ ወጣት የመጣችው:: ከእርሷም ላይ ልክ እንደ ዳናይት ሁሉ ድንጋጤ ይነበብ ነበር... በፈገግታ ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ተቀበልኳት እንደምንም ትንፋሽ አሰባስባ ተናገረች "የሆነ ነገር እንድትረዳኝ ነበር" ምንም ሳልናገር በፍጥነት ተንደርድሬ በሩን ዘጋሁት:: " ዝግ ነው" የሚለውን ፅሁፍ ሰቀልኩት! ዳናይትን ያስቀመጥኳት ወንበር ላይ አስቀመጥኳት::

" ዳዊት እባላለሁ! የዚህ መድኃኒት ቤት ባለቤት ነኝ ምንም ሳትጨነቂ ንገሪኝ የምችለው ነገር ከሆነ እረዳሻለሁ"

" አመሰግናለሁ"

" ስምሽ ማን ነው?"

" ፌቨን ታደሰ"

" እሺ ፌቨን ምን ልርዳሽ ?"

" እህ... የወር አበባዬ ቀረብኝ"

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

"ፊቨን"

" አቤት"

" እንድረዳሽ ከፈለግሽ ሳትጨነቂ ሁሉንም ንገሪኝ?" አልኳት ሚስጥሯን ለመስማት በጣም ቋምጬ::

" ሀያ ሁለት ዓመቴ ነው:: የዛሬ ሁለት ዓመት አግብቼ ባለትዳር ነኝ:: ከሰምንት ወራት በፊት ለሥራ ጉዳይ ባለቤቴ USA ሄዷል:: በመሀከል የመጀመሪያ ፍቅረኛዬን አገኘሁትና አንድ ሁለት ሰንባባል አቤት ወስጇው አብረን አደርን... ወሲብ አንድ ጊዜ ብቻ ነበር ያደረኩት_ የወር አበባዬ ግን ቀረ"

" ምናልባት ቀን ተዛብቶብሽ እንዳይሆን?" የወር አበባ የሚዛባባቸው ምክንያቶች አሉ" 13

" በጭራሽ! የሽንት ምርመራ አድርጌ አውቄያለሁ"

በዝምታ አየኋት:: ከብ ፊት አላት:: ትላልቅ ጡቶች አሏት::ከዚች ወጣት ጋርም የሆነ ዘዴ ፈጥሬ ወሲብ ማድረግ እንዳለብኝ ወሰንኩ::

" እና ምን ወሰንሽ?"

" ፍቅረኛዬ ይህን ጉዳይ ከሰማ ያለ ጥያቄ ትዳራችን ይፈርሳል... ስለዚህ ልጁን ለማስወ...ጣት .. ነው"

" እንደምታውቂው ህጋዊ ካልሆን እና በፍርድ ቤት ውሳኔ ማለትም ወይ በመደፈር አልያም ከቅርብ ዘመድ (ቤተሰብ) የመጣ እርግዝና ካልሆነ በህጉ መሠረት ማስወረድ ወንጀል እንደሆነ ታውቂያለሽ?"

"ሰምቻለሁ! ለዚህ ነው አንተ እንድትረዳኝ የፈለኩት"

ወዲያው ውርጃ በድብቅ የሚሠሩ አራት ሆስፒታሎች እና ዶክተሮች ጓደኞቼ ትዝ አሉኝ .. በእጄ ቆይ አንድ ጊዜ የሚል ምልክት ሰጠኋትና ወደ ዶክተር ተሾመ ዘመድኩን ደወልኩ... ጉዳዩን ገና ሳነሳ "ዴብ ባንተ የመጣ ከሆነ ጣጣ የለውም የመጨረሻ ዋጋ **** ብር ነው.. አመስግኜ ሌሎቹም ጋር ደወልኩ **** ... **** ... **** ብር አሉኝ:: ለፊቨን

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

"ሰው የማገኝ አይመስለኝም"

" ይህ የመጀመሪያ ፍቅረኛዬ ያልሽውስ?"

"አዲስ አበባ ለስራ ጉዳይ ድንገት መጥቶ ነው:: ሚስቱ ጋር ነው ያለው"

" ብዙ አትጨናነቂ ሰው ከጠፋ እኔም ልረዳሽ እችላለሁ::"

ሳቀችና ዝም አለች:: እያዋራኋት መርፌ ክፍል ውስጥ አስገባዋት.. እረ በቃ እውነቱን ለመናገር ፈጣን ሀይለኛ ወሲበኛ ነች! አስደሰተችኝ! አስደሰትኳት.. ሄደች:: ባለፈው ቀን ስቲም ባዝ ምናምን ገብታ፤ አምራ ተውባ ተኳኩላ ... ዘንጣ.. ባጠቃላይ ሽርሞጥሞጥ ብላ (ሴቶች ይቺን ቃል አትወዱዋትም አይደለም ይቅርታ እንግዲህ ልቅ ነገር ስለሆነ ነው) መጣች:: ተደሰትን..በሌላኛውም ጊዜ ተደሰትን... ውርጃው ተፈፀመ:: እኔ ግን ደስታ እና 1200 ብር የድላላ አገኘሁ!!...

የዳዊት ወንጭፍ መድኃኒት ቤት ቀስ በቀስ ታወቀች:: ሰው በሰው ወሬ እየተቀባበሉ . ገላወረድ የሚመጡ ሴቶች በዙ፤ ስራው ጦፈ... ብቻዬን መስራት ስላቃተኝ አንዲት ሴት ቀጠርኩ... ባለችኝ ትርፍ ሰዓት ለመላው የኢትዮጵያ ሚስኪን ህዝብ የመከሸፍ ታሪካችንን ለማከሸፍ መላው ህዝብ የሚውጠውን ታላቅ የለውጥ መድኃኒት ለማዘጋጀት ፕሮጀክት ቀጥያለሁ... የምቀምመው መድኃኒት ከላይ ያሉትን የጠቀስኳቸውን 12 አብይ ችግሮች ከመላው የኢትዮጵያ ሚስኪን ህዝብ ውስጥ ሊያጠፋ የሚችል እና ህዝቡን በከፍተኛ አስተሳሰብ! በፍቅር! በመተሳሰብ! በአንድነት! በወኔ! በሞራል! በሥነምግባር! በታታሪነት! በሠራተኝነት! የሚሞላ የለውጥ መድኃኒት ነው... ቀምሜ ስጨርስ የምሸጠው ልክ እንደ postpill በ7 ብር ብቻ ነው ... ከዚያ መላው የኢትዮጵያ ሚስኪን ህዝብ ያቺን መድኃኒት ይወስድና ለኢትዮጵያ የለውጥ በር ድርሻውን ይወጣል! ያ ሰንቶች ሲያከብሩት! ያሰንቶች ሲፈሩት! ያሰንቶች ሲርበደበዱለት... ያ ሰንቶች ሲንቦቀቦቁለት .. ያ ታላቅ ግርማ ሞገስ

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

የሚረው! ያ አስፈሪው ጎልያድ በትንሹ ብላቴና ዳዊት በወረወራት ጠጠር እንደ ወደቀ ሁሉ..
ይህ ግዙፍ የኢትዮጵያ ችግርም በኔ በዳዊት መድኃኒት ድባቅ ይመታል! ለዚህ እጅግ ወሳኝ፣ እጅግ ድንቅ! እጅግ ችግርም ፈቺ መድኃኒቴ የሰጠሁት ስያሜ የዳዊት ወንጭፍ ነው! እልፍሬድ ኖቤል ለሀገሩ ታላቅ ነገር እንደሠራ ሁሉ እኔ ዳዊትም ስለሀገሬ ኢትዮጵያ ችግር እያወራው ሞት ሳይሆን ታላቅ ነገር ሠርቼ ከመቃብር በላይ እሆናለሁ!!

## ሁነኛ እና እውነተኛ

## መሪ ማጣት

"የሰዎችን ደካማ ጎን ተጠቅሞ ማሸነፍ ራሱ ድክመት ነው" የሚል ትልቅ አባባል አለ.. መሪዎቻችን የሚተገብሩት ይህን ነው ለዘመናት ኢትዮጵያ ውስጥ የነገሱት መሪዎች ትልቁ ግባቸው ኢትዮጵያን በከፍታ ማስቀመጥ ሳይሆን የራስን ጥቅም ለማስከበር መራወጥ እና ልዩ እና ፍፁም ሆኖ ለመታየት ከተቻለም ለመመለክ እንቶ ፍንቶውን ሲሠሩ... ዘመናቸው ያልቃል! የኢትዮጵያን ችግር ለመፍታት ከማስተባበር ይልቅ የስልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም ስማይ መጠጥ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ!! ህዝቡን ያስፈራራሉ! ህዝቡን ይገላሉ! በስመ ዲሞክራሲ ይነግዳሉ! የህዝቡን ለዘመናት የሰፈረውን የፖለቲካ ፍርሀት ከማጥፋት ይልቅ ተጨማሪ ፍርሀት ይሞሉበታል! በትንሽ በትልቁ እናቱን በትልቅ መደሻ ይወግሩታል! ሶስት በሉ(3)

(ምርቃት ፡ መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ ገፅ 1-28 ያንብቡ)

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

## "… እኔ ከሞትኩ ሥርዶ አይብቀል"

## አመለካከት

አሜሪካዊያኑ..እንግሊዛዊያኑ … እስራኤላዊያኑ አቅድ ሲነድፉ… አንድን ነገር ሲሰሩ.. አመለካከታቸው በትንሹ ለ100 ዓመታት የሚቆይ ነው:: ከትንሽ እስከ ትልቁ ሥራ እነርሱ ከሞቱ በኋላ የሚመጣውን ትውልድ ታሳቢ ያደረገ ነው… የሚሠራው መንገድ ፣ የሚሠራው ቤት ፣ የሚረቀቀው ህግ.. ለቀናት ብቻ የራስን ፍላጎት ብቻ ለመጠበቅ የሚሠራ አይደለም፣ ለዘመናት እንዲቆዩ በጣም ታስቦ በከፍተኛ ጥንቃቄ ይሠራል እንዲህ አይነት አመለካከት በጣም ደስ ይላል! እኛ ኢትዮጵያዊያን እኔ ከሞትኩ ሠርዶ አይብቀል በሚል አመለካከት ተሞልተናል… ያለንን ጥበብ ከማውረስ ይዞ ወደ መቃብር መውረድ እንወዳለን .. ዝነኛ ሙዚቀኛ፣ ዝነኛ ደራሲ፣ ዝነኛ መድኃኒት አዋቂ፣ ዝነኛ ተናጋሪ .. ዝነኛ ተዋናይ .. ያለውን ጥበብ እንኳን ለሌላው ለገዛ ልጁ በእኔ ከሞትኩ … ተሞልቶ ሳያወርስ ሆነ ሳያስተላልፍ መቃብር ይዞት ይወርዳል :: በሀገሪቱ ሙሰኝነት ፣ ጉቦ መቀበል፣ ለኔ ብቻ ባይነት ፣ ስግብግብነት ምንጩ ምንድ ነው? እኔ ከሞትኩ ሠርዶ አይብቀል አይደለምን? በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ያደረጉትን መቼም ሰምታቹኋል? ሲመረቁ ሲሉ መፅሐፍ ይቀዳሉ… የመኝታ ቤታቸውን በር፣ መስኮት ይሰብራሉ… የመታጠቢያ ዕቃዎችን ይሠብራሉ.. በቃ እነርሱ ተምረው ስለጨረሱ ሌላ ተማሪ በእነዚያ ንብረቶች መጠቀም የለበትም! ስለራሳቸው እንጂ ለሌላው ግድ የላቸውም! ራስ ወዳድነት! ባጠቃላይ ግለሰቦች.. ማህበረሰቦች .. መንግስት … ተቃዋሚዎችም … የተማረው ያልተማረው… ሀብታሙ.. ደሀው.. መላው ህዝብ በእኔ ከሞትኩ ሠርዶ አይብቀል … ከተሞላ … ታዲያ ይህን መሰል ዘግናኝ አመለካከት ይዘን ኢትዮጵያ እንዴት አትከሽፍ.. አራት በሉ (4)

ለትችት … ለለውጥ ዝግ መሆን

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

"ባለ አእምሮ ልጅ የአባቱን ተግሳጽ

ይሰማል፤ ፌዘኛ ግን ተግሳጽን አይሰማም"

በዓለም ላይ ማንም ፍፁም የለም! ከትሊኖርም አይችልም! እያንዳንዱ ሰው የራሱ እንድ ከፍተት አለበት.. ይህ ግዙፍ እውነታ ነው!! እኛ ሀገር ከትንሽ እስከ ትልቁ ... ተማሪው _ አስተማሪው ... ደራሲው ... ጋዜጠኛው ፤ ባለስልጣኑ፤ ተቃዋሚው... ብቻ ሁሉም የሚሻው ሙገሳን ነው! መወደስን ነው! ከፍ ከፍ የሚያደርገውን ምላስ ነው! እኔ ልክ ነኝ ብሎ ማሰብን ነው! አልሳሳትም ብሎ ከችች ማለትን ነው! ሂስ! ትችት የሚያቀርብ ጠላት ነው! ይህ ከግለሰብ እስከ መንግስት ድረስ የወረረን በሽታ ነው ለዚያውም ግዙፍ በሽታ!!! ለመንግስት አንድ አስተዋይ አዋቂ ተነስቶ ይህ ነገር መለወጥ አለበት ይህ አግባብ አይደለም ይህ በዚህ ነገር መሻሻል አለበት የሚል ሀሳብ ቢያቀርብ ጠላት ነው... አሸባሪ ነው አገር አጥፊ ነው... ተቃዋሚ ነው.. ብሎም ይህ ኢትዮጵያዊ አይደለም ተብሎ ወደ እስር ቤት አልያም ወደ ሞት! ይላካል... እስቲ ራሳችሁን ታዘቡት ትችት ትወዳላችሁ? የሰውን ደካማ ጎን አይታችሁ አሻሽል ብላችሁ ትችት ታቀርባላችሁ?... ምላሹ ምን ይሆናል? እስቲ የምትሰሩት መስሪያ ቤት ላይ ትችት አቅርቡ _ ቀይ ካርድ ይከተላቹኋል... የእድገት በር የሚከፈተው በትችት ነው! በኛ ማህበረሰብ ለመከበር ሆነ ለመወደድ ውሸታም መሆን ብቻ ይበቃል ... ሙተችት ሆነ እውነትን መናገር በኛ ማህበረሰብ ... አያስከብርም! እውነት ከሚናገር ይልቅ የሚሸነግል እና የሚወሸከት ሰው ይከበራል! ጥበቡ ወርቅዬ 'ከሰው ጋር ለመኖር አቋራጭ መንገዱ ለካ ማስመሰል ነው' ሲል የዘፈነው እኮ ትልቅ እውነታ ነው! የኛ ማህበረሰብ ማንነትን ያሳብቃል!! ታላቁ Martin Luther king `if you have no critics you will likely have no success` ያለው ትልቅ የማይካድ እውነት ነው:: በቀላል አማርኛ 'ስለ ስራህ አስተያየት የሚሰጥ / የሚተች/ ከሌለ በጭራሽ ለስኬት አትበቃም

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

እንደማለት ነው:: ትችትን የሚቀበል አዕምሮ በቀና አመለካከት የተሞላ ነው:: እ... አስተሳሰብ ያለው! እኛ ኢትዮጵያዊያን መሸንጋል! መፎጋር! መመሳሰል! የውሸት ... የውሸት የቃላት ክምር እንጂ ትችትን ጨርሶ አንወድም... የሚተች ታላቅ ጠላታችን ነው!!

አምስት በሉ (5)

## በትንሽ እውቀት

### መመፃደቅ

የዘጠነኛ ክፍል የኢንግሊዝኛ አስተማሪያችን ሲፈርምልን "Lkid" እያለ ነበ... የዘወትር ንግግሩ I Hate Lkid ነበረች:: Little knowledge is dangerous ማለ... ነበር... ግዙፍ አባባል ናት! ትንሽ እውቀት በጣም አደገኛ ነች! ትንሽ እውቀት መርዝ ና... ትንሽ እውቀት አስተሳሰብን ታውራለች! ትንሽ እውቀት ግትር ታደርጋለች! ትንሽ እው... ልብን ታሳብጣለች! ትንሽ እውቀት ነገሮችን ሁሉ በአንድ ዓይን ብቻ እንድንመለ... ታደርጋለች! ትንሽ እውቀት ያለው ሰው ሁሉን ነገር ያወቀ ይመስለዋል.. ያ ፈላስፋ ሶቅራጠ... እንኳ በመጨረሻ ያለው " በመጨረሻ አንድ ነገር አወኩ እሱም አለማወቄን ማወቄ ነው" ነ... ያለው! ኢትዮጵያ ውስጥ እኔን ጨምሮ ብዙዎች በትንሽ እውቀት እንመፃደቃለን! ትን... እውቀት ያለው ሰው እኔ ብቻ አውቃለሁ! እኔ ብቻ ያልኩት ልክ ነው... እኔ አልሳሳትም... እኔ ..እኔ.. እኔ በሚል ትምህክት ይወጠራል!! ትንሽ እውቀት ተናገር እንጂ አድምጥ አትልም... ትንሽ እውቀት ተቆጣ እንጂ ታገስ አትልም! ትንሽ እውቀት ዋሽ እንጂ ለእውነት ዘብ ቁ... አትልም ትንሽ እውቀት ጨለምተኛ ታደርጋለች አንድ ድግሪ ያለው ከሱ በላይ አዋቂ የለም... ቢቃ ለሱ የእውቀት መጨረሻ እና ጣሪያ አንድ ዲግሪ መያዝ ነው.. በትንሽ እውቀት የሚመ... ማህበረሰብ ያላት ኢትዮጵያ እንዴት ትደግ... ስድስት በሉ (6)

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

እነዚህን ነገሮች እያውጠነጠንኩ … የእነዚህን ችግሮች መቅረፊያ መድኃኒት ለመፈለግ ታላቅ ጥረት እያደረኩ ቀናት እያለፉ ነው:: የዳዊት ወንጭፍ መድሃኒት ቤቱ አዘዋዋሪች ነው:: አዲስ የቀጠርኳት ወጣትም ፈጥጋታ ያላት እና ስራ ላይ ቀልጣፋ ስለሆነች በፍጥነት ንግዱን ለምደዋለች… በዚያ ላይ ራሷን ለመለወጥ የግቷ ስለምትማር እደንቃታለሁ:: በቃ እንደዚህ አይነት ሴቶች ናቸው የሚመቹኝ!! (ሴቶች ቅድም ያነሳሁትን ወቀሳዬን እንዳዉርስ) ጠንካራ ሴቶችን በጣም እወዳለሁ! ህልማቸው ትልቅ የሆኑ ሴቶች ያማርኩኛል! በዓለማችን ላይ አንድም የቤት ፈላስፋ እንኳን የሌለው ሴቶች ህልማቸው ትንሽ በመሆኑ ነው _ ለዚያ ነው በጣት የሚቆጠሩ ሴቶች ብቻ በዓለማችን ላይ ከስኬት ማማ ላይ የተቀመጡት የኛ ሀገር ሴቶች ኢትዮጵያን ለማሳደግ ምን ማድረግ አለብኝ ብሎ ከመጨነቅ ይልቅ Face book ላይ Tag (ታግ) ያደረጉት ፎቶ ላይ የሚሰጣቸው አስተያየትን ለማንበብ ይጨነቃሉ ! ይጓጓሉ! ጭንቀታቸው ስለ ሀገራቸው ኢትዮጵያ ደሀ መሆን ሳይሆን ስለ ጥፍር ቀለም መወደድ! ስለ ኮስሞቲክስ መወደድ፣ ስለጡታቸው! ስለ ዳሌያቸው! ስለ ወገባቸው… ነው!! አይ ከንቱነት! ለሴቶች አሁንም በድጋሚ እነግራቿለሁ ከወንዶች የተሻለ IQ አላችሁ! አባካችሁ ተጠቀሙበት! ዓለምን በጥበብ ሞሉበት… በዚያ ላይ ሴቶች እንዳይሠሩ ሲያደናቅፏቸው ከአንድ ጠንካራ ወንድ ጀርባ አንዲት ሴት አለች የሚል ስላቅ ወንዶቹ ይዘዋል! _ በዚህ አጋጣሚ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ አምስት ሴቶችን ቀርቤ ርቄያለሁ ከመጨረሻዋ ጋ ስለት ወራት አብረን ቆይተናል… ቆንጆ ቢጤ ናት! በት/ት ጎበዝ ስለሆነች ቀረብኳት… ስሟ ፍቅር አዳነ ትባላለች! በውበቱዋ የተነሳ ነው Face book– people you may know ላይ ተመልክቼያት Add አድርጊኝ አልኳት … አደረገችኝ! በነገራችን ላይ Face book ላይ ቅድም እንዳልኳችሁ ላይ ሴቶች በጣም ያስቁኛል! ትልቁ ደስታቸው Photo ለጥፎ አስተያየት መቀበል ነው! መደነቅ ይወዳሉ! ስለራሳቸው ውዳሴ ይወዳሉ! ሽንገላ ይወዳሉ! እሷም Add ማድረጉዋን ስረዳ … የለጠፈችው Photo ስር ትኩረት ለመሳብ ቆንጆ ነሽ ግን ከጂርሽ በጣም ትልቅ ስለሆነ ያስጠላል የሚል ፃፍኩላት … ይህ የሰው ልጅ ትልቅ ድክመት ነው:: በተለይ ሴቶች አንድ ሺ የሚያደንቃቸው ወንዶች

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ቢኖሩ እና እንዱ ካጣጣላት ትኩረት የምትሰጠው ላጣጣላት ወንድ ነው!! ብቻ ብዙ ሳልችገር ተግባባን Because she was easy going .... ተዋወቅን ... ተባዳን... ከሰባት ወራት በኋላ ማንነቷን ሳውቅ ረከሰችብኝ! መዘንኳት ! በጣም ቀላ ተገኘች!! አላማዋ መመረቅ ፣ ስራ መያዝ፣ ማግባት፣ ልጅ መፈልፈል መሆኑን ስረዳ... ናኳት! በጣም የጠላዋት ግን በመጨረሻው ሰዓት አንድ አስቀያሚ ጥያቄ ጠይቃኝ ነው...

" ፍቅሬ"

"አቤት"

"አሁን ወሳኝ ጥያቄ መልስልኝ"

" እሺ"

" ታገባኛለህ"

" አገባሻለሁ! ግን ሁለተኛ ዲግሪ ለመማር እቅድ ካለሽ! ለኢትዮጵያ የሆነ ነገር ለመስራት እቅድ እና ትልቅ ራዕይ ካለሽ ብቻ ነው እንጂ ተጋብተን ወዲያው ልጅ ለመፈልፈል ከሆነ እውነቱን ለመናገር አልፈልግሽም! ምክኒያቱም ባለሽ እውቀት ለኢትዮጵያ የሆነ ነገር እንድትሰሪ በጣም እፈልጋለሁ! ይህን በጣም አስቢበት"

" እሺ"

በሳምንቱ ዘላ ተጠመጠመችብኝ::

" እሺ!! እስማማለሁ ግን አንድ ወሳኝ ጥያቄ አለኝ"

" ምንድ ነው?"

"ብሔርህ ምንድነው"

" ምን ማለት ነው?"

" ማለቴ አማራ፣ ትግሬ፣ ኦሮሞ፣ አደሬ፣ ጉራጌ..."

" ኢትዮጵያዊ መሆኔ አይበቃም?"

" ቤተሰቦቼ ማወቅ ይፈልጋሉ?"

በዚው ተጣላን:: በነገራችን ላይ የቀበሌ መታወቂያ ለማውጣት ስንት ፍዳ እንዳየሁ

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

ለመናገር ያስቸግረናል 'ብሔር' የለኝም ስላቸው እንግዳውስ መታወቂያ አይሰጥህም ብለውኝ በስንት ክርክር አሸንፌ ኢትዮጵያዊ አስብዬ ተቀብያለሁ!! አሁን ዘመኑ እግሬ _ ትግሬ_ ጃሺ አሮሞ_ የምንባባልበት ዘመን አይደለም! ይህ ዘመን ስልጣኔ ነው:: በዘመነ ስልጣኔ ሰው መሆን ብቻ በቂ መሆን አለበት! አብዱ ኪያር ዘፍኖት የለም እንዴ ? 'ምንድ ነህ አሉኝና ምንድነኝ ልበላት ጥቁር ሀበሻዊነት ከፊቴ እየታያት' ብሎ የለ? በተለይ ጥቁሩም ነጩም ሲጋና ደሙ ቢለያይም... "የአዳም ዘር" የሚለውን ምርጥ ሙዚቃ ስሙለት!!

እንግዲህ ትልቁ የኢትዮጵያ ችግር በዚህ በዘመነ ስልጣኔ በዘመነ ቴክኖሎጂ በዘመነ እውቀት ከግለሰብ እስከ መንግስት ህዝቡን እያወሩት ያለው_ ታውረን ያለነው... ራሱን ከፍ ሌላውን ዝቅ እያደረግን ያለ በመሆኑ ነው!! የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በየዩኒቨርሲቲዎቹ በየዓመቱ የሚደባደቡት እና ከፍ ሲልም የሚገዳደሉት ለምን ይመስላቹኋል? ኢትዮጵያን እንዴት ማሳደግ አለብን ብለው ተከራክረው በክርክሩ ባለመስማማት!! ... ወይ ጉድ!! በብሔር እና ብሔርተኝነት ነች!! ይቺን ርዕስ በሰፋት እንያት እስቲ የዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ እያለሁ ሳምንት የታሰርኩበትን ታሪክ ላጫውታችሁ:: በሀብረት ሆነን ባህር ዳር ከተማ የአባይ ወንዝ አጠገብ የተሰራውን የመታሰቢያ ሐውልት ... መቀሌ የሚገኘውን .. መስቀል አደባባይ የሚገኘውን ሐውልት... እንደ ትልቅ ነገር እያካበዱ ሲነግሩኝ በጣም ገርሞኝ... በጣም በሀዘን ተውጬ አለቀስኩኝ:: ምክኒያቱን ሲጠይቁኝ "እነዚህ ሐውልቶች እኮ የተሠሩት ኢትዮጵያዊያን ከግብፅ፣ ከኬኒያ፣ ከኢጣሊያ.. ተዋግተው እኮ ወይ አሸንፈው ወይ ተሸንፈው አይደለም! እነዚህ ሐውልቶች የተሰሩት ኢትዮጵያዊያን እርስ በርሳቸው ተጫርሰው ነው! ይህ ታሪክ ለምን መጣ ብሎ እንዳይደገም የሰውን እመለካከት ማስፋት እንጂ ሐውልት ማቆም ብቻውን ለኔ ትርጉም አልባ ነው! የግል ሀሳቤን የመናገር መብት ሊኖረኝ እና ሊከበርልኝ ይገባል! ኢትዮጵያዊ ሌላውን ኢትዮጵያዊ ገድሎት ነው! ምክኒያቱ አሳማኝ ይሁን አወዛጋቢ፣ የተፈፀመው ድርጊት ልክ ይሁን አከራካሪ እውነታው ግን እርስ በራሳችን ነው የተጨፋጨፍነው ...ለዚህ ንግግሬ ሳምንት ታስሬያለሁ:: ኢትዮጵያ ውስጥ ምን ያክል የመናገር እና ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት እንዳለ ታዘቡት ... እንዴ አንቀጽ 29 ሆ!

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

መንግስቱ ላይ የተቀመጠው ለኛ ሀበሻዊያን ሳይሆን ለፈረንጅ ነው እንዴ ? ወይስ እንዳያማ ጥራው እንዳይበላ ንሳው ነው? ለምንድ ነው ሀኃችን በወረቀት ላይ ብቻ የቀረው? ስለዚህ አመለካከታችን ትልቅ መሆን አለበት!! አማራ መሆን! ትግሬ መሆን! ኦሮሞ መሆን! ጉራጌ መሆን! ... መርጠነው የምናገኘው አይደለም.. ብናገኘው ራሱ ትርጉም የለውም!! ትርጉም ያለው የሁሉ መነሻ! የሰው ዘር ምንጩ አንድ ነው "የአዳም ዘር ነን" የሚል አመለካከት መያዝ ነው... በቃ ቋንቋችን ሊለያይ ይችላል! ይሄ ውብት ነው! በዓለማችን ላይ ስንት ቋንቋ አለ አይደለም እንዴ? ምድር ላይ እንኳ የተለያየ አፅዋት! አፅዋፋት! የተፈጥሮ ሀብት አይደለም ያለው? ነጭ፣ ጥቁር... ቅዝቃዜ ሙቀት ... ተራራ... ሸለቆ ... ምድረ በዳ ...በቃ ይሄ የተፈጥሮ ውብት ነው ... እኔ ለምን አማራ ነኝ... ትግሬ ነኝ.. ኦሮሞ ነኝ... አደሬ ነኝ... ትላላችሁ አላልኩም ያ መብታችሁ ነው! ደስታ የሚሰጣችሁ ከሆነ ማንነታችሁ ላይ ራሱ መነቀስ መብታችሁ ነው... ሁሉም ሰው አማርኛ ብሔራዊ መግባቢያ ቋንቋ ስለሆነ አማርኛን ብቻ መናገር አለበት እያልኩ አይደለም ... እኔ እያልኩ ያለሁት ሁላችንም ምንጫችን አንድ ነው! የሁላችንም ሀገር ኢትዮጵያ ናት... አመለካከታችን ሰፋ ያለ ይሁን! ትልቅ ይሁን! ቋንቋችን ምንም ይሁን ምንም ... ብሔራችን ምንም ይሁን ምንም ... ሁላችንም ሟች ነን!! የአከሌ ቋንቋን በመናገር! የአከሌ ብሔር በመሆናችን የተነሳ ከሞት አንቀርም!! በሌላ ቋንቋ ሁላችንም ተራዎች ነን! ሁላችንም እኩል ነን! ሁላችንም የሰው ልጅ ነን!! እግዜርም ሲፈጥረን ለየቅል አድርጎ ነው! አንዱን ከአንዱ አበላልጦ ግን አይደለም!! ስለዚህ ይህን ሀቅ አምነን በመቀበል ከመሰነጣጠቅ እና የጎንዮሽ ከመተያየት ከቋንቋ እና ብሔር ... ብሔርተኝነት ተኮር ወንዝ የማያሻግር ስሜት ወጥተን ኢትዮጵያዊ መንፈስ መላበስ አለብን!! የዚያኔ የተለያ ቋንቋ ብንናገርም... የተለያየ ብሔር ብንሆንም... ግባችን እና አመለካከታችን ኢትዮጵያዊ መንፈስ ብቻ ከሆነ ኢትዮጵያችን የሁላችንም ነችና በከፍታ ማማ ላይ ትቀመጣለች!! በቃ እኔ ሳልፈራ እና ሳልዋሽ ነው የምነግራችሁ! አሁን በየቦታው የማየው! የምሠማው፤ የሚሆነው ... ቋንቋ፤ ብሔር እና ብሔርተኝነት እንጂ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል መንፈስ ውስጡ ያዘለ አይደለም!! ይሄ መለወጥ አለበት! ትግራይ ውስጥ ዘመናዊ ሲታዲየውም

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ቢገነባ የሞያሌ ነዋሪ፣ የደብረዘይት ነዋሪ ኢትዮጵያዊ መንፈስ ውስጡ ካለ ሊያስደስተው ይገባል... የሐረር ግንብ ንብረትነቱ የኢትዮጵያ ህዝቦች ነው! የፋሲለደስ ግንብ ንብረትነቱ የኢትዮጵያ ህዝቦች ነው! አጋዴን ውስጥ ነዳጅ በቁፋሮ ሲወጣ ንብረትነቱ የመላው ኢትዮጵያ ነው! የአክሱም ሐውልት ንብረትነቱ የኢትዮጵያ ህዝብ ነው ... ቡቃ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ መንፈስ ካለን የዚህ ፎቅ ባለቤት ትግሬ ነው! የዚህ ድርጅት ባለቤት ኦሮሞ ነው_ የዚህ እርሻ ባለቤት አደሬ ነው... አይነት አመለካከቶች እና ንግግሮች፣ ጥርስ መነካከስ _ መወገድ አለባቸው ! ከስሜታዊነት መላቀቅ አለብን! ከንጠኝነት መላቀቅ አለብን! ከክልላዊነት አስተሳሰብ መላቀቅ አለብን! ስለዚህ ከግለሰቦች አሁን ስልጣን ላይ እስካለው መንግስት እስከ ተቃዋሚ ፖለቲከኞቻችን አመለካከታችሁ ብሔር... ቋንቋ... ብሔርተኝነት ...የሚል ጠባብ ግንዘቤ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን እውነተኛ ኢትዮጵያዊ መንፈስ እና ንፁህ አዕምሮ ይዛችሁ መነሳት አለባችሁ! በዚህ ሚስኪን የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በደካማ ጎኑ እየተጠቀማችሁ በህዝቡ መሀከል ኢትዮጵያዊ መንፈስ ዜሮ እንዲሆን እያደረጋችሁት ነው ይህን የምትሰሩትን ስራ፣ ደብ፣ ሸንጎላ፣ ድብብቆሽ ጨዋታ እግዜርም በዝምታ የተሰፋይቱ ሀገር ኢትዮጵያ ስትናወጥ! አይመለከታችሁም! ህዝቡ ሲባንን ይፋረዳቿኋል! ባጠቃላይ ከዚህ ሁሉ ወጥተን መለወጥ እንችላለን! የማይቻል ምንም ነገር በዓለም ላይ የለምና! ሁለት በጣም የምወዳቸው አባባሎች አሉ

1. where there is a will there's a way. (ፍላጎት ካለ መንገድ አለ)
2. The night is darkest before the dawn. (ሲነጋ ሲል ይጨልማል) ብሔር እና ብሔርተኝነት ለማንኛውም ለእድገታችን ማንቋርት የሆኑትው ይቺ ቋንቋ ... ነች! ... ሰባተኛ ችግር (7)

# የፈረንጅ አምላኪነት

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

በቃ ጠንካራ የስራ ባህል ስላላቸው! አድገዋል! አበየው! የሚበልጡንን ማክበር እና ማድነቅ የጤነኛ አዕምሮ ውጤት ነው !! ፈረንጆች ይበልጡናል የሚበልጡን ግን በአስተሳሰባቸው ነው! ሁላችንም ምንጫችን "የአዳም ዘር" ነን! ሁላችንንም የፈጠረን እግዜር... ሁላችንም የሰው ልጆች ነን! ሰውን የምናወዳድረው ነጭ ቆዳ፣ ጥቁር ቆዳ ... ቡኒ... አማርኛ ተናጋሪ፣ እንግሊዘኛ ተናጋሪ... ስፓንሺ ተናጋሪ፣ አረብኛ ተናጋሪ... እያልን ሳይሆን ... በቁመቱ... በውፍረቱ በቅላቱ ሳይሆን ባለው አመለካከት ነው! እግዜር ለሁላችንም የሰጠንን አዕምሮ በመጠቀም እና ባለመጠቀም በሚል መስፈርት ነው... በቃ የእድገት ማማ ላይ የደረሱት እንደ እኛ ወሬ በመደለቅ ሳይሆን በመስራት ነውና ሊከበሩ ይገባል:: እኛ ግን እያከበርናቸው! የሥራ ባህላቸውን! የጊዜ አጠቃቀማቸውን! ከቋንቋ → ከብሔር → ብሔርተኝነት ላይ ያልተመሠረተውን ጠባብ ያልሆነ ሀገራዊ መንፈሳቸውን ! አንድነታቸውን! ስልጣኔያቸውን እያወረድን ሳይሆን እያመለክናቸው ነው... ከግለሰብ እስከ መንግስት ፈረንጆችን እናመልካለን! እነሱ ያሉት ሁሉ ልክ ነው! ፍጹም ናቸው! አይሳሳቱም! ለእኛ የሚያውቁት እነሱ ብቻ ናቸው! ታሪካችን በኛ ሀገር ምሁራን ሳይሆን በፈረንጅ ሲፃፍ ደስ ይላል! እውነት ይሆናል... እናነበዋለን ... ቢቃ ፈረንጅ የነካው ፣ ያደረገው፣ የተናገረው ሁሉ ልክ ነው! ከግለሰብ እስከ መንግስት ለልመና እጃችንን እንዘረጋለን! እናሸረግዳለን! ጭራችንን እንቆላለን! ለዘመናት በልመና ኖረናል!! የኛ ባህል ትንሽ እና ተራ ነው የፈረንጅ ባህል ግን ትልቅ እና ክቡር ነው:: የኛ ሀገር ደራሲ ደደብ ነው የፈረንጅ ደራሲ አዋቂ ነው... የኛ ሀገር ምግብ፣ ልብስ፣ አነጋገር፣ ምርት... ውቅጥ ነው:: ፈረንጅ የነካው ነገር ግን ድንቅ ነው ከትንሽ ት/ቤት እስከ ትልቅ ኮሌጅ እስከ ዩኒቨርሲቲ... ከትንሽ ክሊኒክ እስከ ግዙፍ ሆስፒታል ... ትልቅነቱን ለማሳወቅ እኛ ጋ ፈረንጅ አለ የሚል ማስታወቂያ የግድ ነው :: የኛ የሀገር ሙዚቃ ፈረንጅ ከደነሰበት ምርጥ ነው! የባህል ልብሳችን ፈረንጅ ከለበሰው ምርጥ ነው... ብቻ ከትንሽ እስከ ትልቁ ፈረንጅ እናመልካለን... ጊዜያችንን ስለ ፈረንጅ አገር ኳስ ፣ ልብስ ፣ ፊልም፣ ሀገር፣ እድገት እያወራን እናቃጥላለን!

ለአንድ ወጣት አንዷት ቀሽት ትሁን አይጥ የመሰለች የፈረንጅ ሴት /አሮጊት ጠብቦ

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

አብሮዋት በየመንገዱ ሲሄድ አረማመዱ እንደ አንበሳ ነው! ደረቱን ነፍቶ ነው!! ሲቆጣችንም ከፈረንጅ ወንድ /ሸማግሌ ጋር መሄድ የስልጣኔ ! የመባነን ምልክት ነው! እስቲ የጋዜጣውን ...FMዎችን ... መፅሔቶችን ... መፅሐፍትን ... ማስታወቂያዎቻችን ... ፊልሞችን ታዘቡ ምን ያህል የፈረንጅ አምልኮት እንደተጠናወተን ትገነዘባላችሁ ... ለአንድ ተራ ፈረንጅ የሚሰጠውን ክብር እኛ ሀገር ለአንድ ፕሮፌሰር ሆነ ሀገሩን ለመለወጥ ታላቅ ተጋድሎ ላደረገ ግለሰብ አይሰጠውም ... ታዲያ ይህን የፈረንጅ አምልኮ ይዘን እንዴት ኢትዮጵያ ታድጋለች?... ስምንት በሉ (8)

# ደካማ የሥራ ባህል

ብዙ ሰዓት ተቀምጦ የሚያወራ ማህበረሰብ ባለበት ማንም የነዛውን ወሬ ያለ አንዳች እውነት ተደርጎ በሚወራበት ማህበረሰብ ... ያለ መረጃ የሰማውን ነገር አምኖ በሚቀበል ማህበረሰብ !! የሚያወራ! የሚለምን! በሚከበርበት ሀገር ውስጥ ጠንካራ የሥራ ባህል ይኖራል ማለት ዘበት ነው!! አባይን ዝቆ ለመጨረስ በጭልፋ የመጨለፍ ያህል ነው ... ቀጥቃጭ፣ ፋቂ፣ መጫኛ ነካሽ፣ ሊስትሮ፣ አስተማሪ፣ አዝማሪ... በሚባልባት ኢትዮጵያ ስራ እና ስኬትን የምናያይዘው ከእጉል እምነት ጋር ነው:: ከአንድ ሆብታም ጀርባ ጥንቆልና አለ እንላለን ... አከሌ እኮ በፍጥነት የተለወጠው ላቡን ጠብ አድርጎ ነው ሳይሆን ጠንቋይ ቤት ሄዶ መተት አስመትቶ ... እሜሪካ ያሉት ዘመዶቹ ልኮውለት ... ወዘተ እንላለን! የምክንያት ተራራ እንከምራለን!! ራስን እናፅናናለን! እጉል ስም እንለጥፋለን ከማድነቅ ይልቅ ጠንክሮ ሠርቶ ከመለወጥ ይልቅ እናናንቃለን ... እናጣጥላለን! ብቻ እጅግ ደካማ የስራ ባህል አለን ... ሊባና ዘራፊውን የእራዳ ልጅ ብለን እናደንቀዋለን ! ሙሰኛውን ከመቃወም ይልቅ እናበረታታዋለን ... እውነቱን ለመናገር የሰው ልጅ በምድር ላይ ሲኖር ወዶ በግድ መስራት

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

አብሮዋት በየመንገዱ ሲሄድ አረማመዱ እንደ አንበሳ ነው! ደረቱን ነፍቶ ነው!! ሴቶቻችንም ከፈረንጅ ወንድ /ሸማግሌ ጋር መሄድ የስልጣኔ ! የመባነን ምልክት ነው! እስቲ የጋዜጣውን ...FMዎችን ... መፅሔቶችን ... መፅሐፍትን ... ማስታወቂያዎቻችን ... ፊልሞችን ታዘቡ ምን ያህል የፈረንጅ አምልኮት እንደተጠናወተን ትገነዘባላችሁ ... ለአንድ ተራ ፈረንጅ የሚሰጠውን ክብር እኛ ሀገር ለአንድ ፕሮፌሰር ሆነ ሀገሩን ለመለወጥ ታላቅ ተጋድሎ ላደረገ ግለሰብ አይሰጠውም ... ታዲያ ይህን የፈረንጅ አምልኮ ይዘን እንዴት ኢትዮጵያ ታድጋለች?... ስምንት በሉ (8)

# ደካማ የሥራ ባህል

ብዙ ሰዓት ተቀምጦ የሚያወራ ማህበረሰብ ባለበት ማንም የነዛውን ወሬ ያለ አንዳች እውነት ተደርጎ በሚወራበት ማህበረሰብ ... ያለ መረጃ የሰማውን ነገር አምኖ በሚቀበል ማህበረሰብ !! የሚያወራ! የሚለምን! በሚከበርበት ሀገር ውስጥ ጠንካራ የሥራ ባህል ይኖራል ማለት ዘበት ነው!! አባይን ዝቆ ለመጨረስ በጭልፋ የመጨለፍ ያህል ነው ... ቀጥቃጭ፣ ፋቂ፣ መጫኛ ነካሽ፣ ሊስትሮ፣ አስተማሪ፣ አዝማሪ... በሚባልባት ኢትዮጵያ ስራ እና ስኬትን የምናያይዘው ከአጉል እምነት ጋር ነው:: ከአንድ ሀብታም ጀርባ ጥንቆልና አለ እንላለን ... አከሌ እኮ በፍጥነት የተለወጠው ላቡን ጠብ አድርጎ ነው ሳይሆን ጠንቋይ ቤት ሄዶ መተት አስመትቶ ... አሜሪካ ያሉት ዘመዶቹ ልኮውለት ... ወዘተ እንላለን! የምክንያት ተራራ እንከምራለን!! ራስን እናፅናናለን! አጉል ስም እንለጥፋለን ከማድነቅ ይልቅ ጠንክሮ ሠርቶ ከመለወጥ ይልቅ እናናንቃለን ... እናጣጥላለን! ብቻ እጅግ ደካማ የስራ ባህል አለን ... ሌባና ዘራፊውን የአራዳ ልጅ ብለን እናደንቀዋለን ! ሙሰኛውን ከመቃወም ይልቅ እናበረታታዋለን ... እውነቱን ለመናገር የሰው ልጅ በምድር ላይ ሲኖር ወዶ በግድ መስራት


t.me/OLDBOOKSPDF
Scanned by CamScanner

አለበት አለምና ሉዋን ወደ መሬት ሲላኩ 'ወደ መጣህበት መሬት እስከምትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ' ተብለው ነበር:: መስራት ግዴታ ነው! የማይሠሩ እጆች መብላት የለባቸውም:: ከወደ አደዋ አንድ ጊዜ የሰማሁት ዜና አስደንግጦኝ ነበር የ80 ዓመቱ ለማኝ ሞተ ደሳሳ ጎጆው አልጋ ሥር ለዘመናት ሲለምን ያጠራቀመው አንድ ሚሊየን ብር ተገኘ. አለመታደል እንግዲህ ከሚሠራ ይልቅ ልመናን የሚያደንቅ ማህበረሰብ ነው ያለን!!

ኤልያስ የሚባል ጓደኛ ነበረኝ:: ቤተሰቦቹ አሜሪካ ይኖራሉ :: በየወሩ ብዙ ብር ይልኩለታል... ኤልያስ ዘናጭ ነው:: ኤልያስ ቤት አሳዳጅ ነው:: ኤልያስ ሥራ የሚባል አይወድም::

"ሥራ ለምን አትሠራም" አልኩት "ምን ያደርግልኛል? ሌሎች ይሠራሉ ብር ይልኩልኛል! ዪ ድርጎ መደሰት! መብላት! መጠጣት! መብዳት ነው:: እፐል ቁርስ ምሳ ጥብስ ራት እያለ የሚባል ምርጥ አባባል አላነበብከም? አንዳንዴ በህይወት እድለኛ ስትሆን መስራት አያስፈልግም! እድለቢሶች ናቸው እየሰሩ የሚኖሩት እኔ እድለኛ ነኝ" ይላል::

"ከንቱ! ከንቱ ነህ" እለዋለሁ:: ይሄን አይነት የዘቀጠ አስተሳሰብ ያለው በሰው ላብ ለመኖር የወሰነ ጓደኛ ስለማይመጥነኝ ተለያይተናል... በሌላ ሰው ላብ መኖር፣ መብላት፣ መጠጣት፣ መዘናናት እድለኝነት፣ እራዳነት ሳይሆን ከንቱነት ነው:: ራስን ማዝቀጥ ነው! ሀጢያት ነው! በራስ ያለመተማመን ነው! የአስተሳሰብ ትንሽነት ነው... ይህን መሰል አመለካከት ያላቸው ብዙ ወንዶች እና ሴቶች ያላት ኢትዮጵያ እንዴት ትደግ? የኢትዮጵያ የጨለማ ዘመናት እንዴት ያብቃ? የኢትዮጵያ የከፍታ ዘመን እንዴት ቶሎ ይድረስ ? የኢትዮጵያ የዘመናት የምሬት ለቅሶ እንዴት ይታበስ? የኢትዮጵያ እንባ እንዴት ይታበስ? ብቻ ከሚሠራ ይልቅ ህገወጡን እናሞግሳለን ታዲያ ስኬት እና እድገት በወሬ አይገኝ... ዘጠኝ ቢሉ (9)

**ጨለምተኛነት ... ምቀኝነት ...**

**ጥገኝነት ... ጠባብነት ...**

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

ስለ እነዚህ መፃፍ ከጀመርኩ በትንሹ 1000 ሺ ገፅ ራሱ አይበቃኝም ስለዚህ ... ብቻ አስረኛው ግዙፍ በሽታ በሉ (10)

## ... እከክልኝ ልከክልይ ባዮች

## መብዛት ....

አንድ ሀብታም ቢጤ ብዙ ሀገራትን የዞረ ጓደኛዬ ስለ እስራኤላዊያን ሲነግረኝ እደነኳቸው::" በጋዛ ጉዳይ እስራኤላዊያን እና ፍልስጤማዊያን ታላቅ ጠላትነት በመሀከላቸው ቢኖርም የፍልስጤም ዜግነት ያላቸው ሠራተኞች ቀንቀን እስራኤል ምድር ገብተው ስራቸውን ሠርተው አመሻሽ ከድንበሩ ይወጣሉ" አለኝ:: ቤቃ እንዲህ አይነት አመለካከት ነው የሚያስፈልገን ...ኬኒያዊ ዜግነት ያለው እውቀት ካለው ሞያሌ መጥቶ ቀኑን ሙሉ ሠርቶ አመሻሽ ላይ ድንበሩ ሳይዘጋ ቢሄድ ፓስፖርት ኖረው አልኖረው ምን ችግር አለው? ኤርትራዊ ዜግነት ያለው አደዋ ሆነ መቐለ መጥቶ ሲሠራ ውሎ አመሻሽ ላይ ወደ ኤርትራ ቢመለስ ምን ችግር አለው ? ኬንያዊውም፣ ኤርትራዊውም፣ ምንሴ የአዳም ዘር! ኢትዮጵያዊውም ምንሴ የአዳም ዘር ... እኛ ኢትዮጵያዊያን ያጣነው ይህን ነው:: ሥራም ለማግኘት ፤ ት/ት ለመማር ፤ ትዳር ለመያዝ፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ፤ በዩኒቨርሲቲዎች፣ እከክልኝ ልከክልህ ባዮች በዝተዋል ... መንግስትም ሰዎችን (አባላቱን) እከኩልኝ ልከክላችሁ... በሚል ባዶ አየነዳቸው ... ሰንት ባለሙያ እና እውቀት ያለው ስራ አጥቶ በጠራራ ፀሐይ እየዞረ... የማያውቁት ... የሚገባውን ባዶ ጭንቅላት ! የማንም ትንሽ አመለካከት እና ምናብ ጠባብ የሆነ ሰው ... የማይገባውን በእከክልኝ ልከክልህ እየሰራ ይገኛል... ላይ እማማ ኢትዮጵያ! አንድ ሳይሆን ሰው "ሰው" የሚለው መስፈርት ተሰርዞ ኢትዮጵያዊ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

መሆን ብቻ ይበቃል የሚለው ማንነቱ ተሰርዞ ... ለት/ት... ለመማር ... ለሥራ ለለውጥ በቋንቋ ፡ በዘር፡ በብሔር ላይ ተመስርቶ አክክልኝ ልክክልይ አይነት Game እያለ እንዴት ይህን የመሰለ ግዙፍ በሽታ! ነቀርሳ እያለ ኢትዮጵያ ታድጋለች ? "ብታምኑም ባታምኑም በቁማችን ሞተናል" አለ ሰውየው፡፡ እስቡት እንግዲህ እስተማሪው ተማሪዎች እንዲወዱት ባለሙያዎች ይህን ነገር" CHEAP POPULARITY" ፍለጋ ይሉታል ማርክ ከጨመረላቸው አማራ አማራውን፣ ትግሬ ትግሬውን፣ ኦሮሞ ኦሮሞውን፣ ወላይታ ወላይታውን፣ ኦርቶዶክስ ኦርቶዶክሱን፣ ሙዝሊም ሙዝሊሙን ፣ጴንጤ ጴንጤውን... ወገን ወገኑን ...ፈልጎ ካገባ፣ ፈልጎ ስራ የሚያሠራ ከሆነ .. የሚረዳ ከሆነ... አክክልኝ ልክክልህ ባይነት ነው ... እስራ አንደኛ ግዙፍ በሽታ በሉ (ii)

ስለ እውነት እስቲ ከስሜታዊነት እንውጣና ቆም ብለን እናስብ ራሳችንን እንጠይቅ በእርግጥ ኢትዮጵያ ለምን አላደገችም የ5000ሺ ዘመን ታሪክ ያላት ሀገር? ትላንት እስከ የመን፣ ሀንድ፣ ግብፅ ድረስ ጦሯን እየላከች ትገዛ የነበረችው ኢትዮጵያ ለምን አላደገችም፣ መተሳሰባችን ሀዘናችን አብሮ መብላታችን ለምን ከአንገት በላይ ብቻ ሆኖ ቀረ? ወይስ የውሸት ታሪክ ነው ሲነገረን የነበረው? ተረት ነበር? ማለት ነው ሲነገረን የነበረው፣ ሙዚቃችን ለምን ከሸፈ? ሥነ ፅሁፋችን ከወዴት ተሰወረ? የሥነ ጥበብ ብቃታችን ለምን ባለበት ቆመ? የእነ አክሱም ስልጣኔ ለምን እስከ ዛሬ መቀጠል አቃተው? ለምን እህቶቻችን በየአረቡ ሀገራት ስቃያቸውን ይበላሉ? የእነ ላሊበላ ስልጣኔ ለምን እዛው ቆመ? ... ብዙ ዘርዓያቆቦች ለምን አልተፈጠሩም ? ብዙ ጥላሁን ግዛዎች ለምን አልተነሱም ? ብዙ ማርታዎች ለምን አልፈለቁም? ለእነዚህ መሰል ወሳኝ ጥያቄዎች ብዙ ምክኒያቶች መጥቀስ ይቻላል/ ምንም እንኳን ምክኒያት ውጤት ባይለውጥም /ኢትዮጵያዊያን ከድህነት ጋ ለዘመናት በፍቅር ወድቀናል ስለዚህ መለየት አንፈልግም...... ኋላቀር የጊዜ አጠቃቀማችን - እጅግ በርካታ ጦርነቶች ውስጥ በየጊዜው ገብተን ወጥተናል ... ስንቶች በምክኒያትም ያለምክኒያትም ሕይወታቸው ቀልጧል! ሞተዋል ... የት/ት ስርዓታችን ለውጥ ፈጣሪ ትውልድ ማፍራት አለመቻሉ ... የተማሩት የምንላቸው ወይ በገንዘብ ፍለጋ ወይ

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

በፖለቲካ ጫና በተለያዩ ሀገራት ቀልጠው መቅረታቸው ስራ መናቅ! ሁሉን ነገር ከመንግስት ብቻ መጠበቅ፣ ወረተኝነት እና ስሜታዊነት ለሴቶች ተገቢውን ክብር አለመስጠት_ ከተማረው እስከ ያልተማረው ስኬትን ከእድል እና 40 ቀን ... ጋር ማያያዙ! ከትንሽ እስከ ትልቁ ሰበበኛ እና ምክኒያት ደርዳሪ መሆኑ! ሰውን ሲሞት እንጂ በሕይወት እያለ ያለማክበራችን ባህል ... ብቻ ከመልካሙ ነገር ጠማማ ነገር መምረጣችን ይህን ጉዳይ ለለሞን ሞገስ ከፀሐይ በታች በተሰኘው የግጥም መድብሉ እንዲህ ያስቀምጠዋል

## የአገሬ ገበያ

ገበያ ወጥቼ
ጨለማና ብርሃን ልሸጥ ተመኘቼ
ጨለማውን ሸጬ አትርፌበት መጣሁ
ግና ብርሃኑን የሚገዛኝ አጣሁ::

በማለት ያስቀምጠዋል:: ብቻ ብዙ ነገር ማንሳት ይቻላል:: እኔ በወፍ በረራ ለማንሳት የሞከርኩት አስራ ሁለቱን ችግሮች ናቸው:: ሁሉ ነገር አለን፣ ብዙ ህዝብ፣ ለምመሬት ፣ አዋቂዎች ፣ ተመራማሪዎች ፣ ትላልቅ ሀሳብ አመንጪዎች ከፍተኛ IQ ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ሴቶች እና ወንዶች!! በርካታ ግዙፍ ወንዞች ግና ቂል ሐይቅ መሐል ቆሞ ይጠማል እሊያም A Fool is thirsty in the midst water ለኛ ለኢትዮጵያዊያን የተተረተ ይመስለኛል!! ለማንኛውም የመጨረሻውን ነጥብ ላንሳ ...

## ባዶ ተስፈኝነት



እንዳላሰለቻችሁ ብቻ ... አሁንም እንግሊዘኛ አስተማሪያችን ላንሳ ነው:: በጣም ምርጡ ወጣት አስተማሪያችን ነበር:: ምን ዋጋ አለው እንዴት ቀልቃላ አፈቀረችውና ሲመከራት ለወሲብ ጠየቀኝ ብላ ከሰሰችው ተማሪዎች ሙድ መያዝ ጀመሩ... እሱም ከኛ

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

ከፍል ጋር የነበረው ግንኙነት ቀዘቀዘ … ያቺን ልጅ ጠብቄ ፈንከትኳት ለማንኛውም ሌላ ቃል ሳልቀላቅል ወደ ተነሳሁበት ልመለስ:: God helps those who help themselves ዘውትር ይለን ነበር :: በቀላል አማርኛ 'አምላክ የሚረዳው የሚፍጨረጨሩትን ብቻ ነው' ማለት ይቻላል:: ኢትዮጵያዊያን ባዶ ተስፋኝነት ተጠናውቶናል… ተረቶቻችን ታሪካችን መፅሐፎቻችን የቢንጥበብ ሆነ ሥነ ጥበብ ስራዎቻችን ሁሉ በባዶ ተስፈኝነት እና በአውነትነት እና በተጨባጭነት ላይ የተመሠረቱ አይደሉም!! ስሜታዊነት ያጠቃናል በጦርነት ከአሜሪካ ጋር ብንጋጠም እናሸንፋለን እንላለን! የዓለም ለምለሟ ሀገር የኛ ነች! ብለን አፋችንን ሞልተን እንደሰኩራለን! በቂ መፀዳጃ ቤት እንኳን የሌላትን ግማታም እና ሽንታሟን አዲስ አበባን የዓለም ምርጧ ከተማ ናት! አየር መንገዳችን የዓለም አንደኛ ምርጥ ነው እንላለን:: ራሳችንን እንቆልላለን በዚህ አንደኛ … በዚያ አንደኛ አንደኛ የሚል ንግግሮች እንወዳለን … በርግጥ ለራስ ክብር መስጠት ጥሩ ነገር ነው እኛ ግን ለራስ ክብር እየሰጠን አይደለም ራሳችንን እየዋሸን እና እየሸነገልን ነው… አሰቡት በርካታ ግዙፍ ወንዞች እያሉን ዝናብ ጠብቀን እናርሳለን የሚደንቀው በረሃ የሆነችው እና ውሃ ከግብፅ የምትገዛው እስራኤል ውሃ አጅን በመሸጥ ትታወቃለች … ከግለሰብ እስከ መንግስት በባዶ ተስፈኝነት ተሞልተናል እግዜር የከፈተውን ጉሮሮ አግዜር ይዘጋዋል እያልን 12 ልጆች እንፈለፍላለን!! ያለ ምንም ስራ ቤት ውስጥ ተቀምጦ እግዜር የሚበላውን መና ቤቱ ድረስ እንዲያመጣለት የሚመኝ ስንት ህዝብ አለ ነው ያለን … ይህን ብሰራ ኖሮ ይህን ባደርግ ኖሮ አግዜር ይህን ቢሰጠኝ ኖሮ ይህ ነገር ባያጋጥመኝ ኖሮ ሎተሪ ቢደርሰኝ ኖሮ… ኖሮ… ኖሮ… /የሙኒት ሙዚቃን ማዳመጥ ነው/ በሙሉ ባዶ ተስፋዎች ተሞልተናል ፈልገን ይሁን ሳንፈልጋቸው ለምንወልዳቸው ልጆች ሁሉ እውነታን እንዲጋፈጡ እና ጠንካራ ስብዕና እንዲኖራቸው ሳይሆን አጉል ባዶ ተስፋ እንሞላቸውና የድርጊት ሰው ሳይሆኑ ባዶተስፋኛ ሆነው ይቀራሉ…በከንቱ ባዶ ምኞት በውሸት እና በእውነት መሀከል ተወጥረናል… እውነት እና ውሸትን ቀላቅሎ ደግሞ የትም መድረስ አይቻልም:: ጌትነት እንየው እውቀትን ፍለጋ በሚለው መድብሉ ምን አለ?

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

# የማይቻል አንድ ነገር

እውነት -ቤት ስትሰራ

ውሸት -ላግዝ ካለች

ጭቃ ካራገጠች

ምስማር ካቀበለች

ቤቱም አልተሰራ

እውነትም አልኖረች::

ተስፋ ማድረግ ትልቅ ነገር ነው:: ታላቁ መፅሐፍ ቅዱስም ሶስት ግዙፍ ነገሮች አሉ ተስፋ፣ ፍቅር እና እምነት ይላል ... የሰው ልጅ ለመኖሩ ትልቁን ሚና የሚጫወተው ተስፋ ነው:: ተስፋ ቢስ የሆነ ሰው በቁሙ የሞተ ነውና... እኛ ግን የተሞላነው በባዶ ተስፋ ነው :: በከንቱ ምኞት ነው... የአብዛኛውን ህዝቡን አካሄድ የሚወክል ታሪክ አዘርግ አዳምና ሔዋን በተሰኘው መፅሐፉ ላይ "ትልቅነት" በሚል የሚከተለውን አስፍሯል!!

ትልቅነት

1

ተቀመጠ

ማሰብ ጀመረ

ብዙ አሰበ፣ እጅግ ብዙ አሰበ:: እንደተቀመጠ ዘመናት አለፉ:: እድሜው ወደ ላይ ፈሰሰ::

2

ቁጭ ብሎ ስለ ትልቅነት እያሰበ አረጀ::

3

ስለ ትልቅነት እያሰበ ትንሽ እንደሆነ ሞተ::

4

ተቀበረ:: አለቀ:: ደቀቀ::

ለማንኛውም እኔም እንደሌላው ወሬኛ የኢትዮጵያን ችግር በባዶ አለፈልፍም፣ ስለ

t.me/OLDBOOKSPDF



Scanned by CamScanner

ችግር ማውራት ቀላል ነገር ነው!! ትልቁ ቁም ነገር ይህን ችግር እንዴት መለወጥ ይቻላል? ከላይ ያሉት 12 ግዙፍ ችግሮች ለምን በህዝቡ ላይ ተገኙ? መፍትሔውስ ምንድ ነው? ማለቱ ነው ትልቁ ቁም ነገር!! እናም እኔ ባደረኩት ትልቅ ጥረት ለሀገሬ የድርሻዬን ተወጥቻለሁ! የሚያወራ ሳይሆን የተግባር ሰው ነው ኢትዮጵያ አሁን የምትፈልገው!! ቢቃ እውነቱን መነጋገር አለብን እንዴ ቢቃ መሸንጋጋል! መፎጋገር! አጉል መደናነቅ! መሸዋወድ! መመሳሰል! የቀበሮ ባህታዊ! የጭቃ ውስጥ እሾክ መሆናችን ማብቃት አለበት!!

አጉል ለምለሟ ሀገሬ የሚል የሸንገላ ሙዚቃ! እንግዳ ተቀባዩ ህዝባችን እይነት ንግግር... ውብ ባህላችን አይነት ዜማ.. እየተባባልን 21ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ደርሰናል!! እኔም እኮ ኢትዮጵያዊ ነኝ ብዙ የምወዳቸው ነገሮች አሉ:: ሙዚቃችን ፤የበዓል ስርዓታችን፤ የመረዳዳት ባህላችን ፣ አብሮ የመብላት ወጋችን፤ እቁብ፤ እድር የለቅሶ ስርዓታችን፤ የሠርግ ሥነ ሥርዓታችን በተለይ የሀገር ፍቅራችን!! እኔ እያልኩ ያለሁት ግን ከላይ ያሉት 12 ግዙፍ ችግሮች ሥር በጣም እየሰደዱ ነውና በፍጥነት መለወጥ አለባቸው ነው!!

# የኔ
# ኢትዮጵያ

እኔ የምፈልጋት ኢትዮጵያ ሙዚቃዋ ወንዝ ተሻግረው በመላው ዓለም ላይ የሚደመጡላት ... ፊልሞቿ ወንዝ ተሻግረው በመላው ዓለም ላይ የሚታዩላት... እግር ኳሷን መላው ዓለም የሚመለከትላት ... ምሁሮቿ እና አዋቂዎቿ የሚከበሩባት ... መንግስት (ባለስልጣናት ) ህዝብን የሚፈራበት እንጂ ህዝቡ መንግስትን የሚፈራበት ያልሆነች ኢትዮጵያን !! ባህላዊ አልባሳቶቿ በመላው አለም ላይ የሚለበሱላት የመኖር የእድሜ ጣሪያ 48 ሳይሆን 88 የሆነባት.. እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በቀን ውስጥ ደረጃውን የጠበቀ ምግብ ባስፈለገው ጊዜ የሚበላባት! እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዘመናዊ ቤት ውስጥ እንጂ ደሳሳ ጎጆ ውስጥ የማይኖርባት... አለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ት/ቤቶች! ዩኒቨርሲቲዎች ፣ ሆቴሎች፣ እርሻዎች ፣ የትራንስፖርት አገልግሎቶች ፣ መንገዶች ... መዝናኛዎች... ያሉባት!!

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

የማንኛውም ግለሰብ ሀሳብ የሚከበርባት ! የመናገር የመፃፍ የእምነት መብት 100% የሚከበርባት ... በተለይ ባለስልጣናቶቿ ሲያጠፉ ፍርድ ቤት ቆመው የሚጠየቁባት ... እውነተኛ ፍትህ እና ዲሞክራሲ የሰፈነባት ... እጅግ በርካታ ጋዜጦች መፅሔቶች የሬዲዮ ጣቢያዎች የቴሌቪዥን ጣቢያዎች እንደሰው ምርጫ እና ፍላጎት የሚገኙባት... በርካታ እንባቢያን ወጣቶች ያሉዋት! ስለ ርሀብ እና ችግር የማይወራባት ...የደራሲዎቿ ድርሰቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ በግርምት የሚነበቡላት ... ምቀኝነት ! ዘረኝነት! ጎጠኝነት! ሙሰኝነት! ወገንተኝነት! ጠባብነት! ወሬኛነት የሌለባት... አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ቀዩ ባንዲራችን በየዓለማቱ በክብር የሚውለበለብላት ታላቋን ኢትዮጵያን ነው!! ይህ ደግሞ በምኞት የሚመጣ አይደለም!! በተግባር ብቻ ነው!! በቃ መወዳደር ካለብን! ምድራዊ ሕይወት መኖር ካለብን! ራሳችንን ማነፃፀር ካለብን እጅግ በስልጣኔ ተመንድገዋል! በልፅገዋል ከሚባሉት ትላልቅ ሀገራት ጋር መሆን አለበት! መድረሻችን ትልቅ መሆን አለበት! እስከ መቼ ሌሎች በስልጣኔ የበለፀጉትን እያደነቅን እንኖራለን እኛስ ለምን እንዲያደንቁን አንጥርም!! ስለዚህ እነዚህ አብይ 12 ግዙፍ ችግሮች ለማጥፋት ዛሬ ነገ ሳንል እንቀሳቀስ! ለውጥ ምንግዜም የሚመጣው በሥራ ብቻ ነውና!!

# ማጠቃለያ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ይህን ሁሉ ግዙፍ ችግር የሚፈታውን የዳዊት ወንጭፍ ያስከትን ታላቅ መድኃኒት ከአስር ወራት አሰልቺ ሙከራዎች በኋላ ቀምሜ ጨረስኩት!! እነሆ ለሁሉ ቀረበ፡ የዳዊት ወንጭፍ መድኃኒት ቤት በፍጥነት እየመጣችሁ በ7 ብር ብቻ ግዙ፡ ከዚያ ህይወታችሁን ለውጡ! መድኃኒት ቤቴ ስትመጡ ብዙ ነገር ስለ ኢትዮጵያ እናወራለን እንከራከራለን ከኔ የተሻለ ሀሳብ ያለው እና ከኔ የተሻለ መድኃኒት መቀመም የሚችል ካለ አብሬው ለመስራት ቀና አመለካከት አለኝ!! ለማንኛውም ንቃችሁን እንዳትቀሩ ማድረግ የምትችሉትን ሁሉ ዛሬ አድርጉ! አበው ሲተርቱ መቼም ቢሆን ዛሬ ልትሠራው የምትችለውን ለነገ አትተው (never Leave till tomorrow what you can do to day) የሚሉት ትልቅ እውነት ነው:: በሉ በፍጥነት ሰባት ብር ብቻ በመያዝ የዳዊት ወንጭፍ መድኃኒት ቤት ከች በሉ!! ከዚህ በላይ ላደርገው የምችለው ነገር የለም:: ፈረንጆች ሲተርቱ 'you can lead a horse to water but you can't make him drink' ፈረስን ወደ ወንዝ ልትወስደው ትችላለህ ግን ውሃ እንዲጠጣ ልታደርገው አትችልም! ይላሉ.. ትልቅ እውነት ነው!! በሠላም ያገናኘን:: የምሠናበታችሁ በኢንግሊዘኛ አስተማሪያችን የመውጫ አባባል ነው::


'if you truly want to change your life, you must first be willing to change your mind.'

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner

ማስታወሻ ፡- ይህን አዝናኝ መፅሐፍ ፤መግዛት ባይችሉ እንኳን አባኮት ተውሰውም ቢሆን "የዳዊት ወንጭፍ" የሚለውን ክፍል ያጣጥሙ... (አዘርግ)


## የአዘርግ ቀደምት ሥራዎች










## ቀጣይ ምርጥ መፅሐፍ

**“እ...ዘንደኪ”**

**USD 55**

ሕትመት ፋር-ኢስት ትሬዲንግ ኃ.ላ.የተ.የግ.ማህ

t.me/OLDBOOKSPDF

Scanned by CamScanner